ንጉሥ ቴዎድሮስ

አሚሞር ታሪኮች



የአንቲን ቹኮቭ

ምርጥ

አጫጭር ልብወለድ ታሪኮች

ትርጉም

በ

በላይነህ አሠጉ

ጌታቸው ካሳ





ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
KURAZ PUBLISHING AGENCY

ስልክ ቁጥር TEL. 11 27 19
ፖስታ ሣ.ቁ. P.O.Box 30933

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ADDIS ABABA
ETHIOPIA

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ሥዕል — ሉቃስ አማረ

ዕቁ ማተሚያ ቤት ታተመ

ማ ው ጫ

ተራ ቁጥር		ገጽ
1	መግለጫ	፮
2	የአንድ የመዝገብ ቤት ጸሐፊ አማኟት ...	1
3	ቫንካ	6
4	ባለሁለት ታዛ ቤት	13
5	ድብቁ ሰው	44
6	እንጆሪ	66
7	ዩኒች	85
8	ባለ ውሻዋ ወይዘሮ	120
9	ሙሽራዋ	150

መግለጫ

አንቷን ፓቭሎቢች ቼኾቭ ፣ እንደ አውሮፓ አቈ ጣጠር በጥር 1860 ተወልዶ ፣ ሐምሌ 2 ቀን 1904 በሳ ንባ ነቀርሳ የሞተ ታዋቂ የሩሲያ ደራሲ ነበር ። ቼኾቭ ከመለስተኛ የነጋዴ ቤተሰብ የተወለደ ሲሆን ፣ በሕፃንነቱ በአባቱ ሱቅ ውስጥ ሥራ እየረዳ አድጓል ። የአባቱ ንግድ በመክሰሩ ቤተሰቡ በሙሉ ወደ ሞስኮ ሲሔድ ፣ ቼኾቭ በትውልድ ቀበሌው ቆይቶ እየሠራ ትምህርቱን ተከ ታትሏል ። በ1879 ትምህርቱን ስለ ጨረሰ ፣ ወደ ሞስኮ ከተማ ሔዶ ከፍተኛ ትምህርት በመቀጠል በ1884 ከሞስኮ ዩኒቨርሲቲ በሕክምና ሙያ ተመርቋል ። ከዩኒ ቨርሲቲዉ እንደ ተመረቀ በወረዳ የጤና ኃላፊነት ተመ ድቦ በሙያው ለተወሰነ ዒዜ ሠርቷል ።

ቼኾቭ ፣ በመኖሪያው አካባቢ ለባላገሩ ልጆች ትምህ ርት ቤት በመሥራት ፣ በሙያዉ የሕክምና ዕርዳታ በመስ ጠት የገጠሩን ሕዝብ ለመርዳት ታግሏል ። በ1892 በሩ ሲያ በረኃብ የተጐዱ አካባቢዎችን ተዘዋውሮ ጐብኝ ቷል ። በ1892—93 ተነሥቶ የነበረውን የኮሌራ በሽታ ለመከላከል በሙያው ተሠልፎ ሠርቷል ። እንዲሁም በ1897 በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፏል ።

ቼኾቭ ፣ መጻፍ የጀመረው በ1870ዎቹ የመጨረሻ ዓመታት ላይ ሲሆን ፣ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ አያሌ ትምህርታዊ የሆኑ ቀልዶች ፣ ተረቶች ፣ አጫጭር ታሪ ኮች ፣ ተውኔቶች ፣ ወዘተ... ደርሷል ። ደራሲው ቼኾቭ

በአጻጻፉ አዲስ ስልት በመቀየሱ ፣ ማክሲም ጐርኪና ሌቭ ቶልስቶይን የመሳሰሉ በዘመኑ የነበሩ ታላላቅ ደራሲ ዎችን ምስጋናና አክብሮት አትርፏል ።

ይህ የአንቲን ቼኾቭ ምርጥ ሥራዎች ቅጽ ስምንት ታሪኮችን አካቶ የያዘ ሲሆን ፣ ታሪኮቹ የተጻፉት ከ1882 እስከ 1903 ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ።

እነሱም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው ።

. የአንድ የመዝገብ ቤት ጸሐፊ አሟሟት 1883
. ቫንካ 1886
. ባለ ሁለት ታዛ ቤት 1896
. ድብቁ ሰው 1898
. እንጆሪ 1898
. ዩኒች 1898
. ባለ ውሻዋ ወይዘሮ 1899
. ሙሽራዋ 1903

የአንድ የመዝገብ ቤት ጸሐፊ አሟሟት

የዋሁ ጸሐፊ ፣ ኢቫን ዲሚትሪች ቼርቭያኮቭ በትያትሩ አዳራሽ በሁለተኛው ማዕረግ ተቀምጦ በኦፔራ መመልከቻ መነጽር እየታገዘ ሌክሎሽ ደ ኮርንቪል የተባለውን ቲያትር ይመለከትባት የነበረች ያች ምሽት ድንቅ ምሽት ነበረች ። ቲያትሩን እያደነቀ በዚች ምድር ከሱ የተሻለ ደስተኛ ሰው እንደሌለ አድርጎ አሰበ ። ድንገት ፊቱ ተጨማደዶ ፣ ወደ ሰማይ አንጋጠጠና ዐይኑ ተጉ ረጠረጠ ። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አለ ። ፊቱን ከኦፔራው መመልከቻ መነጽር ዘወር አደረገና ከመቀመጫው ብድግ ብሎ 'አጪሹ !!' አለ ። በአንድ ቃል ፣ አነጠሰ ። ማንም ሰው በየትም ቦታ ማንጠስ ይችላል ። ገበሬዎች ፣ ፖሊስ መኰንኖች ፣ የተከበሩ ሰዎች እንኳን ያነጥሳሉ ። ማንም ይሁን ማን ያነጥሳል ። ቼርቭያኮቭም በዚህ አልተደናገጠም ። መሐረቡን አውጥቶ አፍን ጫውን ጠራረገና እንደ ማንኛውም በመልካም ሥነ ምግባር እንደታነፀ ሰው ማስነጠሱ ያስቀየመው ሰው እንዳለ ወዲያና ወዲህ ተመለከተ ። በዚህን ጊዜ ክራኙ ደነገጠ ። እፊት ለፊት በመጀመሪያው ረድፍ የተቀመጠ አንድ ትንሽ በራ ሰውዬ እያጉረመረመ በእጅ ጓንቲው ብራ ራሱንና አንገቱን ሲጠራርግ አየ ። ቼርቭያኮቭ ፣

ሰውየው የመገናኛ ሚኒስትሩ ጀኔራል ብሪዛሎቭ መሆኑን ዐወቀ ።

'በእሳቸው ላይ ነው ያነጠስኩት? በእርግጥ አስ ቃዬ አይደሉም ፤ ይሁን እንጂ መጥፎ ድርጊት ነው ። ይቅርታ መጠየቅ አለብኝ' አለ ቼርቭያኮቭ ።

ትንሽ እንደ መሳል ብልሙ ወደፊት ጎንበስ አልና ፣ "ከቡር ሆይ ይቅርታ አድርጉልኝ ! አስነጠስኩብዎት . . . ዐውቄ አይደልም . . ." አለ በሹክሹክታ ።

"ምንም አይደል?"

"ይቅርታ አድርጉልኝ ! እኔ . . . ሆን ብዬ አይደ ልም ?"

"እንዴት ያለ ነገር ነው ፤ እባክህ ዝምበል ! ላዳም ጥበት ?"

ቼርቭያኮቭ እንደ መረበሽ አለ ፤ በድንጋጤ መልክ ፊቱን ፈገግ አደረገና ሐሳቡን ወደ መድረኩ ለመመለስ ሞከረ ። ተዋንያኑን ተመለከተ ። አሁን ግን በዚች ዓለም ተደሳች መሆኑ አልሰማው አለ ። ሰውነቱን ጸጸት መረ ረው ። በትዕይንቶቹ መኻል ወደ ብሪዛሎቭ ጠጋ ብሎ ትንሽ ቆየት አለና በመጨረሻ ፍርሃቱን ሞጥ በማድ ረግ ፣

"አስነጠስኩብዎት አይደል? ጌታዬ . . . ይቅርታ ያድርጉልኝ . . . ዐውቄ አይደለም . . . እባክዎን . . ." አለና አጉተመተመ ።

"እውነቴን ነው የምልህ - . . . እኔ ረስቼዋለሁ ፣ ዝም ብልህ ብትመለከት?" አሉ ጂኔራሉ ፣ ታችኛው ከንፈራቸው በንዴት እየተንቀጠቀጠ ።

'ረስቸዋለሁ ይላሉ ፣ አስተያየታቸው ግን አላማ ረኝም' አለ ቼርቭያኮቭ በጥርጣሬ ወደ ጂኔራሉ እየተ መለከተ ።

"እኔን ማነጋገር አልፈለጉም ማለት ነው ። ሆኖም ዐውቄ እንዳላደረኩ ማስረዳት አለብኝ . . . ይህ የተፈጥሮ ሕግ ነው ። አለበለዚያ ዐውቄ ምራቄን የረጨሁባቸው ሊመስላቸው ይችላሉ ። አሁን እንደዚያ ባያስቡም ቆይቶ ቂም መያዞቸው አይቀርም? . . . "

ቼርቭያኮቭ ፣ ወደቤቱ ከሔደ በኋላ የፈጸመውን አስ ነዋሪ ድርጊት ለባለቤቱ ነገራት ። ባለቤቱ ግን ነገሩን በቀላሉ የወሰደችው መሰለው ። በእርግጥ ለጊዜው ደነገጠች ፤ ብሪግሎቭ አለቃው አልመሆናቸውን ስላ ወቀች ወዲያው ተረጋጋች ።

"ቢሆንም ሔደህ ይቅርታ መጠየቅ ያለብህ ይመስለኛል ። አለበለዚያ በሕዝብ ዘንድ ሥነ ምግባር የጐደለህ ሊመስላቸው ይችላል " አለቸው ።

"ልክ ነሽ ! ይቅርታ መጠየቅ ሞክሬ ነበር ፤ ግን ልዩ ዐይነት ሰው ሆኑብኝ ። የኔ ይቅርታ መጠየቅ ስሜ ትም አልሰማቸውም ። በዚያ ላይ ለማነጋገር ጊዜ አልነበራቸውም ። "

በሚቀጥለው ቀን ቼርቭያኮቭ አዲስ የደንብ ልብ ሱን ለብሶ ፣ ጄኑሩን ተስተካክሎና ጥፍቱን ለመግለጽ

ወደ ብሪዛሎቭ ሔደ ። የጄኔራሉ የእንግዳ መቀበያ ቢሮ በአቤቱታ አቅራቢዎች ጢም ብሏል ። ጄኔራሉም የሰዎቹን አቤቱታዎች እየተቀበሉ እዚያው ክፍል ውስጥ ነበሩ ። ጥቂት ሰዎች ካነጋገሩ በኋላ ወደ ቼርቭያኮቭ ቀና አደረጉ ።

"ትላንት ማታ ፣ ክቡር ሆይ ፣ ያስታውሱት ይሆናል ፤ በስሕተት አነጠስኩ . . . ሳላውቅ ነው ያደረግሁት . . . ይቅርታ . . . " እያለ ንግግሩን ጀመረ ።

"ውጣ ከዚህ ፤ ምን ጅሉ ነው !" አሉና ጄኔራሉ ፣ "ያንተስ ጉዳይ ምንድነው ?" አሉ የሚቀጥለውን ሰውዬ ።

"እኔን አያዳምጡኝም ? " አለ ቼርቭያኮቭ ፊቱ ላንባ እየመሰለ ። "ተቆጥተዋል ማለት ነው . . . ችላ ብዬ የምተወው ጉዳይ አይደለም . . . ማስረዳት አለብኝ . . . "

ጄኔራሉ ባለጉዳዮችን አነጋግረው ከጨረሱ በኋላ ወደ ቤታቸው ጉዞ ሲጀምሩ ፣ ቼርቭያኮቭ እያጉተመተመ ተከተላቸው ።

"ክቡር ሆይ ! ይቅርታ ያድርጉልኝ ። እንዲህ የማስቸግርዎት ከልብ ስለ ተጸጸትኩ ነው እንጂ ሌላ አይደለም . . . "

ጄኔራሉ ሊሳደቡ ያሰቡ መስለው ተመለከቱትና ገፍተረውት ሔዱ ።

"ጌታው ! ታሾፍብኛለህ ?" አሉና በሩን እላዩ ላይ ዘጉ ።

'ማሾፍ ?' አለ ቼርቭያኮቭ በሐሳቡ ። 'ምንም የሚ ያስቅ ነገር አይታየኝም ። አልገባቸውም ፤ እሳቸው አንድ ጄኔራል ? ጥሩ ፣ ከዚህ በኋላ እሳቸውን የመሰለ ትልቅ ሰው ይቅርታ በመጠየቅ አላታክትም ። ገደል ይግቡ ! ደብዳቤ እጽፍላቸዋለሁ እንጂ ፣ ከዚህ በኋላ ዝርም አልላት ! ጨርሶ አለመጣም ፤ አበቃሁ !'

ቼርቭያኮቭ ፣ ወደ ቤቱ ሲጓዝ በአእምሮው የሚ መላለስበት ይህ ነበር ። ደብዳቤውን ግን አልጻፈም ። ደጋግሞ አሰበ ፤ ግን እንዴት መጻፍ እንዳለበት ሐሳብ ሊመጣለት አልቻለም ። ስለዚህ ሁኔታውን ለማቃናት በማግሥቱ ወደ ጄኔራሉ መሐዴድ ነበረበት ።

"ክቡር ሆይ ! ትናንትና በድፍረት ያስቸገርኩዎት እርስዎ እንዳሉት ላሾፍብዎት አልነበረም " እያለ መና ገር ጀመረ ፣ ጄኔራሉ በመጠርጠር ትኩር ብለው ሲመ ለከቱት ። "በማንጠሴ ላደረኩብዎት በደል ይቅርታ ልጠይቅዎት ነው የመጣሁት ... በርስዎ ላይ ለማሾፍ ግን ፣ ጨርሶ አላደርገውም ። እንዴትስ ብዬ እደፍርዎ ታለሁ? ፀሰዎች ላይ ካሾፍንማ መከባበር ይጠፋል ... የበላይን ማክበር አይኖርም ... "

"ወጊድ ከዚህ ?" አሉ ጄኔራሉ ፣ በቁጣ እየተንቀጠ ቀጡ ። ቼርቭያኮቭ በፍርሃት እየራደ ፣ " ይቅርታ ያድር ጉልኝ" በማለት የማንሾካሾክ ድምፅ አሰማ ።

"ውጣልኝ እኮ ነው የምልህ ?" አሉ ጄኔራሉ በእግራቸው መሬቱን እየመቱ ።

ቼርቭያኮቭ ወሽመጡ ብጥስ አለ ። ወደ ውጭ ሲወጣ መስማትም ማየትም ተሳነው ። ወደ ጎዳናው ወጥቶ ጉዞ ጀመረ ። በድኑን ወደ ቤቱ ተጉዞ እንዳለ ከነልብሱ ሶፋው ላይ ተዘረረ ፤ እዚያው ዐረፈ ።

ሻ ን ካ

አልያኪን ለተባለው ጫማ ሰፊ በተልማማጅነት እንዲሠራ ከሦስት ወራት በፊት የተሰጠው የዘጠኝ ዓመቱ ሕፃን ሻንካ ዙኮቭ የገና ዋዜማ ሌሊት እንቅልፍ አልወስደው አለ ። ጌታው ፣ እመቤቲቱና ከሱ ቀድመው የገቡ ተለማማጆች ቤተክርስቲያን እስኪሔዱ ቋሚ ብሎ ቆዩ ። እነሱ እንደ ሔዱም ከቁም ሣጥኑ ውስጥ ብልቃጥ ፣ ቀለምና ብርዕ የጣገ ማንሳል አወጣ ። የተጨረማመተ ወረቀትም ዘረጋና ለመጻፍ ተዘጋጀ ። የመጀመሪያውን ሬደል መጻፍ ከመጀመሩ በፊት ደጋግሞ ወደ መዝጊያውና መስኮቱ ትኩር ብሎ ተመለከተ ፤ በግራና በቀኝ የጫማ ቅርፅ ማውጫዎችን የያዘው መደርደሪያ ያለበትን ጨለማ ግድግዳ አትኩሮ ተመለከተና በረጂሙ ተነፈሰ ። ወረቀቱ በጠረጴዛው ላይ ተዘርግቷል ። ሻንካም ጠረጴዛውን ተደግፎ መሬት ላይ ተንበረከከ ።

“ውድ አያቴ ኮንስታንቲን ማካሪች ፣ ይሀቺን ደብዳቤ እየጻፍኩልዎ ነው ። የልደት ሰላምታዮን እያቀረብኩ አምላክ ከርስዎ ጋር እንዲሆን እመኝልዎታለሁ ። አባትም እናትም የለኝም ። የቀሩኝ እርስዎ ብቻ ነዎት” አለና ጻፈ ።

ሻንካ የሻማው ብርሃን ነጸብራቅ ወደሚታይበት መስኮት ዐይኑን ቀና ሲያደርግ ፣ በሐሳቡ በመስተዋቱ

ውስጥ ዚቫራቪ ልተባለ የመሬት ክበርቴ የሌሊት ዘበኛ ሆነው የሚሠሩትን አያቴን ፣ ኮንስታንቲን ማካሪችን ተመለከተ ። ኮንስታንቲን ማካሪች ዕድሜያቸው ወደ ስድሳ አምስት የተጠጋ ቀጭን ፣ አጭር ሽማግሌ ናቸው ። ሆኖም ጠንካራ ፣ ቀልጣፋና ፈታቸው ፈገግታ የማይለ ለየው ሲሆን ፣ ዐይናቸው ግን በመጠጥ ነብዟል ። ቀን ቀን ማድቤት ገብተው ይተኛሉ ፤ አለበለዚያም ከአሽ ከርና ገረዶች ጋር እየተቃለዱ ይቀመጣሉ ። ማታ ማታ ግን ፣ ከበግ ቆዳ የተሠራ ትልቅ ኮታቸውን ይደርቡና ኩቴአቸውን እያሰሙ በግቢው ውስጥ ወዲያና ወዲህ ይዘዋወራሉ ። ከጓላቸው አፍንጫውን መሬት ላይ ተክሎ የሚሔደው ካሺታንካና በጥቁረቱና በሰውነቱ ርዝማ ኔና በገላው ልስላሴ እምባዛው የሚል ሥያሜ የተሰጠው (ኤል) ይከተሏቸዋል ። ኤል ሰው አክ ባሪና መንገድ ቶሎ የሚለቅ ፣ ወዳጅንም ሆነ እንግዳን በተመሳሳይ ዐይን የሚመለከት ነው ። ይሁን እንጂ ግን ንም አያምንም ። ትሑትነቱና ታዛዥነቱ የክፋቱና የተ ንኮል መሸፈኛ ነው ። ለመስረቅ ፣ ሳይታሰብ የሰውን ቁርጭምጭሚት ለቀም በማድረግ ፣ ወደ በረዶ ቤት ሾልኮ ለመግባት ወይም የገበሬዎችን ዶሮዎች ለመሞ ጭስፍ ልዩ ችሎታ አለው ። በተደጋጋሚ እግሮቹ ተቀ ልጥመዋል ፤ ሁለት ጊዜ በገመድ ተሰቅሏል ፤ በየሳምንቱ ለመሞት ትንሽ እስኪቀረው ይገረፋል ፤ ይህን ሁሉ ችሎ እስካሁን በሕይወት አለ ።

አያቴ ይኸኔ ከቤተ ክርስቲያን መስኩቶች ዐልፎ የሚመጣውን ደማቅ ብርሃን ለማየት ዐይናቸውን አሾ ልቀው አጥሩ በራፍ ላይ ቆመዋል ፤ ወይም ከአሽከሮች ጋር እየተቃለዱ ባለጸጉር ጫማቸውን አድርገው ይንጎ

ራደዳሉ ። ታሞሉ በቀበቷቸው ላይ ይታሰራል ። እጆቹ ቸውን ዘርግተው ከብርድ ለመከላከል ራሳቸውን ታቅ ፊዋል ፣ ወይም የሽማግሌ ቀልድ እየቀለዱ ገረዲቱን ወይም ከወጥ ቤቱቹ አንዷን ይቆነጥጧታል ።

ለሴትዮዋ የሱረት መያዣቸውን እያሳዩ ፣ 'አሽት ቺው ፤ ሳብ አድርጊው ' ይላሉ ።

ሴትዮዋ ትስብና ታነጥሳለች ። አያቴ በደስታ ተው ጠው ፣

"በብርድ ለደነዘዘ አፍንጫ ጥሩ ነው ?" እያሉ በሣቅ ይፈነድቃሉ ።

ውሾች እንኳን ሱረት ይሰጣቸዋል ። ካሽታንካ አሽታ አስነጥሳ ፣ ራሷን ትነቀንቅና ተቆጥታ ከአጠገባቸው ትሸሻ ለች ። ኤል ግን ማስነጠሱን ትዶ በፍቅር መልክ ጭራ ውን ይቆላል ። አየሩ ድንቅ ነው ። አሁንም ሰማዩ የጠ ራና ነፋሻ ነው ። ጨለማ ሌሊት ነው ፤ ግን የቤቶች ንጭ ጣሪያ ፣ ከየጢስ መውጫ የሚወጣው ጢስ ፣ በበ ረዶ ተሸፍነው የሚያንጸባርቁ ዛፎች ሁሉ ይታያሉ ። በሰማዩ ላይ ከዋክብት ብሩህ ሆነው ይታያሉ ፤ ተወ ርዋሪ ኮከቦችም ለበዓሉ ክብር ይመስል ሰማዩ ላይ በድምቀት ይወረወራሉ . . . .

ቫንካ በረጂሙ ተንፍሶ ፣ በመንሱ ቀለም አጠ ቀሰና መጻፍ ቀጠለ ።

"ትናንትና ተደብድቤ ነው የዋልኩት ። ልጆቸውን ሳጫውት ተሳስቼ (ድንገት) እንቅልፍ ስለ ወሰደኝ ባለቤትዮው ጸጉሬን ይዘው እየጎተቱ አትክልት ውስጥ

አስገብተው በጠፍር ጠበጠቡኝ ። ባለፈው ሳምንት ደግሞ እመቤቲቱ የዓጣ ሆድ ዕቃ እንዳወጣ አዛኝ ፥ ከጭራው ብጀምር ጊዜ ዓሣውን ከእጄ ነጥቃ በጭንቅላቱ ፊቴን ፈገፈገችኝ ። ሌሎቹ ሠራተኞችም ይቀልዱብኛል ፤ ሾድካ እንድገዛላቸው በየመጠጥ ቤቱ ይልኩኛል ፤ የባለቤታቸውን ዱባ እንድሠርቅ ያዙኛል ፤ ባለቤትዮውም ባገኙት ሁሉ ይመቱኛል ። በዚህ ላይ የሚበላ የለም ። ጧት ዳቦ ፥ ቀን መቅ ይሰጡኛል ፤ ማታ ደግሞ ዳቦ ይሰጡኛል ፤ የጐመን ሾርባም ሆነ ሻይ ለራሳቸው ይጋቱታል እንጂ አያቀምሱኝም ። ከዚህ ላይ የሚያስተኙኝ በመተላለፊያው በር ላይ በመሆኑና ልጆቸው በነቃት ቁጥር ማጫወት ስላለብኝ ሌሊት እንቅልፍ የለኝም ። ውድ አያቴ በእግዚአብሔር ስም ይገርዎታለሁ ። ከዚህ ያውጡኝ ጨርሶ ልቋቋመው አልቻልኩም ። እባክዎን አባባ በጣም እለምንዎታለሁ ፤ ከዚህ ያውጡኝ አለበለዚያ መሞቴ ነው . . . .”

ቫንካ ከንፈሮቹ ተንቀጠቀጡ ። ዐይኑን በቀለም እጁ ጠራረገና ተንሰቀሰቀ ።

“ሱረትዎን እፈጭልዎታለሁ ፤ ሁል ጊዜ እጸልይ ልዎታለሁ ፤ ካጠፋሁም የፈለገዎትን ያህል ይግረፉኝ ። የሚያሠሩኝ ነገር ከጠፋም ፥ የግቢው አዛዥ እንዲያዝ ንልኝና ጫማዎችን እንዲያስጠርገኝ ወይም በፌዲያ ምትክ ከብቶች እንዲያሳግደኝ እለምነዋለሁ ። ውድ አያቴ አልቻልኩም መሞቴ ነው ። ጠፍቼ ልመጣ አስቤ ነበር ፤ ጫማ ስለሌለኝ በረዶውን ፈራሁት ። ሳድግ እጦር ዎታለሁ ፤ ማንም ሰው እንዳያጠቃዎት እጠብቅዎታ

ለሁ ፤ ሲሞቱም ለእማዬ እንደምጸልየው አጸልይልዎታ ለሁ ።

"ሞስኮ በጣም ትልቅ ኩትማ ስለሆነ ብዙ ጨዋ ሰዎች አሉ ፤ በጣም ብዙ ፈረሶች ሲኖሩ በጎች ግን የሉም ፤ ውሾችም ኃይለኛ አይደሉም ። ልጆች በገና ጊዜ ሌሊት ለሥራ አይወጡም ፤ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ለመዘመር አይፈቅዱም ። አንድ ቀን በሱቆች ውስጥ የዓሣ ማጥመጃ ሲሸጥ አይቼአለሁ ። ትልልቅ ዓሣ መያዝ የሚችሉ አሉ ። እኔታዬ ቤት ያለው ጠመ ንጃ ዐይነት ብዙ ጠመንጃዎችም አሉ ፤ እያንዳንዳቸው መቶ ሩብል ሳያወጡ አይቀሩም ። በየሱክንዳ ቤቶችም የቆቆችና የቀንቸሎች ሥጋ ይሸጣል ፤ የት እንደሚገደሉ ግን ሰዎች አይናገሩም ።"

"ውድ አያቴ ! እትልቁ ቤት ውስጥ የገና ዛፍ ሲያ ዘጋጁ ለኔ ለውዝ አረንጓዴው ሣጥን ውስጥ አስቀም ጡልኝ ። ለኔ ማስቀመጥዎንም ለወይዘሪት አልጋ ኢግ ናትዬሽና ንቭርዋት ። "

ቫንካ ፥ አሁንም ዘረጂመ ተነፈሰና እንደገና ወደ መስኮቱ ትኩር ብሎ ተመለከተ ። አያቱ የልጅ ልጃች ውን አስከትለው ለባለቤቶቹ ለገና ዛፍ ሊቆርጡ ሲሔዱ በሐሳቡ ታየው ። አቤት እንዴት ያሉ አስደሳች ጊዜዎች ነበሩ ! አያቱ ፈገግ ይላሉ ፤ በረዶ የሸፈነው ጫካም ፈገግታ የሚያሳይ ይመስላል ፤ ቫንካም እንደሱ ፈገግ ይላል ። የጥዱን ዛፍ ከመቁረጣቸው በፊት አያቱ ፒፓ ቸውን ያጨሳሉ ፤ ሱረታቸውንም ያሽታሉ ፤ ከዚያም በሚ ንቀጠቀጠው ቫንካ ይሥቃሉ ። ለግላጋው የጥድ ዛፍ በበረዶ ተሸፍኖ ጸጥ ብሎ ቆሟል ፤ ከመካከላቸ ፅ

ግን እንደሚሞት ለማየት ይጠብቃሉ ። በድንገት በበረዶው ውስጥ እመር ብላ አንዷት ጥንቸል ትዘላለች . . . እንደ ቀስት ትወረወራለች . . . አያቴም በመጮህ ሊረዷት አይችሉም ።

ቁም ! ቁም ! . . . ቁም !

"አትቆምም ፣ ተወው! እንት የሰይጣን ቱራጭ!" እያሉ መጮኻቸውን አይተዉም ።

አያቴ ፣ ዛሩን ወደ ትልቁ ቤት ይወስዱና ማስጌጥ ይጀምራሉ . . . የቫንካ ወዳጅ የሆነችው ወይዘሪት አልጋ ኢግናትዬቭና በዝግጅቱ ከሁሉም ይበልጥ ትሠራለች ። የቫንካ እናት ፣ ፔላጊያ ፣ በሕይወት ሆና በትልቁ ቤት ትሠራ በነበረችበት ጊዜ ፣ አልጋ ኢግናትዬቭና በዝግጅቱ ከሁሉም ይበልጥ ትሠራለች ። አልጋ ኢግናትዬቭና ለቫንካ ጣፋጭ ምግቦች ትሰጠዋለች ። ማንበብ ፣ መጻፍና እስከ መቶ ድረስ ቁጥርና ዘፈንም ታስተምረዋለች ። ፔላጊያ ከሞተች በኋላ ግን ፣ ምስኪኑ ቫንካ ከአያቱ ጋር ማድቤት እንዲኖር ተደረገና ከዚያ ለጫማ ሰሪው አልያኪን ፀተልማግጅነት እንዲያገለግል ወደ ሞስኮ ተላከ ።

"ውድ አያቴ ይምጡልኝ" እያለ ቫንካ ጽሑፉን ቀጠለ ። "በኢየሱስ ስም ይገርምዎታለሁ ፤ ከዚህ አውጡኝ ፤ እናት አባት ለሌለኝ ልጅ እዘኑልኝ ፤ በየቀኑ ይገርፉኛል ፤ ረኃብም ያሰቃየኛል ፤ ልነግረዎት አልችልም ፤ በጣም ስለምሠቃይ በየቀኑ እንዳለቀስኩ ነኝ ። አንድ ቀን ባለ ቤትዮው በጫማ ቅርፅ ማውጫው አናቴን ቢሉኝ መሬት ተደፋሁ ፤ እነሣለሁ ብየም አላሰብኩም ነበር ። ክውሻ የባሰ ኑሮ ነው የምኖረው ። ለአልዬና ፣

ለአንድ ዐይናው ዩጎርና ለጋሪ ነጂው ሰላምታ አቅር ቱልኝ ፤ አርሞኒካዬን ለማንም እንዳትሰጡ ። ውድ ልጅዎ ኢቫን ዙኮቭ ፥ ውድ አያቴ እንዳይቀሩ ኑልኝ ።”

ሻንካ ወረቀቱን ሁለት ጊዜ አጠፈና ከትናንት ወዲያ በአንድ ኮፔክ የገዛው ፖስታ ውስጥ ከተተ ።

. . . ትንሽ አሰበና ቀለሙን አጥቅሶ “ለአያቴ” ብሎ ጻፈበት ። ራሱን አከከና እንደገና አሰበ ፣

“ኮንስታንቲን ማካሪች መንደር ”የሚል ጨመረ በት ። ደብዳቤውን ለመጻፍ የከለከለው ሰው ባለመ ኖሩ ተደስቶ ፥ ቆቡን አደረገና በሸሚዙ ላይ ኮት ሳይ ደርብ ወደ ጎዳናው ሮጠ ።

ከትናንት በስቲያ ባለሉካንዳ ቤቶችን ጠይቆ ደብ ዳቤዎች በፖስታ ሣጥኖች ውስጥ እንደሚቀመጡና ከዚያም በሰካራም ነጂዎች የሚነዱና ቃጭል ባላቸው በሦስት ፈረስ በሚጐተቱ ፥ የፖስታ ሰፃመላለሻ ሠረገላዎች አማካይነት በመላው ዓለም እንደሚሠ ራጩ ነግረውታል ። ሻንካ በቅርብ ወዳለው ፖስታ ሣጥን እየሮጠ ሔዶ የተከበረች ደብዳቤውን በቀዳዳው አስገባት ።

ከአንድ ሰዓት በኋላ ፥ በጥሩ ተስፋ ተታሎ ድብን ያለ እንቅልፍ ወሰደው . . . .በሕልሙም የዱሮ ቤታ ቸው ምድጃ ታየው ። በምድጃው አጠገብ ደግሞ አያቱ ባዶ እግራቸውን አጣምረው ተቀምጠው የላከላቸውን ደብዳቤ ለወጥ ቤቶች ያነባሉ . . . .ኤል ጭራውን እየቆላ በምድጃው አጠገብ ወዲያና ወዲህ ይመላለሳል ።

ባለ ሁለት ታዛ ቤት

የአንድ ሠዓሊ ታሪክ

ይህ ሁሉ የሆነው ፥ ከስድስት ወይም ሰባት ዓመት በፊት ቤሌኩሮቭ የተባለው የመሬት ከበርቴ ርስት በሆነችው ቲ. ግዛት ውስጥ እኖር በነረበት ጊዜ ነው ። በሌኩሮቭ በጧት መነሣት የሚወድ ፥ ሙሉ የገበሬ ልብስ የሚለብስ ፥ ማታ ማታ ቢራ መጠጣት የሚያዘወ ትርና ሁልጊዜ ሰዎች እንደማያዝኑለት የሚያማርር ወጣት ሰው ነው ። የሚኖረው በአትክልቱ ውስጥ ባለች አንዲት ጐጆ ሲሆን ፥ የኔ መኖሪያ ትልቁ ቤት ውስጥ ነው ። መኖሪያዬ በመኻሉ አንድ ትልቅ ምሰሶ ያለበት ሰፊ ክፍል ሲሆን ፥ ከምተኛበት ሶፋና ከምሠክ ዝበት ጠረጴዛ በቀር ምንም ዕቃ የለበትም ። ሁል ጊዜ አየሩ ጸጥ ባለበት እንኳን ፥ አሮጌው ምድጃ ድምፁ ይሰማል ። መብረቅማ ባለ ጊዜ ጠቅላላው ቤት ተነኳኩዮ እንደሚወድቅ ይንቀጠቀጣል ። በተለይ ነፋሱ በበዛበትና ዐሥሩም ትልልቅ መስኮቶች የብልጭታውን ብርሃን በሚያሳዩበት ጊዜ ሁኔታው ያስደነግጣል ።

ሰነፍ በመሆኔ አንድም ነገር አልሠራም ። አንዳንዴ ለብዙ ሰዓት መስኮት ላይ እቆምና ሰማዩን ፥ አእዋፋቱን ፥ የአትክልቱን ሥፍራ እመለከታለሁ ፤ ከዚያም ፀፖስታ ቤት የሚመጡልኝን ደብዳቤዎች አነብና

አተኛለሁ ። አንዳንዴ ከቤት እወጣና እስኪመሽ እሠራለሁ ።

አንድ ቀን ከዙረት ወደ ቤቴ ስመለስ ፣ ከዚህ ቀደም አይቼው የማላውቀው አንድ ሰፊ እርሻ አጠገብ ደረስኩ ። ጀንበር እየጠለቀች ነበር ። መዘርዘር በጀመረው የስንዴ ማሳ ላይ የምሽት ጥላ ጥሏል ። በሁለት ረድፍ ጥቅጥቅ ብሎ ያደገው ረጃጅም ጥድ በውስጡ ሲያልፉ ትዝታ ውስጥ የሚያስገባ ውበት አለው ። አንድ መንጤ ላጠያ አግኝቼ ወደ አትክልቱ ገባሁና እንደ ፍራሽ ትምቡክ ፣ ትምቡክ የሚለው የቅጠሎች ርጋፊ ምንጣፍ ላይ መራመድ ጀመርኩ ። ጸጥ ያለና ጥላ የበዛበት ነው ። ወርቃማው የፀሐይ ብርሃን ግን በሸረሪቶች ድር ውስጥ እንደ ቀስተ ዳመና ይንጸባረቃል ። የዛፎቹ መዓዛ አካባቢውን አውዶታል ። ወዲያው የሎሚ ዛፎች የሞሉበት መስክ ላይ ደረስኩ ። እዚህም የሚታየው ሁሉ ስላለፈና ስላረጀ ነገር ያስታውሳል ። የአምና ቅጠሎች በእግሬ ስረግጣቸው የጎዘን እንጉርጉሮ የሚያሰሙ ይመስላሉ ። በዛፎቹ ግንዶች ላይ የምሽት ጥላ ጥሏል ። በግራ በኩል ባለው አሮጌ የአትክልት ስፍራ አንድ ወፍ የጐረነነ ድምፅ ያሰማል ። ወፉም እንደ ማንኛውም በአካባቢው ያለ ነገር ያረጀ መሆን አለበት ። አንድ ሰፊ በረንዳ ያለው አሮጌ ቤት ደጃፍ ስደርስ የሎሚ ዛፎች ተክል አበቃ ። ወዲያው አንድ አጥር ግቢ በዳርቻው የገላ መታጠቢያ ያለበት አንድ ኩሬ ፣ እንዲሁም ጥቅጥቅ ያለ ሽምበቆ ተመለከትኩ ። ከኩሬው በወዲያኛው በኩል ባሉ ቤቶች መኻል አንድ ረጅም ፣ ቀጭን የቤተክርስቲያን ደወል ቤት

አለ ። አናቱ ላይ ያለው መስቀል በመጥልቅ ላይ ባለችው ፀሐይ ብርሃን ይንጸባረቃል ።

ይህን እይታ ከዚፀ ቀደም በሕፃንነቴ እንዳየሁት ሁሉ አንድ የማውቀው ነገር ፣ ማለትም አንድ ከረጅም ጊዜ በፊት ያየሁት መስሎኝ ለጥቂት ጊዜ አሰላሰል ጀመር ።

ከግቢው ወደ ሜዳው የሚወጣበት በር ከነጭ ጥርብ ድንጋይ የተሠራና የአንበሶች ቅርፅ ያልበት ነው ። እበራፉ ላይ ሁለት ልጃገረዶች ቆመዋል ።

ከሁለቱ ተለቅ የምትለዋ ፣ ቀጭን ፣ ወርቃማ ጸጉሯን አናቷ ላይ በወፍራሙ የተሠራችው ፣ አፈ ትንሽ ፣ ኮስታራ ቆንጆ ልጅ እኔን አልተመለከተችም ። ከዐሥራ ሰባትና ዐሥራ ስምንት ዓመት የማይበልጣት ሌላዋ ፀጣም ወጣት የምትመልለዋም ደግሞ ነቃ ያለችና ሸንቃጣ ናት ። አፏ ሰፊ ሲሆን ዐይነ አፋር ብጤ ነች ። እኔ ሳልፍ አንድ ሁለት ቃል በእንግሊዝኛ ጣል አደረገችና በመደነቅ ዐይነት ትኩር ብላ አየችኝ ። ይህንን ውብ ፊትም ከረጂም ጊዜ በፊት አንድ ቀን ያየሁት መሰለኝ ። አንድ አስደሳች ሕልም ያየሁ እየመሰለኝ ወደ ቤቴ ተመለስኩ ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ፣ አንድ ቀን ከሰዓት እኔና ቤሊ ኩሮቭ ከቤታችን ፊት ለፊት ስንንሸራሸር ረጂሙን ሣር በጐማው እያንኮሻኮሸ አንድ ሠረገላ ወደ ግቢ ገባ ። ካየኋቸው ልጃገረዶች ተለቅ የምትለዋ ሠረገላው ላይ ተቀምጣለች ። በእሳት አደጋ ለተጐዱ ሰዎች ዕርዳታ መሰብሰቢያ ዝርዝር ይዛለች ። እኛን ሳታይ በሲያ

ኖቮ መንደር የተቃጠለውን ቤት ፥ መጠለያ ያጡ ሰዎችን ፥ የሴቶችንና የሕፃናትን ቁጥር ፥ ለነዚህ ተጐጂዎች ዕርዳታ ለመሰብሰብ የተቋቋመው እሷ አባል የሆነች በት ኮሚቴ ፥ ሊወስድ ያሰበውን ጊዜያዊ መፍትሔ በዝርዝርና በሚያሳዝን ሁኔታ አብራራችልን ። ዝርዝሩን እንድንፈርምበት ሰጠችንና ፥ ትታው ለመሔድ ተነሣች ።

"ፒዮትር ፔትሮቪች ፥ አሁንስ ጨርሶ ረስተኸናል" አለችው ቤሌኩሮቭን ፥ እጅዋን ወደሱ እየዘረጋች ። "ናና ጠይቀን አቶኒ" በማለት ስሜን ጠራችና ፥ "የሚያደን ቁትን ሰዎች ሊተዋወቃቸው ከፈለገም ፥ እናቴና እኔ ልናስተናግደው ዝግጁ ነን" አለች ።

እጅ ነሣሁ ።

ከሔደች በኋላ ፒዮትር ፔትሮቪች ስለሷ ይነግረኝ ጀመር ። እሱ እንደ ነገረኝ የጥሩ ቤተሰብ ልጅ ስትሆን ስሟም ሉዳ ቮልካኒኖቭ ይባላል ። ከናቷና ከእኅቷ ጋር የሚኖሩበት ቦታም ሆነ ፥ ከኩሬው ወዲያ ያለው መንደር ሽልኮቭካ ይባል ነበር ። አባቷ በሞስኮ የታወቁ ባለሥልጣን የነበሩ ሲሆን ፥ ከመሞታቸው በፊት ልዩ አማካሪ ሆነው የነበሩ ፥ ጥሩ ኑሮ የሚኖሩ ቤተሰቦች ቢሆኑም ፥ የቮልካኒኖቭ ቤተሰቦች ዓመቱን በሞላ ከገጠር አይወጡም ። ሉዳም በተወለደችበት በሽልኮቭካ በሚገኘው የአስተዳደር ክልል ትምህርት ቤት ታስተምራለች ። ደመወዟም በወር ኻያ አምስት ሩብል ነው ። ገን ዘቡን ለግል ወጭዋ በማብቃቃት የራሷን ኑሮ ለመምራት በመቻሏ ተደስታ ትኖራለች ።

“ግሩም ቤተሰብ” አለ ቤሎኩሮቭ፣ “አንድ ቀን ቤታችው መሔድ አለብን ፤ አንተማ ብትሔድላቸው በጣም ደስ ይላቸዋል ።”

አንድ ቀን ከምሳ በኋላ-የሆነ በዓል ቀን ነበር-የቮልካ ኒኖቭን ቤተሰብ አስታወስንና ወደ ቬልኮቭካ ጉዞ ጀመርን ። እናትዮዋና ሁለቱም ልጆቻቸው እቤት ነበሩ ። እናታቸው ፡ የካቲሪና ፖቭሎቭና ፣ በጊዜአቸው ቆንጆ የነበሩ ይመስላሉ ። ሲያዩዋቸው ያለዕድሜያቸው አርጅተው ቁና ቁና ይተነፍሳሉ ፤ ይተክዛሉ ፤ ይፈዛሉ ። ስለ ሥነ ጥበብ በማውራት ሊያስደስቱኝ ሞክሩ ። ልጃ ቸው ወደ ቬልኮቭካ የምመጣ መሆኔን ስለ ነገረቻቸው ሞስኮ በኤግዚቪሽን ካዩዋቸው ስለ መሬት ውበት ከሣልኋቸው ሥዕሎች አንድ ሁለቱን ወዲያው አስ ታወሱና በነሱ ውስጥ ምን ለማሳየት እንደ ፈለግሁ ይጠይቁኝ ጀመር ። እቤት ውስጥ ሌዳ እያሉ የሚጠ ሯት ሊይዲያ ብዙውን ጊዜ ከኔ ይልቅ ከቤሌኮሮቭ ጋር ታወራለች ። ፊቷን ኮስተር አድርጋና ምንም ፈገ ግታ ሳታሳይ ፣ ለምን በአስተዳደሩ ክልል ውስጥ እንደ ማይሳተፍና ለምንስ አንድም ጊዜ በስብሰባ እንዳል ተገኘ ትጠይቀዋለች ።

“ልክ አይደለም ፣ ፒዬትር ፒትሮቪች” አለችው በወቀሳ መልክ ። “ጨርሶ ትክክል አይደለም — በአድራ ጎትህ ማፈር ይገባሃል ። ”

“ልክ ነው ሌዳ ፣ ልክ ነሽ” አሉ እናቷም ። “ደግ አላደረገም ። ”

“ግዛታችን በሞላ በባላጊን እጅ ነው” አለች ሉዳ ወደኔ መለስ ብላ ። “ባላጊን የአካባቢው ቦርድ ሊቀ

መንበር በመሆኑ ፥ የኢክስትና የአጐት ልጆቹን ባለው ዐታ ሁሉ ስላስቀመጣቸው የፈለገውን ያደርጋል ። መቃ ወም አለብን ። እኛ ወጣቶች ጠንካራ ፓርቲ መመሥ ረት አለብን ፤ ግን የኛ ወጣቶች እንዴት እንደሆኑ ታየ ቸዋለህ ። እጅግ መጥፎ ነው ፥ ፒዬትር ፔትሮቪች ።''

ስለ አስተዳደሩ በሚነገርበት ጊዜ ታናሿ ዜንያ ቃልም አልተነፈሰች ። ቤተሰቧ እንዳደገች ስለማይቆ ጥራት ቁም ነገር ሲነገር አትሳተፍም ። አሁንም ትንሽ ሕፃን በነበረች ጊዜ የተቀጠረችላትን አስተማሪ በምት ጠራበት ስም ሚሲ እያሉ ነው የሚጠሯት ። በእጇ ይገፍ ስለማየው የቤተሰብ አልበም ፀዝርዝር እየነገረችኝ ፥ ትኩር ብላ ትመለከታለች ። '' ይኸ አጐቴ ነው . . ይህ የክርስትና አባቴ ነው'' አለች ፎቶግራፎቹን በጣቷ እየነ ካች፤ ደረቷ ፀትካሻዬ ላይ ፊተሻሽ በደንብ ያላጐጠጐጡት ጡቶቿ ፥ ቀጭን ትክሻዋ ፥ ጉንጉን ጸጉሯ ፥ በጠቅላላ ቀጭን ገላዋና በቀበቶ የታሰረው ወገቧ ትክሻዬን እየነካኩት ።

ውጭ ወጥተን ቴኒስ ተጫወትን ፤ በአትክልቱ ውስጥ ተንሸራሸርን ፤ ሻይ ጠጣን ፤ ከዚያም በእራት ላይ ረዘም ላለ ጊዜ ስንጫወት ቆየን ። ከዚያ ባዶ ሰፊ ክፍል ወጥቼ በዚች በግድግዳዎች ላይ ምንም ሥዕል በሌለበት ጠባብ ቤት በደንብ ተዝናናሁ ። አሽክ ሮቻቸውን እንኳ ቢሆን ፥ እንደ ተለመደው አንተ ብለው ሳይሆን ''እርስዎ'' ብለው ነው የሚጠሩት ። ሉዳና ሚሲ አካባቢውን ንጹሕና የወጣትነት ስሜት ያለ በት አድርገው ስለ ያዙት ፥ ሁሉም ነገር በመግባባት ይካ ሔዳል ። በራትም ላይ ሌዳ እንደገና ለቤሉኩሮቭ ስለ አስተዳደሩ ስለ ባላጊንና ስለ ትምህርት ቤቱ ቤተ

መጻሕፍት አሜወተችው ። በእምነቷ የጸናች ፣ ታማ ኝና ጠንካራ ናት ። በተማሪ ቤት ስለ ለመደች ሊሆን ይችላል ፤ ጮክ ብላ ብዙ የምትናገር ቢሆንም ፣ ንግግሯ ማራኪ ነው ። ጓደኛዬ ፒዬትር ፔትሮቪች ግን ፣ ሁሉ ንም ንግግር ወደ ክርክር የመለወጡን የተማሪ ቤት ባሕሪውን ገና አልተወም ። ዕውቀቱንና ተራማጅ አስ ተሳሰቡን ለማሳየት ባለው ፍላጐት ለረጂም ጊዜ ፣ በሚያሰለች መልክ ክርክሩን ይቀጥላል ። በክርክሩ እጁን ሲያወናጭፍ የሾርባውን ማቅረቢያ ማህን ስለ መታው ሾርባው ተደፋና ጠረጴዛው ላይ እንደ ኩሬ ተንጣለለ ። ደግነቱ ከኔ ፀቀር ያለተዋለው ያለ አይመ ስልኝም ።

ወደ ቤታችን ስንመለስ ጨለማና ጭር ያለ ነበር ።

“መልካም አስተዳደግ የሚታየው ሾርባ በጠረጴዛ ላይ በመድፋት ሳይሆን ፣ ሌላው ሲደፋ ባለማስተዋሉ ላይ ነው” አለ ቤሌኩሮቭ ። “በእርግጥ ደስ የሚልና በጥሩ ሥነ ምግባር ያደጉ ናቸው ፤ ከጥሩ ሰዎች ጋር ግንኙነት አጭርጮራሴን ጣልኩት ። ብዙ ፣ ብዙ መደ ረግ ያለበት ነገር አለ ። ”

ጥሩ ባለመሬት ለመሆን ከተፈለገ ምን መደረግ እንዳለበት አሜወተኝ ። ምን ዐይነት ሰነፍና የማይጨ በጥ ሰው እንደሆነ ከአነጋገሩ ገመትኩኝ ። ቁም ነገር ሲያወሩ የነገሩን አቅጣጫ ይለውጣል ። ሁሉንም ነገር እንደሚነገረው በቀስታ ፣ ወደ ኋላ በመጐተት ፣ ነገርን ማራዘም የሚወድ ነው ። የተግባር ሰው አይመስለኝም ፤ ሌላው ቀርቶ ፖስታ ቤት እንዲያስገባ ደብዳቤ ከሰጠ ሁት እንኳን እኪሱ ውስጥ ለሳምንታት ያስቀምጣል ።

ከሁሉም የሚያናድደኝ ከጐኔ እየተራመደ ፡ "ሁል ጊዜ ትሠራለህ ፡ ትሠራለህ ፡ ግን ማንም አያውቅልህም ፡ ጨርሶ የሚያዝንልህ የለም" እያለ ማጉተምተሙ ነው።

የቦልካኒኖቭን ቤተሰብ በየጊዜው እየሔድኩ መጠየቅ ለመድኩ ። እዚያ በሔድኩ ቁጥር ብዙ ጊዜ የም ቀመጠው ፡ ወደ በረንዳው የሚያስወጣው መጨረሻ ደረጃ ላይ ነው ። በቶሎና በከንቱ እያለፈ ያለው ሕይወቴ እያሳዘነኝ ሰውነቴ በጸጸት ይነዳል ። ለህልውናዬ ከባድ ጫና የሆነብኝን ልቤን ባፈነዳው ይሻላል የሚል ስሜት በሰውነቱ ውስጥ ይመላለሳል ። በየጊዜው በበረ ንዳው ላይ ውይይት ይደረጋል ፤ ቀሚሶች ይንሿሿሉ ፤ የመጻሕፍት ገጾችም ይገለበጣሉ ። ወዲያው ሌዳ በሽተ ኞችን እንደምታክም ፡ መጻሕፍት እንደምትሰጣቸውና ቀን ቀን ጃንጥላ ይዛ ወደ መንደር እንደምትሔድና ማታ ማታም ስለ አስተዳደሩና ስለ ትምህርት ቤቶች ጮክ ብላ እንደምታወራ ማወቅ ቻልኩ ። ይህች ዘለግ ላጋ ፡ መልከ ቀናና ኮስተር ያለች ልጃገረድ በርቱዕ አንደበቷ ስለ ተግባራዊ ጉዳዮች መናገር ስትጀምር ፡

"ይህ አንተን አያስደስትም" ትለኛለች ።

እኔን ጠልታኛለች ። በሥዕሎቼ ውስጥ የመሬትን ውበት እንጂ የሰዎችን ፍላጎት ስለማላንጸባርቅና ፡ እሷ በጣም ለምታምንባቸው ነገሮች ደንታ ቢስ አድርጋ ስለ ቆጠረችኝ ጠልታኛለች ። በባይከል ሐይቅ ዳርቻ ፈረስ ስጋልብ ሸሚዝና ሰማያዊ ሱሪ ለብሳ ፡ እግሯን አንፈራጣ የምትጋልብ አንዲት የአካባቢው ልጃገረድ ያገኘሁበት ፅለት ትዝ ይለኛል ። የያዘችውን ዋሽንት

እንድትሸጥልኝ ጠየኳት ። እሷ ግን ፥ አውሮፓዊ መል ኬንና ባርሜጣዬን በጥላቻ ዐይን ትኩር ብላ ካየች በኋላ ፥ ከኔ ጋር በመነጋገር ከአንድ ደቂቃ በላይ ማሳለፏ ስላንገሸገሻት ሸመጠጠች ። ሌዳም ብትሆን በእኔ ላይ አንድ ባዕድ ነገር እንዳለ ይሰማታል ። እንደምትጠላኝ በግልጽ ያሳየችው ምልክት የለም ፤ እኔ ግን ይሰማኛል። ብስጭቴን ዋጥ አድርጌ ደረጃው ጫፍ ላይ እቀመጥና የሕክምና ሙያ ሳይኖር ገበሬዎችን ማከም ማታለል እንደሆነ ፥ ሰፊ መሬት ካለ ለጋስ መሆንም እንደማያዳ ግት እናገራለሁ ።

እኅቷ ሚሲ ግን ፥ ለምንም ነገር ደንታ ስለሌላት ፥ እንደኔው ጊዜዋን የምታሳልፈው ሥራ ፈትታ ነው ። ጧት እንደተነሣች እበረንዳ ባለው ባለ መደገፊያ ወን በር ላይ እግሯን እንጠልጥላ ትቀመጣለች ። ወይም በሎሚ ዛፎች ውስጥ ትደበቃለች ፤ ወይም ወደ ሜዳ ወጥታ መጽሐፍ ታነባለች ። የመጽሐፉን ገጾች በጒጒት እየገለበጠች ሙሉ ቀን ታነባለች ። ዐልፎ ዐልፎ ብቻ ነው የድካም ስሜት የሚታይባት ። እንዲህ የምታነበው በአዕምሮ ጭንቀት ለመሆኑ የፊቷ መገርጣት አንድ ማስረጃ ነው ። እኔ ስመጣና መምጣቴንም ስታይ መጽ ሐፉን ታጥፍና ትልልቅ ዐይኖቿን በፊቴ ላይ ተክላ ክተለያየን በኋላ ስለሆነው ነገር ሁሉ ታጫውተኛ ለች ። ማድቤት ያለው ጢስ መውጫ ተቀጣጥሎ እን ደነበር ፥ ከሠራተኞቻቸው አንዱ ትልቅ ዓሣ መያዙን ሁሉ ትነግረኛለች ። በሥራ ቀናት ብዙውን ጊዜ ደማቅ ሸሚዝና ደማቅ ሰማያዊ ቀሚስ ትለብሳለች ። አብረን ሽርሽር እንወጣና እንጀራ እንለቅማለን ፤ ጀልባም እን

ቀዝፋለን ። እንጆሪ ለማውረድ ወይም መቅዘፊያውን ለመያዝ ስትንጠራራ በሰፊው እጅጌዋ ውስጥ ቀጭን ለስላሳ ክንዶቿ ይታዩኛል ። ወይም ምሥሏን ስሠራ ቆማ በአድናቆት ትመለከታለች ።

በሐምሌ ወር መጨረሻ አንድ እሑድ ፅለት ጧት ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ ቮልካኒኖቮች ቤት ለመሔድ መንገድ ጀመርኩ ። በዚያን ወቅት እንጉዳይ እንደ ልብ ስለሚበቅል ፣ ያልበትን እያስተዋልኩና ሳገኝም በጁላ ከዜንያ ጋር ተመልሰን ለመልቀም እንድንችል ምልክት እያደረኩ ከቤቶች ርቄ ሜዳ ሜዳውን ተጓዝኩ ። ሞቃት አየር ይነፍሳል ። ዜንያና እናቷ ነጣ ያለ ልብስ ልብሰው ከቤተ ክርስቲያን ሲመለሱ አየኋቸው ። ዜንያ ነፋሱን ለመከላከል ባርሜጣዋን በነፋሱ ፀኩል ይዛለች ። ከዚያም እበረንዳው ላይ ተቀምጠው ሻይ ሲጠጡ ድምፅ ተሰማኝ ።

በሰበብ አስባቡ ሥራ ፈቶ ለመዋል ለሚፈልግ ለእንደኔ ዐይነቱ ግድየለሽ ሰው የበጋ ወራት እሑድ ጧት እጅግ ያስደሰታል ። የጧት ጤዛ ያዘለው አረንጓዴ ተክል የፀሐዩን ብርሃን ሲያንጸባርቅ ፣ ከአትክልት ቦታዎች ካሉ አበቦች የሚመጣው መዓዛ አካባቢውን ሲያውድ ፣ ከቤተ ክርስቲያን የተመለሱ የሚያማምሩና ተጊያጊጠው የለበሱ ወጣቶች በአትክልቱ ውስጥ ሻይ ሲጠጡ ፣ እነዚህ ጤናማ ፣ በእንክብካቤ ያደጉና የሚያማምሩ ሰዎች ዕድሜ ልካቸውን ምንም እንደማይሠሩ ሳስብ የእኔም ኑሮ እንደነሱ በሆነልኝ ብዬ እመኛለሁ ። ያን ፅለትም ጧት ይህንኑ እያሰላሰልኩ ሙሉውን ቀን ፣

ሙሉውን በጋ ሳልሠራ ለመንሸራሸር እያሰብኩ በአት ክልቱ ውስጥ ተንዝዤ ።

ዜንያ ፥ ከንዲ ላይ ቅርጫት አንጠልጥላ ብቅ አለች። ከአካሆኗ እኔ አትክልት ውስጥ መኖሬን ዐውቃ ፥ ወይም እንደምታገኘኝ አስባ እንደ መጣች ግልጽ ነበር። እንጉዳይ እየለቀምን እንጫወታለን ። አንድ ነገር ስትጠ ይቀኝ ፊቴን ለማየት ወደፊት ታልፋለች ።

"ትናንትና እዚህ መንደር አንድ ተአምር ተፈ ጸመ" አልችኝ ። "ፔላጊያ የተባለች ሽባ ሴትዮ ዓመ ቱን ሙሉ ታማ ቆይታ ፥ ማንም ሐኪም ፥ ምንም ዐይ ነት መድኃኒት ተሞክሮ ሊያድናት አልቻለም ነበር ። ታዲያ ፥ ትናንትና አንድ ፀዋቂ ሴትዮ በላይዋ ላይ ስታ ፏጭባት ጊዜ ዳነች ፤ እስካሁን ይሽው ጤናማ ናት።"

"ይህ ቀላል ነው" አልኳት ። "ተአምር የምንጠ ብቀው ሰዎች ሲታመሙ ወይም ሲያረጁ ብቻ መሆን የለበትም ። ጤንነት ራሱ ተአምር አይደለም ? ሕይወትስ? ለኛ ሊገባን ያልቻለ ሁሉ ተአምር ነው ።"

"ሊገባህ የማይችል ነገር ሲፈጸም አትፈራም?"

"ጨርሶ ፥ የማይገባኝ ክስተት ሲያጋጥመኝ በድ ፍረት እጋፈጣለሁ እንጂ ፥ በቀላሉ አልቀበልም ። እኔ ከነዚህ በላይ ነኝ ። የሰው ልጅ ራሱን ከአናብስት ፥ ከነብር ፥ ከክዋክብት ፥ ከማንኛውም ተፈጥሮ በላይ አድ ርጐ መገመት አለበት ። ከእሱ ዕውቀት ውጭ በመሆና ቸው ተአምር አድርጐ ከሚቈጥራቸው ነገሮች ሁሉ ራሱን የበላይ አድርጐ መቁጠር አለበት ። አሊያማ

ኮሽታ በሰማች ቁጥር እንደምትደነብር አይጥ እንጂ ሰው ሊሆን አይችልም ።''

ዜንያ አርቲስት በመሆኔ ብዙ የማውቅና የማላ ውታቸውን እንኳን በትክክል መተንበይ የምችል መሰ ላት ። ወደ አንድ አስደሳች ዘለዓለማዊ ዓለም ፣ በሷ ግምት እኔ በደንብ ወደማውቀው ወደ ከፍተኛው ዓለም እንዳበራት ፈለገች ። ስለ እግዚአብሔር ፣ ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወትና ስለ ተአምራት አጫወትኩኝ ። እኔም ፣ እኔ ራሴና የኔም ግምት ከሞት በኋላ የሚጠፉ መሆኑን ላለማመን ፣ '' አዎ ! የሰው ልጅ አይሞትም ፤ በእርግጥ ዘለዓለማዊ ሕይወት ይጠብቀናል'' እያልኩ እመልስላታለሁ ። እሷም ሙሉ በሙሉ አምናኝ ታዳም ጠኖለች ።

ወደ ቤት ስንመለስ ፣ ድንገት ቀጥ አለችና እንዲህ አለችኝ ።

''ሌዳ ቆንጆ አይደለችም ፤ በጣም ስለማፈቅራት ለሷ ስል ሕይወቴን እሠዋለሁ ። አንተ ግን ለምን'' አለችና ዜንያ ጣቷን እጅጌዬ ጫፍ ላይ አድርጋ ፣ ''ልምን ሁልጊዜ ከሷ ጋር ትጨቃጨቃለህ ? ለምን ሁል ጊዜ ታበሳጫታለህ ?'' ስትል ጠየቀችኝ ።

''እሷ ልክ ስላልሆነች ነው ። ''

ዜንያ በተቃውሞ ራሷን ነቀነቀችና ዐይኖቿ እንባ ቋጠሩ ።

''ስለ ሰው ማወቅ አስቸጋሪ ነው'' አለችኝ ።

በዚህን ጊዜ ፣ ከአንድ ቦታ የተመለሰችው ሌዳ በእጅዋ አለንጋ ይዛ እጅግ ተውባና ደምቃ እበረንዳው ላይ ቆማ ለሠራተኛው ትእዛዝ ትሰጣለች ። እየተቻኮለችና ጮክ ብላ እየተናገረች ለሁለት ወይም ለሦስት በሽተኞች የሕክምና ዕርዳታ ሰጠች ። ከዚያም ሥራ እንደ በዛባት አንዱ አንዱን ቁም ሣጥን ፣ ሌላ ጊዜ ሌላ ውን እየከፋፈተችና እበረንዳውም ላይ እየወጣች ከክ ፍል ክፍል ትመላለሰለች ። ፈልገው ለምሳ ጠሯት ፤ ስት መጣ ግን እኛ ሾርባችንን አገባደናል ። በዚህ ዕለት የተደረገ ልዩ ነገር ባይኖርም ፣ እነዚህ ጥቃቅን ድርጊ ቶች በጉልህ ይታወሱኛል ። ይህ ዕለት ልዩ ትዝታ ጥሎ ብኛል ። ከምሳ በኋላ ዜንያ እባለ መደገፊያው ወንበር ላይ ዘና ብላ ተቀምጣ ታነባለች ፤ እኔም እበረንዳው መጨረሻ ደረጃ ላይ ተቀምጫለሁ ። ቃልም አልተነፈ ስን ። ሰማዩ በቁልል ደመና ተሸፍኖ በመጠኑ ያካ ፋል ። ሞቃት ቀን ነው ፤ ነፋሱ ጸጥ ብሏል ፤ የዚህ ዐይ ነቱ ቀን ለምን ጊዜውም የማይለወጥ መሰለ ። ግና ከእንቅልፋቸው ሙሉ በሙሉ ያልነቁት ዩካቴሪና ፖቭ ሎቭና በእጃቸው ማራገቢያ ይዘው ወደ በረንዳው ወጡ።

"እንዴ ፣ እማዬ! የቀን መኝታ ላንቺ ጥሩ አይደ ለም" አለች የእናቷን እጅ እየሳመች ።

በጣም ይዋደዳሉ ።

አንዳቸው ወደ አትክልቱ ውስጥ ከገቡ ፣ አንዳቸው ሁል ጊዜ እበረንዳው ላይ ቆመው በዛፎቹ ውስጥ በዐይ ናቸው እያማተሩ" ኩኩ ፣ ዜንያ" ወይም "እማዬ ፣ የት ነሽ ?" ሳይባባሉ የሚውሉበት ዕለት የለም ። ምንም

ሳይነጋገሩ እንኳን በሐሳብ ይግባባሉ ። ስለ ሌላ ሰው ያላቸው አመለካከትም ይመሳሰላል ። ዩኒቴሪና ፖቭሎቭና እኔንም ወደዱኝ ፤ እቤታቸው ሳልመጣ ሁለት ወይም ሦስት ቀን ካሳለፍኩ ደኅና መሆኔን ለመጠየቅ ይልኩ ብኝ ጀመር ። ሥዕሎቼን በአድናቆት ይመለከታሉ ፤ እንደ ሚሲ የሆነውን ሁሉ በግልጽ ያጫውቱኛል ። በየጊዜው የልባቸውን ያዋዩኛል ።

የትልቋ ልጃቸው ጉዳይ ያስጨንቃቸዋል ። ሌዳ የፍቅር ነገር አታውቅም ፤ ቁም ነገር ብቻ ነው የምታወራው ። በራሷ ልዩ ዓለም ነው የምትኖረው ። እናም በልዩ ክፍሉ የተሸሸገው የመርከብ አዛዥ ፥ ለመርከበኞች ድብቅ የሆነውን ያህል ትልቋ ልጃቸውም ለእናቷና ለእኅቷ ድብቅ ናት ።

“ሌዳኮ ጥሩ ሰው ናት ፥ አይደለችም ?” ይላሉ እና ትየዋ ብዙውን ጊዜ አሁንም ዝናቡ እየዘነበ ሳለ ስለ ሌዳ ተጨዋውተን ። እናትዮዋ በፍርሃት ዙሪያውን እየቃኙ ፥ “እጅግ የምትደነቅ ናት ። እንደሷ ያለ ጨርሶ አልተፈጠረም ፤ ግን እንዲያው የሷ ነገር ያስፈራኛል ። ትምህርት ዌት ፥ ሕክምና ፥ መጻሕፍት በሞላ በጣም ጥሩ ናቸው ። ግን ከመጠን በላይ ሲሆን ለምን ይጠቅማል? ዕድሜዋ ወደ ሻያ አምስቱ እየተጠጋ ነው ፤ ስለ ወደፊት ሕይወቷ በደንብ ማሰብ ይገባታል ። እነዚህ ሁሉ መጻሕፍትና የሕክምና ሥራዎች አንድ ሰው ጊዜ እያለፈ መሆኑን እንዳይገነዘብ ያሳውሩታል ። ማግቢያዋ ነው ።”

ዜንያ ፥ ከማንበብ ተዳክማና ጸጉሯ ተንጨፍሮ አንገቷን ቀና አደረገችና እናቷን እየተመለከተች ለራሷ እንደምትናገር ሁሉ ፥

"ሁላችንም በአምላክ እጅ ነን ፣ እማዬ" አለች ። ከዚያም ወደ መጽሐፏ ተመለሰች ።

ቤለ!ኑሮቭ የገበሬ ኩቱንና ባለጥልፍ ሸሚዙን ለብሶ ብቅ አለ ። ቴኒስ ተጫወትን ። ሲመሽም እራት ላይ ቁጭ ብለን ሌዳ ስለ ትምህርት ቤቶችና ግዛቲቱን በሙሉ በቁጥጥር ሥር ስላደረገው ስለ ባላጊን ታሪክ ውተናለች ። የዚያን ምሽት ከቮልካኒኖቮች ቤት እንደ ወጣሁ ስለማያልቅ አሰልቺ ቀን አንድ ነገር ተሰማኝ ፣ ከዚያም የፈለገውን ያህል ቢረዝም በዚህ ዓለም ሁሉም አንደሚያልፍ ለራሴ በ!ነዘኔታ ገለጽኩ ። ዜንያ እስክ አጥር በሩ ሸኘችን ። ምናልባትም ነጪት እስክ ማታ ሙሉውን ቀን ክሷ ጋር ስላሳለፍኩ ሊሆን ይችላል ፣ ይህ ድንቅ ቤተሰብ ምን ያህል ተወዳጅ እንደሆነ ለመገ ንዘብ ቻልኩ ። ክሷ ስለይ ብቸኝነት ተሰማኝ ፣ ስለዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ በዚያ በጋ መራት ሥዕል የመሰል ፍላ ጐት አደረብኝ ።

ወደ ቤት ስንመለስ ፣"ሕይወትህ ለምን ጨለማና ተስፋ ቢስ ይሆናል?" አልኩት ቤሌኩሮቭን ። "እኔ አርቲስት ፣ ወፈፌ ስለሆንኩ ፣ ቅናትና ጸጸት ስላበገነኝ ፣ ከወጣትነቱ ጀምሮ በራሴ ሥራ እምነት ስለሌለኝ ሕይ ወቴ ጨለማ ፣ አስጠሊታና አሰልቺ ነው ። እኔ ምን ጊዜም ከድህነት አልወጣም ፤ እኔ ከንቱ ነኝ ፤ አንተ ግን ጤናማ ፣ ባለ መራትና ጨዋ ሰው ነህ ። ሕይወ ትህ ለምን እንዲህ ደብዛዛ ይሆናል ፤ ለምን አትጠቀ ምበትም ፣ ለምሳሌ ሌዳን ወይም ዜንያን እንዳታፈቅራ ቸው የሚከለክልህ ምን ነገር አለ?" ፀማለት ይጠይቀ ቀል ።

"ሌላ ፍቅረኛ እንዳለችኝ ዘንግተሃል" አለኝ ቤሉ ክሮቭ ።

ከሱ ቃር በአትክልቱ ውስጥ ባለችው ጐጆ የምት ኖረዋን ሊዩቦቭ ኤቫኖቭናን ማለቱ እንደሆነ ገባኝ ። በየቀኑ ይህቺ ደዘደዝ ፣ ቅርፅ የለሽ ሴትዮ የሩሲያ የባህል ልብስ ለብሳና በአንገቷ ዶቃ አጥልቃ ሁል ጊዜ ጀንጥላዋን ዘርግታ ፣ በአትክልቱ ውስጥ ስትንሸራሸር አሸከሮቿ ለምሳ ወይም ለሻይ ሲጠሯት እሰማለሁ። ከሦስት ዓመታት በፊት የበጋውን ወራት ለማሳለፍ ከነዚህ ጐጆዎች አንዱን ተከራየችና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፣ ምናልባትም ዕድሜዋን በሙሉ ሊሆን ይች ላል ፤ ከቤሉኩሮቭ ጋር ትኖራለች ። ከቤሉኩሮቭ አንድ ዐሥር ዓመት በዕድሜ ትበልጣለች ። በቁጥጥሯ ሥርም ስላደረገችው አንድ ቦታ ከመሔዱ በፊት ክሷ ፈቃድ መጠየቅ አለበት ። ብዙውን ጊዜ በጐረኔነ ወንዳወንድ ድምፅ ስለምትነፋረቅ ፣ ሰው እልክባትና ለቅሶዋን ኪሳ ቆመች ክቤት እንደምወጣ ስነግራት መነፋረቋን ታቆ ማለች ።

እቤት ከደረስን በኋላ ፣ ቤሉኩሮቭ ግንባሩን አኮ ሳትሮ በሐሳብ ተውጦ ሶፋው ላይ ተቀምጧል ። እኔ ቍቅር እንዳደረበት ሰው ሁለመናዬ ተረበሸና መን ፈሴ ተወሮ እክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እመላለሳ ለሁ ። ስለ ቭልካኒኖቮች ማውራት ፈለግሁ ። "ሌዳ ልታ ፈቅር የምትችለው እንደሷ ስለ ሆስፒታሎችና ስለ ትም ህርት ቤቶች ብዙ የሚያስብ የአካባቢውን ሰው ብቻ ነው" አልኩኝ ። "እሷን ለመሰለች ልጃገረድ ግን

የአካባቢው ሰው መሆን ቀርቶ ጥቁር ወተት ይታለ ብላታል ። አይ ሚሲ ፣ እንዴት ያለች ውብ ልጅ ናት!"

ከብዙ ዓመታት በኋላ ቤሌኩሮቭ የጊዜአችን በሽታ የሆነው ረጂም ተስፋ መቁረጥ ታየበት ። በልበ ሙሉ ነት ይናገራል ፤ ከአንጋገሩ እኔ የምከራከረው ይመስላል። ፀሐይ ያንደደው እልም ያለ በረሃ እንኳን በአንድ ክፍል ብቻውን ተቀምጦ ላለማቆም የጀመረ ይመስል ፣ ከሚያ ነበንብ ግለሰብ የበለጠ አሰልቺ አይሆንም ።

"ይህ ተስፋ የመቁረጥ ወይም የተስፋ መኖር ጉዳይ አይደለም" አልኩት ። "ዋናው ነጥብ ከሰዎች መነጣል ዘጠና በመቶውም ማሰብ አለመቻላቸው ነው።"

ቤሌኩሮቭ ይህን አነጋገር እሱን መሳደብ እንደ ሆነ ስለ ቆጠረ ፣ እየተበሳጨ ወጥቶ ሔደ ።

"ልዑል ከማሎዙምቮ ሰላምታ ልከውልሻል" አለች ሌዳ እናቷን ። ገና ከሽርሽር ተመልሳ የእጅ ጓንቶቿን እያወላለቀች ነበር ። "በጣም ደስ የሚል ነው ። በሚቀጥለው የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በማሎዙምቮ የሕክምና ጣቢያ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ሐሳብ እንደሚያቀርብ ቃል ገብቷል ። እንደሚለው ግን ብዙም ተስፋ የለም ። ይቅርታ አድርግልኝ" አለች ፊቷን ወደኔ ዞር አድርጋ ። "እንዲህ ዐይነቱን ነገር በየጊዜው ስለምረሳ ፣ ምንም አይጠቅምፀም ። በጣም አበሳጨኝ ።"

"ለምን አይጠቅምም "አልኳት ትከሻዬን እየነቀነቅሁ ። "የኔን ሐሳብ የማወቅ ፍላጎት የልሽም ፤ ይህ ጉዳይ እንደሚያስደስተኝ ግን በእርግጠኝነት ላረጋግጥ ጥልሽ እወዳለሁ ። "

"ይጠቅምሃል ።"

"አዎን ይጠቅመኛል ። በኔ ግምት በማስዘምፅ የሕክምና ጣቢያ አያስፈልግም" አልኳት ።

ቋጣዩ ራሱ ሐሳቤን ገለጸላት ። አጮልቃ እየተመለከተች እንዲህ አለችኝ ፤

"ታዲያ ምን ያስፈልጋል ፣ የመሬት ውበት ምስልን?"

"የመሬት ውበት ቅብም ቢሆን አያስፈልግም ። የሚያስፈልግም ነገር የለም ።"

የእጅ ጓንቶቿን ካወለቀች በኋላ ፣ አሁን ገና ከፖስታ ቤት የመጣውን ጋዜጣ ገለጠችው ። ለደቂቃ ያህል ስሚታን ለመዋጥ እየሞከረች ፣ "ባለፈው ሳምንት አና በወሊድ ሞተች ። በአካባቢው የጤና ጣቢያ ቢኖር ኖሮ ዛሬ በሕይወት ትገኝ ነበር ። የመሬት ውበት ሠዓሊዎችም ቢሆኑ ፣ ለዚህ ጉዳይ የማያጨነቁበት ምክንያት ያለ አይመስለኝም ። "

"ይህን ጉዳይ በሚመለከት ሙሉ ፍላጐት እንዳለኝ ላረጋግጥልሽ እወዳለሁ" በማለት ደግሜ ተናገርኩ ። እሷ ግን ፣ ለመስማት ያልፈለገች ይመስል በጋዜጣው ተከልላ ዝም አለች ። በእኔ ግምት የሕክምና ጣቢያ ም ፣ ትምህርት ቤቶች ፣ ቤተ መጻሕፍትና የሕክምና ድርጅቶች አሁን ባለው ሁኔታ ሰውን ባሪያ ነው የሚያደርጉት ። ሕዝቡ በከባድ እግረመውቅ ተሰንክሏል ፤ አንቺ ደግሞ ሌላ ማሰሪያ ከምትጨምሪ በቀር እነዚህን ልመ በጣጠስ ምንም ጥረት አታደርግም ፣ እምነቱ ይኸው ነው ።"

ዐይኖቿን ወደፊቱ ቀና አደረገችና በማሾፍ መልክ ፈገግ አለች ። እኔ ግን ፣ መሠረታዊ ሐሳቤን ለማስረዳት ባለኝ ፍላጐት የተነሣ ንግግሬን ቀጠልኩ ።

"ዋናው ነጥብ የአና በወሊድ መሞት አይደለም ። ዋናው ችግር አና ፣ ማርታና ፣ ፔላጊያ ከጥቂት እስከ ማታ ደፋ ቀና ሲሉ መባተላቸው ፣ በከባድ ሥራ የተነሣ ሕመም ላይ መውደቃቸው ፣ ሕይወታቸውን በሞላ ስለ ችግር ፣ ስለ ታመሙ ልጆቻቸው ፣ ስለ ሕመምና በሽታ ሲያስቡ መኖራቸው ፣ በሕይወታቸው ሳያልፍላቸው ፣ በልጅነት ጠውልገው ፣ አለጊዜ አርጅተው ፣ ቆሽሸውና ከር ፍተው መሞታቸው ነው ። ልጆቻቸውም ገና ከፍ አን ዳሉ የእናቶቻቸውን ምሳሌ ይከተላሉ ። በዚህ ሁኔታ በመቶ የሚቈጠሩ ዓመታት ያልፋሉ ። በሚሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች አንዲት ቁራሽ ዳቦ ለማግኘት ከእንስሳ በባሰ ሁኔታ ውስጥ ይኖራሉ ። በማያቋርጥ ፍርሃት ውስጥ መኖር ። ፀጣም የሚያሰቅቀው ደግሞ ፣ ስለ ራሳቸው በእ ግዜር አምሳል ስለ መፈጠራቸው ማሰቢያ ጊዜ የሌላ ቸው መሆኑ ነው ። ረኃብ ፣ ብርድ ፣ አካላዊ ሥቃይ ፣ ዘለዓለማዊ ፍዳ ወደ መንፈሳዊ ተግባር ማለትም ሰውን ከእንስሳ የሚለየውንና ሕይወትን ጣፋጭ የሚያደር ገውን ጐዳና የሚያሳየውን መንገድ እንደ በረዶ ክምር ይዘጉታል ። እነዚህን በሆስፒታሎችና በት/ቤቶች ልት ረጂአቸው ትፈልጊአለሽ ። ስሕኪሞችና ለመጻሕፍት የሚከፈለውንና በዚህም የተነሣ ገንዘብ ለማግኘት ከመ ጥሮው የበለጠ መሥራት ያለባቸው መሆኑን እንኳ ባናነሣ ፣ እነዚህ ተቋሞች አዲስ እምነትና አዲስ ፍላ

ጎት ሕገቡ ላይ ስለሚጨምሩ ፣ የሰውን እግር ብረት የሚበጥሱ ሳይሆኑ ይበልጥ የሚያጠብቁ ናቸው ።

"ካንቱ ጋር አልከራከርም" አለች ሌዳ የያዘችውን ቃዜጣ ዝቅ አድርጋ ። "ይህን ሁሉ ዱሮም ሰምቼአለሁ ። አንድ ነገር ብቻ ነው የምነግርሁ ፣ አንድ ሰው ምንም ሳይሠራ ሊኖር አይችልም ። የሰውን ልጅ ከለበት ሥቃይ ማውጣት አለመቻላችን ግልጽ ነው ፤ ምናልባትም ብዙ ስሕተቶች ልንፈጽም እንችላለን ። ሆኖም የምንችለውን ለማድረግ እየታገልን ነው ፤ ደግሞም ልክ ነን ። በጥሩ ሥነ ምግባር ላደገ ሰው ቅዱስና ክቡር ተግባር ወንድ ሞቹን መርዳት ነው ። እኛም ዐቅማችን በፈቀደ መጠን ይህንኑ እየፈጸምን ነው ። እኛ የምናደርገው አይጥሙም፣ ግን ምን ያደርጋል ፤ ሁሉንም ማስደሰት አይቻልም ።"

"እውነት ነው ፣ ሌዳ እውነትሽን ነው" አሉ እኖቷ ።

ሌዳ ባለች ጊዜ ሁሉ ትፈራለች ። አንድ መጥፎና ተገቢ ያልሆነ ነገር እንዳትናገር ስለምትፈራ ፣ ሌዳ ስት ናገር ዐይኗን ትኩር ብላ ትመለከታለች ። ምን ጊዜም ቢሆን የሌዳን ሐሳብ አትቃወምም ፣ "እውነትሽን ነው" እያለች ክምትስማማ በቀር ።

"የገበሬው መማር ፣ በሚያሳዝኑ ግብረ ገባዊና ፀተራ ምሳሌዎች የተሞሉ መጻሕፍትና የሕክምና ጣቢያዎች ፣ ክመስኩቱ የሚንጸባረቀው ብርሃን ይህን ትልቅ የአትክልት ቦታ ከሚያበራው የበለጠ የገበሬውን ማይ ምንትና የሞት መጠን ሊቀንስ አይችልም" አለኳት፣ "በእነዚህ ሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ ገመግባት

አዲስ ፍላጐት ፣ አዲስ የሥራ ሜና ከምትጨምሪባቸው ፀቀር አንድም የምትፈይጂው ነገር የለም ።"

"ይደንቃል ፣ ግንኮ አንድ ነገር መደረግ አለበት" አለች ሌዳ በቁጣ ። ከአነጋገሯ የእኔን ክርክር ቀላልና የሚያስጠላ አድርጋ መገመቷ ይታወቃል ።

"ሰዎች ከከባድ የጉልበት ሥራ መላቀቅ አለባቸው ። መላ ሕይወታቸውን በምድጃ ሥር ፣ በአጠባ ፣ ፀመስክ ላይ ሲማስኑ ከመዋል ተላቀው ስለ ሕይወታቸው ፣ ስለ እግዚአብሔር እንዲያስቡና ፣ የአዕምሮ ችሎታቸውንም አዳብረው በሥራ ላይ ማዋል ይችሉ ዘንድ ጤናቸው ተጠብቆ የዕረፍት ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል ። እያንዳንዱ ሰው ስለ ሕይወት ምንነት ለመመራመር የሚያስችለው የአዕምሮ ችሎታ አለው ። እስቲ ከአስቸጋሪ የጉልበት ሥራ ነጻ ሆነው ነጻነታቸውን እንዲ ያውቁት አድርጊና የዚያን ጊዜ እነዚህ መጻሕፍትና የሕክምና መስጫዎች ምን ያህል ማሾፍ እንደ ሆኑ ትገነዘቢአለሽ ። አንድ ሰው ትክክለኛ ሥራውን ካወቀ የሚያስደስቱት እምነት ፣ ሳይንስና ሥነጥበብ እንጂ፣ እነዚህ ጥቃቅን ነገሮች አይደሉም" አልኩዋት ።

"የሚቻል ይመስል ፣ ከድካም ነጻ ኤድርጊያቸው" አለችና አሾፈች ሌዳ ።

"አዎን ! አንዳንዱን ሥራ እናንተ እርዱዮቸው ። እኛ የክተማ ነዋሪዎች ፣ እገሌ ከእገሌ ሳንል ፣ ሰፊው የሰው ዘር ለአካላዊ ፍላጎቱ ማርኪያ ሙሉ ጊዜ የሚ ማስንበትን ሥራ አብረን ለመሥራት ከተስማማን ፣ ምናልባትም ለእያንዳንዳችን የሚደርሰን የሥራ ጊዜ

በቀን ከሁለትና ሦስት ሰዓት በላይ አይሆንም ። እስቲ አስቢው ፤ ሁላችንም ሀብታም ደሃ ሳንባባል በቀን ሦስት ሰዓት ብቻ ሠርተን የተረፈውን ጊዜ ለራሳችን ብንጠቀም የሚኖረውን ሁኔታ አስቢ ፤ ሌላም ሁሉንም ሥራ በራሳችን ጉልበት ብቻ ከምናከናውን የጉልበት ሥራን የሚተኩ መሣሪያዎች ብንሠራና ፍላጎታችንን ዝቅ ለማድረግ ብንጥር የሚኖረውን ሁኔታም እስቲ ልብ በይ ፤ ራሳችንና ልጆቻችን በየጊዜው ለረኃብና ለቁር እንዳንፈራ እንጠናከራለን ። አና ፣ ማርታ እኖ ፔላጌያን እንደሚሠሩት በየጊዜው ስለ ጤንነታችን አንሠጋም ። መድኃኒት ባንወስድ ፣ ሐኪም ቤት ፣ የትምባሆ ፋብሪካዎች ፣ የመጠጥ ፋብሪካዎች ባይኖሩን ምን ያህል ትርፍ ጊዜ እንደሚኖረንም አስተውይ ። ይህን ጊዜ ሰላይንስና ለሥነ ጥበብ ዕድገት በጋራ እንጠቀምበታለን። ነበሬው ፀጎብረት መንገድ እንደሚሠራ ሁሉ እኛም በአንድነት ፣ በጋራ ስምምነት እውነትንና የሕይወትን ትርጉም ልናጠና እንችላለን ፤ እናም-እርግጠኛ ነኝ-እውነቱ በአጭር ጊዜ ይወጣል ፤ የሰው ልጅም ክዘለዓለማዊው ፣ ከአስፈሪውና ከተጫነው የሞት ፍርሃት እንዳያውም ከሞት ከራሱ ነጻ ይወጣል ።''

''ስለ ሳይንስ ብዙ ትናገራለህ ፤ የትምህርትን ጉዳይ ግን ትታወማለህ'' አለች ልዳ ።

''አንድን ሰው የቡና ቤት ስሞችን ከማንበብ በቀር መጻሕፍትን አንብቦ ለመረዳት የማያስችለው ዐይነት ትምህርት በአገራችን ከሩሪክ ጊዜ ጀምሮ የነበረ ነው ። በገመል ድርሰት ውስጥ የተገለጸው ፔትሩሽካ ከረጂም ዘመናት በፊት ማንቡዝ ይችል ነበር ፤ ይሁን

እንጂ ዛሬም ገጠሩ በሩራክ ጊዜ እንደ ነበረው ዐይነት ነው ። እኛ የምንፈልገው ትምህርት አይደለም ። ግን የአዕምሮ ችሎታችንን በደንብ ለመጠቀም እንችል ዘንድ የዕረፍት ጊዜ ነው ። እኛ የምንፈልገው ትምህርት በቶችን ሳይሆን ዩኒቨርሲቲዎችን ነው ።''

''በመድኃኒት አታምንም?''

''አዎ ! መድኃኒት የሚያስፈልገው በሽታን በተ ፈጥሮ ክሥተትነቱ ለማጥናት እንጂ ፣ በአዳኝነቱ አይ ደለም ። ሕክምና ካስፈልገም መታከም ያለበት በሽ ታው ሳይሆን መንሥኤው ነው ። ዋናውን ምክንያት ፣ 'የጉልበት ሥራን አስቀሩና በሽታ አይኖርም ። ለማዳን በሚጥር ሳይንስ ላይ እምነት የልኝም' እያልኩ በስሜት ቀጠልኩ ። ሳይንስና ሥነ ጥበብ የሚያተኩሩት በጊዜ አዊና በክፈል ነገሮች ላይ ሳይሆን ፣ በዘላቂና አጠቃ ላይ መፍትሔዎች ላይ መሆኑ ግልጽ ነው ። ሳይንስና ሥነጥበብ እውነትንና የሕይወትን ትርጉም ፣ የአምላክን የነፍስን ምንነት ለማወቅ ይፈልጋሉ ። እንደ ሐኪም ቤትና ቤተ መጻሕፍት ባሉ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ሲያተኩሩ ግን ፣ ሕይወትን ውስብስብና ከባድ ማድረግ ብቻ ነው የሚችሉት ። ብዙ ሐኪሞች ፣ መድኃኒት ቀማሚዎች ፣ የሕግ ምሁራንና በርካታ የተማሩ ሰዎች አሉን ። የሥነ ፍጥረት ተመራማሪዎች ፣ የሐሳብ ዐዋቂዎች ፣ ፈላስፎችና ገጣሚዎች ግን የሉንም ። አእምሮአችን ፣ መንፈሳዊ ኃይ ላችን የሚባዝነው ጊዜአዊና ዐላፊ በሆኑ ፍላጎቶች ነው . . . .ሳይንቲስቶች ፣ ደራሲያንና ሠዓሊዎች በፍላ

ጎት ነው የሚሠሩት ። ዕድሜ ለነሱ የሕይወት ምኞት በየዕለቱ ይጨምራል ፤ አካላዊ ፍላጎታችንም ይበረከታል። ሆኖም ከእውነቱ ግና ብዙ እንርቃለን ። አሁንም ሰው እጅግ ስግብግብ ፣ ክእንስሳት ሁሉ የበለጠ የተበከለ ነው ። በመሆኑም ሁሉም ነገር በአጠቃላይ ወደ ሰው ዘር ማዝቱጥና በማይሻር አኳኋን ጥንካሬን ወደ ማጣት እያዘነበለ ነው ። በእንዲህ ያለ ሁኔታ አርቲስቱ የሚሠራው ሥራ ዛሬ ያለውን ሁኔታ በመደገፍ የስግብግቡን፣ የረከሰውን እንስሳ ፍላጎት ለማርካት ስለሚሆን ፣ ሥራው ትርጉም የለሽና ይበልጥ በሙያው ታዋቂ በሆነ መጠን ፣ አድራጎቱ ይበልጥ የረከሰና ከእውነቱ ጋር ያልተጣጣመ ይሆናል ። እናም መሥራት አልፈልግም ፤ አልሠራምም ፤ የሚፈለግ ነገር የለም ፤ ዓለምም ድራቧ ይጥፋ . . .”

“እስቲ ወጣ በይ” አለች ሌዳ እናቷን ፣ ምናልባትም ንግግሯ ለአንዲት ወጣት ልጃገረድ ተስማሚ አለመሆኑን በመገመት ይሆናል ።

ዜንያ ፣ በጎዘን ከእጎቷ ወደ እናቷ ተመለከተችና ወጥታ ሔደች ። “ሰዎች ብዙዉን ጊዜ የራሳቸውን ግድ የለሽነት ትክክል ለማስመሰል እንዲህ ያለ ጥሩ ነገር ይናገራሉ” አለች ሌዳ ። “ሆስፒታሎችና ትምህርት ቤቶች የሚሰጡትን ጥቅም መካድ ከማዳንና ከማስተማር በጣም ይቀላል . . .”

“እውነት ነው ሌዳ ፣ እውነትሽን ነው” አሉ እናቷ

“ሥዕል እተዋለሁ ነው የምትለው” አለች ሌዳ ። “እንደ እውነቱ ከሆነ ሥራህን ትልቅ አድርገህ ነው የምትገምተው ። እኔ እንቲ አሁን የምታጥላላቸውን

ደካማ ቤተመጻሕፍትና ሐኪም ቤቶች በዓለም ካሉ የመሬት ምስሎች ሁሉ አብልጬ ስለምመለከት ፣ ጨርሶ ልንግባባ አንችልምና ከርከሩ ይቁም ። ” ወዲያው ወደ እናቷ ፊቷን መለስችና ፍጹም በተለየ ድምፅ ማውራት ጀመረች ። “ልዑሉ ባለፈው ጊዜ ከመጣ ወዲህ በጣም ቀጥኗል ፤ ተለውጧል ። ወደ ሺቺ ሊልኩት ነው ።”

ከኔ ጋር ላለ መነጋገር ስለፈለገች ከናቷ ጋር ስለ ልዑሉ ማውራት ጀመረች ። ፊቷ በርበሬ መስሏል ፣ መቆጣቷንም ለመሸሸግ ዐይኗ ማየት ያቃተው በማስ መሰል ጋዜጣው ላይ ተደፋች ። እኔም ይቅርታ ጠየኩና ወደ ቤቴ ለመሔድ ወጣሁ ።

ግቢው ረጭ ብሏል ። ከኩሬው ማዶ ባለው መን ደርም አንድም ድምፅ አይሰማም ። ደብዛዛው የክዋክብት ብርሃን በኩሬው ላይ ተንጸባርቆ ከሚታይ ፀቀር ጨርሶ ብርሃን አልነበረም ። ዜንያ እኔን ለመሸኘት የአንበሶች ምስል ባለበት በር አጠገብ ጸጥ ብላ ቆማለች ። “መን ደርተኛው በሞላ ተኝቷል” አልኳት ፣ በጨለማው ውስጥ ፊቷን በደንብ ለማየት እየሞከርኩ ፤ የሚታየኝ ነገር ቢኖር በግንባሯ ላይ የተተከሉት ሁለት ያዘኑ ዐይኖች ብቻ ናቸው ።“የቡና ቤት ሠራተኞችና የፈረስ ሌቦች እን ኳን ተኝተዋል ፣ እኛ የተከበርን ሰዎች ግን በረፃ ባል ረባ እየተነታረክን እንበሻሸቃለን ።”

የጥቢ ወራት እየተቃረበ መሆኑን የሚያበሥር ቀፋፊ ሌሊት ነበረ ። ከቁልል ደመና ውስጥ የምትወጣው ጨረቃ በሰፊው ግሳ ውስጥ የሚያልፈውን መን

ነድ እንኳን አታሳይም ። ተወርዋሪ ኮከቦች ሰማዩ ላይ ብተከታታይ ይወነጨፋሉ ። ዜንያ ከጐኔ መንገዱን ይዛ ትጓዛለች ። በሆነ ምክንያት የምትፈራቸውን ተወርዋሪ ኮከቦች ላለማየት አንገቷን ቀና አታደርግም ።

የሴሊቱ ቁር እያንቀጠቀጣት ፣ "ልክ ነህ" አለችኝ ። "ሁላችንም በእንድነት ለመንፈሳዊ ተግባራት ብንነሣ ፣ ሁሉም ነገር ከመቅጽበት ጣልጃ ሊሆንልን ይችላል ።"

"ያለ ጥርጥር እኛ ከፀሱ በላይ ነን ። በመሆኑም የሰውን ፅውቀት በተጨባጭ ልናሳድግ ከቻልንና ለላቀ ዓላማ ከተሰለፍን ፣ ሁላችንም ከላቀ ደረጃ ላይ እንደር ሳለን ። ይህ ግን ጨርሶ አይሆንም ። የሰው ዘር እያዘቀጠ ስለሔደ ፣ ምንም የፀዋቂነት ምልክት የማይታይበት ደረጃ የምንደርስበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ።"

ከአጥሩ በር እማንታይበት ድረስ ራቅ ብለን ከሔድን በኋላ ፣ ዜንያ ቀጥ ብላ ቆመችና ከመቅጽበት እጇን ጥብቅ አድርጋ ያዘች ።

"ደኅና እደር" አለችኝ ፣ እየተንቀጠቀጠች ። ትከሻዋ ላይ ከጣለችው ቀጭን ሽሚዝ ሌላ ስላልለበሰች ብርዱ አኮማትሯታል ። "ነገ እንድትመጣ ።"

በራሴና በሌሎች ላይ ባደረብኝ ብስጭት ብቻዬን መቅረቱ አስፈራኝ ። እኔም ተወርዋሪ ኮከቦችን አለ ማየት ጀመርኩ ።

"እባክሽ ትንሽ ጊዜ ከኔ ጋር ቆዪ" አልኳት ።

ከዜንያ ፍቅር ይሰኛል ። ምናልባትም ፍቅር የጣለ ብኝ አቀባበሏ ፣ አሸኛኘቷ ፣ በኔ ላይ የምትጥለው ወብና

ግርማ ያለው አመለካከቷ ሳይሆን አይቀርም ። ብጣሌ ፊቷ ፣ ቁጭን አንገቷና ከንዶቿ ፣ ልስላሴዋ ፣ ብቸኝነቷ ፣ መጻሕፍቷ ሁሉ እንዳፈቅራት አድርገውኛል ። አስተሳሰቧ ቢሆን ፣ ምናልባትም እኔን ከማትወደው ከውቧ ሌዲ የተለየ አስተሳሰብ ስላላት ሊሆን ይችላል ፤ የአስተሳሰቧን ስፋት አደንቃለሁ ። ዜንያ የወደደችኝ ሠዓሊ ስለ ሆንኩ ነው ። በችሎታዬ ልቧን በልቼዋለሁ ። ከኔ ጋር ሆና ይህን መንደር ፣ መስኩን ፣ ጭጋጉን ፣ የምሽቱን ውበት ፣ አስካሁን በብቸኝነትና ክንቱ አኗኗር የባዘንኩባትን ደሀን እጅግ ውብና ማራኪ ገጠር ከኔ ጋር ሆና የምትጣፋ ትንሽ ልዕልት አድርጌ ስለ ገመትኩ ፣ ለሷ ልዩ ሥዕሎች መሥራት ፈልጌአለሁ ።

"ትንሽ ቆዪ ፤ ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ" ብዬ ለመንኳት ።

ኮቴን አወለቅኩና በቀዝቃዛው ትከሻዋ ላይ ጣል አደረግኩ ። የወንድ ኮት መልበሱ የሚያስጠላባትና አስቀያሚ ስለ መሰላት ሣቀችና አውልቃ ጣለችው ። እኔም እቅፍ አድርጌ ያዝኳትና ግንባሯን ፣ ትከሻዋን ፣ እጅጅን ደጋግሚ ሳምኩ ።

የሌሊቱን ጸጥታ ለማደፍረስ የፈራች ይመስል በቀስታ እቅፍ አደረገችኝና ፣ "እስከ ነገ ድረስ" ብላ አንሾካሾከች ። "በኛ መካከል ምስጢር ስለሌለ ፣ የሆነውን ሁሉ ለእናቴና እኅቴ አሁኑኑ እነግራቸዋለሁ ። ፍቅሬ በጣም ፈርቼአለሁ ፣ ስለ እማዬ ግድየለም ። እማዬ ትወደኛለች ። ሌዳ ግን ....." ወደ አጥሩ በር እየሮጠች ሔደች ።

"ደኅና እደር" አለችኝ በሩቁ ።

ለአንድ ወይም ሁለት ደቂቃ ያህል ቆሜ እየራቀ የሚሔደውን ኩቴዋን አዳመጥኩ ። ወደ ቤቴ መሔድ አልፈለግሁም ፤ የምሔድበትም ምክንያት የለም ። ለጥ ቂት ጊዜ በሐሳብ ተውጬ እዚያው ቆምኩ ። ከዚያም እሷ ከምትኖርበት ከበረንዳው በላይ ያሉ መስኮቶች ወይን እንዳላቸውና የሆነውን ሁሉ እንደሚያውቁ አሽ ቆልቁለው የሚያዩኝ መስሎኝ ፥ ያንን ቀውላላ አሮጌ ቤት ለማየት ወደ ኋላ አዘገምኩ ። በበረንዳው አድርጌ አለፍኩና ከቴኒስ ሜዳው አጠገብ አንድ ትልቅ ዛፍ ሥር ባለው ጨለማ ውስጥ የሚገኝ አንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ቁጭ አልኩና ቤቱን ከዚያ ማየት ጀመርኩ ። ሚሲ በምትተኛበት በበረንዳው በኩል ባለው መስኮት ብሩህ ብርሃን ይታያል ፤ ከዚያም ደብዘዝ አለ ። አንድ ሰው ፋኖሱን ከልሎታል ። ጥላው ይንቀሳቀሳል . . . ልቤ በሞ ንቀት ፥ በጸጥታና በደስታ ተሞላ ። ፍቅር ሊይዘኝ በመ ቻሉ ተደሰተ ፤ ሆኖም በዚህ ጊዜ ከክፍሎቹ በአንዱ የምትኖረው የምትጠላኝና የማትፈልገኝ ሴዳ ክኔ ጥቂት እርምጃዎች ርቃ መገኘቷ ደግሞ አስጨነቀኝ ። ጆሮ ዬን አቅንቼ የዜንያን መውጣት እየጠበቅሁ ቁጭ አል ኩኝ ። ከወደ በረንዳው የሰው ድምፅ የሰማሁም መሰ ለኝ ።

አንድ ሰዓት ፀለፈ ። አረንጓዴው ብርሃን ጠፋ ፤ አንድም ጥላ አይታይም ። ጨረቃም ከቤቱ ጣሪያ ፀልፋ ጭር ባለው የአትክልት ቦታና ሰው በሌለበት መተላ ለፊያ ላይ ታበራለች ። ከቤቱ ፊት ለፊት ያሉት ጽጌረ ዳዎችና ሌሎችም አበባዎች ይታያሉ ፤ ቀለማቸው ግን

አንድ ይመስላል ። በጣም ቀዝቅዟል ። ከአትክልቱ ውስጥ ወጥቼ ከመንገዱ ላይ ኮቴን አነሣሁና ወደ ቤቴ አዘገምኩ ።

ቀሚቀጥለው ቀን ከሰዓት ወደ ቮልካኒኖቮች ቤት ለሐድ ወደ አትክልቱ ውስጥ የሚያስገባው የመስታወት በር ወለል ብሎ ተከፍቷል ። ዜንያ ድንገት ወደ ቴኒስ ሜዳው ወይም ወደ መንገዱ ላይ ትወጣለች ብዬ ተስፋ በማድረግ ከቤት የሷን ድምፅ ለመስማት እዬጓጓሁ እበረንዳው ላይ ቁጭ አልኩ ። ከዚያም ወደ ሥዕል ክፍሉና ወደ ምግብ ክፍሉ ሐድኩ ። ማንም የለም ፤ ከምግብ ክፍሉ በረጂሙ መተላለፊያ ወደ አዳራሹ ደርሼ ተመለስኩ ። በመተላለፊያው በኩል ብዙ በሮች አሉ ። ከነዚህ በአንዱ የሌዳ ድምፅ ተሰማኝ ።

"ቁራው አንድ ቦታ ጥቂት " ትላለች ድምጿን ከፍ አድርጋ በዜማ መልክ ፤ ምናልባት የቃል ጽሕፈት እያስጠናች ይሆናል ። " ጥቂት ዐይብ . . .ቁራው——ማነህ?" ብላ ጮኸች ፣ ኮቴዬን በመስማቷ ።

"እኔ ነኝ ።"

"እሺ ይቅርታ አድርግልኝ ፤ ዳሻን እያስጠናኋት ስለሆነ ወዳንተ ልመጣ አልችልም ።"

"የካቴሪና ፖብሎቭና አትክልቱ ውስጥ ናቸው ወይ?"

"አይደለችም ። እሷና እኅቷ ፔንዛ አውራጃ የሚገኘውን አጎቴን ለመጠየቅ ጧት ሐዱ ። ለክረምት ደግሞ ወደ ውጭ አገር ሳይሔዱ አይቀሩም" አለች ቅንጬ ቄየት ብላ ።

"ቁራው .....አንድ ቦታ ..ጥቂት..ዐያለ..አገኘ. ይህንን ጽፏል"

ወዲ አዳራሹ ተመለስኩና ኩፌውንና በሩቁ የሚታየውን መንደር እየተመለከትኩ በድን ሆኜ ቆምኩ። አሁንም "ጥቂት .. ቁራው አንድ ቦታ ጥቂት ዐያለ አገኘ.."የሚሉት ቃላት በሩቁ ይሰሙኛል። በመጀመሪያ በገባሁበት ፣ ግን በተቃራኒው መንገድ ከምድረ ግቢው ወጥቼ የአትክልቱን ቦታና ቤቱን ዐልፌ የሎሚ ዛፎች መደሚገኙበት ጐዳና እስኪደርስ ተጓዝኩ። እዚያ ላይ ስደርስ አንድ ትንሽ ልጅ ሮጦ ደረሰብኝና አንዲት ማስታወሻ ሰጠኝ። "ሁሉንም ነገር ለእኅቱ ነገርኳትና እንዳንገናኝ ነገረችኝ" የሚል አነበብኩ። "ቃሏን ጥሼ ላሳዝናት አልፈልግም። እምላክ መልካሙን ያጋጥምህ ይቅርታ አድርግልኝ እማዬና እኔ በጣም አዘን።"

ከዚያም በጽዶችና በተሰባበረው አጥር በኩል አድርጌ አለፍኩ። የዘረዘረው ስንዴ ተንጣልሎ ይታይ በነበረበትና ቆቆሻ ያሽካኩ በነበረበት ሜዳ ላይ ዛሬ ላሞች ይግጡበታል። ፈረሶችም ደንገላሳ ይጋልቡበታል። ዐልፎ ዐልፎ በየኮረብታው ላይ የበልግ እህል አረንጓዴ ሆኖ ይታያል። የተለመደው አሰልቺ ኑሮ ከበበኝ። ለቮልካኒኖቮች በተናገርክት ሁሉ አፈርኩ። እንደገና ሕይወት አሰልች ሆነች። እቤቴ ስደርስ ዕቃየን ጠቀለልኩና በዚያኑ ምሽት ወደ ቅዱስ ጊተርስ ዑርግ ተነሣሁ።

የቮልካኒኖቮችን ቤተሰብ ከዚያ በኋላ አላየኋቸውም። ብዙም ሳይቆይ ወደ ከሪሚያ ስሔድ ባቡር ውስጥ

ቤሌኩሮቭን አገኘሁት ። አሁንም የገዘሬ ኮቱንና ባለጥ ልፍ ሸሚዝ ለብሷል ። ስለ ኑሮው ስጠይቀው እንዲህ አለኝ ። "በጣም ደኅና ነኝ ፥ ዕድሜ ላንተ" ብዙ ተጨ ዋወትን ። የራሱን ርስት ሸጦ በሊዩቦቭ ኤባኖቭና ስም ሌላ እነስ የሚል ገዝቷል ። ስለ ቮልካኒኖቮች ብዙም ሊነ ግረኝ አልቻለም ። ልዳ አሁንም የምትኖረው ሼልኩቭካ ሲሆን ፥ በመንደሩ ትምህርት ቤት ታስተምራለች ። ቀስ በቀስ የሷን ሐሳብ የሚይጣፉ ሰዎች በዙሪያዋ ማሰባሰብ በመቻሏ ጠንካራ ፓርቲ ሆኗል ። በዚህም የተነሣ ባለፈው የአስተዳደሩ ምርጫ እስካሁን ግዛቲቱን ፀቁዮጥሩ ሥር ያደረገውን ባላጊንን በድምፅ ሊጥሉት ችለዋል ። ስለ ዜንያ የነገረኝ ነገር ቢኖር ፥ ከቤተሰቦቿ ጋር እንደ ማትኖርና የት እንደምትኖር አለማወቁን ብቻ ነው ።

ዐልፎ ዐልፎ ሥዕል ሰሠራ ወይም ሳነብ ካልሆነ ስለ ባለ ሁለት ታዛው ቤት መርሳት ጀምሬአለሁ ። በማላውቀው ምክንያት በሥስኮት በኩል ይታይ የነበ ረውን አረንጓዴ ብርሃን ፥ በውድቅት ሌሊት እሰማው የነበረውን የራሴን ኩቴ ፥ በፍቅር የቀዘቀዙ እጆቼን እያፍ ተለተልኩ ወደ ቤቱ የተመለስኩበትን ያን ሌሊት በደ ንብ አስታውሳለሁ ። አንዳንዴም ብቸኝነትና ነዘን ሲሰ ማኝ ቀስ በቀስ እኔንም እንደሚያስታውሱኝ ፥ እንደ ሚጠብቁኝና እንደገና እንደምንገናኝ ትዝ እስከ ሚ ለኝ እያሰላሰልኩ የጠፈ ትዝታ ውስጥ እገባለሁ ።

"ሚሲ . . .የት ነሽ ?"

ድብቁ ሰው

ስፖርተኞቹ ፣ ሚሮኖ ሲትስኩይ መንደር ሲደርሱ ስለ መሸባቸው ፣ የመንደሯ አዛውንት የሆኑት የፕሮኩሬ ንብረት በሆነው አንድ መጠለያ ውስጥ ለማደር ወሰኑ። ሁለት ነበሩ ። አንደኛው የከብት ሐኪሙ ኢቫን ኢቫኒች ሲሆን ፣ ሌላው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የሆነው ቡርኪን ነበር ። ኢቫን ኢቫኒች ቺምሻ ሃማሊ ይስኪ የሚል ያልተለመደ መጠሪያ ተሰጥቶታል ። ይህ መጠሪያ የሚመጥነው መስሎ ስላልታያቸው ፣ ሰዎች በስሙ ወይም በቤተሰብ ስሙ ኢቫን ኢቫኒች እያሉ ይጠሩታል ። ከከተማዋ ወጣ ብሎ አንድ የፈረስ ዕርባታ አለው ። ንጹሕ አየር ላይ ለመንሸራሸር ሲል ብቻ አንዳንዴ ለአደን ይወጣል ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህሩ ቡርኪን ፣ ክረምት ክረምት ወደ ካውንት 'ተ' እርስት ስለሚሔድ ፣ የአካባቢው ነዋሪዎች ከነሱ አንዱ አድርገው ይቆጥሩታል ።

ሁለቱም አላንቀላፉም ። ረጂም ፣ ቀጭንና ሪዛም የሆነው ኢቫን ኢቫኒች ፒፓውን እያቦነነ ከቤት ውጭ ጨረቃ ብርሃን ላይ ተቀምጧል ። ቡርኪን በጨለማው ተውጦ እቤት ውስጥ በሣሩ ድርቆሽ ላይ ተኝቷል ።

ጊዜ የሚያሳልፉት ተረት በማውራት ነው ። በጣም ጤናማ ፣ ብልህና በሕይወቷ ሙሉ ከተወለደችበት መንደር ወጥታ ስለማታውቀው ፣ የአንድ የመንደሩ አዛው

ንት ባለቤት ስለ ሆነችው ክለ ማቭራ ያወራሉ ። ከተማ ወይም የባቡር ሐዲድ አይታ አታውቅም ። ባለፉት ዐሥር ዓመታት ደግሞ ማታ ማታ ብቻ ወደ ውጭ ለመውጣት ክምትሞክር በስተሩር ከምድጃ ዳር አትነሣም ።

"ይህ ታዲያ በጣም የሚደንቅ ይመስልሃል!" አለ ቡርኪን ። "በዚህ ዓለም ላይ በተፈጥሮአቸው ብቸኛ የሆኑና እንደ ኤሊ ወይም ቀንድ አውጣ ከቤታቸው የማይወጡ ብዙ ሰዎች አሉ ። ምናልባትም ይኸ የሰው በር ማኅበራዊ እንስሳ ከመሆኑ በፊት ፣ በዋሻዎች ውስጥ ወደ ነበረበት የብቸኝነት ኑሮ መመለሻ ምልክት ይሆን ይሆናል ። ወይም እንዲህ ዐይነቶቹ ሰዎች ከሰው ዝርያ አንዱ ዐይነት እንደሆኑስ ማን ያውቃል? ማለት የፈለ ግኩት እንደ ማቭራ ዐይነት ክሥተት የሚያሳዩ ሰዎች ጥቂት አለመሆናቸውን እንጂ ፣ የተፈጥሮ ሳይንስ ዐዋቂ ባለመሆኔ እንዲህ ዐይነቱን ጥያቄ መመለስ የእኔ ፋንታ አይደለም ። ምክንያቱም ከአንድ ወይም ሁለት ወር በፊት ፣ ጓደኛዬ የሆነ አንድ ቢሊኩቭ የሚባል የግሪክ ቋንቋ አስተማሪ ሞተ ። ስለሱ ሰምተህ ይሆናል ። እሱ ታዲያ የአየሩ ጠባይ በጣም ጥሩ ሆኖ እንኳን ጃን ጥላ ፣ ተደራቢ ጫማና የዝናብ ልብስ ሳይዝ በምንም ዐይ ነት ከቤቱ አይወጣም ነበር ። ጃንጥላውን አንድ ከረ ጢት ውስጥ ነው የሚያስቀምጠው ፤ ለሰዓቱ አንድ ቡላ የቆዳ መያዣ አለው ፤ እርሳሱን ለመቅረፅ መቅረጫ የሚያወጣው ከቦርሳ ውስጥ ነው ፤ ፊቱ እንኳን ሁል ጊዜ ወደ ላይ በተቀለበሰ የካፖርቱ ኮሌታ ስለሚሸፈን ቦርሳ ውስጥ ያለ ይመስላል ። ጥቁር መነጽር ያደርጋል፤ ወፍራም ጃርሲ ይለብሳል ፤ ጆሮውን በጥጥ ጥቅጥቅ አድ

ርን ይወትፋል ፤ በጋሪ ሲጓዝ እንኳን ነጂው ቆብ እንዳ ደፋ ያስገድደዋል ። እንደ እውነቱ ከሆነ ራሱን ለማግ ለልና ከውጭ ተጽዕኖ ለመጠበቅ ይህ ነው የማይ ባል ጥረት ያደርጋል ። ገሃዱ አውነት ያበሳጨዋል ፤ ያስ ደንቀዋል ፤ ሁልጊዜም ያስፈራዋል ፤ ስለሆነም ፍርሃቱንና የዛሬው ኑሮ ያሳደረበትን ብስጭት ለመሸሸግ ሁል ጊዜ ያለፈውንና ጨርሶ ያልነበረውን ነገር ያደንቃል ። የሚ ያስተምራቸው የሞቱ ቋንቋዎች እንኳን በሰሩ በገሃዱ ዓለም መካከል ያሉ የሚመስሉ ተደራቢ ጫማዎችና ጀን ጥላዎች ናቸው ።

በሊኩቭ አመለካከቱንም ድብቅ ለማድረግ ሞክ ሯል ። ማንበብ የሚወደው አንድን ነገር የሚከለክልና የሚያወግዝ ጽሑፍ የያዙ ደብዳቤዎችንና ጋዜጦችን ብቻ ነው ። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት በኋላ ተማሪዎች መን ገድ ላይ እንዳይገኙ የሚከለክል ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነትን የሚያወግዝ ጽሑፍ ከወጣ ፣ ሁሉም ነገር ለሱ እንደ ሕይወት መመሪያ ይሆናል ። ለሱ እነዚህ ነገሮች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ውግዝ ናቸው ። በሱ አመለካከት መፈቃቀድና ምሕረት በውስጣቸው አንድ አጠራጣሪ ፣ ያልተገለጸና ሥውር ነገር አለባቸው ። እንድ ጥሩ ማኅበር ወይም ንባብ ቤት ፣ ወይም ቡና ቤት እን ዲከፈት መፈቀዱን ከሰማ ራሱን ይነቀንቅና ቀስ ብሎ፣

“ ጥሩ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም ብቻ.... መጥፎ ነገር አያስከትልም ብለን ተስፉ እናድርግ ” ይላል ።

እሱን የማይመለከተው ቢሆን እንኳ ፣ ሕግን መጣስ ወይም ከሕጉ ዝንፍ ማለት በጣም ያሳዝነዋል ። ከጓደ

ደኖቹ አንዱ በጸሎት ሰዓት ዘግይቶ ከመጣ ፥ አንድ ተማሪ ስለ ፈጸመው ተንኮል ወሬ ከሰማ ፥ አንዲት የተከበረች ባለትዳር ሴት ከመሸ በኋላ ከአንድ መኰንን ጋር ከታ የች ፥ እንዲህ ዐይነቱ ድርጊት መጥፎ መሆኑን እየደ ጋገመ በመናገር በጣም ይቆጣል ። በመምህራን ጉባኤ ላይ የራሱን ሥጋት ፥ ጥርጣሬ ፥ ፍርሃትና መደረግ ያለ በትን ይደረድራል ፤ (የሚነቀት ምልክት ነው) ምናልባት ባለሥልጣኖች ከሰሙልት እሱን የማያስጠይቅ እንደሆነ በመገመት ፥ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ልጆች የሚያሳዩት ባሕርይ በጣም መጥፎ ነው ፤ በክፍል ውስጥ በጣም ይን ጫጫሉ ፤ ከሁለተኛ ክፍል ፔትሮቭን ብናባርር ፥ ከአራ ተኛ ዩጉሮቭ ቢወጣ ፥ ችግሩ የሚቃለል አይመስላች ሁም ፤ ምን ታስባላችሁ ? ርኅሩኅ በሚያስመስለው የገረጣ ነጭ ፊቱ ላይ ባደረገው ጥቁር መነጽር እልህ እየተና ነቀው በመናገሩ ፥ በአንጋገሩ እንድናምንና ለፔትሮቭና ዩጉሮቭ አነስተኛ የጠባይ ማርክ እንድንሰጥ ፥ እክፍል ውስጥ እንድናሠራቸውና በመጨረሻም ከትምህርት ቤት እንድናስወጣቸው አደረግን ። አቤታቸን ድረስ እየ መጣ የመጠየቅ ልማድ አለው ። የሥራ ጓደኛው የሆነ አስተማሪ ቤት ይሔድና ምንም ሳይናገር ሁሉን ነገር እያማተረ ተቀምጦ ይቆያል ። ለአንድ ሰዓት ያህል ከተቀመጠ በኋላ ብድግ ብሎ ይወጣል ። እንዲህ ማድ ረጉን ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር 'በጓደኝነት መጠያየቅ' ብሎ ይጠራዋል ። እንዲህ ማድረጉን እንደማይወደውና ሊጠይቀን የሚመጣው አስተማሪ በመሆኑ ፥ ማድረግ ያለበት እንደሆነ ስለሚገምተው ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው ። ሁላችንም እንፈራዋለን ። የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር እንኳን ይፈራዋል ። አሰቡት እስኪ! አስተማ

ሪዎቻችን የተርጌኔቭንና የሽድሬንን ጽሑፎች ያነበቡ፣ ጨዋና ዐዋቂ ሰዎች ናቸው። ታዲያ ይህ ዘለዓለም ጀንጥ ላና ተደራቢ ጫማ የማይልየው የሰው ምስጥ ለዐሥራ አምስት ዓመት ትምህርት ቤቱን ዘጭላ በቁጥጥሩ ሥር አዋል! ትምህርት ቤቱን ብቻም አይደል፤ ከተማዋን በሙሉ! ሚስቶቻችን እሱን በመፍራት ቅዳሜ ቅዳሜ የሚሠሩትን ቲያትር አቆሙ፤ ቄሶች እሱ ባለ በት ሥጋ ለመብላት ወይም ካርታ ለመጫወት ያፍራሉ። እንደ ቤሊኩቭ ባሉ ሰዎች ግፊት የከተማችን ነዋሪዎች ሁሉንም ነገር መፍራት ጀመሩ። ጮክ ብለው ለመናገር፣ ደብዳቤ ለመጻፍ፣ ጓደኛ ለማበጀት፣ መጻሕፍትን ለማንበብ፣ ነዳያንን ለመመጽወት፣ ማይምናንን ለማስተማር . . . ሁሉ ፈሩ።"

ኢቫን ኢቫኒች ትልቅ አስተያየቶች የሚሰጥ ይመስላል፤ ጉሮሮውን ይጠራርጋል፤ ከዚያም ፒፓውን አቀጣጥሎ ወደ ጨረቃዋ ይመለከትና በቀስታ እንዲህ ይላል።

"ልክ ነው። መምህራኑ የቱርጊኔቭን፣ የሽድሪንን፣ የባክልንና የሌሎችንም ሥራዎች ያነበቡ፣ ጨዋና ዐዋቂ ናቸው። ሆኖም ከቤሊኩቭ ተጽዕኖ አላመለጡም፤ ችለውት ኖረዋል... ሐቁ ይህ ነው።"

"ቤሊኩቭና እኔ አንድ ቤት ውስጥ ነው የምንኖረው" አለ በርኪን፣ "አንድ ፎቅ ላይ፣ የሱ ክፍል ከኔው ፊት ለፊት ነው። ብዙውን ጊዜ እንጠያየቃለን፤ አኗኗሩ እንዴት እንደሆነ ደህና አድርጌ አውቃለሁ። ሁልጊዜ ተመሳሳይ ነው። ካባ ይለብሳል፤ ቆብ ይደፋል፤ ቀበቶና መቀነት አይለየውም፤ በኑሮው ላይ ቁጥብ ነው፤

ምንም መጥፎ ነገር እንዳይደርስበት ይመኛል ። ሰዎች ቤሌኩቭ ሁዳዴን አይጾምም እንዳይሉት ስለሚሠጋ በጾም ውስጥ ሥጋ አይበላም ። ስለዚህ ዓሣ በቅቤ አስጠብሶ ይበላል ፤ ይህ ለሱ የጾም አይደለም ። ሥጋ እንደ መብላትም አይቈጠርም ። ሰዎች ይጠረጥሩኛል ብሎ ስለሚሠጋ ፥ አንድ አፋናሲዮቭ የተባለ ጠጪና ወፈፌ የሆነ የስድሳ ዓመት ሽማግሌ ፥ ዱሮ በወጥ ቤትነት ስለሠራ ቀጥሮ ያሠራዋል እንጂ ሴት ሠራተኛ ቀጥሮ አያውቅም ። አፋናሲዮቭ ሁል ጊዜ እበራፍ ላይ እጁን አጣጥፎ ቆሞ ፥

"አቤት ፥ ዛሬስ ሁሉም ነገር ግልጽ ሆኖ ታዬ.!" እያለ ያጉረመርማል ።

"ትንሿ የቤሌኩቭ መኝታ ቤት ሳጥን ትመስላለች፤ አልጋዋ በአጐበር ተሸፍናለች ። እንቅልፍ ሊወስደው ሲል ፊቱን በአንሶላ ይሸፍናል ። ክፍሉ ሞታትና የታመቀ ነው ። ነፋሱ በተዘጋው በርና በጪስ መውጫው ላይ ያፏጫል ፤ ወጥ ቤቱ ውስጥ የሥቃይ ድምፅ ይሰማል ።

"እሱም በብርድ ልብሱ ውስጥ እየተንቀጠቀጠ ይጋደማል ። ሰይጣን ይመጣ ይሆናል ፤ አፋናሲዬቭ ይገለኛል ፤ ሌባ ሰብሮ ይገባል" እያለ ይፈራል ። የሚያልመውም ዘወትር ይህንኑ ነው ። ጧት አብረን ወደ ትምህርት ቤት ስንጓዝ ፊቱ ይገረጣል ፤ ይጠወልጋል ። በዚህ ሁኔታ ወደ ትምህርት ቤት እየተቃረብን ስንሔድ የሚታየው የሰው ብዛት የሚፈራውና የማይፈልገው መሆኑንና ለሱ ፥ በተፈጥሮ ለተገለለ ሰው ፥ ከኔ ጋር መሔድ የማይፈልገው መሆኑ በግልጽ ይታወቅበታል ።

"'ክፍል ውስጥ በጣም ያንሞሞሌ' ይልኛል ፣ ለአንዳንዱ ጥያቄ መልስ ለማግኘት የሚፈልግ ይመስላል ። "ፀጣም መጥፎ ነው ። "

"አንተስ ምን ታስባለህ ይህ የግሪክ ቋንቋ አስተማሪ ፣ ይህ ድብቅ ሰው አንዴ ሊያገባ ተቃርቦ ነበር ። "

ኢቫን ኢቫኒች ጭንቅላቱን ወደ ጥላው መለሰና ፣

"አችለኝም !" አለ ።

"በእርግጥ ለማመን አስቸጋሪ ቢመስልም ሊያገባ ነበር ። አንድ ኩቫሌንኩ ሚካኤል ሳቪች የሚባል አክ ፊናዊ አዲስ የታሪክና የጂአግራፊ መምህር ተላከልን። ሻሮያ የምትባል እኅቱን ይዞ ነበር የመጣው ። ወጣቱ ረጂም ፣ መልከ መልካም ፣ ትላልቅ እጆችና ከጐርናና ድምፁ ጋር የሚሔድ ዐይነት ፊት ያለው ነበር ። እንደ እውነቱ ከሆነ ድምፁ ከበርሜል ውስጥ የሚወጣ ይመስላል ..... እምብዛም ወጣት ያልሆነቺውና ሠላሳ ወይም ወደዚያ ገደማ ዕድሜ ያላት እኅቱም ረጂም ነበረች ። ቀጭን ፣ ባለጥቁር ሽፋል ፣ ጉንጩ ቀይ የሆነችው ይህቺ ብጫ ልጃገረድ ቅልብልብ ፣ ለፍላፊ ፣ ሁልጊዜ የኡክራይና ዘፈን የምትዘፍን ግቂታ ልጅ ነበረች ። በትንሽ ቀልድ ከትከት ብላ ትሥቃለች ። ከወንድማም ሆነ ከሷ ጋር ካልተሳሳትኩ በቀር ለመጀመሪያ ጊዜ በደንብ የተዋወቅነው በርፅሰ መምህራችን ቤት በተደገሰው የክርስትና በዓል ግብዣ ላይ ነበረ። ቁጥብ ፣ ዝምተኛና ወደ ግብዣ መሔድን እንደ ሥራ ቸው በሚቆጥሩ ሥነ-ሥርዓት ባላቸው መምህራን መካከል ወገኗን ይዛ የምትውረገረግ ፣ ግቂታ ፣ ዘፋኝና ደናሽ ....የንጋት ኮከብ ከዳመና ውስጥ ብቅ አለች ። "ነፋሱ

ነፈስ” የሚልውን ዘፈን በስሜት ዘፈነች ፣ ከዚያም ሌሎች በየተራ አከታተሉት ። በሌኩቪ እንኳን ሳይቀር ሁላችንም ተደነቅን ። ከጐኗ ተቀምጦ ከማር በጣፈጠ አነጋገር እንዲህ አላት ።

“የኡክራይና ቋንቋ ጣፋጭነቱና ውበቱ ጥንታዊውን የግሪክ ቋንቋ አስታወሰኝ ። ”

“ሴትዮዋ ተደለለች፤ እናም በንጹሕ ልቦና የእናቷ መኖሪያ በሆነው በጋድያቺ ስላላቸው [illegible] ፣ እዚያ ስለምትኖረው እናቷና በእርሻው ስለሚበቅለው ከክ ፣ ለሚና ዱባ በዝርዝር አጫወተችው ። በኡክራይና ዱባ ቅልጥም ነው የሚባለው ። ነዕንቁላል ፣ አትክልትና ኪቃሪያ ጋር ተደርጐ አጅ የሚያስቆረጥም ሾርባ ይሠራበታል ። ታውቃለህ !”

ንግግሯን እያዳመጥን ሁላችንም አጠገቧ ተቀምጠናል ። ሁላችንም አንድ ሐሳብ መጣብን ።

“እነዚህ ሁለቱ ለምን አይጋቡም?” አለችኝ ፣ የርዕሰ መምህሩ ሚስት በሹክሹክታ ።

“ለምን እንደሆነ አይታወቅም ፣ ሁላችንም ድንግት ቤልኩቭ ወንደላጤ መሆኑንና በሕይወቱ ውስጥ ወሳኝ ስለ ሆነው ስለዚህ ጉዳይ ምንም ሳናነሣ እንዴት እንደ ቀረን ፣ እንዴትስ በቾልታ ልናልፈው እንደቻልን ተግ ረምን ። ስለ ሴቶች ያለው አመለካከት እንዴት ነው? እንዲህ ፀያነቱን ወሳኝ ጉዳይ ለመወጣት ያለው ዝግ ጅት ምን ያህል ነው ? ከዚህ ቀደም ስለዚህ ጉዳይ አስበንበት አናውቅም ። ዓመቱን ሙሉ ተደራቢ ጫማ የሚያደርግና በአጕበር በተሸፈነ አልጋ ውስጥ የሚ

ተኛ ሰው ፍቅር ያድርበታል ብለን ማናችንም አልነ መትንም ።

"እሱ ከዐርባ በላይ ሲሆነው ፣ የርሷ ዕድሜ ሠላሳ ነው...."አለች የርዕሰ መምህሩ ሚስት ። "የምትፈቅ ደው መሰለኝ ። "

አንድ ሰው በገጠር ሲኖር የሚያደርጋቸውን ተገቢ ያልሆኑና ርካሽ ነገሮች የሚፈጽመው ክመሰ ላቸትና መሆን ያለበት ነገር ሳይፈጸም ሲቀር ነው ። ይህን በጋብቻ ዓለም በመኖር ማስወገድ ይቻላል ብሎ ማንም የማይገምተውን ቤሎኩቭ ለምን ሁላችን ልና ገባው ፈለግን ? የርዕሰ መምህሩ ሚስት ፣ የተቄጣጣ ሪው ሚስትና ሌሎችም ከትምህርት ቤቱ ጋር ግንኙ ነት ያላቸው ሴቶች በሞላ ያሰቡት የተፈጸመላቸው ይመ ስል ሁሉም ፊታቸው ፈካ ፤ እጅግ ደስ አላቸው ። አንድ ቀን የርዕሰ መምህሩ ሚስት ቲያትር ቤት ውስጥ መቀ መጫ ቦታ አስቀድማ ያዘች ። እነዚህ መቀመጫዎች ሳይ ማንን እናያለን ፤ ቫርያ በአንድ ትልቅ ማራገቢያ ፊቷን እያራገበች ተወባና ተደስታ ተቀምጣለች ። አጠገቧ ቤሌኩቭ ከቤቱ በመንጠቆ ተጐትቶ የወጣ ይመስል ተሸ ማቆና ተኮራምቶ ተቀምጧል ። እኔም ራሴ ሴቶቹ አስ ገድደውኝ ቤሌኩቭና ቫርያ የሚገኙበት ፓርቲ አዘጋ ጀሁ ። በአንድ ቃል ጉዳዩን ጀመርነው ። የጋብቻውን ጉዳይ ቫርያ የጠላችው አይመስልም ። ከወንድሟ ጋር በመኖሯ ደስተኛ አይደለችም ። በየቀኑ ሲጨቃጨቁ ከሚውሉ በስተቀር ሥራ የላቸውም ። ስለ ሕይወታቸው አንድ ጥሩ ምሳሌ አለኝ ። ረጂሙና ግዙፉ ኩቫሌንኩ ከባርሜጣው ሥር የወጣው የፊት ጸጉሩ ቅንድቡ ላይ

እየነጠረ ፣ የተጠለፈ ሸሚዝ ለብሶ በመንገድ ላይ ይን ዛል ። በአንድ እጁ በኰረጆ መጻሕፍት ፣ በሌላው መመ ርኰዣ ከዘራ ይዟል ። ከኋላው እኅቱ ትከተለዋለች ፣ እሷም መጻሕፍት ይዛለች ።

"ሚሻ ፣ አንተ ግን አላነበብካቸውም ኮ !" አለች ጮክ ብላ ። "አላነበብክም ፣ እውነቴን ነው ፣ ጨርሶ እንደ ማታነባቸው ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ !"

"አንብቤአለሁ!" አለና ጮኸ ፣ ኰቫሌንኮ በከዘ ራው መሬቱን እየመታ ። ሚሻ ፣ ስለ እግዚአብሔር ብለህ ምን እንዲህ ያስዋሽሃል ? ይህኮ የእምነት ጉዳይ ነው ። "

"...አንብቤዋለሁኮ ነው የምልሽ" አለ ኰቫሌንኮ ይበልጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ ።

"እቤታቸውም ቢሆን ሰው በመጣ ቁጥር ሲነታ ረኩ ነው የሚገኙት ። እንዲህ ዐይነቱ ኑሮ ስላንገፈገ ፋት የራሷ ቤት ኖሯት ከዚህ የምታርፍበትን ጊዜ ትመ ኛለች ፤ ዕድሜዋም ቢሆን ቀላል አይደለም ። ለመምረጥም ጊዜ የላትም ፤ ልጅቱ ማንንም ፣ የግሪክ ቋንቋ አስተማሪ ውን እንኳን ታገባለች ። በነገራችን ላይ ሁሉም ልጃገ ረዶቻችን እንዲሁ ናቸው ። መቀነት ለመፍታት ሲሉ ብቻ ያገኙትን ያገባሉ ። ያም ሆነ ይህ ቫርያ የኛን ቤሌ ኰቭ የመውደድ ስሜት እያሳየች ነው ።

"ቤሌኰቭስ ? ወደ ኰቫሌንኮ ቤት የሚሔደው እኛ ዘንድ ፀሚመጣበት መልክ ነው ። እቤቱ ይሔድና አንድም ቃል ሳይተነፍስ ቁጭ ይላል ። ቫርያ 'ነፋሱ

ነፈስ' የሚለውን ዘፈን እየዘፈነች በጥቁር ዐይኗ ትኩር ብላ ስትመለከተው ፣ ወይም ድንገት 'ከት ከት' ብላ ስትሥቅ እሱ ወይ ፍንክች ! ጸጥ ብሎ ቁጭ ነው ።

የልብን ሲጫወቱ ፣ በተለይ የጋብቻ ጉዳይ ሲነሣ ጠጠር ያለ አስተያየት ይሰነዝራል ። ሁሉም ሰው ፣ ጓደኞቹም ሆኑ ሴቶች ፣ በሕይወቱ የጐደለው ነገር ቢኖር ትዳር ስለሆነ ፣ ማግባት እንዳለበት ይመክሩ ታል ። ጋብቻ ቁላል መሆኑንና የመሳሰሉትን ተራ ነገሮች እያነሣን በፊገግታ 'እንኳን ደስ አለህ' እን ለዋለን ። በዚህ ላይ ቫሬንክ ቁላል ካለመሆኗም በላይ ቆንጆ ልትባል የምትችል ናት ። ከዚያም በላይ የመን ግሥት አማካሪ እኅት ፣ የራሷ የእርሻ መሬት ያላት ፣ ከሁሉም በላይ እሱን በፍቅር ዐይን ለመመልከት የመ ጀመሪያዋ ሴት ናት ። በዚህ የቱንማ ሐሳቡን ቀየረና "ማግባት አለብኝ" ብሎ ወሰነ ።

ኢቫን ኢቫኒች እንዳለው ፣ "ጀንጥላውንና ተደራቢ ጫማውን ማስጫል ጊዜው አሁን ነው!"

ይህ ግን የማይቻል መሰለ ! የቫሬንካን ፎቶግራፍ ጠረጴዛው ላይ አስቀምጧል ፤ እኔ ዘንድ ይመጣና ስልኳ ስለ ቤተሰብ ፣ ስለ ጋብቻ ቁላል ጉዳይ አለመሆኑን ያወራል ። ወደ ኩቫሌንኮም ቤት በየጊዜው ይሔዳል ፣ አኗኗሩን ግን ፣ ቅንጣትም ታህል አልቀየረም ። እንዲ ያውም ለማግባት መወሰኑ ለሕይወቱ መጥፎ ጠንቅ ያመጣበት መሰለ ፣ ከሳ ፤ ገረጣ ፣ ይበልጥ ብቸኛ እየሆነ ሔደ ።

"ቫርቫራ ሰሺሽና የምትስማማኝ ሆና አግኝቻ ታለሁ" አለኝ ፣ ፈዛዛና አታላይ ፈገግታውን እየሳየኝ ። "ማንም ሰው ማግባት እንዳለበት ወሰንኩ ፣ ግን.... በጣም ድንገተኛ ነው... አስቀድሞ ማሰብን ይጠይቃል ...."

"ምኑን ነው ማሰብ ያለብህ?" አልኩት ። "አግባህ ቦቹው ነው"

"የለም ፣ እንዲህ አይሆንም ፤ ጋብቻ ወሳኝ ጉዳይ ነው ፤ በመጀመሪያ አንድ ሰው የወደፊት ኃላፊነቱንና ግዴታዎቹን ማመዛዘን ይኖርበታል...መጥፎ ጠንቅ እንዳያስከትል ፣ ጥንቃቄ ያሻል ...በጣም ስላስጨነቀኝ ሌሊቱን ሁሉ እንቅልፍ ነሥቶኛል ። እውነቱን ልግለጽ ልህና ነገሩ በጣም አስደንቆኛል ። እሷና ወንድሟ አመለካከታቸው ከሰው የተለየ ነው ። ገባህ ፣ በዚህም ላይ እሷ ማንቧረቅ ትወዳለች ። ምናልባት ባገባትና አንድ ነገር ውስጥ ብገባ ...."

እናም ከዕለት ወደ ዕለት ስለሷ ያለውን ሐሳብ እየጣለ ስልሔደ ፣ የርዕሰ መምህሩ ሚስትና ልሎችም ሴቶች ተስፋ ቆረጡ ። ምናልባትም ሁኔታው ያስገድደኛል ብሎ በመሥጋት ከቫሬንካ ጋር በየቀኑ ሽርሽር መሔድን ፣ እኔ ዘንድ እየመጣም ስለ ቤተሰብ ይዞታ መወያየትን የመሳሰሉ የወደፊት ኃላፊነቶችንና ግዴታዎችን ማውጠንጠን ያዘ ። ነገሩ በቶሎ ካልተቋጨ ከመሰላቸትና ከዚዝ ውጮድ ለመውጣት ይዋክራል ። ዞሮ ዞሮ ግን ፣ አስፈላጊ ያልሆነ ጋብቻ ውስጥ መጠመዴ አይቀር ይሆናል ። የቫሬንካ ወንድም ኩሻሌንኮ ከተዋ

ቋቁፀት ዕለት ጀምሮ በቤሌኩቭ ላይ ጥላቻ እንዳደ
ፈበትኖ ጨርሶ እንደማይፈቅደው ልናገር እወዳለሁ ።

"የናንተ ነገር አይገባኝም" ይላል ። ሳቁሻውን
ነቅነቅ አድርጎ ። "ከእንዲህ ዐይነቱ ሾካካ ፍጡር
ጋር እንዴት ልትኖሩ እንደ ቻላችሁ አይገባኝም ። ወን
ድሞቼ እዚህ እንዴት መኖር ትችላላችሁ ? አካባቢው
ቀፋፊና መርዘኛ ነው ። ራሳችሁን መምህራን ፣ የትምህ
ርት ባለሙያዎች አድርጋችሁ ነው የምትቈጥሩት?
እናንተ ለሙያው ክብር የሌላችሁ ናችሁ ። ትምህርት
ቤታችሁ የሳይንስ መፍለቂያ ሳይሆን ፣ የበግ አድራጎት
ድርጅት ነው ። ልማልፋት እንደሚዘጋጅ ቆዳ የሚሸት
ነገር ያልበት ነው ። ወንድሞቼ ከናንተ ጋር መቆየት
አልችልም ፤ ወደ እርሻዬ ተመልሼ ዓሣ እያጠመድኩ
አከራናውያን ሴቶችን ባስተምር ይሻለኛል ። እውነቴን
ነው እመለሳለሁ ፤ እናንተ ግን ካይሁዳችሁ ጋር በመ
ኖር ከሱ ጋር ገሃነም ልትገቡ ትችላላችሁ!"

"ልምንድን ነው እዚያ የሚቀመጠው ? ምንድን
ለመፈለግ ነው አፍጥጦ የሚቀመጠው ?"

ሌላ ጊዜ ደግሞ ፀመጀመሪያ በጐረነን ድምፅ
ከት ብሎ ይሥቅና ከዚያም ከዐይኖቹ እንባ እስኪረግፍ
ድረስ በቀጭን ድምፅ ይንከተከታል ።

ለቤሌኩቭ ፡ (መርዛም ሽረሪት) የሚል የራሱ ቅጽል
ስም አውጥቶለታል ። እኅቱ ይህን "ሽረሪት" ልታ
ገባ እንደ ነበር ከመንገር ተቆጥበናል ። የርዕሰ መምህሩ
ባለቤት እኅቱ እንደ ቤሌኩቭ ያለ ሰው አግብታ ፀት

ዳር ብትቀመጥ የሚሻላት መሆኑን ጠቆም ልታደርግ ለት ኩሰተር ብሎ እንዲህ አላት ።

"እኔ በዚህ የሚያገባኝ ነገር የለም ። ለእኔ ካልች አውሬም ልታገባ ትችላለች ። እኔ በሌላ ሰው ጉዳይ ጣልቃ የምገባ ሰው አይደልሁም ።"

ከዚያ ምን እንደሆነ ላጫውታችሁ ። አንድ ቀን ኩለኛ ሰው ምስል ሠራ ። በዚህ ሥዕል ቤሌኩሽ ተደራቢ ጫማውን አድርጎ ፣ የሱሪውን ጫፍ ወደ ላይ አጥፎ ፣ ሸንጥላውን ዘርግቶ ይዞ ከቫርያ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው ይታያሉ ። ከሥዕሉ ግርጌ 'አንትሮፓሳ በፍቅር ላይ' የሚል ተጽፏል ። ፊቱ ልክ እሱን ቁጭ ነበር ። ሥዕሉን የሠራው አርቲስት በዚህ ሥራ ብዙ የለፋ መሆን አለበት ፤ ምክንያቱም የትምህርት ቤት መምህራን ፣ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ፣ መንፈሳዊው ትምህርት ቤትና የክተማዋ ባለሥልጣኖች ሁሉ ግልባጭ ደርሶአቸዋል ። ለቤልኩቭም አንድ ተልኩለታል ። ሥዕሉ መንፈሱን በጣም ረበሸው ።

"አንድ ቀን አብረን ከቤት ወጣን ። ፅሉቱ የግንቦት የመጀመሪያው እሑድ ነበር ። ተማሪዎች ፣ አስተማሪዎች በመላ ትምህርት ቤት በራፍ ተገናኝተን ክክ ተማዋ ወጣ ብሎ ወዳለ አንድ ጫካ ለመሔድ ተቀጣጥረን ፣ ሁላችንም ወጣን ። እሱ ጥቁር ፣ ክስል ብሏል ።

"በዚህ ዓለም በርካታ ጨካኝ ፣ አረመኔ ሰዎች አሉ" አለ ከንፈሩ እየተንቀጠቀጠ ።

"በጣም አዘንኩለት ። መንገዳችንን ቀጠልን ። እመንገድ ላይ ማንን እናገኛለን ፣ ኩቭሌንኩ በብስኪሌት

ላይ ሆኖ ፣ ከኋላው ሻሬንካ ቁና ቁና እየተነፈሰች በብ ስክሌት ትከተለዋለች ፤ ፊቷ በርበሬ መስሏል ፣ ግን ተውባለች ፣ ተደስታለች ።

"ሁላችሁንም ቀድመን እንደርሳለን !" አሰች ጮክ ብላ ። "ግሩም ቀን ነው አይደል ? በጣም ሙቀ ነው !"

"ወዲያው ክፀደናችን ሪቱ ። ንደኛዬ ቤሌኮቭ ፈገግታው ሁሉ ጠፍቶ ልሳኑ እንደ ተዘጋ በድን ሆነ ። ቆመና ትኩር ብሎ ተመለከተኝ ።

"አሁን ይሆን ምን ትለዋለህ ?" ብሎ ጠየቀኝ.... "ወይስ ወይኔን ላምን አልችልም ? አንድ ሙምሀርና አንዲት ሴት ብስክሌት መጋለብ አሁን ተግቢ ነው !"

"ምንም የሚያስከፋ ነገር የለም" አልኩኝ ። "ብስ ኪሌት ቢጋልቡ ምን አለበት ?"

"ይህን ልቀበለው አልችልም ! እንዴት እንዲህ ትለኛለህ" በማለት ጮኸብኝ ። ሁኔታው በጣም ስላስ ቆጣው ፣ ጉዞውን ለመቀጠል ባለመፍቀድ ወደ ቤቱ ተመለሰ ። በሚቀጥለው ቀን ፣ ቀኑን ሙሉ በብስጭት እጆቹን እያፍተለተለ ዋለ ፤ ደኅና አለመሆኑ ከፊቱ ይነበባል ። የትምህርት ሰዓት ከማለቁ በፊት ወደ ቤቱ ተመለሰ ፤ በሕይወቱ እንዲህ አድርጎ አያውቅም ። ምሳ አልበላም ፣ ወደ ማታ ሞቃት ልብስ ለበሰና ወደ ኩቫሌ ንኩ ቤት አዘገመ ። ሻሬንካ አልነበረችም ፤ መንድሟን ግን እቤት አገኘው ።

" ኖር ፣ ተቀመጥ" አለ ኩቫሌንኩ ፊቱ ሳይፈታና ዛቀዘቀዘ አቀባበል ። ከለመደው የሰዓት በኋላ ዕንቅልፉ ገና እየነቃ ስለነበር ፊቱ አልተፈታም ፣ ተጨነባብሏል ።

ለዐሥር ደቂቃ ያህል ዝም ብሎ ከተቀመጠ በኋላ ቤሌኩቭ እንዲህ አለ ።

"ከጭንቀቴ ነጻ ለመሆን ነው የመጣሁት ። በጣም እጅግ በጣም ተበሳጭቼአለሁ ። አንድ የሆነ አሸ ሚጣጭ እኔንና ለሁለታችንም የሚቀርብ ሌላ ግለ ሰብ የሚያዋርድ አንድ ሥዕል ሠራ ። ይህ የኔ ጥፋት አለመሆኑን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ ። ይህን ተራ ነገር ከቁምነገር አላገባሁትም ፤ ይልቁንስ እንደ ወትሮዬ በጨዋነት መኖር ጀመርኩ ። "

ኩቫሊንኮ አንገቱን ደፍቶ በጸጥታ ተቀምጧል ። ትንሽ ዝም ካለ በኋላ ቢሌኩቭ በጎበኔታ ንግግሩን ቀጠለ።

"ሌላም የምነግርህ ጉዳይ አለኝ ። እኔ የረጂም ጊዜ ልምድ ያለኝ ሰው ነኝ ። አንተ ግን ፣ ገና ወደ ሥራው ዓለም መግባትህ ነው ። ስለሆነም የረጂም ጊዜ ልምድ ያለኝ ጓደኛህ አንድ ነገር ላስጠነቅቅህ እፈልጋለሁ ። ብስክሌት ትጋልባለህ ፤ ይህ ወጣቱን አስተምራለሁ ለሚል ሰው እጅግ አስነዋሪ ሥራ ነው ። "

"ለምን?" አለ ኩቫሌንኩ በጉሮናና ድምፁ ።

"ይህ ተጨማሪ ገለጻ አያስፈልገውም ሚካኤል ሳቪች ? ነገሩ ግልጽ ይመስለኛል ። መምህራቸው ብስ ክሌት ከጋለበ ተማሪዎች በራሳቸው ቆመው መሔድ አለባቸው ማለት ነው ። ደግሞም ብስክሌት ለመጋለብ የሚፈቅድ ምንም ሰርኩላር ስላልተላለፈ ትክክል አይ ደለም ማለት ነው ። ትላንትና በጣም ደነቀኝ ፤ እጎትህ ንማ ላይ ራሴን ሳትኩ ። ሌት ልጅ በብስክሌት ላይ ማየት—የማትረባ!"

"አሁን ችክክለኛ ክኔ የምትፈልገው ምንድነው?"

"ሚካኤል ሳቪች ፥ አንተን ልማስጠንቀቅ ብቻ ነው የመጣሁት ። አንተ ገና ወጣት ነህ ፤ ወደ ፊት ብዙ ነገር የምታይ ሰው ነህ ፤ በጣም ፥ በጣም ልትጠነቀቅ ይገባል ፤ አንተ ግን ግድየለሽ ፥ ጨርሶ ግድየለሽ ነህ፤ የተጠለፈ ሽሚዝ ትለብሳለህ ፤ የተለያዩ መጻሕፍት ይዘህ በየመንገዱ ትታያለህ ፤ አሁን ደግሞ ብስክሌት ጋለብክ ። አንተና እኅትህ ብስክሌት መጋለባችሁ ለር ዕሰ መምህሩ ሊደርስ ይችላል ፤ ተቆጣጣሪዎች ይሰሙ ይሆናል ....ይህ ደግሞ ጥሩ አይደለም ። "

"እኔና እኅቴ ብስክሌት ጋለብን አልቃለብን የሚ ያገባው ሰው የለም!!" አለ ኩቫሊንኩ በቁጣ ። "በግል ሕይወቴና ቤቤተሰቤ ጣልቃ ሊገባ የሚሞክር ክለ ገደል ይግባ ።"

ቤሌኩቭ ከው አለና ልመሔድ ተነሣ ።

"እንዲህ ካስቆጣህ ከኔ ጋር መነጋገር አትችልም" አለው ። በኔ ፊት ስለ አለቆቻችን ባልከው ነጥብ ላስጠ ነቅቅህ እወዳለሁ ። ባለሥልጣኖች ከበሬታ ሊያገኙ ይገ ባል ።"

"በባለሥልጣኖች ላይ የተናገርኩት ምን መጥፎ ነገር አለ?" በማለት ጠየቀ ፥ ኩቫሊንኩ በጥላቻ እየተመ ለከተው ። ጌታዬ ፥ በቃን ፤ እኔ እውነተኛ ሰው ነኝ ። ስለ ዚህ ልእንዳንተ ዐይነቱ የምነግረው ጉዳይ የለኝም ፤ እባ ቦችን አጠላለሁ ። "

ዜሌኮቭ ፀቁጣ ተቈነጠነጠ ፤ ከሩን ፀችኩላ ልበሰ ፤ ከፊቱ ፀጣም የመክፋት ምልክት ይነበብበታል ። በሕ ይወቱ እንዲህ ያለ ብልግና የሚያሳይ ሰው ገጥሞት አያውቅም ።

"የፈለገህን ልትል ትችላለህ" አለ በደረጃው በኩል እየወጣ ። "ግን ተጠንቀቅ ። አንድ ሰው ንግግራችንን ሰምቶ ሊሆን ይችላል ። ንግግራችን በስሕተት እንዳይተረጐምና ችግርም እንዳይፈጥርብን ፥ ፍሬ ሐሳቡን ለርዕሰ መምህሩ አሳውቃለሁ ... ዋና ዋናዎችን ። ይህ ተግባሬ ነው ። "

"ምን ፤ እነግራለሁ ? አሁኑኑ ሒድ !"

ኩቫሊንኩ አንገቱን አነቀውና ገፍትሮ ጣለው ። ቤሌኩቭ ተደራቢ ጫማው በደረጃው ላይ እየተንኳኳ ተንከባሎ ወረደ ። ደረጃው ረጂምና ተዳፋት ቢሆንም ፥ አልተጐዳም ። ብድግ አለና መነጽሩ ተሰብሮ እንደሆነ ለማየት አፍንጫውን ዳበሰ ። እሱ እየተንከባለለ ሲወርድ ቫሬንካ ክሌሶች ሁለት ሴቶች ጋር እበረንዳው አጠገብ ደርሳለች ። ሦስቱም ደረጃው ጫፍ ላይ ቆመው ተመለከቱት ። ለቤሊኩቭ ከሥቃዩ ሁሉ የሞት ሞት የሆነበት ይህ ነበር ።

እንደዚህ ተዋርዶ በሰው ፊት ከሚታይ ፥ አንገቱ ቢቆረጥና እግሩ ቢሰበር በመረጠ ነበር ። የከተማው ሰው ይህን ይሰማል ፤ ርዕሰ መምህሩና ምናልባትም ተቆጣጣሪው ጆሮ ይደርሳል ። ከዚያ ምን እንደሚከተል ምን ይታወቃል ? አንዱ ደግሞ ሌላ ምክል ፍሠራና ሥራ መልቀቅም ይኖርበት ይሆናል ...

"ከወደቀበት ሲነሣ ቫርያ ማንነቱን ለየች ። አሥ ቂኝ ፊቱን ፣ የተጨረማመተ ካፖርቱን ፣ ተደራቢ ጫማ ውን ስትመለከት ያንሸራተተው እንጂ ፣ ሌላ ምንም ሊሆን እንደማይችል በመገመት ከት ከት ብላ ሣቀች።

"ይህ ከጣሪያ በላይ መሣቅ የመጨረሻው ነበር ። ለቤሌኩቭ መሽኮርመምና ለምድራዊ ሕይወቱ የመጨ ረሻው ነበር ። ከዚያ በኋላ ሻሬንካን አላያትም ። ቤቱ እንደ ደረሰ በመጀመሪያ የሷን ፎቶግራፍ ከጠረጴዛው ላይ አነሣና ሁለተኛ ላለመነሣት አልጋው ላይ ተጋ ደመ ።

"ከሦስት ቀን በኋላ የጌታው ሁኔታ ቅላላማረው ሐኪም ማስጠራት ያስፈልግ እንደሆነ ሊጠይቀኝ አፍ ናሲዬቭ ቤቴ መጣ ። ቤሌኩቭን ልጠይቅ ሔድኩ ። በብርድ ልብስ ተሸፋፍኖ አልጋው ውስጥ በአጐበሩ እንደ ተሸፈነ ተኝቷል ፤ አይናገርም ። ስጠይቀው በአንድ ቃል "አዎ" ወይም "አይደለም" ከሚል በቀር ቃልም አይተነፍስ ። አፍናሲዬቭ ተበሳጭቶና ተቆጥቶ በአል ጋው ዙሪያ እየተንጐራደደ በረጂሙ ሲተነፍስና አልኩ ሉን እንደ ውሃ ሲጨልጥ ፣ እሱ ግን ተጋድሟል ።

"ከአንድ ወር በኋላ ቤሌኩቭ ሞተ ። በሁለቱ ትም ህርት ቤቶችና በመንፈሳዊው ትምህርት ቤት የምን ሠራ ሁላችንም ቀብሩ ላይ ተገኘን ። ዛሬ በሬሳ ሳጥን ውስጥ ፊቱን ስናይ ለመጨረሻ ለበላለም በገባበት ከረ ጢት ውስጥ እጅግ የተደሰተ ይመስል ፊቱ ፈክቷል ፤ ተደስቷል ። አዎ ፣ የፈለገውን አግኝቷል ! ለሱ የክ ብር መሰናበቻ የሆነ ይመስል ቀኑ ዳመናማና ቀዝቃዛ

ነበር ፤ ሁላችንም ተደራቢ ጫማ አድርገናል ፤ ጀንጥላ ይዘናል ። ቫርያም ቀብሩ ላይ ነበረች ፤ ሳጥኑ ወደ መቃብሩ ሲገባ እንባዋን አፈሰሰችለት ። የኡክራይና ሴቶች መሣቅ ወይም ማልቀስ እንጂ ዝምታ የማያውቁ መሰለኝ ።

"እንደ ቤሌኩቭ ያሉ ሰዎችን መቅበር ጥሩ ነገር ነው ። ከቀብሩ ቦታ የተመለስነው ፊታችን 'ጸሙኖ' መስሎ ነው ። በሕዳንነታችን ወላጆቻችን ከቤት ሲወጡ ፣ ነጻ ሆነን በየአትክልቱ ውስጥ በመሯሯጥ ለመደሰት እንመኝ የነበረውን ዐይነት ነጻነት አንዳችንም አልተሰማንም ። አዩ ነጻነት ! የነጻነት ስሜት ፣ ይሆን ነጻነት የማግኘት ሞላንሞል ፣ ለነፍሳችን ክንፍ የሚያስወጣ ይመስላል ። አይመስላችሁም ?"

"ከቀብሩ ቦታ በጥሩ ስሜት ተመለስን ። ግን ሳምንት እንኳን ሳይሞላ እንደ ወቅሮው የዕለት ተዕለት ኑሮአችንን ፣ በአንዱ ዘዋሪ ማዘግየ ደብዳቤ የቱከለከለውን ወይም በሌላው የተፈቀደውን አሰልቺና ትርጉም የለሽ ኑሮአችንን ጀመርን ። ከቀድሞው የተሻለ አንድም ነገር የለም ። ቤሌኩቭን ብንቀብረውም ልብ ብለን ካሰብን በከረጢት ውስጥ የሚኖሩ በርካታ ሰዎች አሉ ፣ ብዙዎችም ገና ይወለዳሉ ።"

"አዎ ፤ ልክ ነህ" አለ ኢቫን ኢቫኒች ፒፓውን እያ ቀጣጠለ ።

"ገና ብዙ ይወለዳሉ !" አለ ቡርኪን ።

የሁለተኛ ደረጃ መምህሩ ከጥላ ውስጥ ብቅ አለ። አጭር፣ ወፍራም፣ ራሰ በራና ጥቁር፣ ጢሙ እምብርቱ ድረስ የተንዠረገገ ነው። ሁለቱ ውሾች ተከትለውታል።

"ምን ወይነት ጨረቃ ፍት!" አል፣ ሰማዩን እያየ።

እኩል ሌሊት አልፏል። በቀኝ በኩል ወደ አምስት ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ረጂም ጉዳና የሚያልፍ በት ቅልቅ መንደር ወለል ብሎ ይታያል። ሁሉም ነባቢ ጸጥ፣ ረጭ ብሏል። አንድም ድምፅ፣ አንድም እንቅስ ቃሴ ባለመኖሩ የተፈጥሮ እንዲህ ጸጥ ማለት ይደንቃል። በደማቅ ጨረቃ ሌሊት የመንደሯን ሰፊ ጉዳና፣ ከነዋ ሪዎቿና ከአካባቢዋ ጋር በጸጥታ ተኝታ ማየት መን ፈስን ያረጋጋል። ከሥራ፣ ከጎዘንና ትካዜ በሌሊቱ ጥላ ሥር ያረፈችው መንደር ጨዋ፣ ደስተኛና ውብ ትመስ ላለች። የሰማዩ ከዋክብት በፍቅር ብርሃን ወደ ታች ይመልከቷታል። በዓለም ላይ ክፋት የሌለና ሰላም የወ ረደ ይመስላል። በግራ በኩል መንደሯ ጫፍ ላይ ሰፋፊ ሜዳዎች አሉ። ዐይን እስካረፈ ድረስ ቢመለከቷቸው እነሱም ጸጥ እረጭ ብለዋል። ሰፊው ሜዳ በጨረቃ ብርሃን መለል ብሏል።

"አም፤ እውነት ነው" አለ አሁንም ኢቫን ኢቫ ኒች። "የኛ የከተማ ኑሮ፣ በተጨናነቀ፣ ቁሻሻ ክፍሎች ውስጥ፣ ዋጋ ቢስ ጽሑፎች እያዘጋጀን የምንኖረው ኑሮስ ድብቅ ኑሮ አይደለምን? ሕይወታችንን በሞላ ሁል ጊዜ የማይረባ ነገር ማውራትና ተራ ነገር መል ማት ከሚሹ መንቻካ፣ ስድ አደግና ሰነፍ ሴቶች ጋር የምናሳልፈው ኑሮስ ሽፍን ኑሮ አይደለምን? ፊታድህ ከሆነ አንድ ተረት ልንገርህ..."

“የመኝታ ጊዜ መሰለኝ ፥ ነገ ብታወራ ይሻላል” አለ ቡርኪን ።

ወደ መጠለያው ሔዱና ተጋደሙ ። ገለባው ክምር ውስጥ ተወሽቀው ማንቀላፋት ሲጀምሩ ፥ ከውጭ የሰው ኰቴ ተሰማ ። ከመጠለያው ብዙም ሳይርቅ አንድ ሰው ይመጣል ። ትንሽ ራመድ ይልና ቀጥ ይላል ፤ ከዚያ ጥቂት ይራመዳል ። ውሾች ተንጫጩ ።

“ማቭራ እየተንሸራሸረች ነው” አለ ቡርኪን ። የኰቴው ድምፅ ጸጥ አለ ።

“የሚዋሹትን ሰዎች ለማየትና ለማዳመጥ ነው” አለ ኢቫን ኢቫኒች እየተገላበጠ ። ከዚያም ያን ሁሉ ውሸት ሰምቶ ዝም በማለቱ ለማንጓጠጥ ፥ ስድብን ውርደትን አሜን ብሎ ለመቀበል ፥ ለመናገርና ከእው ነተኞች ጐን ለመቆም አለመድፈር ፥ ራስህ መዋሸት መሳት ፥ ይህ ሁሉ ለአንዲት ቁራሽ ዳቦና ለተመቻቸ ኑሮ ፥ ለአንድ ለማይረባ ሥልጣን ፍጹም ፥ ሕይወት ክንቱ ነች!”

“ኢቫን ኢቫኒች ፥ ይህክ ጨርሶ ከምንነጋገርበት አርዕስት ውጭ ነው” አለ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መም ህር ። “እስቲ እንተኛበት ። ”

በፀሥር ደቂቃ ውስጥ ቡርኪን አንቀላፋ ። ኢቫን ኢቫኒች ግን ያቃስታል ፤ ገለባውን እያንኰሻኰሸ ይገ ላበጣል ። ከዚያ ብድግ አለና ወደ ደጅ ወጣ ። መዝጊ ያው አጠገብ ቁጭ አለና ፒፓውን አቀጣጠለ ።

እንጀራ

ከጠዋት ጀምሮ ሰማዩ ዝናብ ባዘሉ ደመናዎች ተሸፍኗል። ጸጥ ያለ፣ ቀዝቃዛና ቀፋፊ ቀን ነው። ደመናው እየወረደ የሚሔድበትና ከአሁን አሁን ዘነበ ሲባል ሳይዘንብ የሚያልፍበት ጭጋጋማ ዐይነት ቀን ነው። የእንስሳቱ ሐኪም፣ ኢቫን ኢቫኒችና የሁለተኛ ደረጃው ትምህርት ቤት መምህር፣ ቡርኪን እስኪደክማቸው ድረስ ቢጓዙ፣ በመስኩ አቋርጠው የሚያልፈው መንገድ መድረሻ የሌለው መስሎ ታያቸው።

ክፉት ለፊታቸው በርቀት ላይ የሚሮኖሲትሰኮይ መንደር የውሃ ማውጫ የነፋስ መዘውር ይታያቸዋል። ከመንደሩ በስተቀኝ እንደ ሰንሰለት የተያያዙ የአነስተኛ ኮረብታዎች ጉብታ ይታያል። ይህ የኮረብታዎቹ ሰንሰለት የመንዙ ድንበር መሆኑን ሁለቱም ያውቃሉ። ከዚያም ባሻገር ሰፋፊ መስኮች፣ ትላልቅ አረንጓዴ ዛፎችና የመሳፍንቶችና የመኳንንቶች የገጠር መኖሪያ ቤቶችና እርሰቶች አሉ። ኮረብታዎቹ አናት ላይ ቢወጡ ኖሮ ዳር ድንበር የሌለውን መስክ፣ የስልክ መሥመር ምሰሶዎችን፣ ከሩቁ እንደ ትል የሚጥመለመለውን ባቡር ለማየት ይችሉ እንደ ነበር ሁለቱም ያውቁታል። የአየር ጠባዩ ሸጋ ሲሆን፣ ክተማዋ እንኳን ቅታያለች። ተፈጥሮ በሙሉ ርጎሩጎና ደግ መስላ ዐምትታይበት ዐዚህ ዐይነት ቀን ኢቫን ኢቫኔችና ቡርኪን ለዚህ ሥራ መስክ

የፍቅር ስሜት አደረባቸው ። አገራቸው ምን ያህል ሰፊና ውብ እንደ ሆነች በሕሊናቸው አውጥቱው አወረዱ ።

"ባለፈው ጊዜ ፕሮኮራ ጭጆ እያለን " አለ ቡፎ ኪን ። "አንድ ታሪክ አጫውትሃለሁ ብለኸኝ ነበር ። "

"አዎን ፣ ስለ መንድሜ ልነግርህ ፈልጌ ነበር ።"

ኢቫን ኢቫኒች ፣ የወንድሙን ታሪክ ለመናገር ክመ ጀመሩ በፊት በሰፊው አየር ወደ ውስጥ ምጐ የጀፓ ውን ትምባሆ ሲለኩስ ዝናቡ መዝነብ ጀመረ ። ከአም ስት ደቂቃ በኋላ ዶፍ ይወርድ ጀመር ። ዝናቡ በዚህን ጊዜ ይቆማል ብሎ ለመናገርም ያዳግት ነበር ። ኢቫን ኢቫኒችና ቡርኪን በሐሳብ ተውጠው ጸጥ ብለው ቆሙ። ውሾቹም በዝናቡ ርሰው ጭራቸውን ጉያቸው ውስጥ ሸጉጠው ጌቶቻቸውን እንጋጠው ይመለከታሉ ።

"መጨለያ መፈለግና ማግኘት ይኖርብናል" አለ ቡርኪን ። "ወደ አሌኪን ቤት እንሒድ ቅርብ ነው ።"

"እንሒዳ ታዲያ"

ወደ ጐን ታጥፈው ቀኛቸውን ይዘው በቀጥታ አዲስ በታጨደው ማሳ አቋርጠው አንድ መንገድ እስኪደርሱ ድረስ ተጓዙ ። ወዲያው ዛፎች ፣ የወይን ተክሎችና የጐ ተራው ቀይ ጣራ ታየ ። የወንዙ ወለል ያንጸባርቃል ። ሰፊና ትልቅ የውሃ አካል እንዲሁም የውሃ ማውጫ ፣ የነፋስ መዘውርና ኖራ የተቀባ የመታጠቢያ ታዛ ይታ ያቸዋል ። ቦታው ሰፍኖ የሚገኘው የአሌኪን መኖሪያ ነበር ።

የነፋሱ መዘውር ይሠራ ስለ ነበር ፥ ከመዘውሩ የሚ ወጣው ድምፅ የዝናቡን ድምፅ ስለ ዋጠው አይሰማም። ግድቡ በሙሉ ተናወጠ ። በዝናቡ የራሱ ፈረሶች አንገ ታቸውን ደፍተው ጋሪዎች አጠገብ ቆመዋል ። ሰዎች ራሳቸውና ትከሻቸው ላይ ጀንያ ጣል አድርገው ከቦታ ወደ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ ። እርጥብና ጭቃማ ሲሆን ፥ ወን ዙም ቀዝቃዛና የመጥፎ ዕድል ምልክት ያዘለ መስሎ ይታያል ። ኢቫን ኢቫኒችና ቡርኪን ከአሁኑ በጭቃ ፥ በቅዝቃዜና በምቾት መቀነስ እየተሠቃዩ ነው ። ጫማ ቸው በጭቃ ተጨማልቋል ። ግድቡን እንዳለፉ ሽቅብ በመውጣት ወደ ባለንብረቱ ጌታ ጐተራ አመሩ ። አንዱ በአንዱ የተቆጣ ይመስል ሁለቱም ጸጥ አሉ ።

የማበጠርና የማራገብ ድምፅ ከአንድ ጐተራ በኩል ተሰማ ። የጐተራው በር ክፍት ስለ ነበር ፥ አቧራ በብዛት ይወጣል ። በሩ ላይ የቆመው ደንዳና ሰውነትና ረዥም ጸጉር ያለው ፥ የዐርባ ዓመቱ ጐልማሳ ፥ ፕሮፌሰር ወይም የሥነ ጥበብ ሰው እንጂ ፥ የመሬት ከበርቴ የማይመስ ለው አሌኪን እራሱ ነበር ። በጣም ያደፈ ነጭ ሸሚዝ ለብሷል ። ከሥሩ ሱሪ ያልተደረበበት ፒጃማ አጥልቋል። ጫማው በጭቃ ተጨማልቆ ሣር በብዛት አዝሏል ። አፍ ንጫውና ዐይኖቹ አቧራ ለብሰዋል ። ኢቫን ኢቫኒችንና ቡርኪንን ሲያይ ስላስታወሳቸው ፥ በመምጣታቸው በጣም ተደሰተ ።

“ጐበዝ ፥ ሒዱ ወደ ቤት” አለ ፈገግታ በተላበሰ አነጋገር ። “ከጥቂት ጊዜ በኋላ እኔም እመጣለሁ ። ”

ትልቅ ባለሁለት ፎቅ ቤት ነው ። አሌኪን ቀደም ሲል መኪሉ የሚኖርበትንና ወደ ውስጥ የተሰረጐደ

ጣሪያና ትናንሽ መስኮቶች ያሏቸውን ሁለት ክፍሎች የያዘውን ምድር ቤቱን ይዟል ። በጥሩ ሁኔታ ያልተደራጀ ሲሆን የዳጉሳ ዳቦ ፣ የርካሽ ቦድካና የፈረስ ዕቃ ሽታ ይተነፍሳል ። እንግዳ ካልመጣበት በስተቀር ወደ ፎቅ ቤቱ ወጥቶ አያውቅም ። ኢቫን ኢቫኒችንና ቡርኪንን አንድ በጣም ቆንጆ የሆነች ሠራተኛ ልትቀበላቸው ስትወጣ ፣ ፀሐይቷ ደንግጠው ጸጥ ብለው በመቆም እርስ በርስ ተያዩ ።

"ውድ ወዳጆቼ እዚህ ሳያችሁ ምን ያህል እንደ ተደሰትኩኝ ልገልጽላችሁ አልችልም" አለ አሌኪን አዳራሹ ውስጥ ቀድሞዋቸው እየገባ ። "የሚገርም ነው! ፔላጊያ" አለ ወደ ሠራተኛዋ በመዞር ። "የሚቀይሩት ልብስ ፈልጊላቸው ፤ እኔም ራሴ መቀየር አልብኝ ፤ መጀመሪያ ግን መታጠብ ይኖርብኛል ። ካለፈው ጸደይ ወራት ወዲህ የታጠብኩ አይመስለኝም ። እነዚህ እስኪ ዘጋጁ ድረስ መታጠብ አትፈልጉም?" በማለት ጠየቃቸው ።

ለስላሳና ውብ የሆነችው ቆንጆዋ ፔላጊያ ፣ ፎጣና ሳሙና አመጣችላቸውና አሌኪንና እንግዶቹ ወደ መታጠቢያው ቤት አመሩ ።

"አዎን ክታጠብኩ ብዙ ጊዜ ሆኖኛል" አለ ልብሱን እያወለቀ ። እንደምታዩት አባቴ ያሠራው ጥሩ መታጠቢያ ቤት አለኝ ። ነገር ግን ጊዜ አግኝቼ የምታጠብበት አይመስለኝም " ። በመታጠቢያው ደረጃ ላይ ተቀምጦ ረጃጅም የራስ ጸጉሩንና እንገቱን በሳሙና ሲያሸ ዙሪያውን ያለው ውሃ ቡናማ ሆነ ።

“አምን በእርግጥ አንተ ...”አለ ኢቫን ኢቫኒች የአሌኪንን ራስ በቅጡ እየተመለከተ ።

“ከታጠብክ ረጅም ጊዜ ሆኖኛል...”አለ ደግሞ አሌኪን በማፈር ዐይነት ። ከዚያም ሳሙናውን አንሥቶ ገላውን መለቅለቅ ጀመረ ። አሁን ደግሞ ዙሪያውን ያለው ውኃ እንደ ብዕር ቀለም ጥቁር ሰማያዊ ሆነ ።

ኢቫን ኢቫኒች ፣ ከተጠለለበት ቦታ ወጥቶ ውሃው ሙሰጥ ዘሎ በመግባት እጆቹን በማወራጨት ሲዋኝ ዙሪያውን መለስተኛ ማዕበል አስነሣ ። በውሃው ላይ ያሉ ትም አበቦች በተነሣው ማዕበል ዘለሉ ። እስከ ወንዙ መኻል ድረስ በዋና ዘልቆ በመግባት አንድ ቦታ ጠልቆ ትንሽ ቆይቶ በሌላ ቦታ ይወጣል ። ርቆ በመዋኘት ወደ ወንዙ እየገባና ያለማቋረጥ እየጠለቀ የወንዙን መሠረት ይነካ ነበር ።

“ተመስገን አምላኬ!” ይላል ከደስታው ብዛት “ተመስገን አምላኬ...” እስከ ነፋሱ መዘውር ድረስ ዋኝቶ በመሐድ ጥቂት ባላገሮችን አነጋግሮ በዋና ተመልሶ ወንዙ መኻል ሲደርስ ፊቱን ለዝናቡ ሰጥቶ ተንሳፈፈ ። ቡርኪንና አሌኪን ልብሳቸውን ለብሰው ለመመለስ ቢዘጋጁም ፣ ኢቫን ኢቫኒች ዋናውንና መጥ ለቁን ቀጠለ ።

“አምላኬ! አምላኬ!” በማለት ማድነቁንና መደ ሰቱን ቀጠለ ። “አይ አንተ አምላክ!!”

“ና ውጣ” በማለት ቡርኪን ጮኸበት ።

ከዚያ ተያይዘው ወደ ቤት ተመለሱ ። በፎቁ ላይ በትልቁ መልበሻ ክፍል መብራት በርቶ ፣ ቡርኪንና ኢቫን ኢቫኒች የሐር ቀሚስ ለብሰው ደረቅ ጫማ ተጫ ምተው ወንበር ላይ ተቀምጠዋል ። አሌኪን ታጥቦ አዲ ሱን ኮቱን ለብሶ በንጽሕናውና በሚሰጠው መቀት እንዲሁም በተጫማቸው ምቹ ጫማዎች እየተደሰተ ጸጉሩን እያበጠረ በክፍሉ ውስጥ ይንጐራደዳል ። ውበት የተላበሰችው ፔላጊያ ትልቅ ፈገግታ እያሳየችና ድምፅ በሌለው እርምጃ ምንጣፉን እየረገጠች የሻይ ማቅረቢ ያውን ይዛ ብቅ ስትል አሌኪን ታሪኩን መናገር ይጀ ምራል ። በግድግዳው ላይ የተሰቀሉት የጥንት ሴቶች ፣ ወጣት ወይዛዝርትና የጦሮ ሠራዊት መኰንኖች ምስ ሎች እነሱም የአሌኪንን ታሪክ የሚያዳምጡ ይመስል ወደ ታች ይመለከቷቸዋል ።

“ሁለት ወንድማማቾች ነበርን” በማለት ጀመረ ። “እኔ እራሴ ኢቫን ኢቫኒችና የሁለት ዓመት ታናሼ የሆነው ወንድሜ ኒኮላይ ኢቫኒች ፣ ትምህርት ቤት ገብቼ የእንስሳት ሐኪም ስሆን ታናሽ ወንድሜ ገና በዐሥራ ዘጠኝ ዓመቱ በመንግሥት ሥራ ተቀጠረ ። አባታችን ቺምሳ-ሂማላያስኪ የተማረው የተራ ወታደር ልጅች በሚማሩበት ትምህርት ቤት ነው ። በኋላ ግን ፣ የመኰ ንንነት ማዕረግ ስላገኘ ትልቅ ሰው ሆኖ ለትውልድ የሚተላለፍ እርስትም ተሰጠው ። አባታችን ከሞተ በኋላ እርስቱ ዕዳ ለመክፈል ቢሸጥም የልጅነት ጊዜ ያችን ፣ ገጠሩን በመዞር ፣ ፈረሶችን ወደ መስክ በማ ውጣትና ፣ በማገድ ፣ የዛፎችን ቅርፊቶች በመላጥ ፣ ዓሣ በማጥመድና ሌሎችም ብዙ ድርጊቶችን በመፈጸም

ፀገጠሩ በደስታ አሳልፈነዋል ። ማንም ሰው አንድ ጊዜ በሕይወቱ ዓላ ያጠመደ ወይም በመጸው ወራት ጥቁር ወፎች በጅምላ ሆነው ቀዝቃዛማ ብሩህ በሆነ ቀን በመ ንደሩ ላይ ክፍ ብለው ሲበሩ የተመለከተና የከተማ ኑሮ ያሞላቀቀው ቀሪውን ሕይወቱን በገጠር ለማሳለፍ የማይጓጓ የለም ። ወንድሜ በዚያው የመንግሥት መ/ቤት የሙጥኝ ብሎ ቀረ ። ዓመታት ፀለፉ ። እሱ ግን አንድ ቦታ ተቀምጠ በየቀኑ አንድ ዐይነት ሠነድ እየጻፈ ሁል ጊዜ አንድ ነገር ፥ እንዴት ወደ ገጠር እንደሚመለስ ያስባል ። ይህ ምኞቱ ቀስ በቀስ ወደ ቁርጠኛ ፍላጎት በገጠር አንድ ወንዝ መይም ሐይቅ ዳር ያለ አነስተኛ እርሻት ወደ መግዛት ሕልም አደገ ።

"ትሑትና ደግ ልጅ በመሆኑ እወደው ነበር ። ግን ፥ በራስ ቁራጭ መሬት ላይ ለሁልጊዜው ተዘግቶ የመኖሩን ሐሳብ እማልደግፈው ነበር ። አንድ ሰው ስድስት ክንድ መሬት ብቻ እንደሚያስፈልገው ይነ ገራል ። ነገር ግን ፥ ይህ ስድስት ክንድ መሬት የሚያ ስፈልገው በሕይወት ላሉ ሰዎች ሳይሆን ለሙታን ነው ። አሁን ደግሞ ሰዎች ፥ የኛ ምሁራን መሬት መፈለጋቸውና የገጠር መኖሪያ ለማግኘት ሙጣራቸው ጥሩ ምልክት ነው ይላሉ ። እነኝህ እርስቶች ግን እላይ ከተገለጹት ስድስት ክንድ መሬቶች በምንም ዐይነት የሚለዩ አይደሉም ። ከከተማው ዝብርቅርቅ ሕይወትና ከትግል ሸሽቶ በገጠር በሚገኝ መኖሪያ ራስን መደበቅ ሕይወት ሳይሆን ራስ ወዳድነት ፥ ሥራ ፈቅነትና ክህደት መይም ተስፋ መቁረጥ ነው ። ሰው የሚያስፈልገው ስድስት ክንድ መሬት መይም የገጠር

መኖሪያ ሳይሆን ችሎታውን ፥ ዕውቀቱን ፥ የግል ተሰጥ
አውን ሊያሳይ የሚችልበት መላዋ ዓለምና ተፈጥሮ
በአጠቃላይ ናቸው ።

"ወንድሜ ኒኮላይ ፥ ቢፎው ውስጥ ተቀምጠ የሚያ
ልመው ከጓሮው ከተቀጠፈ ጐመን የሚሠራው ጥሩ
የሾርባ መዓዛ ግቢውን ሲያውደው ፥ ሾርባውን ሲጠጣ ፥
ግቢው ውስጥ አረንጓዴው ሣር ላይ ተቀምጠ የሚበላ
ውን ምግብ ፥ ፀሐይ ላይ የሚተኛውን ፥ በግቢው በር
ላይ በሚኖረው አግዳሚ ለብዙ ሰዓታት የሚቀመጠውና
አሻግሮ የሚመለከተውን መስክና ደን ነው ። ስለ ግብ
ርና የተጸፉ መጻሕፍት ፥ በቀን መቁጠሪያዎች ላይ
የሚወጡ ግብርና ነክ ጥቆማዎች ያስደስቱታል ። ተወ
ዳጅ የመንፈስ ምግቦቹ ናቸው ። ጋዜጦች ማንበብም
ይወዳል ። የሚያነበው ግን ፥ በጋዜጦቹ ላይ ስለሚሸጥ
ከመኖሪያ ቤት ጋር ስለ ተያያዙ አያሌ ሄክታር ምንጮች
የሚገቡባቸው ኩሬዎች ያለበትን ማስታወቂያ ብቻ
ነው ። በአዕምሮው የሚያወጣውና የሚያወርደው ስለ
እትክልት ቦታ ፥ መንገዶች ፥ አበቦች ፥ ፍራፍሬ ፥ የወፍ
ጐጆዎች ፥ የዓሣ ኩሬዎችና ስለ መሳሰሉት ጉዳዮች
ነው ። የሚያስበውና የሚያውጠነጥነው ሁሉ በጋዜጦች
ላይ በሚያገኘው ማስታወቂያ ዐይነት ቢለያይም ፥ የእን
ጆሪን ተክል ሐሳብ መጭጭ ብሎ ይዟል ። በሐሳቡ የእ
ንጆሪ ተክል የሌለበት የገጠር መኖሪያ ወይም ጊዜያዊ
መኩብልያ ቦታ ሊያስታውስ አልቻለም ።

"የገጠር ኑሮ ምኞት አለው" ይላል ። "በረንዳው
ላይ ተቀምጠህ ሻይ ስትጠጣ ፥ የግልህ የሆኑት ዳክዬ
ዎች ኩሬው ውስጥ ሲንሳፈፉ ፥ ሁሉም ነገር መልካም

መዓዛ ሲሸትና ...እንጆሪው በዛፎቹ ላይ ሲበስል ማየት ያስደስታል ።"

"ለእርስቱ ፕላን ያወጣል ። የእያንዳንዱ ፕላን ይዘት ግን አንድ ዐይነት ነው ። ፀ/ ዋናው መኖሪያ ፣ ል/የእሽ ክሮች መኖሪያ ፣ ሐ/ የማዕድ ቤትና የአትክልት ቦታ ፣ መ/ የእንጆሪ ተክል ፣ የሚኖረው በቁጠባ ሲሆን ሆዱ እስኪ ሞላ በልቶና ጠጥቶ አያውቅም ። አለባበሱም ልክ እንደ ለማኝ ነው ። የሚያገኘውን ገንዘብ ሁሉ ባንክ ያስቀምጣል ። በጣም ቆንቋናና ስስታም ሆነ ። እሱን ማየትም አስጠላኝ ። ትንሽ ገንዘብ ስላጠው ወይም በበዓላት ቀን ጊዜ ስጦታ ስልክለት ያንንም አይጠቀምበትም ፣ ባንክ መስዶ ያስቀምጣል ። አንድ ሰው አንድ ሐሳብ ሙጭጭ ብሎ ከያዘና ከጨበጠ ምንም ማድረግ አይቻልም ።

"ዓመታት ዐለፉ ። ወደ ሌላ ክፍለ ሀገር ተዛወረ ። ዕድሜው ዐርባ ዓመት ቢሆንም ፣ በጋዜጦች ላይ የሚወጡትን ማስታወቂያዎች ማንበብና ገንዘቡን ባንክ ማስቀመጥ አላቆመም ። በመጨረሻም ማግባቱን ሰማሁ ። ያገባው ለአንድ ዓላማ ፣ የእንጆሪ አትክልት ያለበት መኖሪያ ቦታ ርስት ለመግዛት ነው ። ያገባት ሴትዮ በዕድሜ የገፋችና አስቀያሚ ከመሆኗም በላይ ፣ የሚያፈቅራት አልነበረችም ። ያገባት ትንሽ ገንዘብ ስለ ነበራት ብቻ ነው ። ካገባም በኋላ ስስታምነቱ አልቀነሰም ። ሚስቱን በረኃብ አለንጋ እየገረፈ ገንዘቧን በራሱ የባንክ ሒሳብ ማስገባት ጀመረ ። የመጀመሪያው ባሏ የፖስታ ቤት ኃላፊ ስለ ነበር ፣ ኬክና የፍራፍሬ ጭማቂ አስለምዷት ነበር ። ከሁለተኛው ባሏ ግን ፣ የምትበላው በቂ ጥቁር ዳቦ እንኳን

ማግኘት አልቻለችም ። በዚህ ምክንያት ለሦስት ዓመታት ከተሠቃየች በኋላ ሞተች ። ወንድሜ ለትንሽ ጊዜ እንኳን ቢሆን ለሴትዮዋ ሞት ወንጀለኛነቱ አልታሰበውም ። ገንዘብ ልክ እንደ ፅድቅ ፣ ሰው ሕሊናውን እንዲስት ያደርጋል ። በከተማችን አንድ ነጋዴ ታሞ አልጋው ላይ ተኝቶ ለሞመት ሲያጣጥር አንድ ሣህን ማር እንዲ ቀርብለት ጠይቆ ቢሰጠው ፣ ሌሎች ሰዎች እንዳይጠ ቀሙበት የገዛውን የሎተሪ ትኬትና ያለውን ገንዘብ በሙሉ በማሩ እየጠቀለለ ዋጠው ። አንድ ቀን ወደ ውጭ የሚላኩ ክብቶችን ባቡር ጣቢያ ሲመረምር ፣ አንድ ከብት ነጂ በባቡር ተገጭቶ እግሩ ተቆርጦ ወደቀ ። ደም በደም ሆኖ ተሸክመን ማረፊያ ቤት ስናደርሰው በጣም እያዘነ የተቆረጠውን እግሩን እንድንፈልግለት ለመነን ። በጫማው ውስጥ ኻያ ሩብሎች ስለነበሩ እን ዳይጠፉበት ፈርቶ ነበር ። ”

“ከመሥመር እየወጣህ ታሪኩን እየሳትክ ነው” አለው ቡርኪን ። ኢቫን ኢቫኒች ለትንሽ ጊዜ ቆም ብሎ ትረካውን ቀጠለ ። “ከባለቤቱ ሞት በኋላ ወንድሜ የሚ ገዛው እርስት መፈለግ ጀመረ ። ለአምስት ዓመት ልት ፈልግ ትችላለህ ። በመጨረሻ ግን ተሳስተህ ያልፈለከ ውን ካሰብከው ዓላማ ውጭ ትገዛለህ ። ወንድሜ በላዩ ላይ የባለ ርስቱና የአሽከሮቹ መኖሪያ ቤትና የመና ፈሻ ቦታ ያለው 136 ሄክታር መሬት በወኪል የሚከ ፈል በወለድ አግድ ገዛ ። ነገር ግን ወንድሜ እንዳላማው የወይንና የእንጆሪ አትክልት ወይም በላዩ ላይ ዳክ ዬዎች የሚንሳፈፉበት ኩሬ ያለው አልነበረም ። ወንዝ በአጠገቡ ቢኖርም የሸክላ ሥራና የአጥንት መጥ

በሻ ደርጅዮች በወንዙ ግራና ቀኝ ስላሉ ውሃው ጥቁር ነው ። ወንድሜን ምንም ተስፋ ሳያስቆርጠው ኻያ አራት የእንጀራ ችግኞች ገዝቶ በመትከል የወጣለት ባልር ስት ሆኖ ተቀመጠ ።

"በምን ሁኔታ ላይ እንዳል ለማወቅ ስለ ፈለግሁ ያለፈው ዓመት ሐጂ ጠየቅሁት ። በደብዳቤው ላይ ወን ድሜ የሰጠኝ አድራሻ ቹምባሮክለሻ ጉዮሽ ወይም ሂማ ላይ ስኩዬ የሚል ነበር ። ሂማላይ ስኩዬ ከሰዓት በኋላ ደረስኩ ። በጣም ሞቃት ነበር ። በያለበት ጉድንድ ፥ አጥር ፥ ቁጥቋጦና በመሥመር የተተከሉ ዛፎች ስላሉ ወደ ግቢ ገብቶ ሠረገላ ማቆሚያ ቦታ ለማግኘት አስቸ ጋሪ ነበር ። ወደ ግቢው ስገባ አንድ ጠብደል ዓሣማ እንጂ ፥ ውሻ የማይመስል ውሻ ተቀበለኝ ። ሰነፍ ባይ ሆን መጮህ ነበረበት ። ወፉራምና ዓሣማ የምትመስለው ወጥ ቤት ባዶ እግሯን ከማዕድ ቤቱ በመውጣት ጌታዋ የምሳ በኋላ ፅረፍት ላይ መሆኑን ነገረችኝ ። ወደ ወንድሜ ክፍል ስገባ እግሮቹን በብርድ ልብስ ሸፍኖ አልጋው ላይ ተቀምጧል ። ከማርጀቱም በላይ ወፍሮ ክብደት ጨምሯል ። ጉንጮቹ ፥ አፍንጫውና ከንፈሮቹ ወደ ውጭ አሞጥሙጠው ሳይ በጥላቻ ወደ ብርድ ልብሱ ውስጥ ይገባ ይሆናል ብዬ ጠብቄው ነበር ።

"ተቃቅፈን ተላቅሰን - ደስታና ኀዘን የተቀላቀለበት ለቅሶ - ምክንያቱም ያን ጊዜ ወጣት ነበርን ። አሁን ግን ሁለታችንም ሸብተን ወደ መቃብር የምንወርድበ ትን ጊዜ በመጠባበቅ ላይ በመሆናችን ነው ። ልብሱን ለብሶ መሬቱን ሊያሳየኝ ተያይዘን ወጣን ።"

“ታዲያስ ፥ እንዴት ይዞሃል ይሽ ቦታ?”ስል ጠየ
ኩት ።

“ደኅና ነው ፥ ይመስገነውና በደስታ እኖራለሁ።”

“እንደ ዱሮው ደሃ ፥ ዐይናፋርና ተራ አሐፊ አይ
ደለም ። አሁን ሐቀኛው ባለ ርስት ሆኗል ። ደኅና
ሆኖ ስለ ተደላደለ ፥ በገጠሩ ኑሮ ፀደስታና በፍላጎት ገብ
ቶበታል ። ደኅና አድርጉ እየበላ በመታጠቢያ ቤቱ ስለ
ሚታጠብ ክብደት ጨምሯል ። ከሸክላ ሥራውና ከአጥ
ንት መጥበሻው ድርጅት ጋር መካሰስ ጀምሯል ። የአ
ካባቢውም ባላገሮች በስሙ ላይ የተከበሩ የሚል
ካልጨመሩበት በጣም ይቆጣል ። አንድ ጨዋ ሰው እንደ
ሚያደርገው ሁሉ ፍጹም ሃይማኖተኛ ከመሆኑም በላይ
ሳይግደረደር ስላልፈጸመው በጉ ምግባሩ ይናገራል ። እነ
ኚህ በጉ ምግባሮች ምን ነበሩ? ሁሉንም የባላገሩን የፀ
ሽታ ዐይነት ፀባይካርቦኒት ሶዳና በጉሎ ዘይት ያክ
ማል ። በስሙ በሚከናወን የጸሎት ቀን መደረግ ያለበት
መልካም ትሩፋት ነው ብሎ በማሰብ ግማሽ ባልዲ
ቦድካ ለባላገሩ ይሰጣል ። እነኚያ የተረገሙ ግማሽ ባል
ዲዎች! ወፍራሙ ባለመሬት ከባላገሩ አፈላማ ለማግ
ኘት ዛሬ በጐቻችሁ ሣሬን ጋጡ በማለት ክስ ያቀርብ
ባቸዋል ። ነገ ደግሞ በበዓል ቀን ግማሽ ባልዲ ቦድካ
ሲሰጣቸው እየዘፈኑና እየደነሱ ጠጥተው ሲሰክሩ እግሩ
ሥር ወድቀው ያሞግሱታል ። በኑሮው መሻሻልና መለ
ወጥ በአንድ ሩሲያዊ ውስጥ በጣም ደካማ የሆነ በግል
ሁኔታ የመርካት መንፈስ ይፈጥራል ። ኒኮላይ ኢቫኒች
በመንግሥት መ/ቤት ሲያገለግል ከፍርሃቱ የተነሣ የራሱ
የሆነ ሐሳብ ያልነበረው አሁን ወደ አደባባይ እየወጣ

ሥልጣን በተሞላ ሁኔታ ‘ትምህርት አስፈላጊ ነው ፤ ሆኖም ሕዝቡ ለመማር ገና ዝግጁ አይደለም ፤ የሞት ቅጣት መጥፎ ነው ። ሆኖም በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ጠቃሚና አስፈላጊም ነው’ እያለ ጸጉር ይልነጥቃል ።

“ሕዝቡን ዐውቃለሁ ፤ እንዴት እንደሚያዝም ዐቅ በታለሁ” ይላል ። “ሕዝቡ ይወደኛል ። እኔ ያለብኝ ትንሿን ጣቴን ማንሣት ብቻ ነው ። ከዚያ ሕዝቡ የም ፈልገውን ይፈጽምልኛል ። ”

ይህን ሁሉ የሚናገረው ፈገግታ በቱሞላ ደስታ ነው ። ደግሞ ደጋግሞ ‘እኛ መኳንንት’ ወይም “እንደ ጨዋ ልጅ ስናገር’ እያለ ሲያወራ አያታችን ባላገር፣ አባታችን ተራ ወታደር መሆኑን የዘነጋው ይመስለኛል። የቤተሰባችን ስም-ቺምሻ-ሂማላያስኪ- በጣም ተራ የነ በረው ዛሬ ለእርሱ የተከበረና የታወቀ ስም መስሎ ይታ የዋል ።

“ግን ስለ ራሴ እንጂ ስለ እርሱ አይደለም ! መና ገር የምፈልገው ። በወንድሜ መሬት ላይ ባሳለፍኳ ቸው ጥቂት ሰዓታት ውስጥ በራሴ ላይ የመጣውን ለውጥ ነው ልገልጽላችሁ የምወደው ። ወደ ማታ ተቀ ምጠን ሻይ ስንጠጣ ሠራተኛው አንድ ሣህን እንጆሪ አቀረበችልን ። እንጆሪው በገንዘብ ከገበያ የተገዛ ሳይ ሆን ከመሬቱ ላይ እሱ ራሱ ከተከለው የእንጆሪ ተክል የተለቀመ የመጀመሪያ ምሥራች ነበር ። ኒኮላይ ኢቫኒች በሣቅ እየፈነዳ በሣህኑ ላይ ያለውን እንጆሪ እንባ ባዘሉ ዐይኖቹ ለአምስት ደቂቃ ያህል አፍጥጦ ተመለከተው ። በስሜት መናገር አቅቶት አንድ የእንጆሪ ፍሬ አንሥቶ

ወደ አፉ ፀመከተት ፣ አንድ ሕፃን ለረጅም ጊዜ ሲጓጓ ለት የነበረውን አሻንጉሊት በድንገት ሲያገኝ የሚያ ሳየው መደሰትና መፈንደቅ ዐይነት ዐይኖቹን ወደኔ በመወርወር እንዲህ አለ ።

"ጣፋጭ!"

ፀመስገብጉበ እየበላ ደግሞ ደጋግሞ ፣
"ጣፋጭ ነው ! እልቲ ሞክረው ?"

እንጆሪው ያልበሰለና ኮምጣጣ ነበር ። ግን ፤ ጉሽኪን እንዳለው ፣ ኩራት የሚሰጠን ውሸት ከአንድ ሺህ እውነቶች የበለጠ ተወዳጅ ይሆንብናል ። ከፊት ለፊቴ ምኞቱ የተፈጸመለት ፣ በሕይወቱ ያሰበው ነገር የተሳካለት ፣ የፈለገውን ነገር ያገኘ ፣ ባደረገውና በራሱ ጭምር የተደሰተ ሰው ከፊቴ ተቀምጦ ተመለከትኩ ። ስለ ሰው ልጅ ደስታ የነበረኝ አመለካከት በትንሽ ጎዘን የተሸፈነ ነበር ። ይህ ስሜት በተለይ የሚያይል ብኝ ሌሊት ነው ። መኝታ የተዘጋጀልኝ ወንድሜ መኝታ ቤት ጉን ስለነበር ፣ በአልጋው ላይ ሲወራጭና በመደ ጋገም ከአልጋው ላይ እየተነሣ ከሣህኑ ላይ እንጆሪ ሲያ ነሣ ሁሉ ይሰማኛል ። ለመሆኑ ስንት የተደሰቱና ረክ ተው የሚኖሩ ሰዎች ይኖሩ ይሆን አልኩ ራሴን በራሴ ። ምን ያህል ብዛት ያለው ኃይል!ተመልከቱ ይህቺን ሕይ ወት ። የጠንካራውን ብልግናና ሥራ ፈትነት ፣ የደካማ ውን ማይምነትና አውሬነት ፣ በያለበት የሚያሰቅቅ ድህነት ፣ የተጨናነቀ መኖሪያ ፣ ዝቅጠት ፣ ስካር ፣ አስመ ሳይነት ፣ ውሸት ...እንዲህ ሆኖም በእያንዳንዱ መኖሪያ ቤትና በየመንገዱ ግን ፣ ሰላምና መረጋጋት የሰፈነ መስሎ ይታያል ። ከሃምሳ ሺህ የአንድ ከተማ ነዋሪ

አንድ ሰው እንኳን ድምፁን ከፍ አድርጎ መክፋቱንና ቁጣውን የሚገልጽ አይገኝም ። ምግብ ለመሸመት ወደ ገቢያ የሚወጡትን ፣ ቀን ምሳቸውን በልተው ማታ የሚ ተኙትን ፣ የሆነ ያልሆነውን የሚቀባበሩ ቀባጣሪዎችን የሚያገቡትን ፣ የሚያፈጁትንና ሙታናቸውን ለመቅበር ወደ መቃብር የሚወስዱትን ሁሉ እኖያለን ። ነገር ግን የሚሠቃዩትን ማየትም ሆነ መስማት አንፈልግም ። በሕይወት ወይም በኑሮ ውስጥ በጣም አሠቃቂ የሆኑ ነገሮች ሁሉ የሚካሔዱት ከመጋረጃ በስተጀርባ ከታ ይታ ውጭ ነው ። ብዙዎች አጸደዋል ፤ አያሌ በርሜ ሎች መጠጦች ተጠጥተዋል ፤ ብዛት ያላቸው ሕፃናት በተመጣጠነ ምግብ እጦት አልቅዋል ...ይህም መሆን ያለበት ነገሮ መስል ይታያል ። ደስተኞች የሚደሰቱ የሚመስሉት ፣ የማይደሰቱት ሽክማቸውንና አለመደሰታ ቸውን ሳይገልጡ አምቀው በመያዛቸው ምክንያት ነው። ከእያንዳንዱ ደልተኛ ሰው ሙኖሪያ ቤት በር ጀርባ አንድ መዶሻ የያዘ ሰው ቆሞ ያለማቋረጥ እያንኳኳ ደስተኛ ያልሆኑ ሰዎች መኖራቸውን ፣ ሕይወት አንድ ጊዜ እውነተኛ ስል ጥፍሮቿን እንደምታሳየውና አደጋ ፣ በሽታ፣ ድህነት ፣ ክስረት እንደሚደርስበት ፣ አሁን እርሱ ደስ ተኛ ፀሆነበት ጊዜ የሰዎችን ችግር እንደማያይና እንደ ማይረዳ በሱ ላይ የሚደርሰውን ችግርና አደጋ የሚመ ለከት ሰው የማይኖር መሆኑን የሚያስታውሰው ሰው መኖር አለበት ። ነገር ግን መዶሻ የጨበጠ ሰው የለም። ደስተኛው ሰው የአዱኛ ለውጥ ብዙም ስለማይነካው እንደ ተደሰተ ይቀጥላል ።

"የዚያን ዕለት ምሽት እኔም ደልተኛ መሆኔ ገባኝ" በማለት ንግግሩን ቀጠለ ኢቫን ኢቫኒች ብድግ ብሎ ።

"እኔም ልእደን ስወጣ ወይም ምግብ ጠረጴዛ ላይ ስቀ መጥ ትክክለኛውን መንገድ በመያዝ ለመኖር ፥ ለማም ለክና ሕዝቡን ለማስተዳደር ወሰንክ ። ያለ ዕውቀት ብርሃን እንደማይኖር ለመኖር ነጻነት አስፈላጊ ነው ። ግን መጠበቅ ይኖርብናል" አልኩኝ ። አምን ፤ ይህንኑ ነበር ያልኩት ። "አሁን ደግሞ እንደገና እጠይቃለሁ ፤ በማን ስም ነው የምንጠበቀው ?" እዚህ ላይ ኢቫን ኢቫኒች ቡርኪን ላይ ቁጣ አፈጠጠበት ። "በማን ስም ነው የምንጠብቀው ብዬ እኮ ነው የምጠይቅህ? ምንድነው የሚጠብቀው? እንደዚህ ኢትቸኩል ። እያን ዳንጹ ሐሳብ ቀስ በቀስ ተግባራዊ የሚሆንበት የራሱ ጊዜ አለው ይሉኛል ። ግን ይህን የሚሉት እነማን ናቸው ? ትክክል ለመሆኑ ምን ማስረጃ አለ? የም ትመለከቱት የነገሮችን ተፈጥሮአዊ ክትትል ፥ የእው ነቱን ሥነ አመክንዮታዊነት ነው ። ነገር ግን ፥ በምን ሥነ ሥርዓትና ሥነ አመክንዮ ነው እኔ አንድ ሕያውና የማስብ ፍጡር አንድ ጉድጓድ ቢያጋጥመኝ ዘልዬ ወይም ድልድይ ሠርቼ ለማለፍ ስችል ቀስ በቀስ በአፈር እስኪ ሞላ ድረስ የምጠብቀው ? አሁንም እንደገና በምን ስም ነው መጠበቅ ያለብን? መኖር ቢኖርብንምና መኖር ብንፈልግም የመኖር አቅም ሳይኖረን እንጠብቃለን!"

"በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ከወንድሜ ተለየሁ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የከተማን ኑሮ አልቻልኩትም ። ሰላ ሙና ሥነ ሥርዓቱ መንፈሴን ከበደው ። ለኔ በሻይ ጠረ ጴዛ ዙሪያ በደስታ ከተቀመጠ ቤተሰብ የበለጠ የሚያሳ ዝነኝ ስለሌለ ፥ በመስኮት በኩል ወደ ውጪ ማየት እንኳን አስፈራኝ ። ሽማግሌ በመሆኔ ለትግሉም አልመጥንም ።

ለመጥላት እንኳን ችሎታ የለኝም ። በውበቱ ብቻ እሠ
ቃያለሁ ። ማታ ማታ የሐሳብ ማዕበል ስለሚበዛብኝና
ስለሚያንገላታኝ መተኛት አልችልም ። ወጣት በሆን
ኩኝ ኖሮ!''

ኢቫን ኢቫኒች ወደፊትና ወደኋላ እየተንጐራደደ
ይመደጋገም ፥

''ወጣት በሆንኩኝ ኖሮ!''ይላል ።

በድንገት እሌኪን ወደ ተቀመጠበት ፀመሔድ
መጀመሪያ አንድ እጁን ከዚያም ሁለተኛ እጁን አስ
ቀመጠበት ።

''ፓቬል ኮንስታንቲኒች'' አለው በልመና ዐይነት
አጠራር ። ''ምኞትህንና ፍላጎትህን አትግደለው ፤ ሕሊ
ናህ እንዲተኛ እሽሩሩ አትበለው ! ወጣት ፥ ጠንካራና
የመሥራት ዐቅም እያለህ በጎ ሥራ መሥራት እይ
ድከምህ ። ደስታ የሚባል ነገር የለም ፤ መኖርም የለበትም፤
ግን መኖር ትርጉሙ ወይም ዓላማ ካለው ፥ ይህ የመኖር
ትርጉምና ዓላማ የሚገኘው በኛ ደስታ ውስጥ ሳይሆን
በጣም ትልቅና ትክክል በሆነ ነገር ውስጥ ነው ። ደግ
ሥራ!''

ኢቫን ኢቫኒች ፥ ይህን ሁሉ የተናገረው ለራሱ አንድ
ነገር የሚጠይቅ ይመስል የሚያሳዝንና ልመና ያለበት
ፈገግታ በማሳየት ነበር ።

ከዚያም ሦስቱም ተራርቀው በወንበሮቻቸው ላይ
ዝም ብለው ተቀመጡ ። የኢቫን ኢቫኒች ታሪክ አሌ
ኪንንም ሆነ ቡርኪንን አላስደሰታቸውም ። በግድግዳው

ላይ በጥሩ ማቀፊያ የተንጠለጠሉ የጄኔራሎችና የወይ ዛዝሮት ፎቶግራፎች እየተመለከቱ እንጆሪ ስለሚበሉ፣ የአንድ ተራ ደሃ ጸሐፊ ታሪክ መስማት አልጣማ ቸውም ። ባለግርማ ስለሆኑ ሰዎችና ቆነጃጅት ቢሆን ኖሮ መስማቱ የበለጠ ባስደሰታቸው ነበር ። ሁሉም ነገር የተሟላበት-የሻማ ማብሪያ ፣ ባለመደገፊያ ወንበሮች ፣ ምንጣፍ- አሁን የተቀመጡበት ክፍል ውስጥ ዛሬ ምስ ላቸው ግድግዳ ላይ ተሰቅሎ የሚታዩት መኳንንትና ወይዛዝፍት አንድ ጊዜ በሕይወት ዘመናቸው አሁን ውቧ ፔላጊያ ድምፅ ሳታሰማ ወዲያ ወዲህ በምትል በት በዚህ ክፍል ውስጥ እየተዘዋወሩ በወንበሮቹ መቀመጣቸውንና ሻይ መጠጣታቸውን መተረኩ የተሻለ ነበር ።

አሌኪን ክፉኛ እንቅልፍ ይዞታል ። በመሬቱ ላይ ያለውን ሥራ ለማቀነባበር የተነሣው ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ስለነበር ፣ አሁን ጨርሶ ዐይኖቹን መክፈት አል ተቻለውም ። ነገር ግን ፣ እሱ ከሔደ በኋላ እንግዶቹ የሚያስደስት ታሪክ የሚተርኩ ስለመሰለው ፣ ሔዶ ለመተኛት አልፈለገም ። ኢቫን ኢቫኒች የተረከው ታሪክ ትክክል ይሁን ወይም እንግዶቹ ከእርሱ የዕለት ተዕለት ሥራ-እህል ፣ ድርቆሽ ፣ ናፍታ ጋር የማይገናኝ ነገር በመተረካቸው እርግጠኛ ባይሆንም ፣ ትረካው ደስ ስላልው እንዲቀጥሉ ...ፈልጎ ነበር ።

"ደኅና ፣ እንግዲህ የመኝታ ሰዓት ነው"አለ ቁርኪን ከመቀመጫው በመነሣት ።

"ደኅና እደሩ እንድላችሁ ይፈቀድልኝ ። "

አሌኪን ደኅና እደሩ ብሎ ወደ መኝታ ክፍሉ ምድር ቤት ሲወርድ እንግዶቹ ፎቅ ላይ ቀሩ። በአንድ ትልቅ ሰፊ ክፍል ውስጥ ፱አንድ በኩል የመስቀል ቅርፅ ያለባቸው ሁለት የጥንት አልጋዎች ተነጥፈውላቸው ነበር። ውቢቱ ፔላጊያ ያነጠፈችላቸው የንጹህ አንሶላዎች ጠረን የሚያስደስት ነበር።

ኢቫን ኢቫኒች ልብሶቹን አውልቆ ተጋደመ።

"ጌታ ሆይ! እኛን ኃጢአተኞችን ይቅር በለን" በማለት በአንሶላው ተከናንቦ ተኛ።

ጠረጴዛው ላይ ያስቀመጠው የትምባሆ ፒፓ ኃይለኛ የሚሰነፍጥ ሽታ ስለ ነበረው፥ ይህ የሚሰነፍጥ ሽታ ከየት እንደሚመጣ ያላወቀው ቱርኪን ለረጅም ጊዜ እንቅልፍ ሳይወስደው ነቅቶ ተቀመጠ።

ዝናቡ የመስኮቱን መስተዋት ሌሊቱን ሁሉ ሲደበድብ አደረ።

ዩኒች

ወደ 'ሠ' ከተማ የሚመጡ ባይተዋሮች በከተማ ይቱ ውስጥ የሚያጋጥማቸውን አሰልቺ ሁኔታ አንሥ ተው ሲያማርሩ ፣ የከተማይቱ ነዋሪዎች ደግሞ ከተማ ይቱ ፣ ቤተ መጻሕፍት ፣ ትያትር ቤት ፣ ዐልፎ ዐልፎ የዳንስ ምሽት የሚካሔድበት ክበብ ያላት ፣ አስደሳች ከተማ መሆኗን በመግለጽ ይናገሩላታል ። ከዚህም በላይ ልትውውቅ የሚሆኑ ፀዋቂና አስደሳች ቤተ ሰቦች እን ዳሏት በመናገር ለአብነትም እንዲሆን ሥልጡንና ብል ሁን የቱርኪንን ቤተሰብ ይጠቅሳሉ ።

የቱርኪን ቤተሰብ በከተማይቱ ዋና መንገድ ፣ በአ ገረ ገሾው መኖሪያ ቤት አጠገብ ፣ በራሱ ቤት ውስጥ ይኖራሉ ። የቤተሰቡ ኃላፊ ፣ ኢቫን ፔትሮቪች ፣ ጠንካራና ደልዳላ ሰውነት ፣ ጥቁር ጸጉር ፣ ረጂም ፣ የላይኛው ከን ፈር ጺም ያለው ፣ መልከ መልካም ሰው ነው ። ገቢው ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚውል የትያትር ቡድን አለው ። የትያትር ቡድኑ በሚያሳያቸው ትዕይንቶች እንደ ሽማ ግሌ ጀኔራሎች በመሆን ረሽዎና በሣቅ የሚያፈነዳ ሳል በመሳል ይጫወታል ። ተዘግነው የማያልቁ አስደ ሳችና አስደናቂ ታሪኮች ፣ ቁረትና ምሳሌዎች እንዴ ሁም የማይመሰል ችሎታዎች አሉት ።

ቀልድና ፬ልት የሚያበዛ ሰው በመሆኑ አምርሮ መናገሩን ክቀልዱ መለየት አስቸጋሪ ነው ። ባለቤቱ

ቪራ የሲፎቭና ፣ ቀጭን አስያሳች መልክ ያላትና መነ ጽር የምታደርግ ወይዘሮ ናት ። የአጫጭር ታሪኮችና ልብ ወለዶች ደራሲ ስትሆን ፣ ድርሰቶቿን ለጐብኝዎቿ ድምጿን ከቁ አድርጋ ማንበብ ትወዳልች ። ባልና ሚስቶቹ ፒያኖ መጫወት የምትችል የቴሪና ኢባኖቭና፣ የምትባል ሴት ልጅ አለቻቸው ። ባጭሩ የቤተሰቡ አባላት የተለያየ ችሎታ ያላቸው ናቸው ። ቤተሰቡ እንግዳ ተቀባይ ሲሆን ፣ የቤቱሰቡ አባላት ችሎታቸውን ቀላልና ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያሳዩ ናቸው ። በክረምቱ ወራት ከድንጋይ የታነፀው ቤታቸው ይቀዘቅዛል ። የቤቱ የኋላ መስኮቶች በጸደይ ወራት አዕዋፍ በብዛት ወደሚዘምሩበት የአትክልት ቦታ የሚከፈቱ ናቸው። እንግዶች በሚኖሩበት ጊዜ በማዕድ ቤት የሚሰማው የቢላዋ ግጭትና ፍጭት ፣ ግቢውን የሚያውደው የሽን ኩርት ቱሌት ሽታ መልካም እራት እንደሚኖር ያበሥራል ።

ለክልሉ የተመደበው የጤና - መኮንን ፣ ዶክተር ዲሚትሪ ዩኒች እስታርትዜቭ ፣ ከ "ሠ" ከተማ ዘጠኝ ኪ. ሜትር ርቆ በሚገኘው መኖሪያው ፣ ድያሊኘር ፣ እንደ ደረሰ ማንኛውም ሥልጡንና የተማረ ሰው እንደሚያደርገው ከቱርኪን ቤተሰብ ጋር ሙተዋወቅ እንዳለበት ይነግረዋል ። በክረምቱ ወራት አንድ ቀን በመንገድ ላይ ከኢቫን ፔትሮቪች ጋር ሰዎች ያስተዋውቁታል ። እንደ ተዋወቁ ስለ አየሩ ጠባይ ፣ ስለ ትያትርና በወቅቱ እየተስፋፋ ስለ ነበረው የኮሌራ በሽታ ከተወያዩ በኋላ ፣ ኢቫን ቤተሰቡን እንዲጐበኝ ይጋብዘዋል ። በጸደይ ወራት የሚውለው በአንዱ የበዓል ቀን እስታርትዜቭ

በዕለቱ የሚጐበኛቸውን ሕመምተኞች ከጐበኘ በኋላ ለመዝናናትና ዕቃ ለመግዛት ወደ ከተማ ወጣ ። እስትራ ትዜቭ ገና የራሱን ሠረገላ ያላዘጋጀ ስለ ነበር ፥ "ከሕ ይወት ዋንጫ እንባ መጐንጨትን ተማርኩ" የሚ ለውን ዘፈን እያንጐራጐረ በተዝናና እርምጃ በእግሩ ወደ ከተማ ገሠገሠ ።

በከተማው ምግብ ቤት ተመግቦ በፓርኩ ውስጥ ሲዘዋወር ኢቫን ፔትሮቪች ያደረገለት ግብዣ ትዝ አለውና የቱርኪንን ቤተ ሰብ ለመጐብኘትና ምን ዐይ ነት ሰዎች እንደሆኑ ለማወቅ ወሰነ ።

"እንደምን አለህ ! እንደምን አለህ !" አለ ኢቫን ፔትሮቪች በረንዳው ላይ እየተቀበለው ። "ስትጠበቅ የነበርከው እንግዳችን በመምጣትህ ደስ ብሎናል! ግባ ፤ ባለቤቴን ላስተዋውቅህ ። "ባለቤቴን ከዶክተሩ ጋር እያስቀዋወቀ ቬራ ፥ ሆስፒታሉ ውስጥ ተዘግቶ የሚውልበት ምክንያት እንደሌለው ፥ ወጣ ብሎ ጎብ ረተሰቡን መጠየቅ እንደሚገባውና ግዴታም እንዳል ፀት እየገለጽኩለት ነበር ። ትክክለኛ ነኝ ፥ አይደለሁም ፥ ፍቅሬ?"

"እዚህ ተቀመጥ" አለቹ ቬራ ዩሲፎቭና ጐኗ ያለውን ባዶ ወንበር እያመለከተች ። "እንመጣጠናለን ፤ ባለቤቴ ግን እንደ አቴሎ ቀናተኛ ነው ። ሆኖም እንግ ባባለን ፥ አይመስልህም ?"

"ትንሿ ጠንቋይ!" በማለት እያጉረመረመ ኢቫን ፔትሮቪች አለስልሶ ሽፋሽፍቷ ላይ ስሚት ወደ እን ግዳው ዞሮ ፥ " ለጉብኝትህ ጥሩ ጊዜ መርጠሃል ። ባለቤቴ

አንድ ትልቅ ድርሰት አጠናቃለች ። ዛሬ ማታ ድምጿን ዘልግ አድርጋ ታነብልናለች ”አለው ።

“ውድ ጂያን ፣ ሻይ እንዲቀርብ ይታዘዝልን” አለችው ቬራ ባለቤቷን በፈረንሳይኛ ።

እስታርትሴቭ ቀጥሎ የተዋወቀው እንደ እናቷ ቀጭን ፣ አስደሳች ፊት ካላት የ18 ዓመቷ ኮፈዳ ፣ ክዩካ ቴሪና ኢሻፍቭና ጋር ሲሆን ፣ ገጽታዋ የሕፃን ፣ ቅርጿም ለግላጋ ነበር ። የአፍላ ልጃገረድ እንጦንጌዋ ወደ ሙሉ ጡትነት እያደገ ሲሆን ፣ ውበቱና መፈጠሙ አፍላውን የጸደይ ወራት የሚያሳስብ ነው ። ከትውውቁ በኋላ ሻይ ለመጠጣት ወረፍ አሉ ። ከሻዩ ጋር ማርማላት ፣ ማርኖ ሌሎች ልዩ ልዩ ጣፋጭ ብስኩቶችም ቀርበው ነበር ። ቀኑ ደንግዝግዝ ሰ,ል ሌሎች እንግዶች ቀስ በቀስ መምጣት ጀመሩ ። ኢቫን ፔትሮቪችም ደስታን በሚያንጸባርቁና በሚፍለቀለቁ ዐይኖች እንግዶቹን “እንደምን አላችሁ?” እያለ ተቀበላቸው ።

እንግዶቹ በሙሉ መጥተው መልበሻ ክፍል ውስጥ እንደ ተቀመጡ ቬራ ዩሲፎቭና ድርሰቷን ማንበብ ጀመረች ። ማንበቧን “በጣም ቀዝቃዛ .....ነበር” በሚለው ሐረግ ከፈተች ። መስኩዎች በሙሉ ስለ ተከፈቱ ፣ ከማዕድ ቤቱ ውስጥ ከቢላዎች መፋጨት የሚወጣው ድምፅና የሽንኩርት ቁሌት ሽታ በቀጥታ ወደ መልበሻው ክፍል ይገባል ። የመልበሻ ክፍሉን ከፊል ጨለማ የሚያደርገው ደብዛዛ ብርሃን እየበራ ለስላሳ በሆኑት መንበሮች ላይ መቀመጥ በጣም ያዝናናል ። በዚህ ከረምት ወራት ምሽት ከዋናው መንገድ የሚመጣውን ድምፅና ሣቅ እያዳመጡ ፣ ክአትክልቱ ቦታ ወደ መልበሻው ክፍል

የሚገባውን ጣፋጭ የአበቦች መዓዛ እያሸተቱ ፥ "በጣም ቀዝቃዛ ነበር" የሚለውን ሐረግ ማዳመጡ በጣም የሚክብድ ነበር ። ቬራ ዩሴፎቭና ንባቢን በመቀጠል ወጣቷና ቆንጆዋ እመቤት ለትውልድ መንደሯ ትምህርት ቤት ፥ ሆስፒታልና ቤተ-መጻሕፍት እንዳቋቋመችና በአንድ ዘዋሪ አርቲስት ፍቅር እንደ ተያዘች፥ እንዲሁም በሕይወት ውስጥ ያጋጥማል ተብለው የማይገመቱ ነገሮችን አነበበች ። ሆኖም ታሪኩን ማዳመጡ የሚያስደስትና የሚያዝናና ስለነበር ፥ ማንም ሰው ክመ ቀመጫው አልተንቃነቀም ።

"አይከፋም!" አለ ኢቫን ፔትሮቪች ለስለስ ባለ ድምፅ ። ክእንግዶቹም አንዱ ፥ በሐሳቡ ርቆና መጥቆ በመሔድ ዐልፎ ዐልፎ ሲያዳምጥ የነበረ ፥ በጣም በማይ ሰማ ድምፅ ፥ "በእርግጥ አይከፋም ሰዎች ..." አለ ።

አንድ ሰዓት ፀለፈ ። ሌላም ተተካ ። ክክተማይቱ መናፈሻ ቦታ ኤንድ ኦርኬስትራ የሙዚቃ ድምፅ ያሰ ማል ። ዘማሪዎች ያዜማሉ ። ቬራ ዩሴፎቭና ማስታ ወሻ ደብተሯን ስትዘጋ ሁሉም "ሉቺኑሽካ" የተባለ ውን ዘማሪዎቹ የሚዘምሩትን መዝሙር ያዳምጡ ስለ ነበር ፥ ለአምስት ደቂቃ ያህል ማንም አልተናገረም ። መዝሙሩ በተነበበው ድርሰት ውስጥ ቦታ ያልተገለጸ ውን ግን ፥ በእርግጠኛው ሕይወት ውስጥ ያለውን ሐቅ አሳያቸው ።

"ጽሑፎችሽን በመጽሔቶች ታሳትማያለሽ?" ፈለ እስታርትሴቭ ቬራ ዩሴፎቭናን ይጠይቃታል ።

"የለም ፥ አላሳትማቸውም ። እጽፍና በቁም ሳጥን ውስጥ አስቀምጣቸዋለሁ ። ለምን ኤሳትማቸዋልሁ? ለመ

ኖር የሚያስችል በቂ ገቢ አለን" ስትል ቬራ መለሰች ።

በሆነ ምክንያት ሁሉም በረጂሙ ተነፈሱ ።

"በይ አሁን ደግሞ አንቺ አንድ ነገር ዝፈኚልን ውርዴ" አለ ልጁን ፥ ኢቫን ፔትሮቪች ።

የትልቁ ፒያኖ ገጣሚ ተነሣ ። የሙዚቃ ኖቶች ቦታቸውን እንዳይሠ ተደረገ ። መሣሪያው ተከፍቶ ዝግጁ ሆነ ። የካቴሪና ኢቫኖቭና ተቀምጣ በሁለቱም እጆቿ የሙዚቃውን ቁልፎች ተጫነች ። ክዚያም በመደጋገም በምቷ የፒያኖው ቁልፎች ሁሉ ወደ ውስጥ ጠልቀው እንዲቀሩ ለማድረግ የምትጥር ይመስል ባለ ኃይሏ ቁልፎቹን ደበደበች ። በምቱ ኃይል ትክሻዎቿና ጡቶቿ ተንቀጠቀጡ ። እንግዶቹ የተቀመጡበት ክፍል በጩኸት ተረበሸ ፤ ሁሉም ነገር፡-ወለሉ ፥ ግሪያው ፥ ዕቃው ሁሉ ጮኸ ። ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ውስብስብና ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነ የሙዚቃ ኖታ ተጨወተች ሙዚቃው ረዥምና አሰልቺም ነበር ። እስታርትሴቭ እያዳመጠ ሳለ ፥ ለራሱ ከከፍተኛ ተራራ የሚወረወሩ ቋጥኞች እየተከታተሉ ሲወርዱ በሐሳቡ ስሎ ይመለከት ነበር ። እስታርትሴቭ ዩካቴሪና ኢቫኖቭናን ውብና ቆንጆ ሆና ቢያገኛትም ፥ ሙዚቃውና በሐሳቡ የሳለው ከተራራ አናት ላይ የሚወረወረው የቋጥኝ ናዳ እንዲቆም ፈቃዱ ነበር ። እስታርትሴቭ አንድ ከረምት በዲያሊኽ በገበሬዎችና በሕሙማን መኻል በማሳለፉ ይህን ምሽት በሰፊ ክፍል ውስጥ ተቀምጦ ይህቺን ውብ ወጣት እየተመለከተ ክፒያኖው የሚወጣውን ረጅምና አሰልቺ ሙዚቃ ፥ ሆኖም የሥልጣኔ ድምፅ ማዳመጥ የሚያስደስት ሆኖለት ነበር ።

“ደኅና ፣ ውርዬ በዛሬው ሙከራሽ በጣም ተሻሽለሻል” አላት ኢቫን ፔትሮቪችች ፅንፁ ባዘሉ ፀይሮቹ ሙዚቃውን አብቅታ ከመቀመጫዋ በመነሣት ላይ የነበረችውን ልጁን እየተመለከተ ። “ረቃ ብለሽ ብትለ ማመኟ አልብሽበት ትደርሻለሽ” አላት ደግሞ ።

እንግዶቹ ‘እንኳን ደስ ያለሽ’ በማለት በማድነቅ እንደጨሀ ያለ ሙዚቃ ለረዥም ጊዜ ሰምተው የማያውቁ መሆኑን በመሐላ እየገለጡ ክፀፃ ክበብ አደረጓት ። ዩካቴሪና ኢቫኖቭና የሚወርድላትን አድናቆት በጸጥታ ለማዳመጥና መጠነኛ ፈገግታ በማሳየት አሸናፊነቷን በፍንደቃ ገለጸች ።

“ቆንጆ ነው! ድንቅ ነው!”

እስታርትሴቭ ሙዚቃው ያልጣመው ቢሆንም ፣ ከአድናቂዎቹ እንግዶች ላለመለየት “ቆንጆ ነው!” ሲል ጮኸ ቱናገረ ።

“የት ነው ያጠናሽው ? በሙዚቃ ትምህርት ቤት ነው ? ዩካቴሪና ኢቫኖቭና” ሲል እስትፉትሴቭ ይጠይቃታል ።

“አይደለም ፤ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ለመማር እየተዘጋጀሁ ነው ። እስከዚያው እዚህ ክማዳም ጣሽሎቭስካያ ዘንድ እየተለማመድኩ ነው” ስትል ትመልስለታለች ።

“እዚህ ካለው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቱመርቀሻል?”

“አይ ፣ አትማርም” በማለት እናትዮዋ ቬራ ዩሴፎቭና ትመልስለታለች ። “እንደምታውቀው በከ ፍተኛው ትምህርት ቤትና በአዳሪ ትምህርት ቤቶች መጥፎ ዝንባሌዎች ስለሚኖሩ ፣ ይህ እንዳያጋጥም በቤት ውስጥ እንድትማር መምህር ተቀጥሮላታል። ታዳጊ ሴት ልጅ ምንም ጊዜ ቢሆን በእናቷ ሥር የሷን ዝንባሌ ይዛ ማደግ ይኖርባታል” አለች ።

“ግን ፣ ወደ ሙዚቃው ትምህርት ቤት ለመግባት አስቤያለሁ” አለች ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ።

“አይ ፣ የለም አይሆንም ፤ ውርዬ እናቷን ትወዳለች። ውርዬ እናትና አባቷን አታሳዝንም ።”

“እሔዳለሁ ፤ አልቀርም!” አለች ዩካቴሪና ኢቫ ኖቭና በመሞላቀቅ ዐይነት ወለሉን በእግሯ እየመታች።

በራት ጊዜ ችሎታን የማሳየቱ ተራ የኢቫን ፔት ሮቪች ነበር ። በዐይኑ ብቻ ፈገግታን እያሳየ አስደናቂና የሚያስደስቱ ታሪኮችን መናገር ፣ ቀልዶችን ማሰማት እሱ ራሱ ብቻ የሚፈታቸውን አንዳንድ ፕሮብሌሞ ችን ማቅረብ ጀመረ ። ይህ ሁሉ ሲሆን የሚናገረው እሱ ራሱ ብቻ በሚረዳው የወፍ ቋንቋ በሚመስል ግልጽ ባልሆነ ቋንቋ ነበር ። ይህን ቋንቋ ለፈጥር የቻለው በረዥም ጊዜ መለማመድ እንደሆነ ይታወቅበታል ።

ይህ ብቻ አልነበረም ። እንግዶቹ በዝግጅቱ ተደስ ተውና ረክተው ከዘራዎቻቸውንና ካፖርቶቻቸውን ለማ ንሣት ወደ አዳራሹ ሲገቡ የ14 ዓመት ጉብል የሆነው እነሱ ፓሻ ብለው የሚጠሩት ፓቬል በእንግዶቹ አካ ባቢ ይርበተበት ነበር ።

“ፓሻ ፣ ትርዕይትህን አሳይ ፣ አሳይ !” ሲል ኢቫን ፔት ሮቪች ጮኸበት ። ፓሻ መጋኛ የመታው ይመስል ተግ ተርትሮ ራሱን አንድ ፀይነት ሁኔታ ውስጥ ፀመክተት አንድ እጁን ወደላይ ብድግ አደረገና ፀሚያሳዝን ድም ፉና ቋንቋ መናገር ጀመረ ።

“ድራሽሽ ይጥፉ ፤ ጥፊ ፤ እርጉም !” አለ ።

ሁሉም ጣቱ ።

“የሚደንቅ ነው” አለ እስታርትሴቭ ከቤት ውስጥ እየወጣ ። እንደ ወጣ ወደ አንድ ሬስቱራንት ሔዶ ቢራ ጠጣና ወደ መኖሪያው ድያሊዥ ተመለሰ ። ወደ ቤቱ ሲገዝ ፣

“በለሰለሰው ድምፅሽ የሚሟሙት ቃላት...” የሚለውን ዘፈን ያንጐራጉር ነበር ።

ወደ ቤቱ ለመመለስ የተገዘው ስድስት ማይል ርቀት ምንም አላደከመውም ። በቀጥታ ወደ አልጋው ውስጥ ሲገባ ሌላ ስድስት ማይል ለመገዝ ይችል እን ደነበር ለራሱ በደስታ ይናገር ነበር ።

“አይከፋም!” የሚለውን የኢቫን ፔትሮቪችን አነጋገር አስታውሶ ፣ እየሣቀ አንቀላፋ ።

እስታርትሴቭ የቱርኪንን ቤተሰብ እንደገና ለመ ጐብኘት ቢፈልግም ፣ በሆስፒታሉ ውስጥ ብዙ ሥራዎች ስለነበሩ ትርፍ ጊዜ ለማግኘት አልቻለም ። ከአንድ ዓመት ፀላይ በሥራ ተወጥሮ በብቸኝነት እንዳሳለፈ አንድ ቀን በሰማያዊ ፖስታ የታሸገ ደብዳቤ ከከተማ ደረሰው ።

ቬራ ዮሲፎቭና ለረጅም ጊዜ ፀራስምታት ሕመም ትሠቃይ ነበር ። በቅርቡ ደግሞ “ውርጴ” ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ፣ ወደ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ክልገባሁ

እያለች ፀማስቸገሯ የእናቷ ሕመም እየተባባሰ ሔደ ። በከተማው ካሉት ዶክተሮች የቱርኪንን ቤተሰብ ያልጐበኘ የለም ። በመጨረሻም የክልሉ ሐኪም ተራ ደረሰ ። ቬራ ዮሴፎቭና መጥቶ ከሥቃይዋ እንዲገላግ ላት ልብ የሚነካ ደብዳቤ ጻፈችለት ። እስታርትሴቭ ሔዶ ጠየቃት ። ከዚህ በኋላ የእስታርትሴቭ የቱርኪንን ቤተሰብ መጠየቅ ፣ እየተደጋገመ ሔደ ።

ቬራ ቶሲፎቭናን በመጠኑም ቢሆን ረድቷል ። ሁሉም ገመብኚዎቹ የተደነቀና ልዩ ዶክተር መሆኑ ተነግሯቸው ነበር በኋላ ግን ወደ ቱርኪንስ ይሂድ የነበረው ለራስ ምታት ህመሟ አልነበረም ።

የበዓል ቀን ነበር ። ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ረጅምና አድካሚ የሆነውን የፒያኖ ልምምዷን እንዳበቃች ሁሉም በምግብ ቤቱ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው ሻይ ይጠጡ ነበር ። ኢቫን ፔትሮቪች ከአሥቂኝ ታሪኩቹ አን ዱን በመተረክ ላይ እንዳለ በር በመንኳኳቱ እንግዳውን ለመቀበል ትረካውን አቋርጦ ይወጣል ። ይሀን አጋጣሚ በመጠቀም እስታርትሴቭ ወደ ዩካቴሪና ኢቫኖቭና በመጠጋት በስሜት በጆሮዋ ያንሾካሹክላታል ፤

“ስለ እግዚአብሔር ብለሽ ፤ አታሠቃይኝ ፣ ተለመ ኚኝ ። ወደ አትክልቱ ቦታ ወጣ እንበል ። ”

የሚናገረውና የሚፈልገው እንዳልገባት ዐይነት በመሆን ቅከሻዎቿን ሰብሰብ በማድረግ በመደነቅ መልክ ተነሥታ ወጣች ።

“ለሦስት ወይም ለአራት ሰዓት ትለማመጃለሽ” አላቅ ተክትሏት እየወጣ ። “ከዚያም ክእናትሽ ጋር ልለ ምትቀመጪ ላናግርሽ የምችልበት ጊዜ የለም ። እንድ ፋብ ሰዓት እንዳናግርሽ ተለመኚኝ ! ”

የመጸው ወራት እየተቃረበ ነው ። የአትክልት ቦታው የአግር መንገዶች የረገፉና የጠወለጉ ቅጠሎች አልብ ለዋችዋል ። ዛፎቹ ቅጠሎቻቸው በመርገፋቸው ውበታቸውን ተገፈው በአሳዛኝ ሁኔታ ቆመዋል ። ቀኑም እየተገባደደ ነበር ።

"ሳምንቱን ሙሉ አላየሁሽም" በማለት እስታፎ ትሴቭ ንግግሩን ይቀጥላል ። "እንዴት ያለ ጭንቀት ውስጥ እንዳለሁ ብታውቂልኝ ! እዚህ እንቀመጥና ላጫውትሽ ።"

በአትክልቱ ውስጥ ከንፎቹ በስፋት በተዘረጉት ትልቁ ዛፍ ጥላ ሥር ሁለቱም የሚወዱት መቀመጫ ቦታ አላቸው ። ወደ አግዳሚው ሔደው ተቀመጡ ።

"ምንድን ነው የምትፈልገው" በማለት ቅስተር ባለ እንጋገር ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ጠየቀችው ።

"ለአንድ ሳምንት በሙሉ አላየሁሽም ። ደምፅሽን ከሰማሁ ዘመናት ያለፉ መስሎ ታየኝ ! ናፍቄሻለሁ ። ደምፅሽ ጠምቶኛል ! አጫውችኝ!"

እስታርትሴቭ ፥ በንጽሕናዋ ፥ በዐይኖቿ የዋህና ሮጎ ሩጎ አገላለጥ ፥ በጉንጮቿ መሙላት ተማርኳል ። በአለ ባበሷ እንኳን ልዩ ደስታ ይሰማዋል ። የዋህ ብትሆንም ከዕድሜዋ በላይ የምታስብ ብልህና ዐዋቂ እንደ ሆነች ያስባታል ። ስለ ሥነ ጽሑፍ ፥ ኪነ ጥበብና ሴላ ማንኛውም ጉዳይ ያጫውታታል ። ስለ ሕይወትና ስለ ሰዎች ወይም የፈለገውን አርዕስት በማንሣት ሲያማርርላት በሞውሙቱ መኻል ድንገት ተነሥታ ከትክትክ ብላ በሚ ያስደነግጥ ሁኔታ ትሥቃለች ። ወይም ተነሥታ ወደ ቤት

"ዛሬ ማታ በአምስት ሰዓት በመቃብሩ ቦታ በደሜቲ መቃብር አጠገብ እንገናኝ" የሚለውን መልዕክት እስታርትሴቭ ከማስታወሻው ላይ አነበበ።

እስታርትሴቭ፣ ማስታወሻው ከፈጠረበት መደነቅ ሲነቃ፣ "ይህ በርግጥ የዋህነት ነው። ለምን የመቃብሩን ቦታ መረጠች? ምክንያቱስ" በማለት አሰበ።

ምክንያቱ በጣም ግልጽ ነበር። ውርዬ ልትቀልድበት ነበር የምትፈልገው። ማንም ጤነኛ የሆነ ሰው ቀጠሮውን መንገዶች ላይ ወይም በማዘጋጃ ቤቱ መናፈሻ ቦታ ሊያደርግ ሲችል በውድቅት ሌሊት በመቃብር ቦታ ሰውን አይቀጥርም። ታዲያ ለአንድ የክልል ጤና መኰንን፣ ለተከበረና ለታወቀ ዐዋቂ ሰው ቀጠሮው ይመቸዋል? ከአንድ ኮረዳ ማስታወሻ ተቀብሎ አለጊዜ በመቃብር ቦታ መንቀዋለል፣ አንድ የዘመኑን ወጣት ተማሪ የሚያሥቁ አልባሌ ድርጊቶችን መፈጸም፣ ይህ አድራጎት ወደ ምን ያመራል? ይህን ጉድ የሥራ ጓደኞቹ ቢደርሱበት ምን ይላሉ? እስታርትሴቭ እነዚህን ሐሳቦች በአዕምሮው እያውጠነጠነ ነበር በክበቡ አዳራሽ ውስጥ በወንበሮች መኻል ከወዲያ ወዲህ የሚመላለሰው። ከሐሳቡ ሲመለስ አራት ሰዓት ተኩል ሆኖ ስለነበር በቀጥታ ወደ መቃብሩ ቦታ ተፈተለከ።

እስታርትሴቭ አሁን የራሱ ሠረገላ አለው። ባለ ዘርፍ ሰደርያ ለባሹ፣ ፓንቴሌሞን፣ የሠረገላ ነጂው ሆኗል። ጨረቃ ሙሉ ብርሃኗን ሰጥታለች። ሌሊቱ ጸጥ ያለና አየሩም የመጸው ወራትን ሙቀት ያዘለ ነው።

በከተማው ዳርቻ በሚገኘው የክተማው ቄራ ውሾች ይጮኻሉ። እስታርትሴቭ ወከተማው መዳረሻ

ላይ ከሠረገላው በመውረድ በእግሩ ወደ መቃብሩ ቦታ አዘገመ ። "እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ልዩ ባሕርይ አለው" አለ ለራሱ ። "ውርዬ አስደናቂ ልጅ ናት ። ግን ያውቃል- እውነቷን ሊሆን ይችላል ። በቀጠሮዋ ትገኝ ይሆናል ። " በዚህ ራሱ በፈጠረው ከንቱ ውዳ ሴ ደካማ ተስፋ ሰክሮ ፈነጠዘ ።

መንገዱ በአንድ መስክ ላይ የሚያቋርጥ ነበር ። የመቃብሩ ቦታ ከሩቅ ሲታይ የጠቆረ ቁራጭ መሬት፣ ዙሪያውን የዛፍ ቀለበት ያለበት ወይም ትልቅ መና ፈሻ ይመስላል ። እየቀረበ ሲሔድ ነጭ የድንጋይ ዓዐድ ታየ ። ቀስ በቀስ ደግሞ ዋናው በር ብቅ አለ ። በጨረቃ ብርሃን በመቃብሩ ቦታ መግቢያ በር ላይ ተለጥፎ የሚ ነበበው ጽሑፍ ፣ "ያንተም ሰዓት ይደርሳል" ይላል ። አስታርትሴቭ በሩን ገፍቶ ወደ ውስጥ ሲገባ ግራና ቀኙ ነጫጭ መስቀሎች የተተከሉበት መንገድ ያገ ኛል ። የሙታን ሐውልቶችና የረጃጅም ዛፎች ጥቁር ጥላ በመንገዱ ላይ አጥልቷል ። የማይነቃነቁት ዛፎች ቅፋፊ ቅርንጫፎቻቸውን በነጫጩ የመቃብር ድን ጋይ ላይ በመጣላቸው ፣ በመቃብሩ ቦታ ሁሉም ነገር ነጭ ወይም ጥቁር ሆኗል ። ከመስኩ የመቃብሩ ቦታ የበለጠ ብርሃን ያለበት ይመስላል ። ከዛፎቹ የወደቁት የወየቡ ቅጠሎች በአሸዋማው መሬት ላይ ጐልተው ይታያሉ ። በመቃብሮቹ ላይ የተጻፉት ጽሑፎችም በደ ንብ ይታያሉ ። አስታርትሴቭ በመቃብሩ ቦታ እያጠና እያለ አንድ ሐሳብ መጣበት ። በሕይወቱ ምናልባት ደግሞ ሊያየው የማይችለውን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ እያየ መሆኑን ይህ ቦታ የጨረቃ መፈጠሪያ ቦታ ይመስል የጨረቃ ብርሃን

ለስላሳና ጣፋጭ የሆነበት ፥ ምንም የሚንቀሳቀስ ሕይወት የሌለበት ፥ ሆኖም በእያንዳንዱ ጨለማ ጐጥ ፥ በእያን ዳንዱ መቃብር ዘለዓለማዊ ሕይወት ለመገራት ወይም እስትንፋስ ለማግኘት በጸጥታ የሚጠባበቅ ምስጢር እንዳለና ከመቃብር ድንጋዮች ፥ በመክሰም ላይ ከሚገ ኙት አበቦች ፥ በመጸው ወራት ከጠወለጉ ቅጠሎች የሚነሣ ሽታ ፥ ኀዘንና ሰላም በአንድነት በአየሩ ውስጥ የሚተሙ መስለው ታዩት ።

በአካባቢው ሁሉም ነገር ጸጥ ብሏል ። የሰማይ ከዋክብት በትልቅ ቅሬታ ይመስል ወደ ታች ትክ ብለው ይመለከታሉ ። የእስታርትሴቭ ጫማ የሚፈ ጥረው ያልተቃኘ ሙዚቃ የሚመስለው ድምፅ ብቻ ይሰማል ። የቤተክርስቲያኑ ሰዓት ሲደውል እስታርት ሴቭ ለዘለዓለሙ ሞቱ እንደ ተቀበረና ሌላ ሰው መቃ ብሩን እየገመገው እንደሆነ በሐሳቡ ያሰላስል ነበር ። ለጥቂት ጊዜም ይህ የአሁኑ ሁኔታ ሰላምና ጸጥታ እንዳ ልሆነ ፥ ያለመኖርና የታመቀ ተስፋ መቁረጥ ትልቅ ኀዘን እንደሆነ አሰበ ።

የደሜቲ መቃብር ቤት በጸሎት ቤት ቅርፅ ሆኖ አናቱ ላይ የመልአክ ሐውልት ተተክሏል ። ከብዙ ጊዜ በፊት አንድ የኢጣልያን ሙዚቃ ቡድን ወደ "ሠ" ከተማ መጥቶ በነበረ ጊዜ ከዘማሪዎቹ አንዷ በመሞቷ በዚህ ቦታ ስለ ተቀበረች ፥ መታሰቢያውም የቆመው ለዚያች የጣሊያን አዝማሪ ነበር ። አሁን ከኳ ተማው ሕዝብ ማንም የሚያስታውሳት የለም ። ይሁን እንጂ ወደ መቃብር ቤቷ መግቢያ በር ላይ የተንጠ

ለጠለው መብራት ፥ የጨረቃዋን ብርሃን ስለሚያንጸ ባርቅ ሁል ጊዜ የሚበራ መስሎ ይታያል ።

በአካባቢው ማንም የለም ። ቢሆንስ በደረቅ ውድ ቅት ወደዚህ ቦታ ማን ይመጣል ? እስታርትሴቭ ግን ትመጣለች ብሎ ጠበቀ ። የጨረቃዋ ብርሃን ፍቅር የለኮሰችበት ይመስል በሐሳቡ መሳምን ፥ መታቀፍን ፥ መዳሰስን እያወጣ እያወረደ በፍላጎትና በጉጉት ጠበቀ ። በመቃብሩ አጠገብ ለግማሽ ሰዓት ተቀምጦ ከጠበቀ በኋላ ፥ ተነሥቶ ባርሜጣውን በእጁ ይዞ በአንድ ቀጭን መተላለፊያ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሰ ሲጠብቅ ፥ በዚህ በመቃብር ቦታ በሰላም ያንቀላፉ ወጣት ሴቶችና ሚስቶች ምን ያህል ቆንጆና ተደናቂ እንደ ነበሩ ፥ ወደ ውና ተወደው እንደ ነበር ፥ በፍቅረኛቸው የለሰለሰ ዳሰሳ በየምሽቱ በፍቅር የነደዱ ስንቶች ይሆኑ ? እያለ በሐ ሳቡ ተገረመ ፤ ተደነቀ ። እናት ተፈጥሮ ምንኛ በሰው ልጅች ላይ ትቀልዳለች? ይህንንስ ይሁን ብሎ መቀ በል ምንኛ አለማሰብ ነው ! እስታርትሴቭ ይህን ሁሉ አውጥቶ ሲያወርድ በምንም ዐይነት ፍቅርን ማግኘት እንዳለበት ጮኾ ለመናገር አስመኘው ። ከእንግዲህ በመ ቃብር ላይ የተተከሉ ኑጫጮ የእብነበረድ ጥርብ ድንጋ ዮችን ሳይሆን እውን የሆነውን በዛፎች ጥግ በኃፍ ረት የሚደበቀውን ፥ ሙቀቱ የሚሰማውን የሰው ፥ የሴት አካል ማሰብ ጀመረ ። በመጨረሻም የፍቅሩ ስሜት ከሚቻለው በላይ ገነፈለበት ።

በድንጉት መጋረጃ የተዘጋ ይመስል ፥ ጨረቃዋ ከአ ንድ ክምር ደመና ጀርባ በመግባቷ አካባቢው በሙሉ በጨለማ ተዋጠ ። የሌሊቱ ጨለማ ጥቅጥቅ ያለው የመ

ጸው ወራት ጨለማ ስለነበር ፥ እስታርትሴቭ ወደ መቃ
ብሩ መግቢያ ዋና በር የሚያወጣውን መንገድ ለማ
ግኘት አልቻለም ። ከአንድ ሰዓት ተኩል መንከራተት
በኋላ ሠረገላውን እተወበት መንገድ ላይ ደረሰ ።

"በጣም ስለ ደከመኝ መቆም እንኳን ተስኖኛል"
ሲል ለሠረገላ ነጂው ፥ ለፓንቴሌሞን ይነግረዋል ።

ተዝናንቶ መቀመጫው ውስጥ እየተደላደለ ፥
"እንደዚህ መወፈር የለብኝም "ሲል ለራሱ ተናገረ ።

በሚቀጥለው ቀን ወደ ማታ ሐሳቡን በግልጽ
ለማቅረብ ወደ ቱርኪን ቤተሰብ ሔደ ። ነገር ግን ፥ በክ
ልሉ በሚደረገው የዳንስ ምሽት ላይ ስለምትጫኝ
የዩካቴሪና ኢባኖቭና ጸጉር ሠሪ በመኝታ ቤቱ ውስጥ
ጸጉሯን ትሠራላት ስለነበር ፥ ሐሳቡን ለማቅረብ አመቺ
ጊዜ አልሆነለትም ። በምግብ ቤቱ አዳራሽ ሻይ እየተ
ጠጣ ሌላ ረጅም ጊዜ ዐለፈ ። እንግዳው በሐሳብ የተ
ዋጠና የደበተው መሆኑን የተረዳው ኢቫን ፔትሮ
ቪች ከሰደርያ ኪሱ ወረቀቶች አውጥቶ ከአንድ ጀርመ
ናዊት በተሰባበረና በሚያሥቅ ሩሲያኛ የተጻፈ ደብዳቤ
ድምፁን ከፍ አድርጎ ማንበብ ጀመረ ።

እስታርትሴቭ ኢቫን ፔትሮቪች የሚያነበውን ደብ
ዳቤ በከፊል እያዳመጠ ፥ "ጥሩ ጥሎሽም ይሰጧት ይሆ
ናል" እያለ በሐሳቡ ያወጣ ያወርድ ነበር ።

ያለፈውን ሌሊት ባለመተኛቱ እንቅልፍ የሚያ
ስወስድ መድኃኒት የወሰደ ይመስል ግራ በሚያጋባ
መልክ ፈዞ ይታያል ። የሚያስደስት ፥ ልብ የሚያሞቅ

ሕልም ቢያልምም ሕሊናውን የሚቆነጥጥ ከባድና ቀዝ
ቃዛ ስሜት ያንከዋል ።

"ይህ ጉዳይ ሳይዘገይ በአጭሩ ብታቆመው ይበ
ጃል ። እኩያህ ናት? እስከ ቀኑ ስምንት ሰዓት የምትተኛ
ሞልቃቃ ናት ፤ ፍላጐቷና ምኞቷም ትልቅ ነው ። አንተ
ደግሞ የክልሉ ዶክተር ብትሆንም ፥ የቤተ ክርስቲያን
ደወል ደዋይ ልጅ መሆንህን .... "

"ቢሆንስ ታዲያ" ሲል ይመልሳል ለራሱ ፤

"ከዚህም በላይ" አለ በሐሳቡ ። "ከዚህም በላይ ብታ
ገባት ዘመዶቿ በክልሉ ያለህን ሥራ ትተህ ወደ ከተማ
መጥተህ እንድትኖር ያደርጉሃል ። "

"ታዲያስ" ሲል ራሱን ይጠይቃል ። "ለምን በከ
ተማ አልኖርም ? ለሠርጓ ጥሎሽ ስለሚሰጧት ቤት ሠር
ተን እንኖራለን ..." አለ ።

በመጨረሻም ዩካቴሪና ኢቫኖቭና የዳንስ ልብ
ሷን ለብሳ አምራና ደምቃ ብቅ አለች ። እስታርትሴቭ
ዐይኑ እስኪጠግብ ድረስ ከተመለከታትና ካጠናት በኋላ
ምንም ቃል ሳይተነፍስ መሣቅ ጀመረ ።

ወደ ዳንሱ ቦታ ለመሔድ ሰላምታ መስጠት ስለ
ተጀመረ ፥ እሱም-እሷ ከሔደች የሚቆይበት ምክንያት
ስላልነበረ-ሰዓት ስለ ደረሰና ሕመምተኞችም ስለሚ
ጠብቁት ወደ ቤቱ ለመሔድ ተነሣ ።

"ደግ አይደለም" አለ ኢቫን ፔትሮቪች ። "እን
ግዲህ ከተነሣህ ሒዳ ! እግረ መንገድህንም ውርዬን ታደ
ርሳታለህ!"

ውጭው ጨልሞ በረዶም መጣል ጀምሯል ። ሥረገላው የነበረበትን አቅጣጫ ለማግኘት የቻሉት የሥረገላ ነጂው ፥ የፓንቴሌሞን ከባድ ሳል የሚመጣበትን አቅጣጫ በመከተል ነበር ። የሥረገላው ኦሞበር ተነሣ ።

ኢቫን ፔትሮቪች ፥ የማያቋርጥ ቀልዱን እየቀለደ ልጁን ወደ ሥረገላው አስገብቷት "ደኅና ግቡ" ብሎ ተሰናበታቸው ።

ሥረገላው ተንቀሳቀሰ ።

"ትላንትና ወደ ቀጠሮሽኝ ወደ መቃብሩ ቦታ ፈጺ ነበር" አለ እስታርትሴቭ ። "ምን ያህል ጨካኝ ነሽ ..."

"መቃብሩ ቦታ ሔደህ ነበር?"

"አዎን ፤ ሔጄ ለሁለት ሰዓት ያህል ጠበኩሽ ተሠቃየሁ ..."

"ይገባሃል-ቀልድም አታውቅ?"

ዩካቴሪና ኢቫኖቭና የሚያደንቃትን ሰው በጥሩ ሁኔታ በማታለሏና በከፍተኛ ደረጃ በመወደዷ ጮክ ብላ ሣቀች ። በሚያስፈራ ሁኔታ ሣቋ ስለ ቀጠለ ፥ ሠረገላውን የሚጐትቱት ፈረሶች ደነበሩ ። እስታርትሴቭ እጁን በሽንጧ ላይ አሳረፈ ። እሷም ስለ ፈራች ወደ እርሱ ተጠጋች ። አጋጣሚው እንዲያመልጠው ስላልፈለገ ፥ ወደሱ የበለጠ በማስጠጋት ጥብቅ አድርጎ አቅፎ በጋለ ፍቅር ከንፈሮቿንና አገጯን ሳማቸው ።

"ይበቃል" አለች ቀዝቀዝ ብላ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከሠረገላው ወጥታ ሔደች ። ቦግ ያለ ብርሃን ከሚበራበት የክበቡ መግቢያ በር ላይ ቆሞ የነበረው ፖሊስ በፓንቴሌሞን ላይ በቁጣ ጮኸ በት ።

"ምን ትጠብቃለህ አንተ ደደብ? ተንቀሳቀስ !" አለው ። እስታርትሴቭ ወደ ቤቱ ሔዶ ወዲያውኑ ተመ ልሶ መጣ ። ተመልሶ ሲመጣ የለበሰው የራሱ ያልሆነ የተንዘረፈፈ የሌላ ሰው ኮትና የተጨረማመተ ነጭ ከረባት አስሮ ነበር ። እኩለ ሌሊት ላይ በክበቡ መል በሻ ከፍል ተቀምጠ በደስታ መንፈስ ዩካቴሪና ኢቫኖ ቭናን ያጫውታል ።

"ያላፈቀሩ ሰዎች ስለ ፍቅር ምንም አያውቁም ! ለኔ እንደሚመስለኝ ማንም ሰው ፍቅርን በትክክልና በታማኝነት የገለጸ የለም ። በእርግጥ ይህንን ለስላሳ ፣ አስደሳችና የሚያቃጥል ስሜት በትክክል ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው ። ፍቅርን የቀመሰ ወይም ለአንድ ጊዜ እንኳን የደረሰበት በቃላት ሊገልጸው ያዳግተዋል ። እዚህ ሁሉ ዝግጅትና ገለጻ ውስጥ ምን ያስገባል? ይህ ሁሉ ከንቱ ውዳሴና ንግግር ለምን ያስፈልጋል? ላንቺ ያለኝ ፍቅር ዳር ድንበር የለውም ። እባክሽ ባለ ቤቱ እንድትሆኚ ልለምንሽ ፤ ተለምኚኝ !" በማለት በውስጡ ታምቆ የነበረውን እምቅ ሐሳብ ተነፈሰ ።

"ዲሜትሪ ዩኒች" አለች ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ፊቷን በጣም አኮሳትራ ቆም በማለት ። "ዲሜትሪ ዩኒች ለሰጠኸኝ ክብር አመሰግናለሁ ። አከብርሃለሁ ፤

ግን ...” ተነሥታ ቆማ ንግግሯን በመቀጠል ፣ “ግን ይቅ ርታ አድርግልኝ ፤ ሚስትህ ልሆን አልችልም ። በእርግጥ አንተም ራስህ ታውቀዋለህ ፤ ዲሜትሪ ዩኒች ፣ በሕ ይወቴ ኪነጥበብን ከሁሉ ነገር አብልጬ እወዳለሁ ። ሙዚቃን እወዳለሁ ። እብድ እሆንለታለሁ ፤ ሕይወቴን በሙሉ ልሙዚቃ ሰጥቻለሁ ። ዝናን ፣ ታዋቂነትን ፣ ነጻ ነትን ስለምወድ ሙዚቀኛ መሆን እፈልጋለሁ ። አንተ ግን ፣ እዚሁ ከተማ ተቀምጬ ይህንን የሰለቸኝን ቀሩፈና የማይጥም ሕይወት እንድቀጥል ትፈልጋለህ ። የአንድ ሰው ሚስት እንድሆን ? የለም ። አልፈልግም ። አመሰግናለሁ! አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ አንድ ትልቅ ዓላማ ማለም ይኖርበታል ። ትዳር ደግሞ ከዚህ ሁሉ ይገታኛል ፤ “ዲሜትሪ ዩኒች ፣ ዲሜትሪ ዩኒች” የሚ ለውን ስም ስትጠራ ፣ “አሌክሲፈዎፈላኪችን” ስላስታ ወሰች ፈገግ ብላ ነበር ።

“ዲሜትሪ ዩኒች ፣ ከቱሩት ወንዶች ሁሉ የተሻ ልክ ደግ ፣ ርኅሩኅና ብልህ ሰው ነህ ”በማለት ዐይኖቿ እንባ አዘሉ ። “ምን እንደሚሰማህ በልቤ በሙሉ ይታ ወቀኛል ። ግን ...ግን ችግሬን እንደምትረዳልኝ እርግ ጠኛ ነኝ ...”

እንባ ካዘሉት ዐይኖቿ የተንቆረዘዘው እንባ እንዳ ይወርድ ወይም እንዳይታይባት ፈጠን ብላ የመልበሻ ክፍሉን ጥላ ወጣች ።

የእስታርትሴቭ ልብ እንደ በፊቱ በድንጋጤ መር በትበቱን አቆመ ። ከክበቡ ወደ መንገዱ ሲወጣ በመ ጀመሪያ ደረጃ ያደረገው የታነቀበትን ከረባት በማ

ላላት ትኩሷን አየር በሰፈው ወደ ውስጥ መማግ ነበር። የኃፍረት ስሜት በፊቱ ላይ ይነበባል። ክብሩ የተዋረደ የተናቀ--እምዪ ትለኛልች ብሎ አላሰበም፤ አልጠፈጠረም ነበር-መሰለው። ያሁል ሕልሙ፥ ተስፋውና የሕሊና ሥቃዩ እንዲህ በአንድ ጊዜ ልምድ የሌላቸው አማተር የኪ ነት ሰዎች እንደሚከይኑት አሥቂኝ ድራማ የመጨረሻ ትዕይንት በአጭሩ እንደተራ ነገር ያበቃል ብሎ አያ ምንም ነበር። በስሜቱና በፍቅሩ ላይ ስለ ደረሰው ድን ገተኛ ሁኔታ በጣም አዘነ። ለማልቀስም ቃጣው፤ ወይም ሰፈውን የፓንቴሌሞን ትክሻ በጀንጥላው ለመደብደብ ከጀል።

ለሥስት ቀናት የሚሆነውን አሳጥቶት ፡ምግብ፥ መጠጥና መኝታ አስጠልቶት ነበር። በመጨረሻም ዩካ ቴሪና ኢቫኖቭና ወደ ሞስኮ ሔዳ ሙዚቃ ትምህርት ቤት መግባቷን ሲሰማ እንጂ ስለ ቆረጠ ጸጥ ብሎ ሕይወቱን እንደ ቀድሞው መምራት ጀመረ።

ከብዙ ጊዜ በኋላ በመቃብሩ ቦታ የደረሰበትን መን ከራተት ሲያስታውስ፥ ለዳንሱ ምሽት የለበሰውን ኮት ለመግዛት በከተማው ውስጥ የደረሰበትን መውጣትና መውረድ ሲያስብ እግሮቹን በስንፍና ዐይነት በመዘ ርጋት እንዲህ አለ።

"ምን ዐይነት ቀልድ ነው?"

አራት ዓመታት ዐለፉ። እስታርትሴቭም በከተማው ብዙ የሕክምና ልምድ አደረገ። ጠዋት ጠዋት በዲያ ሊሹ የሚገኙትን ደንበኞቹን በችኮላ ሕክምና ካደረ ገላቸውና ካስተናገዳቸው በኋላ ከተማ ወዳሉት ደንበ ኞቹ ይወጣል። ዛሬ ሠረገላው እንደ በፊቱ የሚንተተው

በሁለት ፈረሶች ሳይሆን የሚንቃጨል ደወል አንገታቸው ላይ ባጠለቁ ሦስት ፈረሶች ሆኗል ። ወደ ቤቱ የሚመለሰው ከመሸ በኋላ ነው ። ውጥረትና ክብደት በጣም ስለ ጨመረ ፥ ልቡ በጣም ስለሚመታ ቸአግሩ አይሔድም ። ፓንቴሌሞንም ወፍሯል ። የመወፈሩና የሰውነቱ መስፋት እየጨመረ መሔድ ሥራውን ፥ "ሠረገላ ነጂነቱን- እያስጠላው ሔዷል ።"

እስታርትሴቭ በሥራው ምክንያት ብዙ ቤቶችን በመጐብኘቱ ብዙ ሰዎችንም ፀወቀ ። ግን ከአንድም ሰው ጋር የቀረበ ግንኙነት አልመሠረተም ። ጨዋታቸው ፥ አመለካከታቸው እንደውም የከተማ ሰው መሆናቸው ራሱ ያበሳጫል ። ቀስ በቀስ በ'ሠ' ከተማ ነዋሪ ከሆነ ሰው ጋር እራቱን መብላትና ካርታ መጫወት ለመደ ። ይህ ሰው ቀልደኛ ፥ ሰላም ፈላጊና ብልህ ሰው ሆኖ አገኘው ። ነገር ግን ፥ የሁለቱ ጨዋታ ከምግብ ዐልፎ ወደ ፖለቲካ ወይም ወደ ሳይንስ ሲቀየር ግለሰቡ የሚይዘውና የሚጨብጠው ጠፍቶት ግራ ይጋባል ። ወይም የማይጨበጥ ፍልስፍና ብጤ ስለሚጀምር ማንም ሰው ቢሆን ብቻውን ጥሎት የሚሔድ ዐይነት ሰው ነው ።

እስታርትሴቭ ፥ በጣም ለዘብተኛ ከሆነ አንድ ሰው ጋር ውይይት ከፍቶ ፥ "እግዚአብሔር ይመስገንና የሰው ልጅ በዕድገት ጐዳና እያመራ ነው ፤ በቅርቡ የሞት ቅጣትና ፓስፖርት እንኳን ይቀርልን ይሆናል" ብሎ ሐሳብ ሲሰነዝር ፥ ሐሳቡ የቀረበለት ሰው ወይም ተወያዩ ፊቱን በማጨማደድ የጐሪጥ እየተመለከተው ፥ "አዎን ፥ ሰዎች በየመንገዱ እርስ በርሳቸው እንዲ

ፋጁ ነው?”ሲል ይጠይቀዋል። እንዲሁም በራት ወይም በሻይ ሰዓት እስታርትሴቭ ሥራ የህልውና መሠረት መሆኑንና ሰው ሁሉ መሥራት እንዳለበት ሲናገር ወይም ውይይት ሲከፍት ሐሳቡን እንደ እርግማን በመውሰድ በጽኑ ይከራከሩታል። በመጨረሻም ተራው ሕዝብ ምንም አይሠራም። ምንም ነገር ስሜት አይሰጠውም። በመሆኑም ለጫወታቸውና እነሱም ሊሳተፉበት የሚችሉት ነገር ማግኘት አይቻልም በማለት ደመደመ። በመጨረሻም ከማንም ጋር ውይይትና ጨዋታ አቁሞ፣ ትኩረቱን በምግብና ቮካርታ ጨዋታ ላይ አደረገ። አንዳንዴም ድግስ ቤት ሲጋበዝ መቀመጫውን ይዞ በዝምታ በምግብ ሣህኑ ላይ በማፍጠጥ ይበላል። በግብግቡ ላይ የሚነሡት ነገሮች ሁሉ ለርሱ ስሜት የማይሰጡ፣ ትክክል ያልሆኑና ጅል ነገሮች በመሆናቸው ያበሳጩታል። ቢሆንም አንድ ነገር ሳይተነፍስ ጭጭ ይላል። ሁልጊዜ ሲበላ በምግብ ሣህኑ ላይ ገም ብሎ ስለሚያፈጥ፣ በደም ሥሩ ውስጥ የፖላንድ ደም ባይኖርም፣ “ባለጌው የፖላንድ ሰው” የሚል የቅጽል ስም አውጥተውለታል።

የትያትርና የሙዚቃ ቤቶችን ከመሳሰሉ መዝናኛ ቦታዎች ራቀ። በየምሽቱ ለሦስት ወይም ለአራት ሰዓት ያህል ካርታ እየተጫወተ ይደሰታል። ሳያውቀውና ሳይ ስማው የገባበት ሌላ መደሰቻም አለው። ይህም በቀን ውስጥ ሲሠራ የተቀበለውን ገንዘብ በሙሉ ከኪሱ ማውጣት ነው። ይህ የወረቀት ገንዘብ ግማሹ ቢጫ፣ ሌላው አረንጓዴ ሲሆን፣ ልዩ ልዩ ሽታዎች አሉት። አንዳንድ ጊዜ ከኪሱ የሚያወጣው ገንዘብ እስከ ሰባ

ሩቅል ይደርሳል ። አያሌ መቶ ሩብሎች ሲያጠራቅም መስዶ ባንክ ያስቀምጣል ።

ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ፡ ከሐይች ፀአራት ዓመት ጊዜ ውስጥ የቱርኪንን ቤተሰብ የጠየቀው ሁለት ጊዜ ብቻ ሲሆን ፡ ያውም የራስ ምታት በሽታዋ ስላልተሻላት በቬራ ዩሲፎቭና ጥሪ ነበር ። የክረምቱን ወራት ከቤተሰቦቿ ጋር ለማሳለፍ ሁል ጊዜ በክረምት ወራት ዩካቴሪና ኢቫ ኖቭና ትመጣ ነበር ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ግን አይታት አያውቅም ።

በዚህ ዐይነት አራት ዓመታት ፀለፉ ። አንድ ሞቃት ጠዋት አንድ ደብዳቤ ለሆስፒታሉ ይደርሳል ። ደብዳ ቤው ከቬራ ዩሲፎቭና ለዲሚትሪ ዩሂች የተጻፈ ነበር ። የደብዳቤው መንፈስ መጥፉቱን ገልጾ ቀኑም የልደት ቀኗ ስለሆነ ፡ ብቅ ብሎ ከደረሰባት ሥቃይ እንዲፈውሳት የተላከ የዕርዳታና የግብግ ጥሪ ነበር ። በደብዳቤው ግርጌ ሌላ ተጨማሪ ጽሑፍ ሠፍሯል ። "የእናቴ ጥያቄ የኔም ጥያቄ ነው" ይላል ዩካቴሪና ።

እስታርትሴቭ ፡ በነገሩ ደጋግሞ ካሰበበት በኋላ ፡ ወደ ማታ ወደ ቱርኪን ቤተሰብ ቤት ሔደ ። ኢቫን ፔትሮቪች በተለመደው ጠባዩ "ሃሎ!ሃሎ!" ፬ሃለት በዐይኑ ብቻ ፈገግ እያለ ፡ "እንደ ምን አመሸህ" በሚል ሰላምታ ተቀብለው ።

ዕድሜዋ ገፍቶ ጀጉሯ የሸበተው ቬራ ዩሲፎቭና የእስታርትሴቭን እጅ ጠንከር አድርጋ በመጨበጥ በተ ጎዳ መንፈስ በክባዱ እየተነፈሰች ፡ "ስላረጀሁብህ አት ፈልገኝ ይሆናል ዶክተር ፡ አትጠይቀንም ! አሁን ግን

ወጣቷ መጥታለች ምናልባት በጣም ዕድለኛ ትሆና ለች" አለችው ።

ውርዴስ? የበለጠ ቀጥና ገርጥታለች ። ሆናም ካለ ፈው የበለጠ ተወዳጅና ማራኪ ሆናለች ። አሁን ውርዴ ሳትሆን ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ናት ። ለግላጋነቷና የሕ ፃንነት የዋህነቷ ጥሏት ሔዷል ። በውስጧ የመቆጠ ብና የሕሊና ወቀሳ ያለበት አመለካከት ወይም በቤተ ሰቦቿ ቤት ምኞት ያልተሰማት ዐይነት ሁኔታ ይታ ይባታል ።

"ለረጅም ጊዜ አልተገናኘንም" አለች እጅዋን እጁ ውስጥ እያስገባች ። ልቧ በትልቁ እንደሚመታ ከሁኔ ታዋ ይታወቅባታል ። ለማወቅ በጓጓ መንፈስ ትኩር ብላ በቀጥታ ፊቱን እየተመለከተች ፣ "በጣም ወፍረሃል ፤ ጠቆር ብለሀ ወንዳወንድነትህ ጨምሯል ፤ በአጠቃላይ ግን ብዙም አልተቀየርክም" አለችው ።

እስታርትሴቭ አሁንም አምራ ተቆንጅታ በጣም ተውባ ነው ያገኛት ። ግን ፣ አንድ የጐደላት ነገር በመ ኖሩ እንደ ወትሮው ያለ ስሜት ሊሰማው አልቻለም ። መገርጣቷን ፣ አዲሱን ሁኔታዋን ፣ ደካማ ፈገግታዋን ፣ ድምፅዋን ፣ ልብሷን ፣ የተቀመጠችበትን ወንበር ፣ ቀደም ሲል ያሳለፉትንም ጊዜ ሲያስታውስ በሙሉ አልወደደ ውም ፤ አስጠላው ። ከአራት ዓመት በፊት የቀሰቀሰውን ያንገበገበውን ፍቅሩን ፣ ሕልሙንና ተስፋውን ሲያስ ታውስ የሚያደርገው ይጠፋዋል ።

ቅቤ የተቀባ ኬክና ሻይ ቀርቧል ። ቬራ ዩሲፎቭና በሕይወት ውስጥ ይደርሳል ተብሎ የማይገመተውን

ድርሰቷን ጮክ ብላ ታነባለች ። እስታርትሴቭ ግራ ጫውን ውብ እራሷን እየተመለከተ እስክትጨርስ ያዳምጣታል ።

“ደካማው ድርሰት ፣ ለመድረስ የማይችለው ሰው ሳይ ሆን” አለ ፊቱን በራሱ ፣ “ድርሰት የመድረስ ችሎታ ያለው ነገር ግን ፣ እውነቱን መደበቅ የማይችለው ሰው ነው ።”

ኢቫን ፔትሮቪች “አይከፋም!” አለ ።

ከዚያም ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ፣ ለረጅም ጊዜ ድም ጿን ከፍ አድርጋ ተጫውታ ስታበቃ ትልቅ ሞብጨባና ምስጋና ተደረደረላት ።

“አለማግባቱ ጥሩ ነገር ነው” በማለት እስታርት ሴቭ አሰበ ።

ወደ አትክልቱ ቦታ እንሒድ ብሎ እንዲጋብዛት በማሰብ እጥብቃ ዐይን ፀይኑን ብትመለከተውም ፍንክች አላለም ።

“እንጫወት” አለችው ወደሱ ዐልፋ እየተጠጋች ። “ኑሮ እንዴት ይዞሃል? ምን ዐይነት ኑሮ ነው እየኖርክ ያለኸው? ይህን ሁሉ ጊዜ ስላንተ ሳስብ ነበር” በማለት በድንጋጤ ንግግሯን ቀጠለች ። “ልጽፍልህ ፈልጌ ነበር ። ዲያሊዥ ድረስም መጥቼ ላይህ ፈልጌ ነበር ። ነገር ግን ተውኩት ፤ አሁን ስለኔምን እንደምታስብ እግዚአብሔር ይወቅ ! የዛሬውን መምጣትህን በተስፋ ስጠባበቀው ነበር ። እባክህ ወደ አትክልቱ ቦታ እንውጣ” ስትል ጠየቀችው ።

ወደ አትክልቱ ቦታ በመውጣት ከአራት ዓመት ዐፊት ያደርጉት እንደ ነበረው በትልቁ ዛፍ ቅርንጫፎች

ሥር ባለው በተለመደው መቀመጫቸው ተቀመጡ ፤ ጨለማ ነበር ።

“ታዲያስ ኑሮ እንዴት ይሆሃል?” ስትል ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ደግማ ትጠይቀዋለች ።

“በጣም ደኅና ነኝ ፥ አመሰግናለሁ ” በማለት እስ ታርትሴቭ ይመልስላታል ።

ሌላ ምንም የሚናገረው ነገር ስላላገኘ ዝም ብለው በጸጥታ ተቀመጡ ።

“በጣም ደክሞኛል” አለች ዩካቴሪና ኢቫኖቭና ፊቷን በእጆቿ በመሸፈን ። “ችላ በለው ወደ ቤተሰቦቼ መመለሴና ሁሉንም ሰው ደኅና ማግኘቴ በጣም አስደስቶኛል ፤ ሆኖም ልለምደው አልቻልኩም ። ምን ዐይነት ትዝታ ዎች ነበረኝ ! እኔና አንተ ሌሊቱን ሁሉ ተቀምጠን ስን ጫወት እናድራለን ብዬ አስቤ ነበር!”

ፊቷንና ብሩህ ዐይኖቿን ይመለከታቸዋል ። እዚህ ጨለማው ውስጥ ደግሞ እቤት ውስጥ ካያት በተሻለ ተውባ የቀድሞው የልጅነት ገጽታዋ ተመልሶላት የሚ ታየው መሰለው ። ይህን አንድ ጊዜ በጣም አድርጎ ያደንቃት ፥ ይወዳትና ያፈቅራት የነበረውን ሰው በፍ ላጎት እየተመለከተች ልትጠጋው የፈለገች መስሎ ታየው ። ላሳያት ፍቅር ዐይኖቿ አመሰገኑት ። እሱም ያለ ፉትን ትዝታዎች ፥ ጥቃቅኑን ነገር ሁሉ እንዴት በመ ቃብሩ ቦታ እንደ ተንከራተተና ሊነጋጋ ሲል በጣም ደክ ሞት እንዴት ወደ ቤቱ እንደ ተመለሰ ሲያስታውስ በቅ

ጽበት ጎዘን ተሰማው ። ባለፈው ነገር ሁሉ ተጸጸተ ። በሥራ አካላቱ እሳት ነደደ ፤ ተቀጣጠለ ።

"ወደ ክበቡ የወሰድኩሽን ዕለት ምሽት ታስታውሻለሽ?" ሲል ጠየቃት ፤ "ጨለማና ገናብ ነበር..."

በውስጡ የነደደው እሳት እየጨመረ ፥ እያደገ በመሔዱ ለመናገር ብርቱ ፍላጎት ስለ አደረበት ፥ በሕይወቱ ያጋጠመውን ጎዘን ዘክገኩ ለመናገር ...

በረጅሙ በመተንፈስ ፥"ስለ ሕይወቴና ስለ ኑሮዬ ጠየቅሽኝ ። እንዴት እንደምኖር? አልኖርም ፤ ኑሮም አይደለ ። እያረጁና ፥ እየወፈሩ ማለፍ ነው ። አንዱ ቀን ሌላውን ተከትሎ ይመጣል ። ሕይወት ምንም አስ ደናቂ ነገር የማይታይበት ፥ የማይታሰብበትና የማይመ ዘገብበት አሰልቺና የማያስደስት ሆኖ ያልፋል ። ቀኑ ገንዘብ በማሳደድ ያልፋል ። ምሽቱ በክበቡ ከካርታ ተጫ ዋቾች ፥ ከጠጪዎችና ከጉረኞች ጋር ያልፋል ። ሁሉም ያስጠላኛል ። ምን ዐይነት ኑሮ ነው?"

"ሥራህስ? በጣም ጥሩ የሥራ መስክ አለህ ። ስለ ሆስፒታልህ ሁልጊዜ በአድናቆት ትናገር ነበር ። ያንጊዜ እኔ ራሴን እንደ ትልቅ ፒያኖ ተጫዋች ስለ ምቆጥር ፥ ራሴን እንደ ልዩ ፍጡር እመለከተው ነበር ። ዛሬ ሁሉም ወጣት ሴቶች ፒያኖ ይጫወታሉ ። እኔም እንደ ማንኛዋም ወጣት ሴት ፒያኖ እጫወታለሁ ፤ ምንም አዲስ ነገር የለም ። እናቴ ደራሲ የመሆኗን ያህል እኔም የፒያኖ ተጫዋች ነኝ ። ያንጊዜ አልተረዳሁልህም ፤ አላ ወቅሁልህም ነበር ። ሞስኮ ከሔድኩ በኋላ ግን ፥ ሁል ጊዜ ስላንተ እንጂ ስለሌላ ምንም ነገር አላስብም ነበር ።

የኤካባቢ ዶክተር ሆኖ የሚሠቃዩ ሰዎችን መርዳት ፣ ሕዝቡን ማገልገል እንዴት መታደል ነው ፤ ምንኛ ያስደስታል !" አለች ዩካቴሪና ኢቫኖቭና በስሜት ። "ሞስኮ ሆኜ ስላንተ ሳስብ ተስማሚና ኩሩ ባሕርይ ... አድርጌ ነው ።"

እስታርትሴቭ በየምሽቱ ከኪሱ እያወጣ ያነባት የነበረችውን ማስታወሻ ሲያስታውስ በውስጡ ሲነድ ሲንቦገቦግ የነበረው እሳት እየበረደለት ሔደ ።

አፈፍ ብሎ ወደ ቤት ለመግባት ሲነሣ እጁን ያዘ ችው ።

"ከአወቅሁዋቸው ሰዎች በሙሉ አንተ በጣም ጥሩ ሰው ነህ" ብላ በመቅጠል ፣ "ተገናኝተን መጫወት ይኖርብናል ፤ አይመስልህም ? ቃል ግባልኝ ። ጥሩ የፒ ተጫዋች አይደለሁም ። ነኝ ብዬም ራሴን አላ ልልም ፤ ሁለተኛም ባንተ ፊት ፒያኖም አልጫ ትም ፤ ስለ ሙዚቃም አላነሣም ።"

እቤት እንደ ገቡ እስታርትሴቭ በቤቱ ብርሃን በጎዘን የጠወለገውን ፊቷንና የጣለችበትን ዘልቆ የሚ ገባው አመለካከቷ ልቡን ቢያዋልለውም ራሱን በራሱ አጠናከሮ ፣

"ባለማግባቴ በጣም ጥሩ አድርጌያለሁ" ብሎ ተሰናብቶ ወጣ ።

"ከራት በፊት መሔድ አትችልም "አለው ኢቫን ፔትሮቪች እየሸኘው ። "ይህ ያንተ ልዩ ጠባይህ ነው ።

ዘል ና ትዕይንትህን አሳይ” ብላት ዞር ብሎ በፓሻ ጮኸበት ።

ፓሻ እንደ ቅድሞው ልጅ ሳይሆን ዲም ያበቀለ ኮረምሳ ነው ። ፓሻ እጁን ወደ ላይ በማንሣት ብሚያ ላዝን ድምፅ ፥

“ድራሽህ ይጥፋ! እርጉም!” አለ ።

ይህም እስታርትሴቭን አስቆጣው ። ወደ መሬገላው ሲገባ አንድ ጊዜ ውብና ድንቅ አድርጎ ይወደው የነበረውን ቤትና የአትክልት ቦታ አተኩሮ በጨለማው ውስጥ ሲመለከት ያለፈው ነገር ሁሉ እየጋለበ በሐሳቡ መጣበት ። የቬራ ዩሲፎቭናን ድርሰቶች ፥ የውርዬን የፒያኖ ጨዋታ ፥ የኢቫን ፔትሮቪችን የዐዋቂ ቀልዶችና የፓሻን አሳዛኝ ቅርፄቶች አስታውሶ ፥ ከከተማው ውስጥ አሉ የሚባሉት ችሎታ ያላቸው ሰዎች እንደ ዚህ ደካማ ከሆኑ ከከተማዋ ምን ይጠበቃል ? ሲል ራሱን ጠየቀ ።

ከሦስት ቀን በኋላ ፓሻ ልንድ ደብዳቤ ኔዩካቴሪና ኢቫኖቭና ይዞለት መጣ ።

“ለምን መጥተህ አትጠይቀንም ? የተቀየርክ ብን ወይም የተለወጥክብን መሰለኝ ። ይህ ከሆነ ነገሩን ግሰቡ ራሱ ያስፈራኛል ። እባክህ መጥተህ አጽናናኝ ፤ ሁሉም ነገር እንደ ነበረ መሆኑን አስረዳኝ ። ላይህ እፈልጋለሁ ። ያንተው ዩካቴሪና” ስትል ጻፈችለት ።

ደብዳቤውን ብአንክሮ አንብቦ ካሰበበት በኋላ ለፓሻ እንዲህ አለው ።

"ደጉ ሰው፥ በጣም ሥራ ስለሚበዛብኝ ዛሬ መም ጣት እንደማልችል ንገራት ። በአንድ ቢሁለት ቀን ውስጥ እመጣለሁ ።"

ምስት ቀኖች ዐለፉ ። ሳምንትም ሆነ ፥ ግን አሁ ንም አልሔደም ። አንድ ጊዜ ለሥራ ጉዳይ በቱርኪን ቤተሰብ በኩል ሲያልፍ ለጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን መግባት አለብኝ ብሎ አሰቦ ነበር ። መለስ አድርጎ ነገሩን ሲያየው ሳይገባ መንገዱን ቀጠለ ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደ ቱርኪን ቤተሰብ አልሔ ደም ።

ጥቂት ዓመታት ዐለፉ ። እስታርትሴቭ ውፍረቱ እየጨመረ ፥ ትንፋሽ እያጠረውና ደረቱን ገልብጦ መሔድ ጀመረ ። ቀይ ፊቱ ፥ የተንጠለጠሉት ጉንጮቹ አንገ ታቸው ላይ የታሰረውን ቃጭል የሚያንቃጭሉት ሦስቱ የሠረገላ ፈረሶች በሚያልፉበት ጉዳና ሁሉ እንደ ትርዕይት እንዲታይ ያደርጉታል ። ፔንቴሊሞንም ፥ ሠረገላ ነጂው ቦታ ተቀምጦ ከተንጠለጠሉት ጉንጮቹ በተ ጨማሪ አንዳች የሚያሀል ስብ በጫንቃው ላይ ተሸክሞ፣ እጆቹ ከዕንጨት የተሠሩ ይመስል ቀጥ ብለው ወደ ፊት ተዘርግተው ፥ ከፊት ለፊት የሚመጡትን የሠረገላ ነጂዎች "ቀኝህን ያዝ" እያለ ሲጮህ ከሰው የሚ ወጣ ድምፅ ሳይሆን አንድ ልዩ ፍጡር የሚያንጸባ ርቅ ይመስላል ። እስታርትሴቭ የሕክምና ሥራው በከ ተማው ውስጥ በመታወቁ ፥ ሥራ ስለሚበዛበት የመተ ንፈሻ ጊዜም የለው ። በገጠር ሰፊ የእርሻ መሬት ሲኖ ረው ፥ በከተማም ሁለት ቤቶች ገዝቶ ሌላ ብዙ ትርፍ

በሚያስገኝ ቤት ላይ ደግሞ ፀይኑን ጥሏል ። በጨረታ የሚሸጥ ቤት መኖሩን ከባንኩ ከሰማ ሳያወላውል ፥ ያለ ይሉኝታ ወደ ቤቱ በመሔድ ኃፍረታቸውን ያልሸፈኑ ሴቶችና ሕፃናት በድንጋጤ እየተመለከቱት አልፎ ቸው ከከፍል ወደ ከፍል እየተዘዋወረ በያዘው ከዘራ እያንዳንዱን በር እያንኳኳ ፥

"ይህ የጥናት ቤቱ ነው ? ይህስ መኝታ ቤቱ ነው? ይህስ ምንድነው ?" እያለ ይጠይቃል ።

ይህን ሁሉ ሲያደርግ በከባዱ እየተነፈሰ በላብ የተጠመቀ ግንባሩን እየጠረገ ነው ።

ብዙ ቃላፊነት ቢኖርበትም ፥ የዜምስትቮ የክልል ዶክተርነቱን ሥራ ለመተው አይፈልግም ።

በስግብግብነቱ የሚፈለገውን ነገር ሁሉም ቦታ እንዲያገኝ ይጥራል ። አሁን በከተማም ሆነ በዲያሊዥ የሚታወቅበት ስም "ዩኒች" ሆኗል ።

ዩኒች በአካባቢው በጣም በመታወቁ በሠረገላ ሲንቀሳቀስና ምክር ለመጠየቅ ሲፈልጉ ፥ "ዩኒች ወዴት ነው የተነሣው? " ወይም "ዩኒችን ብንጠራው አይሻልም ?" ይባባላሉ ።

ድምፁ ፥ ምንም ጥርጥር የለውም ፤ ጉሮሮው ውስጥ ተደራርቦ በተነጠፈው ስብ መሆን አለበት ፤ ቀጭንና የሚቆራረጥ ነው ። ጠባዩም እንደዚሁ ተለውጧል ፤ ቁጡና ነጭናጫ ሆኗል ። ለደንበኞቹም ምርመራ ሲያደርግ በድንገት ተቆጥቶ በከዘራው ወለሉን እየቆረቆረ በማያስደስት ድምፁ ፥ "የምጠይቅህን ብቻ መልስ ፤

የማያስፈልግ ነገር አትናገር" በማለት ሰው ይለከፋል።

ብቻውን ነው የሚኖረው። ኑሮው አሰልቺ ሲሆን ምንም የሚያስደስተው ነገር የለም፤ ደስተኛ አይደለም። በዲያሊሽር በሳለፈው ጊዜ ምናልባት ደስታ አግኝቶ ከሆነ፣ ከውርዬ ጋር ያሳለፈው የፍቅር ጊዜ ብቻ ነው። ማታ ማታ በክበቡ ካርታ ይጫወትና አንድ ትልቅ ጠረጴዛ ብቻውን ይዞ ራቱን ይበላል። ሁል ጊዜ ሲበላ ቆሞ የሚያበላው ከክበቡ ሠራተኞች በሙሉ የታወቀውና የተከበረው ሽማግሌው ኢቫን ነው። የክበቡ ሠራተኞች ከአስተዳደሩ ጀምሮ ወጥ ቤቱና ሌሎችም ሠራተኞች የሚፈልገውንና የማይፈልገውን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፣ ለማስደሰት የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ። ይህን ካላደረጉ፣ እግዚአብሔር አይበልና፣ በጣም ተቆጥቶ በከዘራው ወለሉን መደብደብ ይጀምራል።

በራት ጊዜ ዐልፎ፣ ዐልፎ ከሰዎች ጋር ተግናኝቶ ይጫወታል።

"ምንድን ነው የምታወራው? እ? ማን?"

በሚቀጥለው ጠረጴዛ ላይ እየተካሔደ ያለው ጭውውት ስለ ቱርኪን ቤተሰብ ከሆነ እንዲህ ሲል ይጨይቃል።

"ስለ ቱርኪን ቤተሰብ ነው የምትጫወቱት? አንዲ ልጃቸው እንኳን ፒያኖ የምትጫወቅ?"

ስለ እስታርትሴቭ ማለት የሚቻለው ይኸው ነው።

የቱርኪን ቤተሰብስ? ኢቫን ፔትሮቪች አፁንም አላረጀም። ወይም ከቀድሞው ምንም አልተለወጠም። አሁንም ቀላጅ ነው። አሥቂኝ ታሪኮችን አሁንም ያሰማል። ቬራ ዩሲፎቭናም አሁንም ልክ እንደ በፊቱ በክሜት ድምጿን ከፍ አድርጋ ከእውነታ ጋር ያልተዛመዱ ድርሰቶቿን ልጦብኚዎቿ ታነባለች። ውርዬም በቀን የኔራት ሰዓት የጢያኖ ልምምዷን ቀጥላለች። የዕድሜዋ መማፋት በጉልህ ይታወቅባታል። ዘወትርም ታማሚ ስለሆነች፣ በመጸው ወራት ሁልጊዜ ከእናቷ ጋር ወደ ክራይሚያ ትሔዳለች። ኢቫን ፔትሮቪች ባል ቤቱንና ልጁን ሲሸኝ ባቡሩ ከጣቢያው ሲንቀሳቀስ እንባ ያዘሉ ዐይኖቹን እያበሰ "ደኅና ግቡ" በማለት መሐረቡን እየነሰነሰ ይሰናበታቸዋል።

ባለ ውሻዋ ወይዘሮ

አንድ ውሻ ያላት ፡ ሴት ወይዘሮ በመንገድ ላይ መታ የቷን ሰዎች እርስ በርሳቸው ይንሾካሾካሉ ። ዲሚትሪ ዲሚትሪች ጐሮቭ ወደ ያልታ ከመጣ ሁለት ሳምንት ቢሆነውም ፡ የከተማውን መውጫ መግቢያ ዐውቆ ወደ ከተማዋ ስለሚመጡ አዳዲስ ሰዎች የማወቅ ፍላጐት አድሮበታል ። ከቬርኔት ቡና ቤት የውጭ በረንዳ ተቀ ምጦ ወደ መንገዱ ሲመለከት አንድ ወጣት ወይዘሮ ባርኔጣ ደፍታ ስታልፍ ያያል ። መካከለኛ ቁመት ያላት መልከ መልካም ሴት ናት ። አንድ ትንሽ ነጭ ሶሎማ ውሻ ከኋላዋ ቱስ ቱስ እያለ ይከተላታል ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፡ በማዘጋጃ ቤቱ መናፈሻና በከ ተማው አደባባይ በቀን ለብዙ ጊዜ ያያት ጀመር ። ሁልጊዜ የሚያያት ባርሚጣዋን ደፍታ ትንሹን ሰሎማ ውሻ አስከትላ ብቻዋን ስትዘዋወር ነው ። ማንም የሚ ያውቃት ስላልነበረ ፡ ሰዉ "ባለውሻዋ ወይዘሮ" በማለት ስም አውጥቶላታል ።

"እዚህ ያለችው ያለ ባሏና ያለወዳጅ ከሆነ" ሲል ጐሮቭ በማሰብ ፡ "ብተዋወቃት አይከፋም" አለ ።

ዐርባ ዓመት ባይሞላውም ፡ አንድ የዐሥራ ሁለት ዓመት ሴት ልጅና ሁለት ወንዶች ልጆች አሉት ። እንዲያገባ የተደረገው የሁለተኛ ዓመት ኮሌጅ ተማሪ

ሆኖ ሲሆን ፥ ባለቤቱ አሁን ከእሱ በእጥፍ ያረጀች ትመስላለች ። ረዥም ፥ ቀጥ ያለች ፥ ጥቁር የዐይን ሽፋሉ ሽፍት ያላት ፥ ባለግርማና ስለራሷ እንደምትናገረው "ተፈላሳፊ" ሴት ናት ። ዲሚትሪ በምስጢር ጥልቀት የሌላት ግልብ ፥ ጠባብ አመለካከት ያላት ናት ቢልም ብዙ የምታነብ ሰው ነች ። ዲሚትሪ በጣም ስለሚፈራት ወደ ቤት መግባት ያስጠላዋል ። በዚህም ምክንያት ነው በሷ ላይ ማመንዘር የጀመረውና ታማኝ የማይሆንላት ። በዚህም መነሻ ይመስላል ሴቶችን የሚንቀውና አኮስሶ በመመልከት ፥ "ዝቅተኛ ዘሮች" የሚል መጠሪያ ያወጣላቸው ።

ከመራራ ልምድ የቀሰመው ብዙ ትምህርት ሴቶችን እንደፈለገው ለጠላቸው የሚያስችለው መስሎ ይታየዋል ። ነገር ግን ፥ "ዝቅተኛ ዘሮች" ብሎ ከሚጠራቸው ሴቶች ውጭ አንድም ቀን ሊኖር አይችልም ነበር ። ከወንዶች ጋር በሚሆንበት ጊዜ ስልቹና ቅብጥብጥ ከመሆኑም በላይ ፥ ሁል ጊዜ ቀዝቃዛና ዝምተኛ ነው ። ከሴቶች ጋር ሲሆን ምን እንደሚያጫውታቸው ስለሚያውቅ ሁልጊዜ ደስተኛ ነው ። በመኻከላቸው ምንም ሳይረበሽ ለመቀመጥ ይችላል ። ቁመናውና ግርማው የሚያስገርም ውበት ስለሚሰጠው ፥ ሴቶችን የመሳብና ፍቅራቸውን የማግኘት ችሎታ አለው ። ይህንን ስለሚያውቅ ፥ እሱም በአንድ በማይታይ ኃይል ግፊት ወደ እነሱ ያደላል ።

እያንዳንዱ አዲስ ትውውቅ በመጀመሪያ በዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ደስታና ቀላል ጀብዱን የሚያስከትል መሆኑን ፥ ቀስ በቀስ ግን በጣም በተከበሩ ሰዎች መኻል

(በተለይ ሰዎች ተጠራጣሪ በሆኑበት በሞክክ) እንኳን ሳይቀር ይህ ትውውቅና መወዳጀት በጣም ወደ ተወሳ ሰበና አድካሚ ወደሆነ ችግር እንደሚያድግ የተደጋገመ መራራ ልምድ አስተምሮታል ። ነገር ግን በጣም ቆንጆ ባጋጠመው ቁጥር ይህን ልምዱን ወደ ጎን በመተው ይረሳዋል ። የሕይወት ጣፋጭነት ፀውስው በድንገት ብቅ ስለሚል ፣ ነገሮችን አቅልሎና አስደሳች አድርጎ ይወስዳቸዋል ።

አንድ ምሽት በመኖሪያው ቦታ ባለው የምግብ ቤት ራቱን ሲበላ ፣ ባለውሻዋ ወይዘሮ የተለመደ ባርሜ ጣዋን እንደ ደራች ወደ ምግብ ቤቱ በመግባት አጐራባች በሆነው ጠረጴዛ ተቀመጠች ። ቁመናዋ ፣ አለ ባበቧ ፣ የጸጉሯ አሠራር በአጠቃላይ ሁናቴዋ የሀብታም ቤተሰብ መሆኗን ፣ እንዲሁም ባለትዳር ፣ ወደ ያልታ የመጣችው ብቻዋን እንደ ሆነችና እንደ ሰለቸች ይታ ወቅባታል ። ወደ ያልታ የሚመጡ ጐብኚዎች በሞራል በኩል ደካማ መሆናቸው ተጋኖ ቢነገርም ፣ ይህንን ፈጥረው የሚያወሩት ራሳቸው ችሎታውና ስልቱ ቢኖራቸው ከዚህ የሞራል ግድፈት የማይመለሱ ናቸው በማለት ቅላ አለው ። ወይዘሮዋ ጥቂት እርምጃዎች ርቆ በሚገኘው ጠረጴዛ እንደ ተቀመጠች ስሟን እንኳን ከማያውቀው ሴት ጋር የሚያደርገው ትውውቅና በተ ራራዎች የሚደረግ ጨርሽፎ በድንገት አዕምሮውን ወረ ራው ።

በማጨብጨብ ሶሎጉን ውሻ ጠራው ። ውሻው ኩስ ኩስ እያለ ወደሱ ሲመጣ የሌባ ጣቱን አነቃነቀበት።

ውሻው አጉረመረመ ። ጐሮቭ ጣቱን እንደገና አነቃ ነቀፀት ።

ወይዘሮዋ ቀና ብላ ወደ ጐሮቭ ተመልከታ ፈጥና ፀይኖቿን ሰበር አደረገች ።

"አይናከስም" ብላ አፈር አለች ።

"አጥንት ልስጠው" ብሎ ሲጠይቃት ፣ በአንገቷ የአወንታ መልስ እንደ ሰጠችው ለስለስ ባለ ድምፅ "ያልታ ክመጣሽ ቆየሽ?"

"አንድ አምስት ቀን ይሆነኛል ።"

"እኔም ሁለተኛ ሳምንቴን ይዣለሁ ።"
ለተወሰነ ደቂቃ ሁለቱም ዝም አሉ ።

"ቀኑ በፍጥነት ቢያልፍም ፣ በጣም ይሰለቻል" አለች እሱን ሳትመለከት ።

"አዎን ፤ ሁሉም የሚለው ነው ። እዚህ በጣም ይሰ ለቻል ። እንደ ቤልዬቭ ወይም ቮሮዝድራ ባሉ እግዚ አብሔር በጠላቸው ቦታዎች እንኳን ሰዎች ሰለቹን አይሉም ። እዚህ ሲመጡ ብቻ ውይ መቅፈፉ ! ውይ አቧራው ! ሲሉ ራሳቸውን ከልዩ ቦታ የመጡ ያስመ ስላሉ" አላት ።

ሣቀች ። ሁለቱም እንደማይተዋወቅ እንግዳ በዝ ምታ ራታቸውን መብላት ቀጠሉ ። ከራት በኋላ ሁለቱም ከምግብ ቤቱ ተያይዘው በመውጣት እንደ ሚገናኛውም ነጻና የተደሰቱ ሰው ጭውውት ጀመሩ ። በባሕሩ ላይ ስለሚታየው አዲስ ብርሃን ሐሳብ እየተ

ለዋወጡ በእግራቸው ተንሸራሸሩ ። የባሕሩ ውሃ ሞቃት ነው ። የጨረቃዋ ብርሃን በባሕሩ ወለል ላይ ወርቃማ መሥመር ሠርቷል ። ጮሮቭ ከሞስኮ መምጣቱን ፥ የቋንቋ ሳይንስ ማጥናቱንና አሁን ግን ባንክ ውስጥ እንደ ሚሠራ ፥ በአንድ ወቅት በአንድ የግል አፔራ ተቀጥሮ ይሠራ እንደ ነበርና በኋላ ሐሳቡን እንደ ቀየረ ፥ በሞስኮ ከተማ ሁለት ቤቶች እንዳሉት ..... አጫወታት ። ከእርሷ ደግሞ በፔተርስበርግ ከተማ ማደጓን ፥ በ.ሠ. ከተማ እንዳገባችና ሁለት ዓመት እንደ ሆናት ፥ ለአንድ ወር ያህል በያልታ ከተማ እንደምትቆይ ፥ ባለ ቤቷም ዕረፍት የሚያስፈልገው ሰው በመሆኑ ምናል ባት እንደሚመጣም ተረዳ ። ባለቤቷ ግን ፥ የአስተዳደሩ ምክር ቤት አባል ይሁን ወይም የክልሉ አስተዳደር ቦርድ አባል አልገለጠችም ። ይህን በማድረጓም በራሱ ተደነቀ ። በመጨረሻም ግሮቭ ስሟ አና ሠርጊዬቭና መሆኑን ዐወቀ ።

ወደ ክፍሉ ከተመለሰ በኋላ ፥ ስለ እርሷ ማሰላሰል ጀመረ ። በሚቀጥለው ቀን እንደሚያገኛትም እርግጠኛ ሆነ ። የማይቀር ነበር ። ወደ መኝታው ሲሔድ ፥ ከጥቂት ጊዜ በፊት እንደ ራሱ ልጅ ተማሪ እንደ ነበረች ፥ በጣቋ ውስጥ ምን ያህል ታፍረትና መቆጠብ እንዳለ ፥ ከሰው ጋር ስትጫወት የሚሰማትን ስሜት ፥ ምናል ባትም ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ብቸኛ የሆነችበት ፥ ለሁልጊዜም ለማትከፋበት ምስጢራዊ ዓለማ ሰዎች የሚከተልዋት ፥ የሚያይዋትና የሚያናግሯት ሁኔታ ውስጥ ያለች መሆኑን በመረዳት ራሱን አስጠነቀቀ ። ቀጭንና ለስላሳ አንገቷን እንዲሁም ግራጫ ዐይኖቿን አስታወሰ ።

“ሆኖም አንድ የሚያሳዝን ነገር አለባት” እያለ ሀማሰብ አሸለበ ።

ከተዋወቁ አንድ ሳምንት ዐለፈ ። አንድ የበዓል ቀን ነበር ። ክፍሉ ውስጥ አየሩ የታመቀ ነው ። እውጪ አቧራው እንደ ዳመና ተነሥቷል ። ነፋሱ የሰውን ባር ሜጣ እየነጠቀ ሜዳ ለሜዳ ያንከባልላል ። ሙቀቱ ከባ ድና በጣም የሚያስጠማ ቀን ስለነበር ፥ ጐሮቭ ወደ ቡና ቤቱ እየሔደ በረዶና የፍራፍሬ ጭማቂ ለአና ሰር ጊዬቭና ያመጣላት ነበር ።

ወደ ማታ ነፋሱ በረድ ሲል ፥ ወደ ወደብ የሚገባ ውን መርከብ ለማየት ወደ መርከቡ ማረፊያ ሔዱ ። በማረፊያው ቦታ ብዙ ሰዎች ይንቀሳቀሳሉ ። ግማሾቹ ለሚመጡ እንግዶች የሚበረከት እቅፍ አበባ ይዘዋል ። የያልታ ኅብረተሰብ ሁለት ልዩ ሁኔታዎች በግልጽ ተን ጸባርቀውበት ዕድሜያቸው የገፋ ወጣት ለመምሰል የወጣት ልብስ የለበሱ ሴቶችና ቁጥራቸው የበዛ ጀኔ ራሎች ይታያሉ ።

በባሕሩ ማዕበል መክበድ ምክንያት መርከቡ የደረ ሰው ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ሲሆን ፥ ተስተካክሎ የማረ ፊያ ቦታውንም ለመያዝ ሌላ ተጨማሪ ጊዜ ወሰደ ። አና ሠርጊዬቭና የምትፈልገው ሰው ያለ ይመስል ፥ በያዘ ችው መነጽር መርከቡ ላይ ብዙ ፈልጋ ወደ ጐሮቭ ስት መለስ ዐይኖቿ ረጥበው ነበር ። ብዙ አወራች ። ለማወቅ የፈለገችውን ነገር እስክትዘነጋ ድረስ በማከታተል የጥ ያቄ እሩምታ አወረደች ። ወዲያው ደግሞ በግፊያው ውስጥ መነጽሯ ወደቀባት ።

በወደቡ ላይ ተሰብስቦ የነበረው ሕዝብ ቀስ በቀስ ቸበተነ ። በጨለማው የሰውን ገጽ ለመለየት አይቻልም። የነሩሱም ኃይል እያደር በረደ ። ጐሮቭና አና ሠርጊ ዬቭና ከመርከብዋ የሚመጣ ሌላ ሰው የሚጠብቁ ይመ ስል ቁመዋል ። አና ሠርጊዬቭና ዐልፎ ዐልፎ የያ ዘችውን አበባ እያሸተተች ወደ ጐሮቭ ሳትመለከት ጸጥ ብላ ቆማለች ።

“ጥሩ ምሽት ሆኗል” አለ ። “ምን እናድርግ ፣ ልንወጣ እንችላለን ።”

ምንም መልስ አልሰጠችም ።

ቀስ ብሎ ሊመለከታት ከቆየ በኋላ ፣ በድንገት አፈፍ አድርጎ በማቀፍ ከንፈሯ ላይ ሲስማት የአበባው እር ጥበትና መዓዛ አወደው ። ወዲያው ተገላምጦ ግራና ቀኝ ተመልከተ ፤ ሰው አይታችው ይሆን?

“ወደ ክፍልሽ እንሒድ” ሲል አጉረመረመ ።

እርምጃውን ፈጠን በማድረግ በአንድነት ሔዱ።

ከጥቂ ከሻፓኖች ሱቅ በገዛችው ሽቶ ታውዲል ። ጐሮቭ ለራሱ እያሰበ ተመልከታት ፤ “ሕይወት ምን ያህል አስደናቂ አጋጣሚ የሞላባት ናት !” አለ ። ግድ የሌ ላቸውና ሽጋ ተፈጥሮ ያላቸው በሚፈጽሙት የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚደሰቱ ፣ ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ፣ በሚ ሰጣቸው ደስታ ባለውለታ ሆነው የሚያመሰግኑት ሴቶች እንዳሉ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ፣ የእርሱን ሚስት የመሳሰሉ -ፍቅራቸው ከልብ ያልሆነ ፣ ተግደርዳሪና ስሜታቸው ገደቡን ያለፈ ፣ ብዙ የሚያወሩ ፣ በፖለት ተቃራኒ ጾታ

ዎች መኻል የሚኖረውን ግንኙነት ከመሲብ ወይም ከፍቅር ዐላይ አድርገው ከበው የሚመልክቱት ሴቶች መኖራቸውን ፣ እንዲሁም ሁለት ወይም ሦስት የሚሆኑ ዕድሜያቸው ከወጣትነት መሥመር ያለፈ ፣ በየጊዜው የሚለዋወጥ ቋሚ ያልሆነ ባሕርይ ያላቸው ፣ ቁጡ ፣ የሚያስብ አዕምሮ የሌላቸው ሁለት ወይም ሦስት በጣም ቆንጆ የሆኑ የመሲብ ስሜታቸው የቀበቀዘ ሴቶች እንዳጋጠሙት ያስታውሳል ። ጐሮቭ ይህን ሁሉ ሲያስብ ቆይቶ ሐሳቡ ዐረፈለት ። በሐሳቡ ሲያወጣና ሲያወርዳቸው የነበሩ ውብ ሴቶች ሁሉ ስሜቱን አላንቀሳቀሱትም ። ለስላሳው የሴቶች የውስጥ ልብስ ሻካራ የዓሣ ቅርፊት መስሎ ታየው ።

እና ሠርጊዬቭና ግን ወጣትነት ፣ ዐይን አፋርነትና የልምድ ማነስ በጉልህ ይታይባታል ። ያሉበትን ክፍል በር ሰው ያንኳኳ ይመስል በክፍሉ ውስጥ ያለው ስሜት የመደንገጥና የመረበሽ ዐይነት ነው ። እና ሠርጊዬቭና "ባለ ውሻዋ ወይዘሮ" ብርካሽ የተገኘች መስሏት ፣ ሁኔታውን ልዩና ብርቱ ጐዳና አድርጋ ስለ ወሰደችው ግር የሚያሰኝና የማያስደስት ሆነባት ። መንፈሷ የተጐዳ መሰለ ። ረሽም ጸጉሯ ጎዘንተኛ በመሰለው ፊቷ ግራና ቀኝ ወረደ ። አንድ የጥንት ሠዓሊ የሣላት የኃጢያት ሥርየት የምትጠብቅ በጎዘንና በጸጸት የተመጠረች ቅርፅ መስላ ቆመች ።

"ልክ አይደለም" አለች ። "ከዚህ በኋላ ምንም ከብር አትሰጠኝም ፤ አታከብረኝም ። "

በጠረጴዛው ላይ አንድ ሀብሀብ ተቀምጧል ። ጐሮቭ አንድ ቁራጭ በስሱ ቆርጦ ቀስ እያለ መብላት ጀመረ ። ቢያንስ ግማሽ ሰዓት ያህል በዝምታ አሳለፉ ።

እና ሠርጊዬቭና ሕይወትን ብዙም ያላየች የተከበሩ ንጹሕ ሴቶችን ሁኔታ የምታንጸባርቅ የምታሳዝን ሴት ናት ። በክፍሉ ውስጥ የሚበራው አንድ የሻማ ብርሃን ፊቷን በሙሉ ባያሳይም ፥ ልቧ በጎዘን የተነካ መሆኑ በግልጽ የሚታይ ነበር ።

"ለምን የምሰጥሽን ክብር አንድላለሁ? ለምን አላከብርሽም?" ሺል ጐሮቭ ይጠይቃታል ። "የምትናገሪውን አታውቂም ።"

"እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ!" ብላ ዐይኖቿ እንባ አንቆረዘዙ ። "በጣም አስፈሪ ነው ።"

"ኃጢያተኛ ላለመሆንሽ ማስረጃ መፈለግ አያስፈልግሽም ።"

"እንዴት ኃጢያተኛ አይደለሁም ልል እችላለሁ? ደካማ ፥ ርካሽና ዋጋ የሌለኝ ሴት ስለሆንኩ ፥ ራሴን ከኃጢአት ለማንጻት አልችልም ። ያታለልኩት ባሌን ሳይሆን ራሴን ነው ። ዛሬ ብቻ አይደለም ። ለረጅም ጊዜ ራሴን ሳታልል ኖሬአለሁ ። ባለቤቴ ያለጥርጥር ታማኝና የተከበረ ሰው ቢሆንም አሽከር ነው ። ቢሮው ውስጥ ምን እንደሚሠራ ባላውቅም አሽከር መሆኑን አውቃለሁ ። ያገባሁት ገና የኻያ ዓመት ወጣት ሆኜ ሲሆን ፥ ከፍ ያለ ባል ለማግኘት ከፍተኛ ፍላጎት ነበረኝ ። ሌላ ሕይወት እንዳለ ራሴን በራሴ እነግረው ነበር ። ለመኖር ክፉኛ ፈለኩ ፤ ለመኖር .... በፍላጐት ተቃጠልኩ....ሊገባህ አይችልም ። በእግዚአብሔር ስም እምላለሁ ፤ ራሴን መቆጣጠር አልቻልኩም ፤ ምንም ነገር ከፍላጎቴ ሊገታኝ አይችልም ብዬ በመተማመን

ለባለቤቴ ነግሬ ወደዚህ መጣሁ ። እዚህ ከመጣሁ በኋላ እንደ ተለከፈና እንደ አበደ ሰው ...መንቀዋለል ጀመ ርኩ ፤ ተራና ርካሽ ሴት ሆንኩኝ ፤ ማንም ሰው ሊን ቀኝና ሊጠላኝ መብት አለው'' አለች ።

ጐሮቭ በጣም ተሰላችቶ ያዳምጣት ነበር ። የዋህ ንግግሯና በምሬት ያወረደችው ጸጸት ያልጠበቀውና ያላ ቦታው ዕንባ ያቀረሩት ዐይነቻ ቀልደኛ ወይም ተዋናይ አስመሰለዋት ነበር ።

''አልገባኝም'' አላት በለሰለሰ አንደበት ። ''ምን ድን ነው የምትፈልጊው?'' ፊቷን ደረቱ ላይ በመደ በቅ በቅጡ ወደ እርሱ ተጠጋች ። ''እመነኝ እባክህን ? እንድታምነኝ እለምንሃለሁ '' አለችው ። ''በሕይወት ውስጥ ንጹሕና ታማኝ የሆነውን ሁሉ እወዳለሁ ። መጥፎ ነገር ያስጠላኛል ። አሁን የማደርገውን በእር ግጥ አላውቅም ። ተራው ሕዝብ በሰይጣን ተለከፍኩ ይላል ። እኔም አሁን በሰይጣን የተለከፍኩ ያህል ሆኜ አለሁ ።''

''ተይ ፣ ተይ'' በማለት አጉረመረመ ።

አንድ ቦታ ላይ የተሰኩና የተቆጡ ዐይኖቿን ውስጥ አፍጥጠ በመመልከት እየሳማት የመውደድና የማፍቀር ቃላት እየወረወረ ሲያጽናናት ፣ ቀስ በቀስ በመቅዝቅዝ ቀድሞ ወደ ነበረችበት አስደሳች ንቁ ሁኔታ ተመለ ሰች ። ወዲያው ደግሞ አብረው መሣቅ ጀመሩ ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከነበሩበት ክፍል ሲወጡ በመ ንገዱ ላይ ሰው አልነበረም ። ከተማዋና በውስጧ ያሉት ዛፎች በሙሉ የሞቱ ይመስል ጸጥ ብለዋል ። ባሕሩ

ግን ፣ እንደ ተቆጣ አንበሳ እያገሳ ክዳፎቻው ጋር ይላ ተማል ። አንድ ደብዛዛ ብርሃን ያላት የዓሣ አጥማጅ ጀልባ ብቻ በማዕከሉ ከወዲያ ወዲህ ትንገላታለች ።

ፀአንድ ጋሪ ተሳፍረው ወደ አሪያንዳ ሔዱ ።

"ልምሽ ማን እንደሆነ አዳራሹ ውስጥ ከጥቂት ጊዜ በፊት አወኩኝ" አላት ጐሮሽ ፣ "ማስታወቂያ ሠሌዳው ላይ ተለጥፏል ። ፎን ዳይዴሪትገ ። ባለቤትሽ ጀፀ መናዊ ነው?"

"አይደለም ። እያቱ ነበሩ መሰለኝ ። እሱ ግን ኦር ቶዶክስ ክርስቲያን ነው" አለችው ።

አሪያንዳ ፣ እንደ ደረሱ ከቤተክርስቲያኑ ብዙም ሳይ ርቁ አንድ አግዳሚ መቀመጫ ላይ ተቀምጠው ንግግር ሳይለዋወጡ ዝም ብለው ባሕሩን ይመለከቱ ጀመር ። የያልታ ከተማ በጠዋቱ ጭጋግ ስለ ተሸፈነች ፣ በደንብ አትታይም ። ነጫጭ የበረዶ ክምሮችም በተራሮቹ አና ዶች ላይ ተቆልለዋል ። አንድ ቅጠል እንኳን ለያስ ሙላ አይንቀሳቀስም ። የፌንጣዎች ስርቅርቅታ ብቻ በያለበት ይሰማል ። አሰልቺው የባሕሩ ባዶ ጩኸት ብቻ ስል ሰላም ፣ እያንዳንዳችን ስለሚጠብቀን ዘላለ ማዊ ፅንቅልፍ ፣ እየተናገረ ወደነርሱ የሚመጣ ይመ ስላል ። የያልታ ከተማ ወይም ቦሪያንዳ ከመኖራቸው በፊትም ፣ ባሕሩ እንደዚሁ ቁጣውን እያሰማ ይኖር ነበር ። አሁንም ይጮኻል ። ወደፊትም እንደዚሁ ባዶውና አሰ ልቺው ጩኸት እኛ በሞት ካለፍንም በኋላ በግድ የለ ሽነት ይቀጥላል ። ምናልባትም በዚህ ተከታታይነት ፣ ፀሞትና ሕይወት ባለን ፍጹም ግድ የለሽነት ፣ በምድ

ራችን ላይ ያለው የሕይወት ምንጭ ምሥጢር ሳያቋ ርጥ ወደ ፍጹምነት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ይሆናል -የመጨረሻ ተስፋችን ።

በማለዳው ብርሃን ስትታይ በጣም ውብ ከሆነች ሴት ወይዘሮ ጋር ጐን ለጐን ተቀምጠ በተፈጥሮ ማራኪ ውበት ፣ ባሕር ፣ ተራሮች ፣ ደመናና መሰን የሌለው ሰማይ እየተደነቅ ጐሮቭ ራሱን በራሱ አናገረ ። ፀሐሳባችንና በተግባራችን የሕይወትን ክቡር ዓላማና ሰብአዊ ክብ ራችንን ከመርሳታችን በስተቀር በእርግጥም በዓለም ያሉ ነገሮች ሁሉ ውብ ናቸው ።

አንድ ሰው እየቀረባቸው መጥቶ ምናልባት ዘበኛ ይሆናል- ተመልከቷቸው ዐልፎ ሔደ ። በዚህ እንኳን በጣም ውብና ምስጢራዊ ነገር አለ ። ከፊዎዲሲያ የሚ መጣው መርከብ መብራቱን አጥፍቶ በጠዋቱ ብርሃን እየተመራ ወደ መርከቡ ማረፊያ ሲመጣ ይታያል ።

"ሣሩ ጤዛ አዝሏል" አለች እና ሠርጊዬቭና ንግግር ለመጀመር ያህል ።

"እዎን ወደ ቤት የመግቢያ ጊዜ ነው ። "

ወደ ከተማ ተመለሱ ።

ከዚህ በኋላ ፣ በየቀኑ በምሳ ስዓት በጐዳናው ላይ እየተገናኙ ምሳና ራት መብላት ፣ ሽርሽር መውጣትና ባሕሩን ማድነቅ ጀመሩ ። በእንቅልፍ ማጣትና በልቧ ምት መጨመር ታማርራለች ። አያከብረኝም ፣ ይንቀኛል በሚል ፍራቻና በቅናት ሳቢያ አንዱን ጥያቄ በመደ ጋገም ትጠይቃለች ። በመናፈሻው ወይም በአደባባዩ

የሚያያቸው ሰው ሳይኖር ወደ እርሱ ጠጋ አድርጎ በፍቅር ይስማታል ። ጕሮቭ ሥራ መፍታቱ ፣ ቀን በቀን የሚደረገው መሳሳም ፣ የሁልጊዜ ግልምጫና የመጋለጥ ፍራቻ ፣ ሙቀቱ ፣ የባሕሩ ሽታ ፣ በእይታቸው ሥር የሚያልፉትን ሥራፈት ቆንጆና የተንደላቀቁ ሰዎች ይህ ሁሉ በአንድ ላይ ተደማምሮ ዕድሜውን የሚያራዝምለት መስሎ ታየው ። እና ሠርጊዬቭና ቆንጆና ሰውን የሚስብ ውበት እንዳላት እያጫወታት ከባድ ወሲባዊ ግንኙነት ይፈጽማሉ ። ከአጠገቧ ጨርሶ አይለይም ። እርሷ ግን ሁልጊዜ በሐሳብ እንደ ተዋጠችና እንዳዘነች ነው ። ትንሽም እንደ ማይወዳት ፣ እንደማያከብራትና እንደ አንድ ተራ ሴት ብቻ እንደሚቆጥራት ለማረጋገጥ ትጥራለች ። በየምሽቱ ወደ አሪያንዳ ፣ ወደ ወንዙ ፏፏቴ ወይም ወደ አንዱ መዝናኛ ቦታ ተያይዘው ይወጣሉ ። እነኚህ ጉብኝቶች ሁሉ አስደሳች ስለነበሩ ፣ አንዳንድ አዳዲስ ትዝታ እየጣሉ ያልፉሉ ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ፣ ባልዮው ይመጣል ብለው ይጠባበቃሉ ። በመጨረሻም ባልዮው የዐይን ሕመም እንዳጋጠመውና በፍጥነት ወደ ቤቷ እንድትመለስ የሚለምን ደብዳቤ ደረሳት ። እና ሠርጊዬቭናም ወደ ቤቷ ለመመለስ አጣዳፊ ዝግጅት አደረገች ።

“ወደ ቤቴ መመለሱ ጥሩ ነገር ነው” አለችው ጕሮቭን ። “የዕድል ጣልቃ ገብነት ነው ። ”

በጋሪ ሆና ከያልታ ከተማ ወጣች ። ጕሮቭም እስከ ባቡር ጣቢያው አብሯት ሔደ ። ጉዞው አንድ ሙሉ ቀን ፈጀ ። ወደ ባቡሩ ውስጥ ገብታ የባቡሩ መንቀሳቀሻ

ማስጠንቀቂያ ሁለተኛ ደወል ሲደወል እንዲህ አለ ችው ፤

“አንድ ጊዜ ደግሜ ልይህ .....አንድ የመጨረሻ እይታ ። አምን ፥ ልክ ነው ።”

ባታለቅስም በጣም አዘነና የታመመች መሰለች ። የጉንጮቿ ጡንቻዎች ይንቀጠቀጣሉ ።

“አስታውስሃለሁ... ሁል ጊዜም አስታውስሃለሁ” አለችው ። “እግዚአብሔር ይባርክህ ! አስበኝ ፤ አስታ ውሰኝ ፤ ለሁልጊዜው ልንለያይ ነው ፤ መሆንም አለ በት ። ምክንያቱም ቀድሞውንም መገናኘት አልነበረብ ንም ። ደኅና ሁን ! እግዚአብሔር ይባርክህ !”

ባቡሩ በፍጥነት ጣቢያውን እየለቀቀ ተፈተለከ ። በአጭር ጊዜ ውስጥ መብራቱ ተሰወረ ፤ ከአንድ ደቂቃ በኋላ ፥ ሁሉም ነገር ይህን እብደት በአፋጣኝ ወደ ፍጻ ሜው ለማምጣት ያበረ ይመስል የባቡሩ ድምፅም ጠፋ ። ጐሮቭ በደረጃው ላይ ቁሞ በሩቁ ጨለማ ላይ አፍጥጦ ፌንጣዎቹ በያለበት ድምፃቸውን ሲያስረቀርቁ ነፋሱ ከቴሌግራፍ መሥመሮች ጋር ሲጋጭ የሚፈጥረው ፉጨት ከእንቅልፉ ገና እንደነቃ ሰው ስሜት ያዳምጥ ነበር ። ይህ በሕይወቱ ካጋጠሙት ብዙ አጋጣሚዎች አንዱ መሆኑን ፥ ይህም ትዝታ ብቻ ጥሎለት ማለፉን ለራሱ በራሱ ተናገረ ። መንፈሱ ተነክቶ አዘነ ፤ መጠነኛ ጸጸ ትም ተሰማው ። ይህች ሁለተኛ የማያያት ወጣት ሴት አብራው በቆየችበት ጊዜ ደስተኛ አልነበረችም ። አፍ ቃሪዋና ወዳጅዋ ሆኖ ቆይቷል ። በጠቅላላው ግን ባሕ ርዩ ፥ ድምፅና የሰውነት ማሻሸቱንና ዳሰሳው የትምክ

ተኛ ወንድ ፥ ያውም ዕድሜው የሴቲቱን እጥፍ ከሆነ ፣ ዕድለኛ ወንድ የሚሰነዘር ስድብ ያዘለ ነበር ። ጥሩ ፥ የሚ ደነቅና ኩሩ አድርጋ ልትጠራው ተገዳለች ። በእርግጥም ከተፈጥሮ ፀሕርዩ ለየት ብሎ ቀርቧታል ። በአጠቃላይ ሳያውቀው ..... አታሏታል ።

አየሩ የመጸው ወራት ጠባይ አዝሏል ። ምሽቱ ደግሞ ፀጣም ቀዝቃዛ ነው ።

"እኔም ወደ ሰሜን የመሔጀ ጊዜዬ ደርሷል" ሲል ጐሮቭ አሰበ ። ከባቡር ጣቢያው ደረጃ እየወጣ ሲሔድ "ጊዜው ደርሷል" አለ ።

ወደ ሞስኮ ሲመለስ የከረምቱ ወራት መግባት ጀምሯል ። ምድጃው ሁል ጊዜ እንደ ሞቀ ነው ። ልጆቹ ከመኝታቸው ተነሥተው ወደ ትምህርት ቤት ለመ ሔድ ሻያቸውን ለመጠጣት ሲነሡ ፥ ገና ጨለማ በመ ሆኑ ሠራተኛዋ ለአጭር ጊዜም ቢሆን መብራቱን ትለ ኩሳለች ። ውርጭ ገብቷል ። የመጀመሪያው በረዶ ሲወ ርድ ለበረዶ ሸርተቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲወጣ ነጭ መሬት ፥ ነጭ ጣሪያ ማየት ያስደስታል ። በቀላሉና ያለ ችግር መተንፈስ መቻል የልጅነት ጊዜን ያስታውሳል ። ቅጠሎቻቸው በጤዛ የተሸፈኑ ግርማ ሞገስ ያላቸው ትል ልቅ አሮጌ ዛፎች እይታን ይማርካሉ ። ከሌሎች የበለጠ ልብን ያስደስታሉ ። በነዚህ ዛፎች ቅርንጫፎች ሥር ሲሆኑ ፥ የተራሮችና የባሕር ትዝታ እየመጣ አያስቸግርም ።

ጐሮቭ የሚኖረው በሞስኮ ሲሆን ፥ አሁን ወደ ሞስኮ የተመለሰውም በአንድ ውርጫም ቀን ነው ። ጸጉራም ካፖርቱን ለብሶ ፥ ወፍራም የእጅ ጓንቱን አጥልቆ ወደ

ፔትሮቭካ ጐዳና ሲወጣ ፥ ቅዳሜ ማታ ደግሞ የቤተክር ስቲያን ደወሎች ሲደወሉና ድምፃቸውን ሲሰማ ፥ በቅ ርቡ ያደረገውን ጉዞና የጐበኛቸውን ቦታዎች ውበትና ትዝታ ያደበዝዝበታል ። ቀስ በቀስ በሞስኮ ኑሮ ውስጥ ልምጠ ገባ ።

ፀመሠረቱ የሞስኮን ጋዜጦች አንብቤያቸው አላ ውቅም የሚለው ሰው በቀን የሦስት ጋዜጦች ደንበኛ አንባቢ ሆነ ። እንደገና በምግብ ቤቶች በክበቦች ፥ በግ ብዣዎችና በክብረ በዓል ማዕከል ተያስ ፤ ቱወጠረ ። እንዲሁም የታወቁ ጠበቆችና ክያኒያን ቤቱ መምጣታ ቸውና በሕክምና ክበብ ከአንድ ፕሮፌሰር ጐን ተቀ ምጠ ካርታ መጫወቱ አኩራራው ። ሕሊናውን አሳበ ጠው ።

በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እኖ ሠርጊዬቭና አሳዛኝ ከሆነው ፈገግታዋ ጋር ከሷ በፊት እንደ ነበሩት ሴቶች ሁሉ ግልጽ ያልሆነች ትዝታ ሆና እንደምትቀር ፥ ፀልፎ ፀልፎ ብቻ በሕልሙ ልትመጣበት እንደምት ችል አመነ ። አሁን ወሩም ወደ መገባደዱ ነው ። የክረ ምቱ ወቅት አጠንክሮ ይዞታል። የእና ሠርጊዬቭና ትዝታ ግን ፥ ልክ ትላንት እንደሆነ ሁሉ ቁልጭ ብሎ ይታየ ዋል ። ትዝታዎቹም በየዕለቱ የበለጠ እየተሰሙት ሔዱ። ልጆቹ ጥናታቸው ላይ ሆነው የሚፈጥሩት ንትርክ በሌ ሊቱ ጸጥታ ፀልፎ በጥናት ቤቱ ውስጥ ሲደርሰው ፥ ሙዚቃ ወይም ዘፈን ከሆቴሎች ሲሰማ ፥ ነፋሱ ከጭስ መውጫ ጋር ሲላተም የሚፈጥረው ድምፅ ያለፈውን ትዝታ በሙሉ ቀሰቀሰበት ። በመርከቡ መቆሚያ የነበረው ጠዋት ፥ በጭጋግ የተሸፈኑት የተራሮች አናቶች ፥

ከፊዎዶስያ የሚመጣው መርከብ ፥ ፍቅር የተሞላው መሳሳም ሁሉ በዐይነ ሕሊናው ታየው ። ተነሥቶ በክፍሉ ውስጥ ትዝታውን እያስታወሰ በፈገግታ ተሞልቶ ይንጐራደዳል ። ትዝታ ደግሞ ወደ ሕልም ይለወጣል ። ቀደም ሲል የሆነው በሐሳቡ ውስጥ አሁን ከሚሆነው ነገር ይደባለቅበታል ። እና ሠርጊዬቭና በሕልሙ ተለ ይታው አታውቅም ። ልክ እንደ ጥላው በሔደበት ሁሉ ተከትላው ፥ አጅባው ትሔዳለች ። ዐይኖቹን ሲጨፍን ቀደም ሲል ከነበረችበት ሁኔታ አምራና ደምቃ ፊቱ ቆማ ትታየዋለች ። ራሱንም ሲመለከት ቀደም ሲል ያልታ ከነበረው ሁኔታ የተሻለ መሆኑ ይታየዋል ። ማታ ማታ ከመጻሕፍት መደርደሪያው ውስጥ ፥ ከምድጃውና ከማዕዘኑ አቅጣጫ ሆና ትታየዋለች ። ትንፋሿና የቀሚሷ መንኮሻኮሽ ሁሉ ይሰማዋል ። በጐዳናዎቹ በዐይኑ ሴቶችን እየተከተለና እየማተረ እሷን የሚመስል እንዳለ ይፈልጋል ።

ይህን የሚሰማውን ስሜት ፥ ትዝታውን የሚያካፍለው ሰው ለማግኘት ከራኛ ፈለገ ። ስለ ፍቅሩ ቤቱ ውስጥ ሊያወራ አይችልም ። ታዲያ ፥ ይህን ጉዳይ ለማን ይንገረው ? ቤቱን ለሚከራዩት ተከራዮችና ባንክ ለሚሠሩት ጓደኞቹ ለመናገር አልፈለገም ። ለማን ይናገር ? ፍቅር ይሆን የሚሰማው ? ቀስፎ የሚይዝ ወይም ደራሲ በጥሩ ብዕሩ የሚስለው ዐይነት ፍቅር ይሆን ? ወይም ከእና ሠርጊዬቭና ጋር ያለው የሚያስደስት ግንኙነት ምን እንደሆነ የሚጠቁም ነገር ይኖር ይሆን ? ግልጽ ያልሆኑ አጠቃላይ ነገሮችን ስለ ሴቶችና ፍቅር እያነሣ ራሱን ከሚያዝናና በስተቀር የሚናገረው ነገር ለማንም

ግልጽ አይደለም ። ባለቤቱ ብቻ ቅንድቧን ወደ ላይና ወደ ታች እያነቃነቀች ፣

“ዲሚትሪ ፣ የጉረኛ ሚና መጫወት አያምርብህም” ትለዋለች ። አንድ ምሽት ከአንድ የመንግሥት ባለ ሥልጣን ከሆነ የካርታ ጓደኛው ጋር ሆኖ ከሕክምናው ክበብ ሲወጣ ፣ ደብቆት የቆየውን ሐሳቡን ከመግለጥ ሊቆጠብ ባለመቻሉ ፣

“በያልታ ያገኘሁዋትን አስደሳች ቆንጆ ልጅ ብታውቅ!” በማለት ሐሳቡን ገለጠለት ።

ባለሥልጣኑ የበረዶ ጋሪው ውስጥ ገብቶ ሊንቀ ሳቀስ ሲል ወደ ኋላው መለስ በማለት ፣

“ዲሚትሪ ዲሚትሪች !” በማለት ተጣራ ።

“አቤት ?”

“ታውቃለህ ፤ ትንሽ ሳትቀብጥ አትቀርም ።”

እነኚህ ቃላት በጣም ተራ ነገሮች ቢሆኑም ፣ ጐሮቭን ክፉኛ አናደዱት ፤ የተዋረደም መሰለው ። ምን ዐይነት ባሕርይ ፣ ምን ዐይነት ሕዝቦች ናቸው ! ምን ዐይነት የተበላሸ ምሽት ፣ አድካሚና ባዶ ቀን ነው ! የሚያበሽቅ ካርታ ጨዋታ ፣ ስግብግብነት ፣ ስካር ፣ ስለ አንድ ነገር ብቻ ተደጋጋሚ የማያባራ ወሬ ፣ የአንድ ሰው ጊዜና ኃይል ለማንም ሰው ጥቅም በማይሰጥ አንድን ነገር መልሶ ደግሞ ደጋግሞ በማውራት ብቻ የሚያልፍበት፣ ውጤት የሌለው ፣ ዕድገትን የሚያቆረቁዝ ደካማ ኑሮ ነው ። ማምለጫ ቦታ በሌለው በዕብዶች ወይም በወንጀለኞች መታጐሪያ ቦታ የመኖር ያህል ነው ።

ጕሮቭ ፣ ሌሊቱን ፀሙሉ ሳይተኛ እንደ በሸቀ በግ ደሩ ለሚቀጥለውም ቀን የማይልቀው የራስ ምታት ሕመም አተረፈ ። የሚቀጥሉትንም ጥቂት ቀኖች ጥሩ እንቅ ልፍ ባለማግኘቱ ተነሥቶ አልጋው ላይ በመቀመጥ ፣ በማሰብ ወይም ክፍል ውስጥ በመንጐራደድ ያሳልፈው ነበር ። ልጅቱና የሥራ ገበታው አሰልቺ ሆኑበት ። ከሰው ጋር ተገናኝቶ ለመጫወት ወይም ወጣ ብሎ ፀሙ ንሽራሸር ፍላጐት አጣ ።

የልደት በዓል ሲመጣ ፣ ስል አንድ ወጣት ሰው ጉዳይ ወደ ፒተርስበርግ ከተማ እንደሚሔድ ለባለቤቱ ነግሯት ልብሱን ከቶ ወደ "ሠ" ከተማ ሔደ ። ለምን ጉዳይ ? የሔደበትን ምክንያት እሱም ራሱ አያውቀ ውም ። የሚያውቀው እና ሠርጊዬቭናን ማየት ፣ ማና ገርና ከተቻለም ቀጠሮ መያዝ እንዳለበት ብቻ ነበር ።

"ሠ" ከተማ እንደ ደረሰ በሆቴሉ ውስጥ ያለውን ትልቅ ክፍል ተከራየ ። የክፍሉ ወለል በግራጫ ምን ጣፍ ከዳር እስከዳር ለብሷል ። በጠረጴዛው አናት ላይ አንድ ራስ የሌለው ጋላቢ ባርሜጣውን በእጁ እንደያዘ የሚያሳይ ቅርፅ ያለበት አንድ አሮጌ የቀለም ብልቃጥ ተቀምጧል ። የሆቴሉ አዳራሽ ሠራተኛ ጕሮቭ ለማወቅ የፈለገውን ነገር ሁሉ ነገረው ። ፎን ዳይዲ ሪትዝ በእስታሮ- ጉንቻርናያ ጉዳይ የራሱ የሆነ ቤት እንዳለው ፣ ቤቱ ከሆቴሉ ብዙም እንደማይርቅና በከፍ ተኛ ደረጃ በትልቅ ደስታና ምኞት እንደሚኖር ፣ ብዙ የሠረገላ ፈረሶች እንዳሉት ፣ የከተማው ሰው ሁሉ እን ደሚያውቀው መረጃ አገኘ ። ሠራተኛው የዳይድራት ዝን ስም "ድራይዲሪትዝ" ብሎ ነበር የጠራው ።

ጕሮቭ ፣ ወደ እስታሮ-ጕንቻርናዬ መንገድ በመ ሔድ የሚፈልገውን ቤት በቀላሉ አገኘው ። ከፊት ለፊቱ በረጃጅም አጥር ታጥሯል ። ለመከላከያ እንዲያመች ሹል ብረቶች በአጥሩ አናቶች ላይ ተሰክተዋል ።

"እንደዚህ ያለ አጥር ራሱ ሰውን ለማባረር የሚያስችል ነው" በማለት አሰበ ጕሮቭ ፣ የቤቱን አጥ ርና መስኮቶች በመመልከት ።

በዓል ስለሆነ የእና ሠርጊዬቭና ባለቤት እቤት እን ደሚገኝ ገመተ ። በመሆኑም በር አንኳኩቶ መጥራት እንደሚያስደነግጣትና እንደሚያስፈራራት ፣ ትክክልም እንደማይሆን አሰበ ። ማስታወሻም ቢሆን ባለቤቷ እጅ ሊወድቅ ስለሚችል አደጋ እንደሚያመጣ ታየው ። መል ካሙ ነገር ሊያያት የሚያስችለውን አጋጣሚና ፅድል መጠበቅ መሆኑን ተረዳ ። ዐይኖቹን ከቤቱ አጥር ላይ ሳይነቅል በመንገዱ ላይ እየተመላለሰ ፅድሉ የሚያ መጣልትን አጋጣሚ መጠበቅ ጀመረ ። እንደ ለማኝ የፅለት ምግቡን ፍለጋ ወደ ግቢው ሲገባ ውሾች ተጥ ናኮሉት ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ደግሞ በጣም ደካማ የፒ ያኖ ድምፅ ጆሮው ገባ ። እና ሠርጊዬቭና መሆን አለ ባት የምትጫወተው ። በድንገት የቤቱ የፊት በር ተከ ፍቶ እንዲት አሮጊት የሚያውቀው የሚመስል አንድ ነጭ ሶሎማ ውሻ አስከትለው ወጡ ። ጕሮቭ ውሻውን ለመጥራት ሞከረ ። ነገር ግን ፣ በድንጋጤ ልቡ በጣም በመምታቱ የውሻውን ስም እንኳን ማስታወስ አልቻ ለም ።

መንቀሳቀሱን ቀጠለ ። ቀስ በቀስ የግቢውን አጥር እየራቀ ሔደ ። እና ሠርጊዬቭና እንደ ረሳችው እንደ

ውም ምናልባት ሐሳቧን የሚከፍልላት ሌላ የወንድ ጓደኛ ሳታገኝ አትቀርም በማለት በቁጣ ለራሱ ለማስ ታወቅ ተዘጋጅቶ ነበር ። ከጠዋት እስከ ማታ እዚህ የተረገመ አጥር ውስጥ ተዘግታ ለምትቀመጥ ወጣት ሴት ከዚህ የበለጠ የተፈጥሮ አማራጭ ምን ሊኖራት ይችላል? ወደ ሆቴሉ ተመልሶ በክፍሉ ውስጥ በሶፋ ላይ ለጥቂት ጊዜ ተቀምጦ የሚያደርገው ጠፍቶት ሲያ ወላውል ራት አዝዞ ከበላ በኋላ ለረጅም ጊዜ ተኛ ።

"ምን መጥፎ ዕረፍት የሌለው ሥራ ነው" እያለ አሰበ ፡ ነቅቶ ወደ መስኮቱ እየተመለከተ ።"ጊዜው መሽ ቷል ። እንቅልፌን አሁን ጨረስኩ ፤ ሌሊቱን እንዴት ላሳልፈው ነው ?" እያለ ራሱን ጠየቀ ።

አልጋው ላይ ተነሥቶ ሲቀመጥ ፡ የለበሰውን ርካሽ ግራጫ የአልጋ ልብስ ሲያይ በጣም በመናደድ ራሱን ወቀሰ ። ርካሹ የአልጋ ልብስ የሆስፒታሎችን የብርድ ልብስ አስታወሰው ።

"አንተና ባለውሻዋ ወይዘሮ...ጅብደኞች ናችሁ ! ተመልከት ለድካምህ ያገኘኸውን ፍሬ" እያለ ራሱን ይወቅሳል ።

ጠዋት ባቡር ጣቢያው ሲደርስ በትልልቅ ፊደ ሎች የተጻፈው ማስታወቂያ 'ጌሻ' የተሰኘው ትርዒት ለመጀመሪያ ጊዜ በትያትር ቤቱ እንደሚታይ ያነበ በውን አስታውሶ ወደ ትያትር ቤቱ ሔደ ።

"የመጀመሪያውን ቀን ትርዕይት ለማየት እንደም ትሔድ ያለው ዕድል ከፍተኛ ነው" ሲል ለራሱ ተና ገረ ።

ትያትር ቤቱ ጢም ብሏል ። እውነተኛው የገጠር ትያትር ቤት ነበር ። መብራቶቹ በትምባሆ ጢስ ተጋ ርደዋል ። በሠገነቱ ላይ የተቀመጡት ደንበኞች ደግሞ ያለ ዕረፍት ይንቀሳቀሳሉ ። በመጀመሪያው ረድፍ መቀ መጫ የአካባቢው ምርጥ ለባሾች እጆቻቸውን ወደኋላ አጣምረው ቆመው የመጋረጃውን መከፈት ይጠባበቃሉ። በክብር መቀመጫው የመጀመሪያው ረድፍ የአገረ ገዢው ሴት ልጅ ጸጉራማ የአንገት ልብሷን ደርባ ተቀ ምጣለች ። አገረ ገዢው እራሱ በክብር መቀመጫው መጋረጃ ሥር ተደብቆ እጁ ብቻ ይታያል ። መጋረጃው ሲከፈት አርኬስትራው ሙዚቃ አሰማ ። ተመልካቹ እየ ገባ መቀመጫውን ሲይዝ ጮርቃ በጉጉት በተመልካቹ ላይ ዐይኖቹ ተንቀዋለሉ ።

እና ሠርጊዬቭናም መጥታለች ። በሦስተኛው ረድፍ መቀመጫ ተቀምጣለች ። ጮሮቭ ሲያያት ልቡ የቆመ መሰለው ። ዓለም ፥ ለሱ ቅርብና ውድ ፥ ለደስታው ምንጭ የሆነ ነገር ብቻ እንዳቀፈች ከመቅጽበት ተገለ ጠለት ። ይህች በሰዎች ስብስብ ውስጥ የተዋጠች ትንሽ፥ በምንም ዐይነት ልዩ ፍጥረት ሆና የሰውን መንፈስ የማትስብ ፥ በእጅጅ አስቀያሚ የሆነ አቅርቦ የሚያሳይ መነጽር የያዘች ሴት አሁን ሕይወቱን ሞላችው ፤ ጎዘኑ ፥ ደስታውና ሌላም የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ሆኖ ታየ ችው ። ከአርኬስትራው የሚወጣው ድምፅ እሽሩሩ እያ ለው እንዴት ውብና ቆንጆ እንደ ሆነች...ማሰብና ማለም ጀመረ ።

እትና ሠርጊዬቭና ጋር አንድ ረጅም ፥ክብ ትከሻና ሽከን ጢም ያለው ወጣት ሰው አለ ። አጠገቧ በተቀ

መጠ ቁጥር ጐንበስ እያለ እጅ ይነሣታል ። እንዲሁም ሳያቋርጥ በተደጋጋሚ እጅ የሚነሣው ሰው ያለ ይመ ስላል ። ያልታ ላይ በምሬት "ተላላኪ" ብላ የጠራችው ይህ ሰው ባሷ ሳይሆን አይቀርም ። በእርግጥም በዚህ ትልቅ ሰውነት ላይ የበታችነት ወይም የአድርባይነት ሁኔታ ይነበባል ። ጣፋጭ ፈገግታ ያሳያል ። በኩቱ ዶረት ላይ የተሰካው የሆነ የሳይንስ ማኅበር አባልነት ምልክት የሞቱል ቤት ተላላኪ መለያ ቁጥር ይመስል በታል ።

በመጀመሪያው የዕረፍት ጊዜ ባሷ ሲጋራ ለማ ጨስ ጥሏት ወጣ ። ጐሮቭ መቀመጫውን ጥሎ ወደ እርሷ በመሔድ እየተንቀጠቀጠ የግዴታ ፈገግታ እያ ሳየ ፥ "እንደ ምነሽ?" አላት ።

ገልመጥ ብላ ስታየው ክው ብላ ደነገጠች ፤ ዐመዷ ቡን አለ ። ለማረጋገጥ እንደገና በፍራቻ ተመለከተችው ወይኖቿን ለማመን አቅቷት በድንጋጤ እንዳትወድቅ እየታገለች በአንድ እጅዋ የያዘችውን መነጥርና ማራገ ቢያ መጭጭ ብላ ያዘች ። ሁለቱም አንድ ቃል አል ተነፈሱም ። በተቀመጠችበት ቀረች ። እሱም መደንገ ጧን በማወቁ ደፍሮ አጠገቧ አልተቀመጠም ። የቫዮሊ ንና የዋሽንት ድምፅ ይሰማል ። መቀመጫው ላይ ያለው ሰው ሁሉ እነሱን ብቻ የሚመለከት ስለ መሰላቸው ተደናግጠዋል ። በመጨረሻም አፈፍ ብላ በመነሣት ወደ አንዱ መውጫ አመራች ። እሱም ተከትሏት በመ ውጣት ኮሪደር ለኮሪደር ፥ ደረጃ ለደረጃ ዓላማ ቢስ በሆነ መንገድ ተዘዋወሩ ። ሲዘዋወሩ ሁሉ የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች ፥ የሁለተኛ ደረጃ መምህራንና የመንግሥት

ሠራተኞች ሁሉም በደረታቸው ላይ ባጅ የለጠፉ እያ ለፏቸው ይሔዳሉ ። የወይዛዝርት ካፖርቶች በመስቀ ያው ላይ ተሰቅለዋል ። ጠንከር ያለ የሲጋራ ሽታ ያዘለ የንፋስ ሽውታ ይነፍሳል ። ይህን የተመለከተ ልቡ በኃ ይል የሚመታው ጐሮቭ እንዲህ ሲል አሰበ ፤ "ይህ ሁሉ ሰውና አርኬስትራው ለምንድነው የተሰበሰቡ በት ?...." ወዲያው ሐሳቡ እና ሠርጊዬቭናን ባቡር ጣቢያ ድረስ ሔዶ የሸኘበትን አስታወሰ ። በዚያን ምሽት ሁለተኛ እንደማይገናኙ ፥ ሁሉም ነገር እንዳለቀና እንዳ በቃ ለራሱ ተናግሮ ነበር ። "እዙንስ መጨረሻው ምን ያህል እሩቅ ይሆን !"

አንድ ጠባብ ደረጃ በላዩ ላይ ፥ "ለከፍተኛ ባለሥ ልጣኖች" የሚል የተለጠፈበት አጠገብ ስትደርስ ቆመች ።

"እንዴት አስደነገጥከኝ !" አለች በድንጋጤ ዐመዷ ቡን እንዳለ በከባዱ እየተነፈሰች ። "እንዴት አስፈራ ኸኝ ! በድንጋጤ በድን ሆኜአለሁ ለምን መጣህ ? ለምን ?"

"ግን ፥ እና "አለ በቀስታና በቸኮለ ድምፅ ። "ግን ፥ እና.....ልትረጂኝ ሞክሪ..... እባክሽ ተረጂልኝ...."

በፍርሃት ፥ በልመናና በፍቅር ዐይን ገልመጥ ብላ አየችው ። ቀስ ብላም መልኩና ገጽታው በሐሳቧ ተቀ ርጾ እንዲቀር የምትፈልግ ይመስል ትክ ብላ ተመለ ከተችው ።

የእሱን ንግግር በመተው ፥ "በጣም ደስተኛ አልነበ ርኩም" በማለት ንግግሯን ቀጥላ ፥ "ካንተ በስተቀር

ሌላ የማስበው ነገር አልነበረም ። የኖርኩት ስላንተ ሳስብ ነው ። ለመርሳት ስሞክር ነበር—ለምን ፥ እንዴ ለምን መጣህ ?'' አለችው ።

ከብላያቸው ባለው ወለል ላይ ሁለት ተማሪዎች ሲጋራ እያጨሱ ወደታች ይመለከታሉ ። ጐሮቭ ግን ግድ አልነበረውም ። እና ሠርጊዬቭናን ወደ እርሱ በማ ስጠጋት ፊቷን ፥ ከንፈሯንና እጆቿን መሳም ጀመረ ።

''ምን እያደረግህ ነው ፥ እንዴ ፥ ምን ማድረግህ ነው ?'' አለችው በድንጋጤ ወደ ኋላዋ እየሸሸች ፥''ሁለ ታችንም አብደናል ። በዛሬው ሌሊት ተመልሰህ እንድ ትሔድ.... እንድትሔድ ቅዱስ በሆነው ነገር ሁሉ እለምንሃለሁ.... አንድ ሰው እየመጣ ነው'' አለችው ።

አንድ ሰው ፥ ወደ ላይ ደረጃውን እየወጣ ነበር ። ''መሔድ አለብህ'' አለች እና ሠርጊዬቭና በሹክሹ ክታ ። ''ትሰማኛለህ ፥ ዲሚትሪ ዲሚትሪች ? ሞስኮ ወደ አንተ እመጣለሁኝ ። ደስተኛ አልነበርኩም ። አሁንም ደስተኛ አይደለሁም—ፈጽሞ ! የበለጠ እንድሠቃይ አታ ድርገኝ ! እምልልሃለሁ ! ሞስኮ እመጣለሁኝ ። በል አሁን መለያየት አለብን ! ተወዳጁ ፥ ርኅሩኅና ደጉ ጓደ ኛዬ ፥ ውድ ወዳጄ ፥ በቃ አሁን መለያየት አለብን'' አለ ችው ። እጁን ጠንከር አድርጋ ጨብጣ ወደ ኋላዋ ደጋ ግማ እየተገላመጠች ደረጃውን ወረደች ። በእርግጥም ዐይኖቿ የደስተኛ ሰው አይመስሉም ። ጐሮቭ ለትንሽ ጊዜ በነበረበት ቦታ ጸጥ ብሎ ቆመ ። አካባቢው ጸጥ ሲል ካፖርቱን ከአስቀመጠበት አንሥቶ ከትያትር ቤቱ ወጥቶ ሔደ ።

ከዚያም እና ሠርጊዮቭና ልታየው ወደ ሞስኮ መሔድ ጀመረች ። በሁለት ወይም በሦስት ወር አንድ ጊዜ ስለ ሴቶች ህመም እነጋግራለሁ እያለች ለባሏ በመንገር ከ "ሠ" ከተማ ወደ ሞስኮ ትሔዳለች ።ባለ ቤቷ ያምናታልም ፤ አያምናትምም ። በሞስኮ የምትቀመጠው በእስላቪያንስኪ ባዛር ሲሆን ፥ ሞስኮ እንደ ደረሰች ወዲያው አንድ ቀይ ቆብ የሚደፋ መልዕክተኛ ወደ ጐሮቭ ትልካለች ። ጐሮቭም እየሔደ ያገኛታል ። ስለዚህ ጉዳይ በሞስኮ ከተማ የሚያውቅ አንድም ሰው አልነበረም ።

በክረምቱ ወራት አንድ ጠዋት እንደ ተለመደው ሊያያት ሔደ ፤ (መልዕክተኛው ባለፈው ዕለት ምሽት ሔዶ እቤት አላገኘውም ነበር ።) የልጁም ትምህርት ቤት በመንገዱ ላይ ስለነበር ፥ በዚያው እግረ መንገዱን ልጁን ሊያደርሳት ነበር ።

"ሙቀቱ ከዜሮ በላይ ሦስት ዲግሪ ነው" አላት ጐሮቭ ለልጁ ። "እንዲህም ሆኖ በረዶ ይወርዳል ። አየሽ ምድር አጠገብ ከዜሮ በላይ ነው ። በላይኛው አየር ንጥፍጣፍ ውስጥ የሙቀቱ መጠን የተለየ ይሆናል ።"

"ለምንድነው በክረምት ወራት የሰማይ ጉርምርምታ ወይም ነጐድጓድ የሌለው አባባ ?" ስትል ልጁ ትጠይቀዋለች ።

ይህንንም ገለጸላት ። እየተናገረ እያለ የሚሔድበት ወደ ራንዶቩ የተለየ ዓላማ እንዳለው ፥ ይህንን ደግሞ ማንም ሰው ማወቅ የሌለበት መሆኑን ራሱን በራሱ አስ

ታወሰ ። የሚኖረው ሁለት መልክ ያለው ሕይወት ነው ። አንዱ በግልጽ ማንም እያየው እንደ ጓደኞቹ ቤልምድ የሚያካሒደው የእውነትና ሐሰት ኑሮ ሲሆን ፣ ሌላው ፀድበቅ የሚፈሰው የምስጢር ሕይወት ነው ።

አንድ እንግዳ ቢሆነ ምክንያት ምናልባትም ደን ገተኛ ክሆነ ተከታታይ አጋጣሚ በሕይወቱ ውስጥ የሚ ያደርጋቸው እውነተኛ ነገሮች ሁሉ ጠቃሚ ፣ አስፈላጊ፣ አስደሳች ፣ ፊሱን ሲያታልል በእርግጥ ሐቀኛ ሆኖ የሚፈጽማቸው ፀአጠቃላይ አብነቱን የሚገልጡ ነገ ሮች ሁሉ የሚካሔዱት ድብቅ በሆነ ምሥጢራዊ ሕይ ወቱ ነው ። በሌላው በኩል ማንኛውም በጉልህ የሚ ያደርገውን እንቅስቃሴ - የባንክ ሥራው ፣ በክበብ የሚያደርጋቸው ውይይቶች ፣ ‘‘ዝቅተኛ ዘርፎች’’የሚ ለው አነጋገሩ ፣ ከባለቤቱ ጋር የሚገኝባቸው ዓመታዊ በዓላት- ላይ ላዩን ያለ ፣ ምሥጢራዊ ሕይወቱን የሚሸ ፍንበት የውሸት ሕይወቱ ነው ። ሌላውንም ሰው በራሱ መመዘኛ ይለካ ጀመር ። እውነተኛውን ፣ ሐቀኛውንና ተጨባጩን የሚያየውን ሁሉ ማመን ወይም መቀበል በመተው የእያንዳንዱ ሰው አስደሳች ሕይወት በጨለማ በምሥጢር የሚካሔድ ነው ብሎ ተቀበለ ። እያንዳ ንዱ ግላዊ ኑሮና ሕይወት በምሥጢር ዙሪያ የሚሽከረ ከር በመሆኑ ነው ፣ ሁሉም ሥልጡን ሰዎች ስለ ሰው ምሥጢር መጠበቅና መከበር አጠንክረው የሚከራክ ሩት ።

ጐሮቭ ፣ ልጁን ትምህርት ቤቷ በር ላይ ትቶ ወደ እስላዘያንስኪ ባዛር አመራ ። እንደ ደረሰም ካፖርቱን በኮሪደሩ አንድ መስቀያ ላይ ሰቅሎ ደረጃውን በመው

ጣት እንድ ቦር በዝግታ አንኳኳ ። እና ሠርጊዮቭና ጕሮቭ በጣም የሚወደውን ግራጫ ልብስ ለብሳ ፣ በጉ ዦው ተዳክማና እሱን በመጠበቅ ልቧ ተሰቅሎ ካለፈው ምሽት ጀምሮ ቅጠብቀው ነበር ። ፊቷ ቢገረጣና በፊ ነግታ ባትቀበለውም ፣ ገና በሩን ጨርሶ ከመግባቱ በፊት እቅፉ ውስጥ ወደቀች ። ለዓመታት ያልተገናኙ ይመስል ለረጅም ጊዜ ተሳሳሙ ።

“ታዲያስ እንደ ምነሽ?” ሲል ጠየቃት ። “አዲስ ነገር አል?”

“ቆይ እነግርሃለሁ .....አልቻልኩም ....”

ስለምታለቅስ መናገር አልቻለችም ። ከርሱ ራቅ ብማለት በመሐረቧ ዐይኖቿን ዳበሰች ።

“ለቅሶዋን እስክታበቃ ልጠብቃት” ብሎ አጠ ገቡ በነበረው ወንበር ላይ ተቀመጠ ።

ሻይ እንዲመጣለት ደወል ደወለ ። ሻዩን እየጠጣ ጥቂት ጊዜ ቢያልፍም ፣ እሷ ፊቷን ወደ መስኮቱ መልሳ በነበረችበት ቆማለች ። የምታለቅሰው በስሜት ፣ ስለ መራራውና አሳዛኙ ሕይወታቸው ሕሊናዋ እየኮረኮራት ነበር ። የሚገናኙት በምሥጢር ሌባ ይመስል ከሕዝብ ተደብቀው ነው። የተበላሸ ሕይወት አይደለም የሚኖሩት?

“አታልቅሺ” አላት ።

ፍቅራቸው ቶሎ እንደማያልቅ በዚህ ጊዜ ያልታል ብሎ ሊናገር ወይም ሊገምት የሚችል ሰው እንደማይ ኖር ለጕሮቭ ግልጥ ነበር ። እና ሠርጊዮቭና ቀደም

ሲል ከምትወደው የበለጠ እየወደደችውና እያመለከ ችው በመሐዲ አንድ ቀን ፍቅራቸው ማለቁ እንደማ ይቀር መናገሩ አስፈላጊ አልነበረም ። ቢነግራትም አታ ምነውም ነበር ።

ከተቀመጠበት ተነሥቶ ወደ እርሷ በመጠጋት ትከ ሻዋን አቅፎ በለሰለሰ ቃላት ሊያሞካሻት ጠጋ ሲል ፥ በድንገት ምስሉን በመስተዋት ውስጥ ይመለከተዋል።

ጸጉሩ ወደ መሸበቱ ነው ። በአለፉት ጥቂት ዓመ ታት ውስጥ ይህን ያህል ማርጀቱ አስደነቀው ፤ ገረመው፤ እጆቹ ያረፉበት ትከሻ ይሞቃል ፤ ይንቀጠቀጣል ። ለዚህ ሕይወት ፥ ትኩስና ውብ ለሆነ ሕይወት በቅርቡ እንደ እርሱ ለሚከስምና ለሚጎብጥ ሕይወት አዘነ ። ለምንድን ነው እንደዚህ የምትወደው ? ሴቶች ሁልጊዜ በእውን ካለው እሱነቱ የተለየ መሆኑን ያምናሉ ። የሚወዱት እሱን ሳይሆን በሐሳባቸው የቀረፁትን በውስጡ ያለ ውን ፥ በሕይወታቸው በሙሉ በጉጉት የፈለጉትን ሰው ነው ። በመጨረሻ ስሕተታቸውን ሲገነዘቡም ፥ ቀደም ሲል እንደ ነበረው መውደዳቸውን ይቀጥላሉ ። ማንኛቸ ውም ግን ፥ ከእርሱ ጋር ደስተኞች አልነበሩም ። በማ ከታተል ብዙ ሴቶችን ተራ በተራ ዐወቀ ። ያፈቅራል ፤ ይለያያል ። ወድዶ ግን አያውቅም ። በሕይወታቸው ውስጥ ምንም ያልሆኑትና ያላደረጉት ነገር የለም ፤ ፍቅር ግን አልነበረም ።

ዕድሜው ሲገፋና ጸጉሩ ሲሸበት ፥ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕይወቱ እውነተኛና ሐቀኛ ፍቅር የያዘው አሁን ብቻ ነው ። እሱና እና ሠርጊዬቭና በጣም ቅርብ እንደሆኑ ሰዎች ፥ እንደ ባልና ሚስት በጣም እንደሚ

ዋደዱ ወዳጆች ፍቅራቸው ጸና ። አንዳቸው ለአንዳቸው የተፈጠሩ መስሎ ታያቸው ። እርሱ ለምን ሚስት እንዳለው ፣ እሷም ለምን ባል እንዳላት ፈጽሞ ሊገባቸው አልቻለም ። ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ ተይዘው በተለያዩ ጐጆ የተከተቱ ሴትና ወንድ ወፎች ይመስላሉ ። አሁን ያሳቸው ፍቅር ሁለቱንም ስለ ለወጣቸው ፣ ቀደም ሲልና አሁንም ሁለቱም ያፍሩበት ስለ ነበረው አድራጐታቸው ይቅርታ ተደራረጉ ።

ቀደም ሲል ጎዘንና ትካዜ ሲሰማው ፣ መጀመሪያ በአእምሮው በሚፈጠረው አስተሳሰብ ይጽናና ነበር ። አሁን ግን ፣ በዚህ አድራጎቱ በጣም ጎዘንና ጸጸት ተሰማው ። ከዚህ ዐይነቱ ሁኔታ በመራቅ ሐቀኛና ደግ ለመሆን ፈለገ ።

“ፍቅሬ ፣ ለቅሶሽን አቁሚ” አላት ። “በቂ አልቅሰሻል ፤ አሁን አቁሚና ....ምን ማድረግ እንዳለብን እያሰብን እንነጋገር ። ”

ከዚያም ስላሉበት ሁኔታ መደበቁ ፣ ማታለሉ ፣ በተለያየ ቦታ መኖሩ ፣ ሳይገናኙ ረዥም ጊዜ መቆየቱን አንሥተው እንዴት ይህንን አስፈላጊ ነገር ሊያስወግዱ እንደሚችሉ በረጅሙ ተወያዩ ። ይህንን የማይፈለግ፣ የማይቻል ሰንሰለት እንዴት ያስወግዱት ይሆን ?

“እንዴት ፣ እንዴት?” በማለት ራሱን ይዞ ደጋግሞ ጠየቀ ። “እንዴት ?”

ውሳኔ ላይ ለመድረስ በጣም ጥቂት የቀራቸውና ከዚያም አዲስ ፣ ቆንጆና ሸጋ ሕይወት የሚጀምሩ መስሎ ታያቸው ። ሆኖም መጨረሻው በጣም ሩቅ መሆኑን ሁለቱም ተገነዘቡ ። ከባዱና በጣም ውስብስብ የሆነው ክፍል ገና መጀመሩ ነበር ።

ሙ ሽ ራ ዋ

ክምሽቱ ሦስት ሰዓት ሆኖ ሙሉ ጨረቃ አትክ
ልት ቦታው ላይ እያበራች ነው ። የሹሚን ቤተሰብ
ሴት አያት በሆኑት በማርፋ ሚካሂሎቭና ታዞ የነበረው
የጸሎት ሥነ ሥርዓት ተካሒዶ ገና ማብቃቱ ነው ።
ሥነ ሥርዓቱ እንዳበቃ ለአንድ ደቂቃ ወደ አትክልቱ
ቦታ ብቅ ብላ የነበረችው ናድያ ቀዝቃዛ ምግብ ፥ ምግብ
ቤቱ ውስጥ ጠረጴዛ ላይ ሲደረደር ፥ አያቷ የሐር ልብ
ሳቸውን ለብሰው በምግቡ ጠረጴዛ አካባቢ ከወዲያ
ወዲህ ሲሉ ፥ የካቴድራሉ ቄስ ፥ አባ አንድሬ ፥ በመስ
ኮት በኩል በሰው ሠራሹ ብርሃን ስትታይ በጣም ወጣት
መስላ ከምትታየው ከእናቷ ፥ ከኒና ኢቫኖቭና ጋር ሲጫ
ወቱ ትመለከታለች ።

የአትክልቱ ቦታ ቀዝቃዛና ጸጥ ያለ ከመሆኑም
በላይ ፥ ጥቁር ጥላዎች በወለሉ ላይ ጠልተዋል ። ከሩቅ
ቦታ ፥ ምናልባትም ከከተማው ውጭ ይመስላል ፤ የእን
ቁራሪቶች ጩኸት ይሰማል ። የግንቦት ስሜት ፥ አስደሳቹ
የግንቦት ወር ስሜት በአየሩ ውስጥ ይነፍሳል ። አንድ
ሰው ትኩሱን አየር ወደ ውስጥ በመሳብ ፥ ከከተማው
ባሻገር ራቅ ብሎ ፥ ከሰማዩ በታች ፥ ከዛፎቹ አናት በላይ
በመስኩቱና በጫካዎቹ ውስጥ ፥ የሚታየው ሁኔታ
ምሥጢራዊ ፥ አስደሳች ፥ ውድና ቅዱስ ፥ ቃጨያተኛች
በሙሉ እንዳይገቡ የሚከለክሉበት ፥ ጸደይ የራሷን ሕይ

ወት ልትጀምር ዝግጁ መሆኗን ያሳስባል ። ከደስታ ብዛት ለመጮህም ታስቃጣለች ።

ናዲያ ፣ ዛሬ ኻያ ሦስት ዓመት ሆኗታል ። ፅድሜዋ ፀሥራ ስድስቅ ዓመት ከሆናት ጊዜ ጀምሮ ለማግባት ጽኑ ፍላጎት ነበራት ። አሁን በመጨረሻ ምግብ ቤት ውስጥ ክቆመው ወጣት ፣ አንድሬ አንድሬች ጋር ለመጋባት ተጫጭታለች ፤ ትወደዋለች ። ሠርጉም ለሐምሌ ሰባት ቀን ተቆርጧል ። ግን ደስታ አይሰማትም ። ጥሩ እንቅ ልፍ አይወስዳትም ። ብሩህ ገጽታዋም ሸሽቷታል ። ክፍት ከሆነው ከምድር ቤቱ ማዕድ ቤት መስኮቶች በኩል የሥራ መብዛት እንቅስቃሴና የቢላዋ መፋጨት ድምፅ ይሰማል ። ወደፊትና ወደኋላ ተካፋች የሆነው የማዕድ ቤቱ በርም ሳያቋርጥ ወደ ውስጥና ወደውጭ ይላተማል ። የዶሮ ጥብስ ሽታና የፍራፍሬ መዓዛ ያውዳል ። ለሚመለከት ሰው ነገሮች ሁሉ ሳይለወጡ ለዘ ለዓለሙ እንደዚህ የሚቀጥሉ መስለው ይታያሉ ።

አንድ ሰው ፣ ከቤት ውስጥ ወጥቶ በረንዳው ላይ ቆመ ። ክዐሥር ቀን በፊት ሰው ለመጠየቅ ክሞስኮ የመጣው ሰዎች ሳሻ የሚሉት አሌክሳንደር ቲሞፌች ነበር። ለናድያ አያት የሩቅ ዝምድና ያላትና ከረጅም ጊዜ በፊት ባለቤቷ የሞተባት ደሃ ፣ ትንሽ ፣ ቀላልና ደካማ የሆነችው ፣ ማርያ ፔትሮቭና ዕርዳታ ለመጠየቅ ትመጣ ነበር ። ሳሻ የሚባል ልጅ አላት ። ሰዎቹ ጥሩ ሠዓሊ ነው ይሉታል ። ከዚያም እናቱ ስለ ሞተች ፣ የናድያ አያት ለጽድቅ ብለው ሞስኮ በሚገኘው ኮሚሳሮቭ ትምህርት ቤት አስገቡት ። ከአንድ ወይም ክሁለት ዓመት በኋላ ወደ ኪነጥበብ ትምህርት ቤት ተዛውሮ ለአንድ ፀሥራ

አምስት ዓመታት ከቆየ በኋላ የመጨረሻ ፈተናውን በአርኪቴክቸር ወሰደ ። በመሀንዲስነት ባይሠራም ፣ በአንድ የሞስኮ ከተማ ማተሚያ ድርጅት ውስጥ ተቀ ጠረ ። ታማሚ በመሆኑ ለማረፍና ለማገገም በክረምት ወራት ይመጣ ነበር ። እስከ አንገቱ የሚቆለፍ ኮትና ዙሪያውን የተቀደደ አስቀያሚ የሸራ ሱሪ ይለብ ሳል ። ሸሚዙም አይተኮስም ። በአጠቃላይ ንጽሕና የጐደለው ነው ። ሰውነቱ የተጐዳ ፣ ትልልቅ ዐይኖቹና ረጃጅም የሆኑ አጥንታም ጣቶች ፣ ጺም ፣ ጠቆር ያለ ቆዳ ያለው ቢሆንም ፣ መልከ መልካም ነው ። የሹሚን ስን ቤተሰብ የሚያየው እንደ ራሱ ቤተሰብ ነው ። በዚህም ቤተሰብ ውስጥ ጨርሶ ባይተዋርነት አይሰማ ውም ። ለዕረፍት ሲመጣ የሚተኛበት ክፍል የሳሻ ክፍል እየተባለ ይጠራል ።

ከቆመበት ከበረንዳው ሆኖ ናድያን ስለ ተመለ ከታት ወደ እርሷ ሔደ ።

“እዚህ ይሻላል” አላት ።

“በጣም ጥሩ ነው ፣ እስከ መጸው ድረስ መቆየት ይኖርብሃል ።”

“አዎን ፣ ዐውቃለሁ ፤ መቆየት ያለብኝ ይመስለ ኛል ። እስከ መስከረም ከእናንተ ጋር እቆያለሁ ።” ምንም የሚያሥቅ ምክንያት ሳይኖረው እየሳቀ ጐኗ ተቀመጠ ። “እዚህ ቆሜ እማዬን እየተመለከትኩ ነበር” አለች ናድያ ። “ከዚህ ሲያዩዋት ገና ወጣት ትመስ ላለች ። እማዬ ድክመት እንዳለባት አውቃለሁ” በማለት

ከትንሽ ዝምታ በኋላ ትቀጥልና ፥ "ቢሆንም የምታስደንቅ ሴት ናት ። "

"እውን በጣም ጥሩ ናት" በማለት ሳሻ ተስማማ። "በእርሷ መንገድ እናትሽ በእርግጥ በጣም ጥሩና ደግ ናት ፤ ግን ...እንዴት ልበለው ? ዛሬ ጠዋት ወደ ማዕድ ቤት ስገባ አራት አሽከሮቻችሁ ወለሉ ላይ ተኝተው አየሁ ። አልጋ የላቸውም ፤ ቡቲቱ ላይ ነው የሚተኙት ፤ መጥፎ ሽታ ፥ ትሁዋን በልበላ...ሞልቷል ። ልክ ከኻያ ዓመት በፊት እንደ ነበረው ነው ፤ ምንም ለውጥ የለም። አያትሽ በዚህ አይወቀሱም ፤ አሮጊት ናቸው ። እናትሽ ግን ከፈረንሣይ ትምህርቷን የአማተር ቲያትር ችሎታዋ ...የተሻለ ነገር ለማድረግ የሚያዳግታት አይመስለኝም ።"

ሳሻ ፥ ሲናገር አጥንት ብቻ የሆኑትን ሁለት ጣቶቹን ወደ አድማጩ ማመልከት ይወዳል ።

"እዚህ ስመጣ ሁሉም ነገር እንግዳ ይሆንብኛል" በማለት ቀጠለ ። "እንደዚህ ያለ ነገር አለመድኩም ። ስለ እግዚአብሔር ፥ ማንም ምንም አያደርግም እዚህ! እናትሽ ምንም አትሠራም ፤ እንደ አንድ ትልቅ ሠፋኒት ትንሸራሸራለች ። አያትሽም ሆነች አንቺ ራስሽ ምንም አታደርጉም ። እጮኛሽ አንድሬ አንድሬችም ምንም አይሠራም ፤ አያደርግም ።"

ሳሻ ፥ የተናገረውን ያለፈው ዓመትም ሰምታዋለች ፤ ካለፈው ዓመት በፊት የተናገረው መሆኑን አስታውሳ ፥ የሳሻ አእምሮ የሚሠራው በዚህ መንገድ ብቻ መሆኑን ዐወቀች ። በሚናገረው ነገር የተደሰተችበት ጊዜ ቢኖርም ፥ ዛሬ ግን በሆነ ምክንያት አስቆጥቷታል ።

"ያፈጀ ፥ የቆየ ነገር ነው የምትነግረኝ ። መስማቱ ራሱ ይሰለቸኛል ፤ ያሳምመኛል" አለችው ከመቀመጫዋ እየተነሣች ። "አዲስ ነገር ማሰብ አትችልም ?"

እሱም ሥቆ ከመቀመጫው በመነሣት ሁለቱም ወደ ቤት አመሩ ። ከጐኑ ሆና ስትሔድ መልከ መልካም፥ ረጅም ፥ ቀጭንና በጥሩ ሁኔታ የለበሰችና ጤናማ ትመስላለች ። ይህ ሁኔታሞ ስለሚገባት ታዝንልትና ይቅርታ ወደ መጠየቅ ገደማ ትደርሳለች ።

"ብሠ የማያስፈልግ ነገር ትናገራለህ አለችው ። "ተመልከት አሁን ፥ ስለ እጮኛዬ ፥ ስለእኔ አንድሬ ፥ የተናገርከውን በእርግጥ ስለእርሱ ምንም የምታውቀው ነገር የለም!"

"የኔ አንድሬ ... ያንቺን አንድሬ ተይው ! እኔ ብወጣትነትሽ ነው የማዝነው ። "

ወደ ምግብ ቤት ሲደርሱ ሰው ሁሉ ለእራት እየተቀመጠ ነበር ። የናድያ አያት ፥ ወይም ቤተሰቡ ፥ በሞላ እንደሚጠላቸው ፥ ቦርጫም ፥ ሰፊ ሽፋሽፍትና ጺም ያላቸው ሲሆኑ ፥ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ያወራሉ ። ከአነጋገራቸውና ከድምፃቸው የቤተሰቡ መሪ መሆናቸውን ለማወቅ ይቻላል ። በገቢያው ቦታ በረድፍ የተሠሩ ማረፊያ ቤቶች አሏቸው ። አሮጌው ቤት ከነአትክልት ቦታው የርሳቸው ሲሆን ፥ በወትር ጠዋት እግዚአብሔር ከጥፋትና ከክስረት እንዲያድናቸው እያልቀሱ ይጸልያሉ ። የልጃቸው ሚስት ፥ የናድያ እናት ፥ ኒና ኢቫኖቭና ፥ ሐር የመሰለ ወርቅማ ጸጉር ያላት ፥ አንጀቷን ጥፍር አድርጋ ፀሥራ ፥ በሁሉም ጣቶቿ የአ

ልማዝ ቀለበቶች አጥልቃ መነጽር አድርጋለች ። ሲያዩ ዋቸው ሁል ጊዜ አንድ አሥቂኝ ነገር ለመወርወር የተ ዘጋጁ የሚመስሉት ጥርሳቸው የረገፈው ፥ ቀጭኑ አባ አንድሬና እንደ ተዋናይ ወይም ሠዓሊ ሲበጠር ደረቅ የሚያወጣ ጸጉር ያለው መልከ መልካምና ደልዳላው የናድያ እጮኛ ሆነው ስለ ሂፕኖቲዝም ይጫወቱ ነበር ።

"በአንድ ሳምንት ውስጥ ሰውነትህ ይመለሳል ፤ ትወፍራለህ" አሉት አያት ሳሻን ። " ብዙ መብላት ግን አለብህ ። እስቲ ራስህን ተመልከተው!" ብለው በረ ጅሙ ተነፈሱ ። "በጣም ታስፈራለህ ። የተሞላቀቀ ልጅ ትመስላለህ ። "

"ቅጥ ባጣ ሕይወት ቁም ነገሩን ሁሉ አጠፉ" አሉ አባ አንድሬ ጣልቃ በመግባት ፥ ቃላቱን ቀስ ብለው ከአፉቸው እያወጡ ። " ይባስ ብሎ ዓሣማ እንዲያግድ ወደ መስክ ተላከ ። "

"ሽማግሌ አባቴን እወደዋለሁ" አለ አንድሬ አን ድሪች የአባቱን ትከሻ ቸብ ቸብ እያደረገ በእጁ ። "ውድ ሽማግሌ ! መልካሙ ሽማግሌ!"

ማንም ምንም አልተናገረም ። ሳሻ በድንገት በሣቅ ፊንድቶ እየሣቀ መሐረቡን አውጥቶ አፉን ለመዝጋት ሞከረ ።

"ታዲያ በዚህ ሰውን በሐሳብ የማስተኛት (ሂፕኖ ቲዝም) ችሎታ ታሞኚያለሽ ማለት ነዋ !" አሏት አባ አንድሬ ኒና ኢቫኖቭናን ።

"በትክክል እንኳን አምንበታለሁ ለማለት ያስቸ ግረኛል" ስትል ኒና ኢቫኖቭና መለሰች ፣ ፊቷን በማ ኮሳተር ። "ነገር ግን በተፈጥሮ ውስጥ ብዙ ምሥጢ ራዊ ፣ ግልጽ ያልሆኑና የማይታወቁ ነገሮች እንዳሉ እገነዘባለሁ ።"

"እምነት ምሥጢራዊ የምንለውን ነገር ወይም አመ ለካከት በጣም ያጣብብብናል የሚለውን ሐሳብ በመጨ መር አንቺ ባልሽው ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ ።"

አንድ ትልቅ የዶሮ ጥብስ ምግብ ጠረጴዛው ላይ ቀርቦ ተዘረጋ ። አባ ኔንድሬና ኒና ኢቫኖቭና ንግግራቸ ውን ቀጥለዋል ። በኒና ኢቫኖቭና ጣቶች ላይ ያሉት የአ ልማዝ ቀለበቶች ያበራሉ ። በንግግሩ ስሜቷ በመነካ ቱም ፀይኖቿ በእንባ ተሞልተው ያንጸባርቃሉ ።

"በእርግጥ ከእርስዎ ጋር ለመክራከር አልደፍርም" አለች ። "በኑሮ ውስጥ ብዙ ያልተፈቱ ችግሮች እን ዳሉ ያምናሉ ?"

"ምንም ፣ እንድም እንኳን እንደሌለ አረጋግጥልሻ ለሁ ።"

ከእራት በኋላ ፣ አንድሬ አንድሪች በቫዮሊን የሙ ዚቃ መሣሪያ ሲጫወት ኒና ኢቫኖቭና በጥያኖ ታጅ በው ነበር ። ከዐሥር ዓመት በፊት ከዩኒቨርስቲው የቋንቋ ክፍል ቢመረቅም ፣ ስላልተቀጠረ መደበኛ ቋሚ ሥራ የለውም ። ዐልፎ ዐልፎ ብቻ ገቢው ለበጎ አድራጎት ለሚውል የሙዚቃ ዝግጅት ውስጥ እየገባ ይጫወታል። በከተማው ውስጥ ሙዚቀኛነቱ ይነገርለታል ።

አንድሬ አንድሪች ሲጫወት ሁሉም ጸጥ ብለው ያዳምጣሉ ። ጠረጴዛው ላይ የሻዩ ማንቆርቆሪያ (ሳሞ ቫር) ይንተከተካል ። ሻይ የሚጠጣው ሳሻ ብቻ ነበር ። ልክ ስድስት ሰዓት ሲሆን የቫዮሊኑ አንድ ሽቦ ሲበጠስ ሁሉም እየሣቁ ልመሔድ በመነሣት ተሰነባበቱ ።

ናዴያ እጮኛዋን ከተሰናበተች በኋላ ፣ ከእናቷ ጋር ወደምትጋራቸው ክፍሎች ወደ ፎቅ ወጣች ። (የምድር ቤቱ በአያቷ የተያዘ ነው ።) እምድር ቤት ምግብ ቤቱ ውስጥ መብራት እየጠፋ ቢሆንም ፣ ሳሻ ዝም ብሎ ተቀምጦ ሻዩን ይጠጣል ። በሞስኮ ባህል መሠረት ስድስት ወይም ሰባት ብርጭቆ ደጋግሞ በመጠጣት ሁል ጊዜ ሻይ ላይ ረጅም ጊዜ ይፈጃል ። ናዲያ ልብሷን አውልቃ አልጋዋ ውስጥ ከገባች ከብዙ ጊዜ በኋላ ፣ ሠራተኞች ጠረጴዛውን ሲያጸዱ አያትየዋ ሲሳደቡ ትሰማለች ። በመጨረሻም ከሳሻ ክፍል ዐልፎ ዐልፎ ከሚሰማው ሳል በስተቀር ቤቱ ጸጥ አለ ።

ናድያ ፣ ከእንቅልፏ ስትነቃ ከሌሊቱ ልክ ስምንት ሰዓት ነበር ። ከሩቅ ዘበኛው በከዘራው በረንዳውን ጓ—ጓ— ሲያደርግ ይሰማል ። ናድያ ለመተኛት አልቻለችም ፤ ተዝናንቶ ለመተኛት ኤልጋዋ በጣም ለስላሳ የሆነባት ይመስላታል ። ቀደም ሲል እንዳሳለፈቻቸው ሌሊቶች ሁሉ ፣ በዚህ በግንቦት ወርም አልጋዋ ላይ ተነሥታ በመቀመጥ በሐሳብ ትዋጣለች ። አዲስ ሐሳብ የለም ። እነዚያው ያለፉት ሌሊቶች አሰልቺ ሐሳቦች—አንድሬ አንድሪች እንዴት እንደ ተግባባትና ለጋብቻ እንደ ጠየቃት ፣ እርሷ እሺ እንዳለችውና ፀመጨረሻም እንዴት ቀስ በቀስ ይህን መልካምና

ብልህ ሰው ማድነቅ እንደ ጀመረች—ናቸው ተደጋግ መው የሚታሰቧት ። አሁን ግን ፥ የጋብቻው ቀን አንድ ወር ሲቀረው በጣም ግልጥ ያልሆነ አሳዛኝ ነገር የሚጠብቃት ይመስል በሆነ ባልሆነው ምክንያት ፍር ሃትና አለመረጋጋት ይታይባት ጀመር ።

"ጓ—ጓ ፥ ጓ—ጓ" ያደርጋል ዘበኛው በከዘራው "ጓ—ጓ..."

"አሮጌ በሆነው መስኮት ውስጥ አሻግረው ሲመ ለከቱ የአትክልት ቦታውና የፈኩ አበቦች ያዘሉት የአበባ ቁጥቋጦዎች በሌሊት ቁርና ብርድ ፈዘው የቆሙ ይመስላሉ ። ጥቅጥቅ ያሉ ነጭ ጉም አበቦቹን ለመሸፈን ያሰበ ይመስል ቀስ እያለ እየዋጣቸው ነው ። ራቅ ካሉ ዛፎች የእንቅልፋም አሞሮች ጩኸት ይሰማል ።

"አቤት ፥ አምላኬ ! እንደዚህ የሚያሳዝነኝ ነገር ምን ይሆን ?"

ከጋብቻ በፊት ሁሉም ልጃገረዶች እንደዚህ ይሆኑ ይሆን ? ማን ያውቃል ? ወይስ ሳሻ ያሳደረባት ተጽ ዕኖ ነው ? ግን ሳሻም በቃል ያጠናው ይመስል በየዓመቱ ደጋግሞ የሚናገረው አንድ ነገር ነው ። የሚናገረውም ነገር ተራና ተቀባይነት የሌለው ነገር ነው ። ታዲያ የሳ ሻን ጉዳይ ለምን ከአእምሮዋ አውጥታ አትጥልም ? ለምን ?

የሌሊት ዘበኛው ተዘዋውሮ መጠበቁን ካቆመ ቆየ ። በመስኮቱ ሥርና በዛፎቹ ጫፍ ላይ ወፎቹ መጮህ ጀምረዋል ። በአትክልት ቦታው ያለው ጉም እየገለጠ

ቦታውን ለጸደይ ፀሐይ እየተወ ሲሔድ ሁሉም ነገር ፈክቶ ፈገግታ የሚያሳይ መሰለ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በፀሐይዋ ሙቀት የነቃው የአትክልት ቦታ ነፍስ ዘራ ። የጤዛ ጠብታዎቹ ከዛፎቹ ቅጠሎች ላይ እንደ አልማዝ ያበራሉ ። አሮጌው ፥ ተንቆና ተትቶ የነበረው የአትክልት ቦታ ለዚያች ጠዋት አዲስና ደስተኛ መስሎ ታየ ።

አያት ነቅተዋል ። ሳሻም ከባድ ሳሉን ይስላል ። ምድር ቤትም ሠራተኞቹ የሻዩን ማንቆርቆሪያ ሲያስ ገቡና ወንበሮችን ሲያስተካክሉ ይሰማሉ ።

ሰዓቱ ቀስ እያለ ነው የሚሔደው ። ናድያ ቀደም ብላ ተነሥታ አትክልቱ ውስጥ ስትንሸራሸር ብትቆ ይም ጠዋቱ ገና እየተጐተተ ነበር ።

ኒና ኢቫኖቭና ፥ ዐይኖቿ እንባ አዝለው የጠበል ውሃ በብርጭቆ ይዛ ወጣች ። ስለ ሃይማኖትና ስለ መድ ኃኒት ለማወቅ እየተከታተለች ነው ። ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ታነባለች ። በሃይማኖት ላይ ስላላት ጥርጣሬ ብዙ ስለምታወራ ፥ ናድያ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ አንድ ትልቅና ምሥጢራዊ ቁምነገር ሳይኖር አይቀርም ብላ አሰበች ። እናቷን ስማ ከጐኗ ሆና መራመድ ጀመረች ።

"ለምንድን ነበር ስታለቅሺ የነበረው ፥ እማማ ?" ስትል ጠየቀቻት ።

"ትላንትና ማታ ስለ አንድ ሽማግሌና ሴት ልጃ አንድ መጽሐፍ አነበብኩ ። ሽማግሌው አንድ መሥ ሪያ ቤት ውስጥ ይሠራል ። ምን ልበልሽ አለቃው ከልጁ ፍቅር ይይዘዋል ! መጽሐፉን አንብቤ እንደ

ጨረስኩትም ፣ አንድ ቦታ ላይ ስደርስ አስለቀሰኝ" አለች ኒና ኢቫኖቭና ፣ ከያዘችው ብርጭቆ የጠበሉን ውሃ እየተጐነጨች ። "ዛሬ ጠዋትም ታሪኩን እንደገና አስታወስኩና አለቀስኩ ።"

"ለጣዙ ቀናት ቅፍፍ ብሎኛል" አለች ናዲያ ክት ንሽ ቆይታ በኋላ ። "ለምን እንቅልፍ አይወስደኝም ?"

"እኔ ምን ዐውቃለሁ ፣ ልጄ ! እንቅልፍ እምቢ ሲለኝ ዐይኔን—እንዲህ— በኃይል እጨፍነውና ካሬኒና ምን እንደምትመስልና እንዴት እንደምትናገር ወይም እንድ ታሪካዊ የሆነ የጥንት ነገር አስታውስና አስባለሁ።"

ናዲያ ፣ እናቷ እንዳልረዳቻትና ልትረዳትም የማ ትችል መሆኑ ተሰማት ። ቀደም ሲል የዚህ ዐይነት ስሜት አልነበራትም ፤ ሁኔታው አስፈራራት ። ለመደ በቅ ስል ፈለገች ወደ ክፍሏ ተመልሳ ሔደች ።

በሁለት ሰዓት ሁሉም ለእራት ቀረቡ ። የጹም ቀን ረቡዕ ስለነበር ፣ ለእያት የአትክልት ሾርባ ፣ ዓሣና የስ ንዴ ገንፎ ቀርቦላቸዋል ።

ፀእያት ለመቀለድ ሳሻ የአትክልትና የሥጋ መረ ቁን እንድ ላይ ይጠጣል ። በራት ሰዓት ሁሉ ይቀልድ ነበር ። ቀልዱ ግን ፣ ረጃጅምና በሞራል ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የሚያሥቅም አልነበረም ። የሚያሥቅና የሚያስ ደስት ቀልድ ከማምጣቱ በፊት ረጃጅም ፣ አጥንታማና የሞቱ የሚመስሉትን ጣቶቹን ወደ ላይ ያነሣል ። በጣም የታመመና ምናልባትም የሕይወት ዘመኑ አጭር እን ደሆነ ፀሐሳብ ሲመጣ የሚታዘንለትና የሚለቀስለት ሰው ነው ።

ከራት በኋላ አያት ለማረፍ ወደ ክፍላቸው ሔዱ። ኔና ኢቫኖቭና ለአጭር ጊዜ ፒያኖ ከተጫወተች በኋላ ወደ ውጭ ወጣች ።

"ታዲያስ ውድ ናድያ" ኤለ ሳሻ ፣ ወደ ተለመደው ከራት በኋላ ወደሚያነሣው አርዕስት እየተመለሰ። "እንዴ ያው ብታዳምጪኝ !"

ዐይኖቿን ጨፍና እግሮቿን አኮራምታ አንድ እሮጌ ሶፋ ላይ ተቀምጣለች ። እሱ ደግሞ ክፍሉ ውስጥ ይን ጐራደዳል ።

"ከዚህ ወጥተሽ ብትጣሪ" ይላታል ። "የሚፈለ ጉት የተማሩት ፣ ብሩህ የሆኑ ቅዱሳን ሰዎች ናቸው ። የእንደነዚህ ያሉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሔድ በም ድራችን ላይ የሚፈጠረውን የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት ያፋጥናል ። ከዚያም ምንም የሚተርፍ ነገር የለም ፤ በዚህ ዘመንደራችሁ በምትሐት ይመስል አንድ ድንጋይ በሌላው ላይ ተቀምጦ አይገኝም ። ሁሉም እንዳልነበረ ሆኖ ይገለባበጣል ፤ ይለዋወጣል ። ከዚያም በጣም ግዙፍና ቆንጆ ሕንፃዎች ፣ ውብ መናፈሻዎች ፣ የሚያስደንቁ ወደ ሰማይ ሽቅብ የሚወረወሩ ሰው ሠራሽ ፏፏቴዎች ፣ ጥሩ ጥፋ ሰዎችም ይፈጠራሉ ። ዋናው ቁም ነገር ግን ይሄ አይደለም ። ቁም ነገሩ ይኼ አሁን የምናየውና የምንመለከተው የተዘበራረቀ ሥር ዓት የሌለው ሁኔታ አይኖርም ። ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው በራሱ እምነት ይኖረዋል ፤ ለምን እንደሚኖር ያውቃል ፤ ከተራው ሕዝብ ዕርዳታ የሚፈልግ ሰው አይኖርም ። ወዳጄ ፣ ትንሿ ለማዳ እንስሳ ፣ ሒጂ ! ይህ

የማይለወጥ ፥ የማይቀየር ቀፋፊ ኑሮ የሰለቸሽ መሆኑን አሳያቸው ። ቢያንስ አንቺ የተሰላቸሽ መሆንሽን ለራ ስሽ አሳይው ።"

"አልችልም ፥ ሳሻ ፤ ላገባ ነው እኔ ።"

"ለሱ ግድ የለም ! ምናለበት ?"

ወደ አትክልቱ ቦታ ወጥተው ተንሸራሸሩ ።

"ሆኖም ፥ ወዳጄ ፥ ይህ ሥራ ፈት ሕይወትሽ ምን ያህል የሚያስጠላና ሞራል የሚጥል መሆኑን ማሰብና መረዳት አለብሽ" በማለት ሳሻ ንግግሩን ቀጠለ ። "አንቺ ፥ እናትሽና አያትሽ የተንደላቀቀ ሥራ—ፈት ሕይወት እንድትኖሩ ሌሎቹ የሚሠሩላችሁ ፥ የሚደክ ሙላችሁ መሆኑን አትመለከቺም ? የሌሎቹን ሕይወት እየበላችሁ ነው ። ይሽ አይታሰብሽም ? ይህ ትክክል ነው ? ቆሻሻ ተግባር አይደለም ?"

ናድያ ፥ "አዎን ፥ ልክ ነው" ለማለትና ነገሩ እንደ ገባት ለመግለጽ ፊልጋ ፥ ዐይኖቿ እንባ ስለ አቀረሩ ዝም ብላ ወደ ክፍሏ ሔደች ።

ማታ አንድሬ አንድሬች መጥቶ እንደ ተለመደው ቫዮሊኑን ይዞ ለረጅም ጊዜ ተጫወተ ። በተፈጥሮው ብዙ የማይናገር ቁጥብ ስለሆነ ፥ ምናልባት ከሰው ጋር ላለመነጋገር ከቫዮሊኑ ፍቅር የያዘው ይመስላል ። ከአ ራት ሰዓት በኋላ ለመሔድ ኮቱን ለብሶ ሲነሣ ናድያን አቅፎ በፍቅር ስሜት ፊቷን ፥ ትከሻዋንና እጆቿን ደጋ ግሞ ሳማቸው ።

"የኔ ቆንጆ ፥ የኔ እመቤት ፥ የኔ ወለላ" እያለ አሞ ጋገሳት ።

"እቤት ፣ እንዴት ያስደስታል ! በደስታ የማብድ መስለኝ !"

ይህንንም አባባሉን አስቀድማ ሰምታዋልች ። ከረጅም ጊዜ በፊት በአንድ የተዘነጣጠለ ፣ ከእንግዲህ ወዲህ የመነበብ ፅድል የሌለው ፣ አሮጌ መጽሐፍ ውስጥ ያነበበችው መስላት ።

ሳሻ ፣ በምግብ ቤቱ ውስጥ ተቀምጠ የሻዩን ስኒ ማስቀመጫ በረጃጅም አምስት ጣቶቹ ደግፎ ይዞ ሻይ ይጠጣል ። አያት ብቻቸውን ተቀምጠው ካርታ ይጫወታሉ ። ኒና ኢቫኖቭና ደግሞ ታነባለች ። በቅዱሳኑ ምስል ፊት ለፊት የሚበራው መብራት ይውለበለባል። ሁሉም ነገር ጸጥ ያለና ደኅና ይመስላል ። ናድያ ደኅና እደሩ ብላ ደረጃውን ወጥታ ወደ ክፍሷ በመሔድ አልጋዋ ውስጥ እንደ ገባች እንቅልፍ ጭልጥ አድርጉ ወሰዳት ። ግን እንዳለፈው ሌሊት ሁሉ በመጀመሪያው የጠዋት ብርሃን ነቃች ፤ መተኛት አልቻለችም ። አንድ ከባድና ዕረፍት የሚነሣ ነገር እልቧ ውስጥ ተጋድሟል። ራሷን ጉልበቶቿ ላይ ደፍታ ስለ እጮኛዋና ስለ ሠርጉዋ ቀን ታስብለች ። በሆነ ምክንያት እናቷ ባሏን የማትወደው እንደ ነበረ ፣ በዚህም ምክንያት የራሷ የሆነ ምንም ንብረት እንደ ሌላት ፣ ለኑሮዋም ሙሉ በሙሉ የምትመካው በአማቷ ፣ በራሱዋ አያት መሆኑን አለ ታወሰች ። ናድያ በተቻላት ሁሉ ብትሞክርም ፣ ለምን እናቷን ልዩ ሊታሰብላት የሚገባ ፣ደስተኛ ያልሆነች እናት አድርጋ እንደምትቆጥራት ሊገባት አልቻለም።

ምድር ቤት ሳሻም ነቅቷል ። ደረቅ ሣሉን ሲስል ትሰማለች ። አስገራሚ ንጹሕ ተፈጥሮ እንደሆነ አስ

በች ። ናድያ እነኝያ ግሩም መናፈሻዎችና አስደናቂ ሰው ሠራሽ ፏፏቴዎች ሕልሞቹ የማይታመኑ መሆና ቸውን አሰበች ። በንጽሕናውና ግልጽ ባልሆነው አመ ለካከቱ ውስጥ ግን ብዙ ቆንጆ ነገሮች አሉበት ።አን ዳንድ ጊዜ ብድግ ብላ መሔድና መማር እንዳለባት በመደነቅ ስታስብ የሠራ አካላቷ ሰውነትን እንደገና በሚያድስ ቅዝቃዜ የምትታጠብ እየመሰላት ሞልጥ ብላ በደስታ ትዋጣለች ።

"አለማሰብ ይሻላል" ትላለች ቀስ ብላ ።"ስለ እሱ አለማሰብ ይሻላል ።"

"ጓ—ጓ ።" እሩቅ ያለው የሌሊት ዘበኛ ማስጠን ቀቂያ ወይም ማስፈራሪያ ቆርቆሮውን ያንኳኳል ። "ጓ—ጓ...ጓ—ጓ።"

ላሻ ፥ በጣም ስለ ተሰላቸ ፥ በሰዓ ወር አጋማሽ ወደ ሞስኮ ለመመለስ የሚፈልግ መሆኑን ማውራት ጀመረ።

"እዚህ ከተማ መቆየት አልፈልግም" አለ በጎዘን ። "የቧንቧ ውሃ ፥ የቆሻሻ ማስተላለፊያ ቱቦ የለም ! ማዕድ ቤቱ ለመግለጽ ከሚቻል በላይ...ቆሻሻ በመ ሆኑ ምግብ እንኳን መብላት ያስጠላኛል ።"

"ቆይ ትንሽ ፥ ሞልቃቃ" አሉ አያት ።

"ሠርጉ እኮ በሰባተኛው ቀን ላይ ነው ።"

"አልችልም ፤ አልቆይም !"

"እስኪ መስከረም አብረኸን እንደምትቆይ ተናግ ረህ አልነበረም ?"

"አሁን ግን መቆየት አልችልም ። መሥራት ይና ርብኛል ።"

የክረምቱ ወቅት ቀዝቃዛና ዝናባማ ሆኗል ። ክዛ ፎቹ ላይ የውሃ ጠብታ እንደ ተንጠባጠበ ነው ፣ የአት ክልቱም ቦታ ጨለማ ፣ ጎዘንተኛ ይመስላል ። በዚህም ምክንያት ከዚህ መውጣትና ሥራ መፈለግ ትክክል ነው ። የማያውቀው የሴቶች ድምፅ ከምድር ቤትና ከፎቅ ላይ ይሰማል ። የልብስ ስፌት መኪና ድምፅ ከኋያት ክፍል ይሰማል ። የሙሽራዋን ልብስ ለማዘጋ ጀት የሚደረግ ሽር ጉድ ይመስላል ። የክረምት ኳፖርት ብቻ ስድስት እንደሚኖራት ፣ ከዚህ ውስጥ በጣም ርካሽ የተባለው ባለሦስት መቶ ሩብል መሆኑን አያት በኩ ራት ትናገራለች ። ይህ ሁሉ ቀልድ ሳሻን ያበሳጨ ዋል ። ክፍሉ ውስጥ ተቀምጦ ያዝናል ፤ ይተክዛል ። በመጨረሻም ያግባቡትና ከሐምሌ አንድ ቀን በፊት እንደማይሔድ ቃል ይገባል ።

ጊዜው በፍጥነት ዐለፈ ። በቅዱስ ጴጥሮስ በዓል ዕለት አንድሬ አንድሪችና ናድያ ሲጋቡ ፣ እንዲኖሩበት እሱ የተከራየላቸውንና የተዘጋጀውን ቤት ለማየት ወደ ምስኮ ጐዳና ይዟት ይወጣል ። ቤቱ ባለሁለት ፎቅ ሲሆን እስከ አሁን ግን የተዘጋጀው ፎቁ ብቻ ነው ። የመዝናኛው ክፍል ወለል ሣንቃ የለበሰ እንዲመስል በተቀባው ቀለም ያንጸባርቃል ። በክፍሉ ውስጥ ወንበ ሮች ፣ አንድ ትልቅ ፒያኖና ለቫዮሊን ማስቀመጫ የሚሆን የሙዚቃ መሣሪያ ማንጠልጠያ አለ ። የተቀ ባው የግድግዳ ቀለም ይሸታል ። በግድግዳው ላይ አንድ ትልቅ የዘይት ቅብ ሥዕልና አንድ የተሰበረ እጀታ ያለው አበባ ማስቀመጫ አጠገብ እርቃንዋን የቆመች ሴት ምስል ግድግዳው ላይ ተሰቅሏል ።

"ቆንጆ ምስል" አለ አንድሬ አንድሪች በሚያ ስፈራራ ሁኔታ ወደ ውስጥ አየር በመሳብ ።" የተሳለው በሲሸማቼቭስኪ ነው ።"

የሚቀጥለው የታየው የመልበሻ ክፍሉ ሲሆን አንድ ክብ ጠረጴዛ ፣ አንድ ሶፋና ብሩህ በሆነ ሰማያዊ ጨርቅ የተለበዱ ጥቂት የእጅ መደገፊያ ያላቸው ወን በሮች አሉ ። ከሶፋው በላይ ሚዳሊያቸውን ደርድረውና የክብር ባርኔጣ አድርገው የተነሡት የአባ አንድሬ በት ልቁ የታጠበ ፎቶግራፍ ተሰቅሏል ። ወደ ምግብ ቤቱ ዐልፈው በመግባት የዕቃ ማስቀመጫውን አይተው ወደ መኝታ ቤቱ ዐለፉ ። በመኝታ ቤቱ ውስጥ በግ ማሽ ብርሃን ሁለት አልጋዎች ጐን ለጐን ይታያሉ ። ይህን ያዘጋጁ ሰዎች በዚህ ቤት ሕይወት ወይም ኑሮ ሁል ጊዜ በደስታ የተሞላ እንደሚሆን ሳያስቡ የሚቀሩ አይመስልም ። አንድሬ አንድሪች አንድም ጊዜ ከአቀፈው የናድያ ሽንጥ ላይ እጁን ሳያነሣ ክፍሎቹን በሙሉ አዘዋውሮ አሳያት ። ናድያ ግን ፣ ድካምና የጥፋተኛነት ስሜት ተሰማት ። በክፍሎቹ ውስጥ ያሉትን ዕቃ ዎች ሁሉ አልጋዎቹን ፣ ወንበሮቹን ጠላቻቸው ። በግድ ግዳው ላይ የተሰቀለው እራቁቷን ያለችው ሴት ምስል አስጠላት ። አሁን በእርግጥ አንድሬ አንድሬችን እን ደማትወደው ምናልባት ቀደም ሲልም የማትወደው እንደ ነበረ ተገነዘበች ። ነገር ግን ፣ ይህንን እንዴት አድ ርጋ እንደምትገልጠው ፣ ለማን እንደምታጫውተው ፣ ለማን እንደምትናገረው አላወቀችም ። ቀን ከሌት ስለ ዚህ ጉዳይ ብታስብም ወደ ማወቁ አልተቃረበችም ። ወገቧን በእጁ ጥምጥም አድርጐ ይዞ ፣ በፍቅርና በደስታ

እያጫወታት የመኖሪያ ቤቱን እየተዘዋወረ ያያል ። ለእርሷ ግን ፥ የሚታያት የነበረው ተራነት ፥ ቀላልነትና ጅልነት ነበር ። በወገቡዋ ላይ የተጠመጠመውም እጅ ሕይወት እንደሌለው ቀዝቃዛና ድርቅ ያለ ብረት ሆኖ ተሰማት ። ለማምለጥ ፥ ለማልቀስና ከመስኮት ዘልላ ለመሞት ዝግጁ ነበረች ። አንድሬ አንድሪች ወደ መታጠቢያው ቤት ይዟት በመግባት ፥ ግድግዳው ላይ የተተከለውን ቧንቧ ሲከፍት ውሃው በኃይል ፈሰሰ ።

"ይኸስ ምን ይመስልሻል?" ብሏት ሣቀ ።

"በመታጠቢያ ቤታችን የቧንቧ ውሃ እንዲኖር አንድ መቶ ባልዲ ውሃ የሚይዝ ማጠራቀሚያ እንዲ ሰቅሉ አዝገፎአለሁ ። "

በግቢው ውስጥ ትንሽ ከተንሸራሸሩ በኋላ ፥ ወደ አውራ መንገድ ወጥተው በጋሪ ተሳፍረው ሔዱ ። አቧራው ጥቅጥቅ እንዳለ ደመና በመነሣቱ ሊዘንብ የተቃረበ ይመስል ነበር ።

"በረደሽ?" አለ አንድሬ አንድሪች ዐይኖቹ ውስጥ አቧራ እንዳይገባ እየጨፈናቸው ።

መልስ አልሰጠችውም ።

"ታስታውሻለሽ ፤ ምንም ሥራ ባለመሥራቴ ትላትና ሳሻ ሲወቅሰኝ?" አለ ትንሽ ቆይቶ ። "አምን፥ በእርግጥ ትክክል ነው ። ምንም አልሠራም ። ምን ለመሥራት እንደምችልም አላውቅም ። ለምንድን ነው ይህ የሚሆነው ፥ ፍቅሬ? ለምንድን ነው ሥራ ለመሥራት የቢሮ ሠራተኛ ምልክት ባርኔጣዬ ላይ ሰክቼ ወደ ቢሮ የመሔድ ሐሳብ እንኳን የሚያስጠላኝና የሚያሳምመኝ?

ለምንድን ነው ጠበቃ ወይም የላቲን አስተማሪ ወይም የከተማ ሹም ማየት የሚያስጠላኝ? አቤት ፣ እናት ሩስያ! እናት ሩስያ ፣ ስንት ሥራ ጠል ፣ ስንት ዋጋ ቢስ ፍጥረቶች በጉያሽ አቅፈሻል! ስንት የኔ ዐይነት ሰዎች፣ አቤት! ለረጅም ጊዜ የምትሠቃይው ፣ እናት ሩሲያ!" የሱ ሥራ ጠልነት የዘመኑ ወይም የጊዜው ሁኔታ ስለመሆኑ መላ-ምት ይደረድራል ።

"ስንጋባ" ብሎ ይቀጥልና ፣ "ፍቅሬ ወደ ባላገር ሔደን እየሠራን እንኖራለን ። አንድ ትንሽ መሬት የአ ትክልት ቦታና ወንዝ ያለበት ገዝተን እየሠራን ሕይ ወትን እናያለን . .. አቤት ! እንዴት የሚያስደስት ይሆንልናል !" ባርኔጣውን ሲያወልቅ ጸጉሩን ነፋሱ እመሳቀልው ። የሚናገረውን ሁሉ ታዳምጠው የነበረው፣ "አቤት አምላኬ! ወደ ቤቴ መመለስ እፈልጋለሁ! አቤት አምላኬ" እያለች ነበር ። እነ ናድያ ቤት ከመድረሳቸው በፊት ፣ አባ አንድሬን ለትንሽ ቀደሟቸው ።

"ተመልከቺ ፣ ያውና አባቴ!" አለ አንድሬ አንድ ሪች ደስ ብልኅት ባርኔጣውን ለአባቱ እያወዛወዘ ። "ሽማግ ሌውን አባቴን እወደዋልሁ ፤ በእርግጥ እወደዋለሁ ።" አለ ለባለጋሪው ሒሳቡን እየከፈለ ። " ውዱ ሽማግሌ! ደጉ ሽማግሌ !"

ማምሻውን እንግዶች እንደሚመጡ ፣ ሁሉንም ማስ ተናገድ እንደሚጠበቅባት ፣ ፈገግታ ማሳየት ፣ የቫዩሊ ኑን ጨዋታ ማዳመጥ እንደሚኖርባት ፣ ዕርባና የሌለው የሆነ ያልሆነውን ጨዋታና ስለ ሠርጉ ብቻ የሚነገ ረውን አሰልቺ ወሬ መስማት እንደሚገባት ብታውቅም

ደኅንነት ስላልተሰማት ወደ ቤቷ ገባች ። አያት ፣ የሐር ልብሳቸውን ለብሰው ሁልጊዜ እንግዳ ሲኖር እንደሚያደርጉት ፣ ሁሉ በኩራት ተወጥረው ሻዩ ማፍሊያ መሣሪያ አጠገብ ተቀምጠዋል ። አባ አንድሬ የተለመደውን አታላይ ፈገግታቸውን እያሳዩ ወደ ክፍሉ ገቡ ።

"በመልካም ጤንነት ላይ ስለ አገኘሁሽ በጣም ተደስቻለሁ" አሉዋቸው አያትን ። ይህ አነጋገራቸው ከልባ የፈለቀ ይሁን የቀልድ ልማወቅ አይቻልም ።

ነፋሱ ከመስኮቶቹና ከጣሪያው ጋር ይላተማል ። የነፋሱ ፉጨት በያለበት ይሰማል ፤ በጭስ መውጫው አጠገብ ያለው ወፍ አሳዛኝ ዜማውን ያንቆረቁራል ። ከምሽቱ ሰባት ሰዓት ነበር ። ቤቱ ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ አልጋው ውስጥ የገባ ቢሆንም እንቅልፍ የወሰደው አልነበረም ። ናድያም ከምድር ቤት የባዩሲን ድምፅ የምትሰማ እየመሰላት ታስባለች ። ከውጭ በኩል አንድ ከባድ ድምፅ ተሰማ ፤ ምናልባት የመስኮት መጋረጃ ተገንጥሎ ወድቆ ይሆናል ። ከአንድ ደቂቃ በኋላ ኒና ኢባኖቭና በሽሚዝ ሆና በእጅዋ አንድ የሻማ መብራት ይዛ መጣች ።

"ምንድን ነው ይኸ ድምፅ ናድያ ?" ስትል ጠየቀች ። በዚህ ነፋሻ ሌሊት የናድያ እናት ጸጉሯን በነጣላ ጉንጉን ተሠርታ የየዋህ ፈገግታ እያሳየች ከወትሮው የበለጠ ተራ ሆና አርጅታና አጥፉ የምትታይ ትመስላለች ። በቅርቡ እናቷን እንዴት ያለች ልዩ ፍጡር አድርጋ ትመለክታት እንደ ነበረ ስትናገር ፣ የምትጠቀም ባቸውን ቃላት ሁሉ እያዳመጠች ኩራት ይሰማት እንደ

ነበረ ናድያ ታስታውሳለች ። አሁን ግን ፣ እነዚህ ትኩራዛ ቸው የነበሩ ቃላት ምን እንደሆኑ አታስታውሳቸውም ።

ከጭስ መውጫው አካባቢ በወፍራም ድምፅ የሚ ዘመር ይመስላል ። "አቤት አምላኬ!" የሚለው ድምፅ እንኳን በትክክል ይሰማል ። ናዲያ አልጋዋ ላይ ፉተቀ ምጣ ጸጉሯን እየነጨች ታለቅሳለች ።

"እማማ ፣ እማማ " ስትል ጮኸች ። "ወይ ልጄ ያለሁበትን ችግር ብትረጂልኝ! ልለምንሽ ፣ ተለመኚ! ልቀቂኝ ፣ ፍቀጂልኝ ፣ ከዚህ ልሒድ! " አለቻት ።

"ወዴት? "ብላ በመጠየቅ ኒና ኢባኖቭና በመገ ረምና በመጨነቅ አልጋው ላይ ከጐኗ ተቀመጠች ። "የት ለመሒድ ነው የምትፈልጊው ?"

"ጋብቻው መፈጸም የለበትም ፤ አላገባም ፤ እመኚኝ ፤ ያንን ሰውዬ አልወደውም ... ስለ እርሱ መናገር አልፈ ልግም ። "

"የለም ፣ የኔ ልጅ ፤ የለም አይሆንም" አለች ፈጥና ኒና ኢቫኖቭና በድንጋጤ አቅሏን አጥታ ። "ተረጋጊ ፣ ራስሽን አረጋጊው ። ብስጭት ብለሽ ስለሆነ አሁን ያልፍልሻል። እንደዚህ ያለ ነገር ዐልፎ ዐልፎ ያጋጥማል። ምናልባት ከአንድሬ ጋር ትንሽ ተጋጭታችሁ ይሆናል ። ነገር ግን ፣ የፍቅረኞች ጊዜያዊ ጥል በመሳሳም ያበ ቃል ። "

"ሒጂ ፣ እማማ ፣ ሒጂ!" እያለች አለቀሰች ናድያ።

"እሺ" አለች ኒና ኢቫኖቭና ከትንሽ ቆይታ በኋላ ። "ትላንትና ግና ትንሽ ልጃገረድ ነበርሽ ፤ ዛሬ ደግሞ

ሙሽራ ነሽ ። ተፈጥሮ በማያቋርጥ ለውጥ ላይ ነች ፤ የት እንደ ሆንሽ ሳታውቂ ባለልጅ ትሆኚያለሽ ፤ ከዚ ያም አርጅተሽ ልክ እንደኔ የአስቸጋሪ ልጅ እናት ትሆ ኛለሽ ።”

“እማዬ ፥ ርጎሉጎ ደግና ብልህ ሆነሽ ደስተኛ እይደለ ሽም” አለች ናድያ ። “በጣም ደስተኛ አይደለሽም ፤ ለምን፥ ንደዚህ ያለ ተራ ነገር ትናገሪያለሽ? ስለ እግዚአብሔር ለምን ?”

ኒና ኢቫኖቭና ለመናገር ሞከረች ፤ ነገር ግን አንድ ቃል ለመተንፈስ ባለመቻሏ እንባ እየተናነቃት ወደ ክፍሏ ሔደች ። እንደገና ከጭስ መውጫው አካባቢ ወፍ ራሞቹን ድምፆች ስትሰማ ናድያ በድንገት ደነገጠች ፤ ፈራች ። ከአልጋው ውስጥ ዘልላ ወጥታ ወደ እናቷ ክፍል እየሮጠች ሔደች ። ኒና ኢቫኖቭና ከማልቀሷ ብዛት የተነሣ የዐይኖቿ ሽፋኖች አብጠው ፥ አልጋዋ ውስጥ ገብታ ፥ ሰማያዊ የብርድ ልብስ ለብሳ ፥ አንድ መጽሐፍ ይዛ ተኝታለች ።

“እማማ ፥ አዳምጪኝ ” አለች ናድያ ። “አስቢ ፤ ልትረጂኝ ሞክሪ ፤ እንድትረጂኝ እለምንሻለሁ ! ሕይወ ታችን ወይም ኑሮዋችን ምን ያህል ተራና የተዋረደ እንደሆነ አስቢ! አሁን ዐይኖቼ ተከፍተዋል ፤ ሁሉንም ነገር በትክክል አያለሁ ። ያንቺ አንድሬ አንድሪች ምን ድን ነው ? ለምን ፥ ትንሽ እንኳ ብልህና ዐዋቂ አይደ ለም ፥ እማማ ። አቤት አምላኬ! አስቢ እማማ ፥ ለምን ፥ እሱ ደደብ ነው ። ”

"እንቺና አያትሽ እያንገበገባችሁ ፥ እያቃጠላችሁኝ ነው" አለች በልቅሶ መኻል እየተናገረች ። "ለመኖር እፈልጋለሁ! መኖር!" አለች ደጋግማ በብስጭት ደረቷን እየደቃች ። "ነጻነቴን እንዳገኝ አትፈልጊም? ገና ወጣት ነኝ ፥ ለመኖር እፈልጋለሁ ፤ እወዳለሁ ፤ እናንተ አሮጊት አድርጋችሁ ታዩኛላችሁ!"

በምሬት በማልቀስ አልጋዋ ውስጥ ተጋድማ በመንከባለል ፥ በብርድ ልብሱ ተጠቅልላ በጣም አሳዛኝ ትንሽ ፍጡር መስላ ታየች ። ናድያ ወደ ክፍሏ በመመለስ ልብሷን ለብሳ መስኮቱ አጠገብ ተቀምጣ መንጋቱን ትጠባበቃለች ። ሌሊቱን ሁሉ ተቀምጣ አሰበች ። ከውጭ ደግሞ የሚያንኳኳና የሚያፏጭ ሰው ያለ መሰሎ ተሰማት ።

ጠዋት ነፋሱ ፍሬዎቹን ማርገፉን ፥ የአንድ አሮጌ የፍሬ ዛፍ ቅርንጫፍ የመገንጠሉን መርዶ አያት እያረዱ ይብከነከናሉ ። ግራጫ ፥ ጨለም ያለ ፥ ደስታ የሌለበት ፥ ከጠዋት ጀምሮ መብራት በርቶ የሚውልበት ቀን ዐይነት ጨፍጋጋ ማለዳ ነው ። ስለ ብርዱና ቅዝቃዜው ሰው ሁሉ ያጉረመርማል ፤ የዝናቡም ውሽንፍር የመስኮቶቹን መስተዋቶች ይደበድባል ። ከቁርስ በኋላ ናድያ ወደ ሳሻ ክፍል በመሔድ ፥ አንድ ቃል ሳትተነፍስ ፥ ፊቷን በእጆቿ ሸፍና አንድ ወንበር አጠገብ ተንበረከከች ።

"ምንድን ነው ነገሩ?" ብሎ ጠየቀ ሳሻ ።

"እንደዚህ ሆኜ ለመቀጠል አልችልም ፥ አልችልም" ስትል ሙቼች በቁጣ ። "ከዚህ በፊት እዚህ

እንዴት እኖር እንደ ነበር ማወቅ አልችልም ። አይገባ ኝም ! እጮኛየን እንቀዋለሁ ፤ ራሴንም እንቃልፁ ፤ ይህ ንንም ሥራ ጠል ባዶ ሕይወት በሙሉ እንቀዋለሁ...”

“ተይ ፥ ተይ ...” በማለት ሳሻ ኤቂርጪት ስለምን ጉዳይ እንደምትናገር ሳይገባው ፥ “ምንም አይደለም.... ትክክል ነው ....”

“ይህ ኑሮ ያስጠላኛል” በማለት ቀጠለች ናድያ ። ‘ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ቀን እንኳን እዚህ ልቆይ አልችልም ። ነገ መሔድ አለብኝ ። ስለ እግዚአብሔር ብለህ ከአንተ ጋር ውሰደኝ !” አለችው ሳሻን ።

ሳሻ በመደነቅ ለተወሰነ ጊዜ አንጋጦ ተመለከታት። በመጨረሻ ሐቁ ስለ ተከሰተለት እንደ ሕጻን ልጅ እጁን እያወዛወዘ ተደሰተ ። በተጫማው ነጠላ ጫማ ሲወላ ገድ በደስታ የሚደንስ ይመስል ነበር ።

“ግሩም!” አለ እጆቹን እያፋጨ ፤ “አምላኬ ፥ እን ዴት ጥሩ ነገር ነው!”

አያሌ ጠቀሜታ የያዘ ቁም ነገር ያለው ሐሳብ የሚያፈልቁ ይመስል ፥ በሰፊው የተከፈቱ ዐይኖቹን በፍ ቅር አመለካከት አፍጥጣ ትመለከታለች ። እስከ አሁን አንድም ነገር የነገራት ባይሆንም አንድ አዲስና ሰፊ ነገር ፥ እስከ ዛሬ ያላወቀችው ነገር ከፊቷ እየተከፈተ ያለ ሆኖ ተሰማት ፤ ታያት ። ለማንኛውም ነገር ለሞት እንኳን ለራሱ ቢሆን ፥ ዝግጁ ሆና በጉጉት እያየችው የሚለውን ለመስማት ቅጠባበቃለች ።

"ነገ እሔዳለሁ" አለ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ። "እኔን ለመሸኘት እስከ ባቡር ጣቢያው ልትመጪ ትች ያለሽ ። ፅቃሽን በሻንጣዬ ይገቢልሽ እሔድና ቲኬትም እገዛልሻለሁ ። ሦስተኛው ደወል ሲደወል ባቡሩ ላይ ትወጪኖ አብረን እንሔዳለን ። እስከ ሞስኮ ከኔ ጋር ትሔጂና ወደ ፒተርስበርግ ብቻሽን ትሔጃለሽ ። ይለፍ አለሽ ?"

"እውን ። "

"አትጸጸችበትም ፤ አታዝኝበትም ፤ እርግጠኛ ነኝ!" አለ ሳሻ በስሜት ።

"ከዚህ አካባቢ ርቀሽ ሔደሽ ትማሪያለሽ ። በዚህ ጊዜ ውስጥ ነገሮች የራሳቸውን መሥመር ይይዛሉ ። ኑሮ ሽን ስትለውጭ ሁሉም ነገር ይቀየራል ። ዋናው ነገር ግን ኑሮሽን ወይም አኗኗርሽን መለወጥ መቻል ነው ፤ ሌላው ነገር ቀላል ነው ። ስለዚህ ነገ እንንቀሳቀሳለን ማለት ነው ?"

"እሺ ፥ ይሁን ፤ አምላክ ይርዳን !" አለች ።

"ስሜቴ በከፍተኛ ደረጃ ተቀስቅሷል ፤ እስከ ዛሬ ልቤ እንደዚህ ከባድ ቅሬታ ተሰምቶት አያውቅም" የም ትለው ናድያ ፥ ዛሬ በጉዞው ዋዜማ በአዕምሮ ጭንቀ ትና በሐሳብ እንደምትሠቃይና እንደምትንገላታ ይታወ ቅባት ነበር ። ግን ፥ ፎቁን ወጥታ መኝታ ክፍሏ ደርሳ አልጋዋ ውስጥ እንደ ገባች ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ስለ ወሰዳት ፥ እንባ ባራሰው ፊቷ ላይ ፈገግታ ተላብሳ እስከ ማታ ድረስ ተኛች ።

ሠርገላው እንዲመጣ ተልኮበታል ። ናድያ ኮቷን ለብሳ ፣ ባርሜጣዋን አድርጋ ለመጨረሻ ጊዜ ለማየት ወደ ፎቅ ወጣች ። ክፍሏ ውስጥ አልጋው አጠገብ ፣ አሁንም ይሞቃል ፤ ለትንሽ ጊዜ ቆም ብላ ወደ እናቷ ክፍል ሔደች ። ኒና ኢቫኖቭና ተኝታ ስለ ነበር ፣ መኝታ ቤቷ ጸጥ ብሏል ። እናቷን ስማ ጸጉሯን በእጅዋ ከዳሰሰች በኋላ ናድያ ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ያህል ቆመች ። ከዚያም ሳትቸኩል ቀስ ብላ ደረጃውን ወረደች ።

ዝናቡ እንደ ዶፍ ይወርዳል ። በዝናብ የበሰበሰው ሠረገላ የሸራ አጎበሩን ዘርግቶ በረንዳው አጠገብ ቆሟል ።

"ቦታ የለሽም ፣ ናድያ" አሏት አያት ፣ አሽከሩ ዕቃውን ጋሪው ላይ እያስቀመጠ ።

"በእንደዚህ ያለ የተበላሸ የአየር ጠባይ ልትሸኚው መነሣትሽ ይደንቀኛል ። ቤት ብትቀሪ ይሻልሻል ። ተመልከቺው ዝናቡን!"

ናድያ አንድ ነገር ለመናገር ፈለገች ፤ ግን አልቻለችም ። ሳሻ ወደ ሠረገላው ደግፎ ካወጣት በኋላ ጉልበቷን በምንጣፉ ሸፍኖላት አጠገቧ ተቀመጠ ።

"ደህና ግባ! እግዚአብሔር ይባርክህ!" ብለው መረቁት አያት ። ከበረንዳው ላይ ሆነውም ፣ "ልብ አድርግ ሳሻ ፤ ሞስኮ ስትደርስ እንድትጽፍ ። "

"እሺ ፣ ደህና ይሁኑ አያት ! "
"ማርያም ትጠብቅህ!"
"ምን ዐይነት የአየር ጠባይ ነው !" አለ ሳሻ ።

አሁን ነበር ናድያ ማልቀስ የጀመረችው ። መሐ
ዲን ፣ መለየቷ መሆኑን ያወቀችው ገና አሁን ነበር ።
እያቷን ስትሰናበት ወይም እናቷ አጠገብ ቆማ በነበረ
በት ጊዜ እንኳን መሐዲን እስከ አሁን ድረስ አላመ
ነችም ነበር ። ደኅና ሁኚ ፣ ከተማችን! ሁሉም ነገር
ከመ ቅጽበት እየተጓዘ መጣባት ። እንድሬ ፣ አባቱ ፣ አዲሱ
ቤት ፣ ከአበባ ማስቀመጫው አጠገብ እፉቱቷን የቆመ
ችው ሴትዮ ምስል ሁሉ ታያት ። ይህ ሁሉ አሁን አያ
ስፈራራትም ፤ ወይም አይጫናትም ፤ በጣም ትንሽና ተራ
ነገሮች ስለሆኑ አልፈዋል ፤ ያልፉ ትዝታዎች ብቻ
ናቸው ። ባቡሩ ፉርጎ ውስጥ ገብተው ባቡሩ ሲንቀሳቀስ
ያ ግዙፍና ትልቅ ይመስል የነበረው ያለፈ ነገር ሁሉ
አንድ ትንሽ ቅንጣት ሲሆን ፣ ከፊት ለፊቷ ደግሞ እስከ
ዛሬ ያልታያት ያላለመችው አዲስና ብሩህ ሕይወት
ተከፍቶላታል ። የዝናብ ጠብታ ፉርጎው መስኮቶች ላይ
ይንጠባጠባል ፤ ከአረንጓዴው መስክ ፣ የስልክ መሥመሮች
ምሰሶዎች ፣ በሽቦዎቹ ላይ ያረፉት ወፎች ውልብ እያሉ
ከሚታዩ በስተቀር ሌላ የሚታይ ነገር የለም ። በድን
ገት የደስታ ሲቃ አፍኖ ያዛት ። ነጻ መሆኗ ፣ ነጻ መው
ጣቷና ለመማር መቻሏ ታሰባት ። በዱሮው ጊዜ ትም
ህርት ለመማር ወደ ውጭ መውጣት ፣ "ወደ ኩሳኮች
መፈርጠጥ" ይባል ነበር ። በደስታ እጣቀችና እያለቀ
ሰች ጸለየች ።

"ተይ ፣ ተይ" አለ ሳሻ በትልቁ ፈገግ በማለት ።
"ተይ ፣ ተይ!"

መጸው ከዚያም ክረምት ተከታትለው ዐለፉ ።
ናድያ ቤቷን ናፈቀች ፤ በየቀኑ እናትዋንና አያቷን እንዲ

ሁም ሳሻን ማሰብ ጀመረች ። ከቤት የሚላክላት ደብዳቤ ጥሩ ነበር ። ነገሮች ሁሉ የተረሱና ምሕረት የተደረገላት ይመስላል ። በግንቦት ወር ላይ የሚሰጠውን ፈተናዋን ተፈትና ካለፈች በኋላ ፣ በደስታ እየፈነደቀች ወደ ቤቷ ለመሔድ ተነሥታ ሳሻን ለማየት ብቻ ሞስኮ ወረደች ። ሳሻ ልክ ባለፈው ዓመት እንደ ነበረው ፣ ጺማም ጸጉራም ፣ ያንኑ አስቀያሚ ረጅም ኮትና የሸራ ሱሪ እንደ ለበሰ ፣ ዐይኖቹም እንደዚያው ትልልቅና ቆንጆ እንደሆኑ ናቸው ። ግን የታመመና የሚያዝን ይመስላል ። ቀጥኖ አርጅት ከማለቱም በላይ ሳያቋርጥ ይስላል ። ለናድያ ንጽሕና የጐደለውና ገጣሬ መስሎ ታያት ።

“ናድያ ናት እንዴ!” ብሎ ጮኸ በደስታ እየሣቀ ። “የኔ ወዳጅ ፣ የኔ ለማዳ!” እያለ ሳሻ ተቀበላት ።

በማተሚያ ክፍሉ ውስጥ በትንባሆ ጭስና በማተሚያ ቀለም ሽታ መካል ተያይዘው ተቀመጡ ። ከዚያም የትምባሆው ሽታ በሚሰነፍጠውና ቆሻሻ በሞላበት ፣ ዕቃው ተዝረክርኮ ወደ ተቀመጠበት መኖሪያ ቤቱ ተያይዘው ሔዱ ። በጠረጴዛው ላይ በቅዝቃዛው የሻይ ማፍሊያ መጣሪያ አጠገብ አንድ የተሰበረ አሮጌ ሣህን ትንሽ ጥቁር ወረቀቶች ይዞ ተቀምጦአል ። በወለሉና በጠረጴዛው ላይ ጉዳያቸው ያለቀ ሩይሎች ተዝረክርከው ተቀምጠዋል ። በቤቱ ውስጥ የሚታየው የተዘበራረቀ ሁኔታ ሁሉ የሚያሳየው ሳሻ ለግል ኑሮው ግድ እንደሌለውና ምኞትን እንደሚጠላ ነው ። አንድ ሰው ስለ ግል ሕይወቱ ፣ ስለ ደስታው ፣ የሚያፈቅረው ሰው እንዳለ ቢጠይቀው ፣ ጠያቂው ምን ማለቱ እንደሆነ ስለ

ማይገባው መልስ ሊሰዮ ስልማይችል ፥ ሊያደርግ የሚ ችለው ነገር መሣቅ ብቻ ነበር ።

"ሁሉም ነገር በደኅና ዐለፈ" አለች ናድያ ፀመ ቹኮል ። "እማማ በመጸው ወራት ልታየኝ ፒተርስበርግ መጥታ ነበር ። አያቴ እንዳልተቆጪት በየጊዜው ግን ወደ መኝታ ክፍሌ እየገባች መስቀል በግድግዳው ላይ ታስቀምጣለች" አለችኝ ።

ሳሻ ደስተኛ ቢመስልም ፥ የሚነጋገረው እየሳለ በተቆ ራረጠ ድምፅ ነው ። ናድያ በመደነቅ የተመለከተችው በእርግጥ ታሚል ወይስ የእኔ የሐሳብ ፈጠራ ነው እያ ለች ታስባለች ።

"ሳሻ ፥ ውድ ሳሻ ፥ ታመሃል እኮ!" አለችው ።

"ደኅና ነኝ ፤ ትንሽ ነው የሚያመኝ ፤ እስከዚህም የሚያሠጋ አይደለም ..." በማለት ይመልስላታል ።

"ስለ እግዚአብሔር" አለች ናድያ በተቆጣ ድምጽ። "ለምንድ ነው ወደ ሐኪም የማትሔደው ? ለምን ጤንነ ትህን አትጠብቅም ? ወንድሜ ፥ ውድ ሳሻ !" እያለች በማጉረምረም እንባ እየተናነቃት በአንድ ምክንያት አንድሬ አንድሪች ፥ ከአበባ ማስቀመጫው ጋር ዕርቃን ዋን የቆመችው ሴትዮ ምስል ፥ አሁን ስታየው እንደ ልጅነቷ ያሰፈውና የተረሳው የኋላ ታሪኳ ሁሉ በሕሊ ናዋ ታያት ። አሁን የምታለቅሰው ፥ ሳሻ እንዳለፈው ሁሉ ብልህ ፥ ዐዋቂና የሚያስደንቅ ሆኖ ስለ አላገኘ ችው ነው ። "ውድ ሳሻ በጣም ፥ በጣም ታመሃል ! እንደዚህ ከስተህና ገርጥተህ ሳይህ ይጨንቀኛል ። ብዙ ወሮታ አለብኝ ! ሳሻ ወዳጄ ፥ ምን በጐ ነገር እንዳደ

ረክልኝ የምታውቅ አይመስለኝም ! ታውቃለህ ፤ አሁን በሕይወቴ ውስጥ በጣም ቅርብና ውድ ሰው አንተ ነህ።”

ተቀምጠው ማውራት ቀጠሉ ። በፒተርስበርግ አንድ ክረምት ካሳለፈች በኋላ የሚናገረውና ፈገግታው ሁሉ ያረጀ ፥ ያፈጀ ፥ ያለቀና የደቀቀ ፥ ምናልባትም ግማሽ አካሉ መቃብር ውስጥ ያለ ሰው ፈገግታ ፥ አነጋገርና አስተሳሰብ መስሎ ታያት ።

“ከነገ ወዲያ ለሽርሽር ወደ ቮልጋ ወንዝ እወርዳለሁ” አለ ሳሻ። “ከዚያም የሆነ ቦታ ሔጄ ለመድኃኒት የተቀመመ የባዝራ ወተት እጠጣለሁ ። ወተቱን በመድኃኒትነት መሞከር እፈልጋለሁ ። ጓደኛዬና ባለ ቤቱ አብረውኝ ይሔዳሉ ። ባለቤቱ የምታስደንቅ ሰው ናት ። ሔዳ እንድትማር እየጐተጐትኳት ነው ። ተምራ ሕይወቷን ፥ ኑሮዋን ትለውጥ ።”

ጨዋታውን ከጨረሱ በኋላ ወደ ባቡር ጣቢያው ሔደው ሳሻ ሻይና ፍራፍሬ ገዛላት ። ባቡሩ ሲንቀሳቀስ መሐረቡን አውጥቶ እያወዛወዘ ፈገግ ብሎ ተሰናበታት። ናድያ ፥ እግሮቹን እየተመለከተች ክፉኛ መታመሙንና ብዙም በሕይወት እንደማይቆይ ተገነዘበች ።

ናድያ ፥ ስድስት ሰዓት ሲሆን ትውልድ ከተማዋ ደረሰች ። ከባቡር ጣቢያው ወደ ቤቷ በጋሪ ስትሔድ የከተማው መንገዶች ከሚፈለገው በላይ በጣም ሰፋፊ ፥ ቤቶቹ በጣም ትንንሽና ከመንገዶቹ ጋር የማይጣጣሙ ሆነው ታዩዋት በእካባቢው ማንም ሰው ስላልነበረ ፥ ያገኛቸው አሮጌ ካፖርቱን ለብሶ የሚዘዋወረውን ጀርመናዊውን የጢያኖ ታኚ ብቻ ነበር ። ቤቶቹም በአቡዋራ የተሸፈኑ መሰላት።

እያት ፥ በሻም ቢያረጁም ውፍረታቸውና ግልጽነታቸው እንደ ነበረ ነው ። እጆቿን በናድያ ዙሪያ ጠምጥማ ፊቷን ከናድያ ትከሻ ላይ ለማንጣት ያቃታት ይመስል ቅክ ሻዋ ላይ ተክላ ለረጅም ጊዜ አልቀሰች ። ኒና ኢሻና ቭና በዕድሜ መግፋቷ ቢታወቅባትም ከስታለች ።ያው እንደ ቀድሞው ዝምተኛ ስትሆን ፥ የአልማዝ ቀለበ ቶቿ ከጣቶቿ ላይ እንደ ተሰኩ ናቸው ።

"ወዳጄ" አለች ሁለመናዋ እየተንቀጠቀጠ ። "የኔ የግሌ ፥ ሕይወቴ !"

ከዚያም ተቀምጠው ጸጥ ብለው አለቀሱ ። ሁሏ ቱም ፥ እናትና አያቷ ፥ ያለፈው በማይመለስ ሁኔታ ያመ ለጠ መሆኑን የተገነዘቡት ይመስላል ። ያ የጥንቱ ማኅ በራዊ ደረጃቸው ፥ ክብራቸው ፥ ቤታቸው እንግዶች የመጋበዝ አቅማቸው ሁሉ ፀልፏል ። አንድ ቀን ሌሊት የተለመደ ግድ የለሽ ሕይወታቸውን ሲቀጩ ፥ ፖሊስ መጥቶ ቤቱን ሲፈትሽ አባወራው የመንግሥት ገንዘብ እጦደለ፤ወይም በሐሰትና በተጭበረበረ ገንዘብ ተጠቅሟል ሲባሉ እንደ ሌላው ተራ ሰው ሁሉ ኑሮ ይከብዳቸውና ይሰማቸው ጀመረ ። ከዚያም እስከ መጨረሻው የተንደ ላቀቀ ግድየለሽ ኑሮን ተሰናበቷት !"

ናዲያ ፥ ወደ ፎቅ ወጥታ ያንኑ የጥንቱን አልጋ ፥ መስኮቶችና ነጫጭ መጋረጃዎች ፥ ከመስኮት ሆኖ የሚ ታየው በፀሐይ ብርሃን የፈካውና በድምፅ የተሞላው የአትክልት ቦታ አይታ እንደ ነበረ ሆኖ አገኘችው ።

ጠረጴዛውን በእጅዋ እየነካካች አጠገቡ ተቀምጣ በሐሳብ ተዋጠች ። ጥሩ ራት ፀልታ ሻይ በቅቤ ብትጠ

ጣም አንድ ነገር የጐደለ ፥ በከፍሎቹ ውስጥ ልንድ ባዶ ነት ያለ መስሎ ታያት ። የክፍሎቹ ኮርኒሶችም በጣም ቀረቡባት ። ማታም ወደ መኝታዋ ሔዳ በአልጋ ልብ ሶጅ ተሸፋፍና ስትተኛ ፥ በዚህ ሞቃትና በጣም ለስላሳ አልጋ ውስጥ መጋደሙ በጣም የሚያስጠላ ሆኖ ተሰ ማት ።

ኒና ኢቫኖቭና ፥ ለአፍታ ያህል ብቅ ብላ አንድ ጥፋ ተኛ ሰው እንደሚያደርገው ሁሉ እየተገላመጠች በታ ፍረት ሹክክ ብላ ገብታ ተቀመጠች ።

"ታዲያስ ናድያ ፥ ነገሮችን እንዴት አገኘሻ ቸው ?" ስትል ጠየቀቻት ።

"ደስተኛ ነሽ ? በእርግጥ ደስተኛ ነሽ ?"

"አዎን ፥ እማማ !"

ኒና ኢቫኖቭና ፥ ክሙቀመጫዋ ተነሥታ ወደ ናድያና ወደ መስኮቱ እየዞረች አማተበች ።

"እንደምታይኝ ሃይማኖተኛ ሆኜአለሁ" አለቻት ። "ፍልስፍና እያጠናሁ ነው ፥ ታውቂያለሽ ? ስለዚህም አስ ባለሁ...አስባለሁ ። ብዙ ነገሮች አሁን እንደ ቀን ብር ሃን ግልጽ እየሆኑልኝ ነው ። ዋናው ቁም ነገር ፥ ለኔ እንደሚመስልኝ ፥ ሕይወትን በመኖጥር ማየቱ ነው ።"

"እማማ ፥ አያቴ እንዴት ናት ?"

"ደኅና ትመስላለች ። ከሳሻ ጋር መሔድሽን ከቴ ሌግራሙ ስታነብ ወደያው ወደቀች ። ለሦስት ቀን ክመ ኝታዋ ሳትነቃነቅ ተኛች ። ከዚያም እያለቀሰች ጸለየች ። አሁን ግን ደኅና ናት ።"

ከመቀመጫዋ ተነሥታ ክፍሉ ውስጥ መንጐራደድ ጀመረች ።

“ዓ—ዓ” የሌሊት ዘበኛው አንኳኳ ። “ዓ—ዓ ።”

“ትልቁ ነገር ሕይወትን በመነጥር ውስጥ መመልከቱ ነው” አለች ።“በሌላ አነጋገር ሕይወት ተሰነጣጥቆና ተተንትኖ ወደ ሰባቱ ቀለማት ወርዶ ቀለል ባለ መንገድ አዕምሮዋችን ውስጥ መቀመጥ ፣ እያንዳንዱ ንጥረ ነገር በጥንቃቄ ተነጣጥሎ መጠናት ይኖርበታል።”

ናድያ ፣ እንደ ተኛች ወዲያው እንቅልፍ ወስዷት ስለ ነበር ፣ ኒና ኢቫኖቭና ምን እንደ ተናገረችና መቼ ወጥታ እንደ ሔደች አላወቀችም ።

ግንቦት ዐልፎ ሰኔ ተተካ ። ናድያ እንደገና ከቢታና ከአካባቢዋ ተላመደች ። አያት ሻይ ማፍሊያው መጣሪያ አጠገብ ተቀምጠው በኃይል እየተነፈሱ ሻይ እየቀዱ ያሳልፉሉ ። በየማታው ፣ ኒና ኢቫኖቭና ፣ ስለ ፍልስፍናዋ ታወራለች ። አሁንም የምትኖረው በጥገኝነት ስለሆነ ፣ ሳንቲም በፈለገች ቁጥር የምትጠይቀው አያትን ነው ። ቤቱ በሙሉ በዝምብ ከመሞላቱም በላይ ኮርኒሱም ከዕለት ወደ ዕለት እየወረደ ነው ። አያትና ኒና ኢቫኖቭና አባ አንድሬንና ልጆቸውን ፣ አንድሬ አንድሪችን ፣ አፍረው ላለማየት ወደ ውጭ ወጥተው አያውቁም ። ናድያ በአትክልት ቦታውና በከተማው መንገዶች ስትዘዋወር ቤቶቹንና የወደቁ አጥሮችን እያየች ይህቺ ከተማ ካረጀች የቆየች ፣ ጊዜዋ ያለፈባትና ጨርሶ ለመውደቅ ወይም አዲስ ጊዜ መጥቶ ለመታደስ የምትጠባበቅ መስሎ ታያት ። አቤት ! ይህን አዲስና ንጹሕ

ሕይወት ለመጀመር የሚቻለው ፥ አንድ ሰው በትክክ ለኛ መሥመር ላይ ነኝ ብሎ በልበ ሙሉነት የራሱን ዕድል ፊት ለፊት በትክክል ለማየት ሲችል ነው ። ይህ አዲስ ሕይወት ዘግይቶም ሆነ ፈጥኖ መምጣቱ የማይ ቀር ነው ። እንደ አያታችን ቤት እራት አሽከሮች በቆ ሻሻ ተውጠው እምድር ቤት በአንድ ክፍል ውስጥ የማይኖሩበት ጊዜ ይመጣል ። አዎን እንደዚህ ዐይነት ቤት ጨርሶ የሚጠፋበት ለመኖሩም የሚመሰክር ወይም የሚያስታውስ ሰው የማይገኝበት ጊዜ ይመጣል ። የና ድያ ቁጣ ቱግ የሚለው በአትክልቱ ቦታ ስትንሸራሸር ጐረቤት ያሉት ትንንሽ ልጆች አጥሩ ላይ እየተንጠለ ጠሉ ፥ "ሙሽሪት ያቻትና!" እያሉ የሚሥቁባትና የሚ ጮሁባት ጊዜ ነው ።

ከሳራቶቭ ፥ ከሳሻ ፥ አንድ ደብዳቤ መጣ ። ደብዳ ቤው ግድ የለሽ በሆነው የተንጋደደ አጻጻፍ የተጻፈ ነው ። የቦልጋ ጉዞው ውጤት አጥጋቢ ቢሆንም ፥ ሳራ ቶቭ እንደ ደረሰ ታሞ አንደበቱን ስለ ዘጋው ፥ ሆስፒ ታል ከገባ ዐሥራ አምስት ቀን እንደ ሆነው ጽፏል ። መልእክቱ ምን እንደሆነ ስለ ገባት መክፈል የሚገባት ውለታ ወይም ወሮታ መስሎ ቢታይበትም ፥ ይህ መልዕክት ወይም የሳሻ ሐሳብ ራሱ እንደ ቀድሞው መን ፈሷን አለመንካቱና አለማነሣሣቱ አበሳጫት ። የፒተ ርስበርግ ኑሮ ናፈቃት ። ከሳሻ ጋር ያላት ግንኙነት ውድ መሆኑን ብትረዳም ያለፈና የቆየ ታሪክ ሆኖ አገኘችው ። ሴሊቱን ሁሉ እንቅልፍ ሊወስዳት አልቻ ለም ። ጠዋትም የምታዳምጠው ነገር ያለ ይመስል መስኮቱ አጠገብ ተቀመጠች ። ከዚያም በእርግጥ ከም

ድር ቤት የሰው ድምፅ ትሰማ ጀመር—በችኮላ የሚነገር የአያት እሮሮ ነበር ። አንድ ሰው ጮኸ...ናድያ ወደ ምድር ቤት ስትወርድ ፥ አያት አንድ ጥግ ይዘው ፊታቸው ፥ በእንባ ፈለግ ታርሶ ይጸልያሉ ። ጠረጴዛው ላይ አንድ ቴሌግራም ተቀምጧል ። ናድያ ቴሌግራሙን አንሥታ ከማንበቧ በፊት የአያቷን ልቅሶ እያዳመጠች ክፍሉ ውስጥ ትንጐራደዳለች ። የቴሌግራሙ መልክት የሚለው ትላንትና ጠዋት በሳራቶቭ ከተማ አሌክሳንደር ቲሞፊች ፥ በእጭሩ ሳሻ በሳንባ ነቀርሳ ሕመም መሞቱን ይገልጻል ።

አያትና ኒና ኢቫኖቭና ፥ ፍትሐት እንዲደረግለት ለማዘዝ ወደ ቤተክርስቲያን ሲሔዱ ፥ ናድያ በክፍሉ ውስጥ እያሰበች ለረጅም ጊዜ ተንጐራደደች ። ሳሻ እንደ ፈለገው ሁሉ ሕይወቷ መገልባበጡን ፥ መለዋወጡን ፥ ብቸኛ ፥ ባይተዋር ፥ እዚህ የማትፈለግና እሷም የማትፈልገው አካባቢ መሆኑዋን ፥ ያለፈው ታሪኳ በእሳት እንደ ተበላና ወመዱም እንደ ተበተነ ሁሉ ያለፈ መሆኑን ተገነዘበች ። ወደ ሳሻ ክፍል ሔዳ ቆመች ።

“ደኅና ሁን ፥ ውድ ሳሻ !”አለች ። አዲስና ሰፊ ሕይወት ከፊቷ ተዘርግቷል ። ይህ አዲስ ሕይወት ምሥጢራዊና ግልጽ ያልሆነ ቢሆንም ፥ ወደ ፊት እየሳበ ይጠራታል ።

ዕቃዎቿን ለማዘጋጀት በደረሻው ላይ መጣት በማግስቱ ጠዋት ቤተሰቦቿን ተሰናብታ ከተማውን በደስታና በሙሉ መንፈስ ልቃቅ ሄደች ደግም ላትመለስ እርግጠኛ ነበረች ።



ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት

ዋጋው ብር 3.25

በሁሉም ቦታ